አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

በ

ቀለሟ መኮንን ንጉሴ

ሰኔ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

በ

ቀለሟ መኮንን ንጉሴ

አማካሪ

ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)

ሰኔ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

በ

**ቀለሟ መኮንን ንጉሴ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| የአማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
| --- | --- | --- |
| ------------------------------------ | -------------------------------- | --------------------------- |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ------------------------------------ | -------------------------------- | --------------------------- |
| ------------------------------------ | -------------------------------- | --------------------------- |

# ምስጋና

በቅድሚያ ጥናታዊ ጽሁፉን በየደረጃው በማረምና ጠቃሚ ምክር በመስጠት ለጥናቱ ዕውን መሆንና እዚህ መድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉት አማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚሆን በጀት ስለፈቀደልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን እንዲሁም፤ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የትምህርት ሰዓትና ከፊል የትምህርት ክፍያ በመሸፈን ላደረጉልኝ አስተዋጽኦ ማመስገን እወዳለሁ፡፡ የባለስልጣኑ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሰራተኞች በሙሉ (ፋንታ፣ ወልዴ፣ ነዳች፣ ሸዋነሰሽ፣ ወሰኔ፣ መንግስቱና ተክሌ፤ እንዲሁም ሳሚ፣ ሸዋዬ፣ ፍቅርተ፣ መነንና አስናቁ) በልዩ ልዩ መልኩ ለነበራችሁ ድጋፍ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡ መምህር ባለው ደምሴ፣ ያሲን ዑመር፣ ቸርነት ጥላሁን፣ በላይነህ ተሰራ፣ ዓለሙ ኃይሌ፣ መንክር ቢተው፣ መልካሙ ተክሌና ኤፍሬም አማረ በትምህርት ቆይታዬ ለነበራችሁ ምክር፣ የማቴሪያልና ሞራል ድጋፍ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በመስክ ቆይታዬ በገንዘብ ለማይተመነው ውለታቸው ለጥናቴ መሳካት በተለያየ መልኩ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለኮንሶ ወዳጆቼ ለከርቲታ ጎሳ መሪ ካላ ገዛኸኝ ከነቤተሰቡ፣ ለአቶ ዲኖቴ ኩስያና ቤተሰቡ፣ ዘመዶቼና ጎረቤቶቹ፣ ለወ/ሮ መርከብ ከነቤተሰቦቿ እንዲሁም ለአቶ ሰሎሞን ደስታ ምስጋና ያንሳችኋል፡፡ ለኮንሶ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ፍትሕ፣ ፖሊስና ጸጥታ አስተዳደር እንዲሁም ለወረዳው ሴቶችና ሕጻናት ቢሮና ለአካባቢው የወጣቶች አሰጎብኚ ቢሮ ሰራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ከምንም በላይ ለባለቤቴ ለዶ/ር መንግስት ኃ/ማርያም እንደትዳር ጓደኛ የሚስትነት ፍቅሬን፣ ለልጆቻችን ለሮቤል፣ ብሩክና ሎዛ የእናትነት ፍቅሬን ትቼ ራሴን ብቻ በማሰብ ሙሉ ትኩረቴን ለትምህርቴ ሳደርግ ለነበራችሁ ትዕግስት እና የሞራል ድጋፍ ሁልጊዜም በልቤ የቀረ ነውና ምን እላለሁ! ቤተሰቦቻችን በተለያየ መልኩ ድጋፎቼና ሞራሎቼ ነበሩና ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥልኝ ምኞቴ ነው፡፡ ለዚህ ስራ መሳካት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ድጋፋቸው ላልተለየኝና ስማቸውን ያልጠቀስኳቸው ብዙዎች ናቸውና ሁሉም ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ቀለሟ መኮንን

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና....................................................................................................... i

ማውጫ ........................................................................................................ ii

ሙዳየ ቃላትና ፍችዎቻቸው................................................................................ vi

የሠንጠረዥ ዝርዝር ........................................................................................ viii

የገላጭ ስዕላት ዝርዝር..................................................................................... viii

አጠቃሎ.......................................................................................................... ix

**ምዕራፍ 1. መግቢያ ......................................................................................1**

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........................................................................ 3

1.2. የጥናቱ ዓላማ ............................................................................................ 4

1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች ..................................................................... 5

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ......................................................................................... 6

1.5. የጥናቱ ወሰን............................................................................................. 6

1.6. የጥናቱ ዘዴ .............................................................................................. 6

1.6.1. የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታ ........................................................................ 7

1.6.1.1. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥና የዐውድ ሁኔታ .......................... 7

1.6.1.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች.................................................. 8

1.6.1.2.1 የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ...................... 8

1.6.1.2.2 የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................ 10

1.6.2. የጥናቱ መተንተኛ ዘዴ ........................................................................ 10

1.7. በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች................................ 11

1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች .................................................................................. 11

1.7.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................................................ 12

1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ጠቃሚ ተመክሮዎች...................................... 13

**ምዕራፍ 2. ክለሳ ድርሳን..................................................................................... 15**

2.1. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................................................................ 15

2.1.1. የግጭት ምንነት ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች . ......................................... 15

2.1.2. የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎች ..................................................... 17

2.1.3 የግጭት አፈታት ዘዴዎች............................................................. 18

2.1.4. የግጭት ፋይዳ ......................................................................... 21

2.1.5. የግጭት አፈታትና ፎክሎር .......................................................... 22

2.1.6. በኢትዮጵያ የባህላዊና መደበኛ ግጭት አፈታት ስርዓት ቅኝት............. 24

2.1.7. ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት በኢትዮጵያ የሚኖረው አንድምታ... 25

2.2 ሀገረሰባዊ ጥናቶች በባህላዊ ግጭት አፈታት........................................... 27

2.2.1. በአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የተጠኑ .......... 27

2.2.2. በሶሺዮሎጂና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ ትምህርት የተጠኑ .............. 27

2.2.3. በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የተጠኑ ..................................... 28

**ምዕራፍ 3. የኮንሶ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ........................................................ 31**

3.1 የብሔረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ ....................................................... 31

3.2 የወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ . ..................................................... 32

3.3 የኢኮኖሚ መሠረት ............................................................................... 36

3.4 ቋንቋና ኃይማኖት ................................................................................ 36

3.5 ማህበራዊ ተቋማት.................................................................................. 37

3.6 ባህላዊ አስተዳደር ................................................................................. 40

3.6.1 ፓሌታዊ አደረጃጀት .......................................................................... 40

3.6.2 ጉሳዊ አደረጃጀት ............................................................................... 41

**ምዕራፍ 4. ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኮንሶ ብሔረሰብ ........................... 45**

4.1. የግጭት ጽንሰ ሀሳብ በኮንሶ ብሔረሰብ ...................................................... 45

4.2. የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቻቸው ........................................................ 48

4.2.1. የግለሰብ ግጭት ................................................................................ 48

4.2.2. የቤተሰብ ግጭት ................................................................................ 49

4.2.3. የጉረቤት ግጭት ................................................................................ 51

4.2.4. የቡድን ግጭት .................................................................................. 51

4.2.5. ከሀብት ንብረት ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ግጭት ................................... 53

4.2.6. ወንጀል ............................................................................................ 54

4.3. የግጭት መፍቻ ተቋማት አደረጃጀት፣ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት........................................................................ 55
4.3.1. የተቋማቱ አደረጃጀትና አስታራቂዎች ........................................... 55
4.3.1.1. ሞራ-ከንታ.......................................................................... 55
4.3.1.2 ሞራ-ፓሌታ...................................................................... 56
4.3.1.3. ፖቅላ ............................................................................... 56
4.3.1.4. “ኻኻ” ወይም የመሀላ ስርዓት ............................................ 57
4.3.2. የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት ............................... 58
4.3.2.1. በሞራ-ከንታ ደረጃ.......................................................... 58
4.3.2.2 በሞራ-ፓሌታ ደረጃ.......................................................... 60
4.3.2.3. በፖቅላ ደረጃ..................................................................... 64
4.4. ባህላዊ ስርዓቱ የሚከወንባቸው የዳኝነት ቦታዎች ........................................ 68
4.4.1. ፓሌታዊ የዳኝነት ቦታዎች (ሞራዎች)................................................ 68
4.4.1.1. ሞራ-ከንታ ........................................................................ 68
4.4.1.2. ሞራ-ፓሌታ ...................................................................... 69
4.4.1.3. ሞራ-ኪርባ ........................................................................ 69
4.4.1.4. ሞራ-ኻኻ ......................................................................... 69
4.4.2. ጐሳዊ የዳኝነት ቦታዎች .......................................................................70
4.5. የግጭት አፈታት ሂደት ................... ........................................................70
4.5.1. በሞራ-ከንታ ደረጃ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው.................75
4.5.2. በሞራ-ፓሌታ ደረጃ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው.................84
4.5.2.1. የቀላል ግጭቶች አፈታት ሂደት ..............................................84
4.5.2.2. የከባድ ግጭቶች አፈታት ሂደት ............................................. 87
4.5.3. በፖቅላ ደረጃ የሚፈቱ ወንጀሎችና የአፈታት ሂደታቸው ................... 104
4.6. በባህላዊ ስርዓቱ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችና የተሰጡ ውሳኔዎች ........................................................................ 113
4.7. የፎክሎር ሚና በኮንሶ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት......................... 118
4.8. የባህላዊ ስርዓቱ ፋይዳ ........................................................................ 121

**ምዕራፍ 5. የባህላዊና የመደበኛው የፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ………………. 124**

5.1 ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ የተመሰረተባቸው ማህበራዊ እሴቶች……… 124

5.2 በመደበኛ የፍትህ ተቋማት መፍትሄ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች………………….. 130

5.3 ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከመደበኛ የፍትህ ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት……. 132

5.3.1 ከፍርድ ቤትና ዐቃቢ ህግ እንዲሁም ከጸጥታና አስተዳደር ጋር………… 132

5.3.2 ከፖሊስ ጋር ያለ ቅንጅታዊ አሰራር ………………………………….. 137

5.3.3 ከሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ቢሮ ጋር ያለ ቅንጅታዊ አሰራር…………….. 139

5.4 የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች……………………………… 143

5.5 ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ዘላቂነት እንደስጋት የሚነሱ………………146

**ምዕራፍ 6. ትንተናና ቁዘማ ………………………………………………………………149**

6.1 ማህበራዊ መሠረት የተጣለላቸው ተቋማትና መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው….. 149

6.2 በባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ የልዩ ልዩ ትዕምርቶች ፍችና ፋይዳ …………151

6.3 በባህላዊ የፍትህ አፈፃፀም ወቅት የሚታዩ ልዩ ልዩ ስነ-ስርዓቶች………….. 155

**ምዕራፍ 7. ማጠቃለያ እና ይሁንታዎች…………………………………………………… 162**

7.1. ማጠቃለያ ………………………………………………………………… 162

7.2. ይሁንታዎች ………………………………………………………………165

ጥቅስማ (Reference) ……………………………………………………………… 167

አባሪ ሰነዶች

አባሪ አንድ፡- የአውራ መረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ

አባሪ ሁለት፡- የሌሎች መረጃ ሰጪዎች አጭር መግለጫ

አባሪ ሦስት፡- የመረጃ አቀባዮችና የልዩ ልዩ ክንውኖች ፎቶና መግለጫ

አባሪ አራት፡- የአቤቱታ ደብዳቤዎች

ማረጋገጫ

## ሙዳየ ቃላትና ፍችዎቻቸው

**አታ፡-** የኮንሶ ባሕል ማለት ነው።

**ዴኻ፡-** የሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለጉዳዮች ክርክርን የሚያመለክት ነው። ነገር ግን የኮንሶ ባሕላዊ ሕግ ስርዓት መጠሪያ ስምም ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል የብሔረሰቡ አባላት ይስማማሉ።

**ፓሌታ፡-** በድንጋይ ካብ የታጠረ ወይም ያልታጠረ ባሕላዊ ከተማ ወይም መንደር ማለት ነው።

**ከንታ፡-** በአንድ ፓሌታ ውስጥ የሚገኝ ንዑስ መንደር ማለት ነው። አንድ ፓሌታ ከ2-10 በሚደርሱ ከንታዎች የተከፈለ ነው።

**ካፋ፡-** ጉሳ ማለት ነው። በኮንሶ ዘጠኝ ጉሣዎች አሉ። የራሳቸው መዋቅራዊ አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራና ተግባር አላቸው።

**አፓ-ቲንባ፡-** ‹‹አፓ›› ማለት አባት ሲሆን ‹‹ቲንባ›› ማለት ደግሞ ከበሮ ማለት ነው። ‹‹አፓ-ቲንባ›› የከበሮ አባት ማለት ሲሆን፣ የአንድ ፓሌታ የበላይ መሪና ተወካይ ነው።

**ቲንባ፡-** ከበሮ ማለት ነው። ማንኛውም ከበሮ ሳይሆን የኮንሶ ብሔረሰብ ሹመትና ማዕረግ አሰጣጥ ስርዓት የሚታጀብበት ማለት ነው። ሦስት የቲንባ የማዕረግ ደረጃዎችና ዓይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም የፓሌታ-ቲንባ፣ የቀጠና-ቲንባና የፖቅላ-ቲንባ ናቸው። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ለተመሳሳዩ ሹመት የሚሰጠው "ቲንባ" ሳይሆን "ኡሌታ" ነው፣ አጭር ዱላ ናት፡፡

**አፓ-ሰሌታ፡-** አዋጅ ነጋሪ ማለት ነው።

**ፖቅላ፡-** የአንድ ጉሣ አጠቃላይ መሪ ማለት ሲሆን፣ ባለ አንድ ቱማ (የብር አምባር) በቀኝ እጁ ክንዱ ላይ ያደርጋል።

**ፖቃላ (ቱራይታ)፡-** በየፓሌታው ውስጥ የአንድ ጉሣ አባላትን የሚወክል የጉሣ መሪው ምክትል ማለት ነው። አምስት የብረት አምባሮችን በቀኝ እጁ በክንዱ ያደርጋል። በአንድ ፓሌታ ውስጥ የዘጠኙም ጉሣዎች አባላት በጋራ ስለሚኖሩ ዘጠኝ ፖቃላዎች ሊኖሩ ይችላሉ ማለት ነው።

**ኼላ፡-** በሥልጣን ላይ ያለው የወጣት ትውልድ ማለት ነው። በኮንሶ በየ 18 ዓመት የሚቀያየር የወጣት ትውልድ የሥልጣን ሽግግር ይካሄዳል። ይህ ስርዓት "ኸልታ" ተብሎ ይታወቃል። ሥልጣኑን የተረከበው ትውልድ "ኼላ" ይባላል። የቡድኑ አባል የሆነ ወጣት "ኸሊታ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

**ሰገን፡-** ወንዝ ማለት ሲሆን ወንዙ የሚያዋስናቸው የአምስቱ ወረዳ ሕዝቦች ማለትም አማሮ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ አሌና ኮንሶን ለመጥቀስ ነው፡፡

**ሰንቀሊታ፡-** የኼላ (በሥልጣን ላይ የሚገኝ የወጣቶች ቡድን) መሪ ማለት ነው፡፡

**አፓ-ኩማ፡-** "አፓ" ማለት አባት፣ "ኩማ" ማለት "ዱላ" ማለት ነው፡፡ "አፓ- ኩማ" የዱላው ባለቤት ማለት ሲሆን የወጣቶች የትውልድ ስልጣን ሽግግር በሚካሄድበት ወቅት ሥልጣን ለያዘው ትውልድ መሪ (ሰንቃሊታ) የምትሰጥ ዱላ ናት፡፡

**አፓ-ሊሻ፡-** ‹‹አፓ›› ማለት አባት ሲሆን ‹‹ሊሻ›› ማለት የጉማሬ አለንጋ ማለት ነው፡፡ ‹‹አፓ-ሊሻ›› የጉማሬ አለንጋ ባለቤት ማለት ነው፡፡ አደገኛ ድብቅ ሌቦችንና መሰል ሌሎች ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን ማውጣጫና መግረፊያ አለንጋ ናት፡፡ በድሮ ጊዜ ራሱን የቻለ አፓ-ሊሻ (የአለንጋው ባለቤት) ይመረጥ ነበር፡፡ አሁን ግን አለንጋዋ ሰንቀሊታው ዘንድ ትቀመጣለች፡፡

**አፓ-ቢላ፡-** የቢላው ባለቤት ማለት ሲሆን በባህላዊው ከተማ ውስጥ የግለሰብ ዛፎች መንገድ ሲዘጉ፣ አጥር ተሻግረው የሌላን ሰው ግቢና ቤት ሲያስቸግሩ ተነግሮት በራሱ አመራር ያስቸገሩ ቅርንጫፎችን በመቁረጥ የሚያስተካክል መሪ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ ስልጣን ለሰንቀሊታ በተደራቢነት ተሰጥቷል፡፡

**ቂማያ(ቂሞታ)፡-** ሽማግሌ፣ ሽማግሌዎች ማለት ነው፡፡ በኮንሶ "አታ" ከፍተኛ ሥፍራ አላቸው፡፡ በባሕላዊ አስተዳደሩና የዳኝነት ስራ ድርሻቸው ጉልህ ነው፡፡

**ከታ ወይም ዳውራ፡-** ባሕላዊና ኃይማኖታዊ ስርዓቶችን የሚመሩ፣ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ መንፈሳዊ አባቶች ናቸው፡፡

**ሞራዎች፡-** በፓሌታዎች ውስጥ ለሕዝባዊ አገልግሎት ተብለው የሚሰሩ ቤቶች ማለት ነው፡፡ ከአገልግሎታቸው አንፃር አራት ዓይነት ምራዎች አሉ፡፡ ሞራ-ፓሌታ፣ ሞራ-ኻኻ/ ሞራ ዳውራ፣ ሞራ ከንታና ሞራ- ኪርባ ናቸው፡፡

**ዲና፡-** በፓሌታዎች ዙሪያ የሚገኝ ጥብቅ ደን ማለት ነው፡፡ በዋናነት አገልግሎቱ ሁለት ነው፡፡ የፓሌታው ሰው ደጅ መጸዳጃ ቦታ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ የእሳት አደጋ ቢከሰት ከዲና ዛፍ ቆርጦ የመከላከል ስራ ይሰራበታል፡፡

**አኩታ፡-** የመሀላ ዓይነት ሲሆን፣አፈጻጸሙም በእርሻ መሬት ድንበርተኞች በድንበር ሲጋጩ በቦታው አንዱ ባንዱ ላይ አፈር ብናኝ በመበተን የሚማማሉበት ነው፡፡

## የሠንጠረዥ ዝርዝር


ሠንጠረዥ 1 በኮንሶ ብሔረሰብ የወራትና ወቅቶች ሥያሜ .................................. 35

ሠንጠረዥ 2 የኮንሶ ጐሳ መሪና መጠሪያ ........................................................ 42

ሠንጠረዥ 3 በሞራ-ከንታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት......... 58

ሠንጠረዥ 4 በሞራ-ፓሌታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት....... 60

ሠንጠረዥ 5 በፖቅላ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት................ 64


## የገላጭ ስዕላት ዝርዝር


ገላጭ ስዕል 1 የኮንሶ ልዩ ወረዳ ካርታ.............................................................. 33

ገላጭ ስዕል 2 የኮንሶ ልዩ ወረዳ አቀማመጥ በኢትዮጵያ ካርታ ላይ ...................... 34

ገላጭ ስዕል 3 የጎሳዊ አደረጃጀት መዋቅር ............................................... 44

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ትኩረት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከናወን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን በመመርመር የግጭት መፍቻ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና እና ስርዓቱ ምን እንደሚመስል በመተንተን በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ አባባሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ትዕምርቶችን በመለየት የስርዓቱን ፋይዳ ማሳወቅ ነው።

ይህንንም ለማሳካት በቅድሚያ በዘርፉ ስለብሔረሰቡና ስለ አካባቢው የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብና መነሻ ሀሳብ ይዞ ወደ መስክ በመሄድ በቃለመጠይቅ (መደበኛና ኢ-መደበኛ)፣ በአካል ምልከታ እንዲሁም፤ የውስን አትኩሮት ቡድን ውይይት መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፣ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት መቅረፀ ድምጽና ምስል ጥቅም ላይ ውሏል። መረጃው የተሰበሰበው በኮንሶ ወረዳ በካራት አገልግሎት ስር ባሉ ሶስት ቀበሌዎች ሲሆን፣ ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪ፣ ሴቶችና የወጣት ቡድን ተወካይ እንዲሁም ከፍትህ አካላት በጠቅላላ 16 ሰዎች በመረጃ አቀባይነት ተሳትፈዋል። የተሰበሰበው መረጃ ገላጭ ዘዴን በመጠቀም ተተንትኗል።

በብሔረሰቡ ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶችን በመፍታት ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍኑበት በየደረጃው የሚከናወን ሶስት ባህላዊ የዳኝነት መዋቅር እንዳላቸው ጥናቱ ያሳያል። ከሶስቱ ባህላዊ የዳኝነት መዋቅርና አደረጃጀት በላይ የሆኑ ጉዳዮች ወደ "ኻኻ" ወይም መሀላ ተመርተው የመጨረሻ ዕልባት እንደሚያገኙ ጥናቱ ይጠቁማል። በዕርቅ ድርድሩ ወቅት ለስርዓቱ የሰመረ አካሄድ በሽማግሌዎች የሚነሱ የተለያዩ አባባሎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ምርቃቶችና ምስጋናዎች ትልቅ መሳሪያ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል።

በብሄረሰቡ ባህላዊውና መደበኛው የፍትህ ስርዓት የግጭት አፈታት ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ የሚሰሩበት አሰራርና ቅብብሎሽ መኖሩ ለባህላዊው የፍትህ ስርዓቱ ዘላቂነት የጎላ ድርሻ እንዳለው ጥናቱ ይጠቁማል። ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዋነኛ የፍትህ ተቋም ሆኖ የዘለቀ ቢሆንም፣ የማህበረሰቡን አቅም ያላገናዘበ ቅጣት የሚጣልበት ሁኔታ መኖሩና አወሳሰኑ ወጥነት የሌለው መሆኑ የስርዓቱ ክፍተት እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል።

ሽማግሌዎች ጠበኞችን በማስታረቅ ሂደት ደረቅ ማሽላ አኝከው በመትፋት፣ ጠበኞችም በዕርቅ ስርዓቱ አንድ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ በአንድ ቅል በጋራ ባህላዊ መጠጥ (ጨቃ) በመጠጣት እንዲሁም እንደወንጀሉ ክብደት ከሚፈጽሙት ዕርቅ በኋላ አካባቢውን በደም፣ በፈርስና በቅዱስ ውኃ በመርጨትና በመታጠብ (የማንጻት ስራ) ዕርቁን እንደሚያፀኑ ጥናቱ ያሳያል።

# ምዕራፍ 1.   መግቢያ

የፍላጎቶች አለመጣጣም በሚኖርበት በማንኛውም ቦታና ጊዜ ቅራኔና ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ በእነዚሁ ፍላጎቶች አለመጣጣም ሳቢያ የሚከሰቱ አለመግባባቶች ደግሞ ከባድ ወይም ቀላል ግጭቶችን ሲጭሩ ይስተዋላል፡፡ ግጭቶች በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ በአንድ ወይም በሁለት አሊያም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል በተከሰተ አለመግባባት የሚነሱ ክስተቶች ሲሆኑ መንስኤዎቹም የተለያዩ ናቸው፡፡

ለአብነት በማህበራዊ ህይወትም ቢሆን አንደኛው ከሌላኛው የበለጠ ኃይል ወይም ክብር እንዳለው ሲያምንና ይኸው አመለካከቱ በሌላኛው ወገን ተቀባይነት ሲያጣ በሁለቱ መካከል ግጭት ይቀሰቀሳል፡፡ የባህላዊ ዕሴቶችና እምነቶች ልዩነትም ተመሳሳይ ግጭትን ያስነሳል፡፡ በአገራችን የመሬትና ውሀ አጠቃቀም ችግር ከግጭት መንስኤዎች መካከል የሚመደብ ነው፡፡ በእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች አንደኛው ወገን ይበልጥ ተጠቃሚ እንደሆነና ሌላኛው ተገቢ ድርሻውን እንደተነፈገ ሲያስብ ወደግጭት ሊያመራ ይችላል፡፡ ይህም ውስን የሆኑ ሀብቶችን የራስ ለማድረግ ወይም በሀብት የመጠቀም ዕድልን ለማስፋት ባለ ፍላጎት የሚፈጠር ሽኩቻ ነው፡፡ በማህበራዊ አደረጃጀትም ሆነ በፖለቲካዊ አወቃቀር ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የስልጣን ጥማት መኖርና ስልጣናቸውን ለማቆየት ወይም ከፍ ለማድረግ ሲሉ በሚኖራቸው ፍላጎት ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ ግጭቶች ተራ ከሚባሉ አለመግባባቶች ጀምሮ ከባድ የሕይወት መጥፋትንና የንብረት ውድመትን እስከሚያስከትሉ ጦርነቶች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ ግጭቶች በግለሰቦች፣ በቡድኖች እንዲሁም በሀገራት ደረጃ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ የቤተሰብ፣ የጎሳ፣ የብሔር፣ የክልል ወዘተ እየተባሉ የሚከሰቱ ግጭቶችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ግጭቶች በመነሻ ምክንያታቸው፣ በተሳታፊዎቻቸው፣ በውጤታቸውና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚለያዩ ቢሆኑም መፍትሄ የሌላቸው ግን አይደሉም፡፡ እንደ ግጭቶች ደረጃና እንደባህርየ ፍጥረታቸው ሊያደርሱት ከሚችሉት ጉዳት ለመታደግ፣ ለመቆጣጠርና ለመፍታት በዋናነት መደበኛና ባህላዊ ህጎችና ደንቦች አገልግሎት ላይ ውለው ይታያሉ፡፡ መደበኛ  የግጭት ማስወገጃ (የፍትህ) ስርዓት ምንም እንኳን በተወሰነ መልኩ ከአካባቢ አካባቢ፣ ከአገር አገር፣ ከመንግሥት መንግሥት ቢለያይም በአካባቢው ሰላምና መልካም አስተዳደር እንዲኖር ህግና ደንብ ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ባህላዊ (ሀገረሰባዊ)

የግጭት አፈታት ስርዓቶች ረዘም ላሉ ዘመናት ትኩረት ሳይሰጣቸው ወይም በመደበኛው ስርዓት ተፅዕኖ ስር ወድቀው ቢቆዩም አንዳንዶቹ ግን ስርዓቱን ጠብቀው ከዘመን ዘመን፣ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገሩ እስካሁን ቆይተዋል፡፡ ለአብነትም በአብዛኛዎቹ የሀገራችን ብሔረሰቦች በፍትህ ስርዓትነት የሚያገለግለውንና በተናጠል ደግሞ ከየብሔረሰቡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቡናዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ምግባራዊ፣ ልማዳዊ፣ አስተዳደራዊ እና ባህላዊ አሻራ ጋር ተዛማጅነት ያለውን የግጭት አፈታት ስርዓት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሀገር በቀል ከሆኑ ባህላዊ ተቋማት መካከል የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ፓሌታዊ (ሞራ-ከንታ እና ሞራ-ፓሌታ) የዳኝነት ስርዓትና ጐሳዊ የዳኝነት ስርዓት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በኮንሶ የሚፈፀመው የግጭት አፈታት (የዕርቅ) ስነ-ስርዓት በብሔረሰቡ ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ አስታራቂዎቹም በሕዝቡ ዘንድ ልዩ አክብሮትና ተሰሚነት አላቸው፡፡ በፓሌታዊ አደረጃጀትና በጐሳዊ አደረጃጀት የሚፈፀሙ የዕርቅ ስነ-ስርዓቶች ጊዜ የማይወስዱና በማህበረሰቡ የተፈጠሩ ግጭቶችን አስወግደው ዘላቂ ዕርቅና ስምምነት በማምጣት ረገድ ለብሔረሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰገን አካባቢ ሕዝቦች አስተዳደር ዞን በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከናወነውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን በመመርመር አስታራቂዎች (የግጭት መፍቻ ተቋማት) በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን የጐላ ሚና፣ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበትን ስልትና ሂደት ወይም የግጭት አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል በመተንተን በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ አባባሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንዲሁም ትዕምርቶችን በመለየት የስርዓቱን ፋይዳ ማሳወቅ ላይ ያተኩራል፡፡

ጥናቱ በሰባት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን መግቢያ ይዞ በስሩ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብና መተንተኛ ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው እንዲሁም የመስክ ተመክሮን አካትቶ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን ስር የተዛማጅ ድህፎች እና ጥናቶች ቅኝትን እንዲሁም የግጭት ምንነትና መንስኤዎች፣ አይነቶችና የአፈታት ዘዴዎች የሚሉ አጠቃላይ የግጭት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገፅታ

የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህም የብሔረሰቡን ታሪክና ስያሜ፣ ማህበራዊ ተቋማቱንና ባህላዊ አስተዳደርና አደረጃጀቱን የሚያስረዱ መረጃዎችን አካቷል። ምዕራፍ አራት የኮንሶ ብሔረሰብ አባላት ስለ ግጭት ያላቸውን አመለካከት፣ ለግጭት መከሰት መነሻ የሚሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶችና ግጭቶች ሲከሰቱ እንዴት በባህላዊ ዘዴ እንደሚፈቱ አጠቃላይ የግጭት አፈታት ተቋማት አደረጃጀቱንና የአፈታት ሂደቱን ያመላክታል። በምዕራፍ አምስት የብሔረሰቡ ባህላዊውና መደበኛው የፍትህ ስርዓት ቅንጅታዊ አሰራር ቀርቧል። ምዕራፍ ስድስት ትንተናና ቁዘማን ምዕራፍ ሰባት ደግሞ ማጠቃለያና ይሁንታዎችን አካትቶ ይዟል። በመጨረሻም ጥቅስማ እና አባሪዎች ተካትተዋል።

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የኮንሶ ብሔረሰብ ለአካባቢውና ለማህበራዊ ግንኙነቶቹ በተለይም ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚሰጠው ግምት እጅጉን የላቀና ከፍተኛ ነው። ይሁንና እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች የማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ አልዳሰሱም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀዳሚነት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ የተገፋፋሁበት (ያነሳሳኝ) መሰረታዊ ምክንያት "የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር" የአገራችን ዘጠነኛ ቅርስ[1] ሆኖ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና ባህል ተቋም (ዩኔስኮ) በ2003 ዓ.ም መመዝገቡን ተከትሎ በ2004 ዓ.ም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጋር በመተባበር በሰገን አካባቢ ሕዝቦች አስተዳደር ዞን በኮንሶ ወረዳ ካራት ከተማ ባዘጋጁት "ሀገር አቀፍ የእውቅና ፕሮግራም" ላይ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በኩል የበዓሉ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆኜ በመወከል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አካባቢው በሄድኩበት ወቅት ከብሔረሰቡ ተወላጆችና ከአንዳንድ የጎሳ መሪዎች ጋር የመተዋወቅ ዕድሉ ተፈጥሮልኝ ስለብሔረሰቡ አንዳንድ ነገር ለማወቅ ባደረግኋቸው ኢ-መደበኛ ውይይቶች ስለብሔረሰቡ ታሪክ በርካታ ጉዳዮችን ለመረዳት መቻሌ ነው። በወቅቱ ካገኘኋቸው መረጃዎች መካከል እጅግ መስጦኝ የነበረው ብሔረሰቡ ውስጣዊ ግጭቶቹን የሚፈታባቸው የቆየ ባህላዊ ስርዓቱ ነበር። የማህበረሰቡ የመተጋገዝ፣ የመተባበርና የመከባበር ሚስጥር ብሎም አሁን ላለበት ደረጃ መድረስ ቁልፉ ጉዳይ

---

[1] ዘጠኙ አለምአቀፍ ቅርሶችና የተመዘገቡበት ጊዜ (እ.ኤ.አ)፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ (1978)፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት (1978)፣ የፋሲል ግቢና ሌሎች ግብረ ሕንጻዎች (1979)፣ የታችኛው አዋሽ ሸለቆ (1980)፣ የጢያ ትክል ድንጋዮች (1980)፣ የአክሱም ሐውልት (1980)፣ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ (1980)፣ የሐረር ጀጎል (2006)ና የኮንሶ ባሕላዊ መልክዓ-ምድር (2011)።

የባህላዊ ስርዓቱ በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት መሆኑን ተገነዘብኩኝ፡፡ ይህ በውስጤ የቀረው ሀገር በቀል ዕውቀት በ2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን ለመከታተል ስወስን የመመረቂያ ጥናቴ "በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት" ላይ እንደሚሆን ውስጤ አምኖበት ለዚሁ ጥናቴ ቀዳሚ አነሳሽ ምክንያቴ አድርጌ አቀረብኩት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

- የማህበረሰቡን እሴት የሚያሳዩ ውስን ጥናቶች ቢኖሩም ከማህበረሰቡ ግጭት አፈታት ጋር በተያያዘ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የቆየው ባህላዊ ስርዓትና ፋይዳ በወጉ አለመጠናቱ፣
- አጥኚዋ ከአንዳንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች ጋር ባደረገችው ኢ-መደበኛ ውይይት ማህበረሰቡ ከመደበኛ የህግ ስርዓት ይልቅ በዚህ ስርዓት መዳኘትን እንደሚፈሩ በመገንዘብ በዚሁ መነሻነት ማህበረሰቡ ይህንን ባህል አጠናክሮ እንዲቀጥልበት ጥናቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እሳቤ መኖሩ፣
- ጥናቱ በብሔረሰቡ እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች ያልተዳሰሰውን የማህበረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማጥናት የታየውን ክፍተት በከፊል በመሙላት በዘርፉ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች ጥሩ የመነሻ ግብዓት ይሆናል የሚሉት ጥናቱን ለማካሄድ ብርቱ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከሰቱ ግጭቶች በባህላዊ የሽምግልና ስርዓት እንዴት እንደሚፈቱ ሂደቱን ማጥናት ነው፡፡

የሚከተሉት ደግሞ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ናቸው፡፡

- ግጭት በኮንሶ ብሔረሰብ ምን ማለት ነው? የሚለውን መግለጽ፣
- በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቻቸው፣ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ሁኔታ እንዲሁም የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት ምን ምን እንደሆኑ መተንተን፣

- የግጭት አፈታት ሂደቱ አስተማማኝነት (የዘላቂነት ሁኔታ)፣ ግጭቶች የሚፈታባቸው ሂደቶችና ዓውዳዊ ክዋኔ፣ብሔረሰቡ ለስርዓቱ ያለውን አመለካከትና ባህላዊ ስርዓቱ ከመደበኛው የህግ ስርዓት ጋር ያለውን ግንኙነት በዝርዝር ማሳየት፣
- በብሔረሰቡ የግጭት መፍቻ ስርዓት ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች፣ በግጭት መፍቻነት የሚያገለግሉ ዘዴዎች፣ በግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ፎክሎርና ሚናቸው፤ እንዲሁም የዕርቅ ማጽኛው ምን እንደሆነ ማሳየትና
- ባህላዊው የሽምግልና ስርዓቱ ያሉትን ጥንካሬና ድክመቶችን መዘርዘር።

## 1.3 የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ ለመመለስ ጥረት የሚያደርግባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ግጭት በኮንሶ ብሔረሰብ ምን ማለት ነው? በብሔረሰቡ የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቻቸው፣ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ሁኔታ እንዲሁም የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት ምን ምን ናቸው?
- የግጭት አፈታት ሂደቱ አስተማማኝነት፣ ግጭቶች የሚፈታባቸው ሂደቶችና ዓውዳዊ ክዋኔው እንዲሁም ብሔረሰቡ ለስርዓቱ ያለው አመለካከትና ባህላዊ ስርዓቱ ከመደበኛው የህግ ስርዓት ጋር ያለው የግንኙነት ሁኔታ ምን ይመስላል?
- በብሔረሰቡ የግጭት መፍቻ ስርዓት ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች፤ በግጭት መፍቻነት የሚያገለግሉ ዘዴዎች ምን ምንድናቸው?
- በግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ፎክሎርና ሚናቸው፣ የዕርቅ ማጽኛው ሁኔታና ባህላዊው የሽምግልና ስርዓቱ ያሉት ጥንካሬና ድክመቶች ምን ምንድናቸው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከላይ የተገለፁትን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች በመያዝ በኮንሶ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ላይ ትኩረት ያደረገው ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የብሔረሰቡን ማንነት፣ ማህበራዊ ህይወትና የአካባቢውን ትውፊታዊ ልማድ ያስተዋውቃል፡፡
- ሀገር በቀል ዕውቀቱ የተሻለ ትኩረት የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥቆማ ያደርጋል፡፡
- በዘርፉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ይደፍናል፡፡
- ስለ አካባቢው (ስለ ማህበረሰቡ) ማንነት ማወቅና ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ ሰዎች እንደግብዓት ያገለግላል፡፡
- ለህግ አጥኚዎችና ተመራማሪዎች የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን፣ በኮንሶ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 3 (ሶስት) ቀበሌዎች ማለትም በዱራይቴ፣ በጋሞሌና ዶካቱ ቀበሌዎች በተሰበሰበ መረጃ ላይ በመመስረት 6 (ስድስት) የግጭት ዓይነቶችን በመለየትና ቀላልና ከባድ በሚል በመመደብ የባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደቱንና በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ አባባሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ትዕምርቶችንና ፋይዳቸውን ይመለከታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከሰቱ ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ ሂደቱን የመግለጽና የመተንተን፤ እንዲሁም በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ አባባሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንዲሁም ትዕምርቶችን በመለየት የማህበረሰቡ አባላት ለስርዓቱ ያላቸውን አመለካከት በጥልቀት መፈተሽና የስርዓቱን ፋይዳ ማሳወቅ ላይ እንደመሆኑ ይህንኑ ዓላማ

ከግብ ለማድረስ ከአውራ መረጃ አቀባዮችና ከሌሎች መረጃ ሰጪዎች እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የተፃፉ የተለያዩ ጽሑፎችን (ዶክመንቶች)ን ተጠቅሞ መረጃ ተሰብስቧል።

### 1.6.1 የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታ

#### 1.6.1.1 የመረጃ አቀባዮች አመራረጥና የዐውድ ሁኔታ

በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ የሚከናወኑ ሂደቶችን፣ የአስታራቂዎችን ሚና፣ እና የሽምግልና ስርዓቱ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ስላለው ግንኙነትና በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ ፎክሎርና ሚናቸውን በተመለከተ የመረጃ ስብሰባው የመጀመሪያው ከጥር 3 እስከ የካቲት 2 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ፣ ሁለተኛው ከሚያዚያ 4-6 ቀን 2006 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን፣ በዋናነት በኮንሶ ወረዳ ከሚገኙ 41 (አርባ አንድ) የገጠር ቀበሌ ማህበራት ውስጥ በካራት አገልግሎት ስር ባሉ 3 (ሶስት) ቀበሌዎች ማለትም በዱራይቴ፣ በጋሞሌና በዶካቱ ቀበሌዎች ነው። እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡት በዋናነት የአገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎችን ልምድና ችሎታ መሰረት በማድረግ በቂ መረጃ መስጠት የሚችሉ ሰዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንደሚቻል የኮንሶ ወረዳ ዋና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊዎችና ተወካዮች ጥቆማ ነው። ከተመረጡት ቀበሌዎች በዱራይቴ ቀበሌ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች ቁጥራቸው ከፍተኛ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የኮንሶ ወረዳ አስተዳደር ጥቆማ እንደተጠበቀ ሆኖ የአጥኚዋም ጊዜያዊ ማረፊያ ይሄው ቀበሌ በመሆኑ እነዚህኑ አውራ መረጃ አቀባዮች በቀላሉ ለማግኘት በመቻሉም ነው።

የአውራ መረጃ አቀባዮች የስልጣን ስብጥር ሁኔታን በተመለከተ አንድ የጎሳ መሪ (የዳውራነት ወይንም የመንፈሳዊ አባትነትን) ስልጣን ደርቦ የሚሰራ ከጋሞሌ ቀበሌ፣ አንድ የወጣት ትውልድ ቡድኑን (ኼላውን) የሚወክል ከዱራይቴ ቀበሌ፣ አንድ የክስ መስራች (ኾራታ) ተቀባይ ወኪል ከዱራይቴ ቀበሌ፣ 5 በባህላዊ የሽምግልና ስርዓቱ ረጅም ዓመታት ልምድ ያላቸው ታዋቂ ሽማግሌዎች 3ቱ ከዱራይቴ፣ 2 ከዶካቱ፣ 3 ሴቶች ከዱራይቴ በድምሩ 11 በአውራ መረጃ አቀባይነት፣ ከፍትህ አካላት 3 ሴቶችና 2 ወንዶች በድምሩ 5 በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል። በአጠቃላይ ለዚህ ጥናት በአውራ መረጃ አቀባይነትና በሌሎች መረጃ ሰጪነት የጎሳ መሪ፣ ሽማግሌዎች፣ ሴቶች እና የወጣት ቡድን ተወካይ እንዲሁም ከፍትህ አካላት በጠቅላላ 16 ሰዎች (11 ወንዶች እና 5 ሴቶች) የተሳተፉ

ሲሆን ከ25-73 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። የሴቶቹ ቁጥር ያነሰበት ምክንያት በብሔረሰቡ ሴት ልጅ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ላይ አትቀመጥም የሚለው አባባል ያለና አሁንም እየተተገበረ፣ ሴቶቹም አሜን ብለው የተቀበሉት ስለሆነ እንደወንዶቹ በነጻነት ለመናገር ስለማይደፍሩም ነው። በተጨማሪም ሴቶች በብሔረሰቡ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳትፎ ባይኖራቸውም ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የጎላ ተሳትፎ እንዳላቸው ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ግንዛቤ በመያዙ የሴቶችን ልምድ፣ ዕውቀትና ለአንዳንድ መድረኮች የመብቃት ተመክሮ እንደተለየ ስልት በመጠቀም በጊዜያዊ ማረፊያነት ከምኖርበት ዱራይቴ ቀበሌ 3 ሴቶች በአውራ መረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል፡፡

### 1.6.1.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለፎክሎር ጥናት መስክ በመውጣት በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች ማለትም በምልከታ (observation)፣ ቃለ መጠይቅ (interview) እና መጠይቅ (questionnaire) መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል (ፈቃደ፣ 1991፡ 90) በገለጸው መሰረት በኮንሶ ብሔረሰብ የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሚከናወንበት ተፈጥሮአዊ ዐውድ ላይ በአካል በመገኘትና ከነዚሁ ሶስት ዓይነት የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ለዚህ ጥናት ምልከታ እና ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ጥሬ መረጃዎችን በማሰባሰብና መልክ ሰጥቶ በማደራጀት ትንታኔው ተካሂዷል። መረጃውን ለማሰባሰብና መልክ ሰጥቶ ለመተንተን ሁለት ዓበይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እነሱም የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ በሚል ጥቅም ላይ ውለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ምልከታና ቃለመጠይቅ በሚደርግበት ወቅት መረጃው በመቅረፀ ድምጽና በምስል በመታገዝ ተሰብስቦ ትንታኔው ዳብሯል።

#### 1.6.1.2.1 የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

**ቃለ-መጠይቅ**

ቃለመጠይቅ ከተጠኚው ብሔረሰብ አባላት መካከል በዕድሜ፣ በጾታ፣ በሙያ፣ በልምድ ወዘተ የተመረጡ መረጃ አቀባዮችን በጥያቄና በመልስ አማካይነት ስለተፈለገው መረጃ በገለጻና በማብራሪያ እንዲሁም በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ጽሁፍ ማስታወሻ በመያዝ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል ዘዴ ነው (የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ኢንቬንተሪ ማንዋል፣ 2002፣ 60-70)፡፡ ዘዴው ዕድሜን፣ ጾታን፣ ሙያንና ልምድን መሰረት በማድረግ መረጃ

የሚሰበሰብበት በመሆኑ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት እንደሚያግዝ ያብራራል፡፡ በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት ስለኮንሶ ብሔረሰብ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘትና ስለብሔረሰቡ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት ተፈጻሚነት ላይ ተቀዳሚ ሚና ያላቸውን አውራ መረጃ አቀባዮችን በብሔረሰቡ ዕይታ የግጭት ምንነት፣ ዓይነትና መንስዔ፣ የግጭት መፍቻ ተቋማት ማንነት፣ ሚና፣ የመምረጫ መስፈርትና የአፈታት ሂደትን የሴቶችን ሚና፣ ወንጀለኛን በማጋለጥ ረገድ የማህበረሰቡ የትብብር ሁኔታ ምን እንደሚመስል፣ የችሎት ቀናትና ጊዜ፣ ስለ ሞራ አገልግሎት፣ ለመሀላ ስለሚዳርጉ ወንጀሎችና መሀላ መፈጸም የሚሰጠው ግምት፣ ወንጀለኞች ቅጣታቸውን ፈጽመው ወደቀያቸው ሲመለሱ ስለሚኖረው ስርዓትና ተያያዥ ጉዳዮች፣ በተደጋጋሚ ለፍትህ ስርዓቱ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች እንዲሁም በብሔረሰቡ ስላሉ የማህበራዊ ተቋማት ሁኔታን አስመልክቶ በቃለመጠይቅ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም ከመደበኛ የፍትህ ስርዓት ጋር ያለ የቅንጅት ስራ፣ የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ብርታቶችና ድክመቶች ከአውራ መረጃ አቀባዮችና ከመረጃ ሰጪዎች ተሰብስቧል፡፡ በቃለ-መጠይቁ ውስጥ ክፍትና ሁነት የሚጠራቸው እግረ-መንገዳዊ ጥያቄዎች እየተነሱም የተፈለገውን መረጃ ለማሰባሰብ አገልግሏል፡፡

### የአካል ምልከታ

የአካል ምልከታ ከተጠኚው ማህበረሰብ ጋር አብሮ በመኖር የዕለት ተዕለት ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በመመልከት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ስለጉዳዩ ማስታወሻ በመያዝ፣ በፎቶግራፍና በቪድዮ በመቅረጽ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል ዘዴ ነው (የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ኢንቬንተሪ ማንዋል፣ 2002፡ 70)፡፡ ዘዴው በቃለመጠይቅ ወቅት አጥኚው ግራ የተጋባበትንና በምልከታው ወቅት የተለያዩ ግርታዎችና ጥያቄዎች የፈጠሩበትን ጉዳዮች በማስታወሻ ይዞ በመጠየቅ ከመረጃ አቀባዮች በሚሰጠው ምላሾች ግርታዎችን በማጥራት ለጥያቄዎች ምላሽ የሚያስገኝ በመሆኑ ጠቃሚ ዘዴ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናት በብሔረሰቡ ከቀላል ግጭት የግለሰብና የጎረቤት፣ ከከባድ ግጭት ድብደባ መፈጸምን አስመልክቶ ግጭቱ በባህላዊ የሽምግልና ስርዓት ፍጻሜ እንዴት እንደሚያገኝ ሂደቱንና አውዳዊ ክዋኔውን የአካል ምልከታ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

**የውስን አትኩሮት ቡድን ውይይት**

የውስን አትኩሮት ቡድን ውይይት ስለተጠኚው ብሔረሰብ አጠቃላይ ሁኔታ ሰፊ ዕውቀትና ክህሎት አላቸው የተባሉትን አስረጂዎች አንድ ላይ አሰባስቦ (ቁጥራቸው ከ3-5 ሊሆኑ ይችላሉ) ውይይት የሚደረግበትና መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ስልት ነው (የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ኢንቬንተሪ ማንዋል፣ 2002፡ 70)። በዚህ መሰረት የብሔረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማዋቀርና በመተግበር ሂደት የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉ፣ የጾታና ዕድሜ ስብጥሩን ሚዛናዊ ባደረገ መልኩ ከ5-7 የሚሆኑ አባላትን አካቶ በተደረገ የቡድን ውይይት ላይ በመሀከላቸው በመገኘትና በማዳመጥ ግጭት ስለሚወገድበት ሁኔታ፣ ስለባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ አጀማመር፣ ፋይዳና የዘላቂነት ሁኔታ፣ በቃለመጠይቅና በአካል ምልከታ ወቅት አሻሚ አሊያም ግልጽ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ለመረዳት ለምሳሌ የሴቶችን በስርዓቱ ኢ-ቀጥተኛ ተሳትፎ፣ ስለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ የአጀማመር ቅደም ተከተል ሁኔታ በተለይ በሶስት ሽማግሌዎች ስለመጀመሩና ተምሳሌትነቱ ምን እንደሆነ፣ የወንጀለኞች ከቅጣት በኋላ ወደቀያቸው መመለስ ከአዲስ ዓመት ጋር ስለመያያዙ፣ በሞራ ላይ ስላለ የቅጣት ሁኔታና ወንጀለኛን በማጋለጥና በማቅረብ ረገድ የኼላውን ሚና የተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል።

**1.6.1.2.2 ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ**

አንድ የፎክሎር አጥኚ በመስክ ስራ ላይ ከመሰማራቱ በፊት የመስክ ምርምሮች አከዋወን፣ በዘርፉ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችና መጣጥፎችን ማንበብ የቅድሚያ ስራው መሆን እንዳለበት (ፈቃደ፣ 1991፡ 91) ይገልጻል። በዚህ መሰረት የኮንሶ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ ስያሜ፣ ቋንቋና ኃይማኖትና የኢኮኖሚ መሠረት፣ አካባቢውን የሚያስተዋውቁ፣ ስለግጭት ጽንሰ ሀሳብ ምንነት የሚያወሱ፣ ስለባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓቶች ምንነት የሚተነትኑ የተለያዩ መጻሕፍትና የምርምር ጽሁፎችን በመመልከት እንደ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ይህ አካሄድ በመስክ ለተከናወነው የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ማሰባሰቢያ ስራ በቂ ግንዛቤ እንዲያዝ አግዟል።

## 1.6.2 የጥናቱ መተንተኛ ዘዴ

ከላይ በቀረበው መልኩ የተሰበሰበው መረጃ በዋነኛነት ገላጭ በመባል የሚታወቀውን ዘዴ በመጠቀም የተተነተነ ሲሆን፣ የጥናት ዘዴው የተመረጠው በኮንሶ ብሔረሰብ የሚከሰቱ

ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ የሽምግልና ሰርዓቶች ምንነት ለማብራራት፣ አስታራቂ ሽማግሌዎች በማንና እንዴት እንደሚመረጡና በሽምግልና ስርዓቱ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመግለጽ፣ ተግባራቱ የት፣ መቼ፣ በማንና እንዴት እንደሚከናወኑ ለመተንተንና ትንተናውን መሠረት በማድረግ ወደ ማጠቃለያውና ይሁንታው ለመድረስ አመቺ በመሆኑ ነው። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ በባህላዊ የሽምግልና ስርዓትና በመደበኛ የፍርድ ቤት አሰራር መካከል ያለውን ግንኙነት በመጠኑ ለመግለጽና ለመተንተን የተሻለ አማራጭ ዘዴ በመሆኑ ተመርጧል። በዚህ ሂደት በመቅረፀ ድምፅ እና በምስል የተገኙ መረጃዎች አስፈላጊውን መግለጫ በመስጠትና በ "መከስበር" (Transcribe በማድረግ) ትንታኔው ተሰርቷል። በዚህ ወቅት በመገኛ ቋንቋቸው (በኮንስኛ) ለተሰበሰቡ መረጃዎች የብሔረሰቡን ቋንቋ በጥሩ ሁኔታ እንደሚያውቁና የማህበረሰቡን ዕውቅና ባገኙ የብሔረሰቡ ተወላጆች እገዛ የትርጉም ስራ ተካሂዷል።

## 1.7 በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

### 1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት በሚከናወንበት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው።

- የኮንስኛ ቋንቋ ፊደሎች ሲነገሩ ድምጻቸው የሚዋጡ በመሆናቸው ቃላቱን በትክክል ለመጻፍ መቸገር፣ ፊደላቱም ሲጻፉ ከላይ ጭረት ያላቸው በመሆኑ ለኮምፒዩተር ጽሁፍ አስቸጋሪ መሆን፣
- ለአንዳንድ ኮንስኛ ቃላት ወጥ የአማርኛ ፍች አለመገኘትና ትክክለኛውን ለመጻፍ መቸገር፣
- አንዳንድ መረጃ አቀባዮች በቀጠሮ ሰዓት ያለመገኘትና የተለያዩ ምክንያቶችን መፍጠር፣
- በመጀመሪያው ዙር የአንድ ወር የመስክ ቆይታ ቀላልና ከባድ ግጭቶችን በአካል ምልከታ መረጃ ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት በርካታ የቀላል ግጭቶች የአፈታት ሂደት ማየት የሚቻልበት አጋጣሚ ቢፈጠርም የተለያዩ ሕዝባዊ ስራዎች የሞራ (ባህላዊ የዳኝነት ጎጆዎች) ጥገና፣ ምርቃት ወዘተ መኖርና በዓላትም መከታተላቸው ብዙ የጉዳይ ማያ ቀናት መውሰዳቸው፣ ከባድ ግጭትንም በተመለከተ በአጋጣሚ የሚከሰት

በመሆኑ በመጀመሪያው ጉዞ ይህ ባለመሳካቱ የሁለተኛ ዙር የመስክ ምልከታ ማስፈለጉ፣ ተጨማሪ ጊዜና በጀት መጠየቁ፣

- በአካባቢው ለረጅም ጊዜ ውኃና መብራት አለመኖር፤ እንዲሁም ለስራው ምቹ ቦታና የስልክ አገልግሎት ችግር በከፍተኛ ሁኔታ መኖር በየዕለቱ የሚገኙ መረጃዎችን ወደጽሁፍ ለመቀየር ጫና መፈጠሩ፣ ከጤንነት አኳያም መረጃን ለመሰብሰብ በተወሰነ መልኩ ችግር መግጠሙ፣

### 1.7.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ መፍትሄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የብሔረሰቡ ተወላጆች የሆኑ የተማሩ ሰዎች በመፈለግ ፊደላቱን ወደጽሁፍ እንዲቀይሩት በማድረግ ትክክለኛ የፊደላቱን አጻጻፍ ለማግኘት ተሞክሯል፣
- ወጥ የአማርኛ ፍች ላልተገኘላቸው አንዳንድ የኮንስኛ ቃላት የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅና የብዙ ሰው ሀሳብ (ፍች) የሆነውን በመጠቀም፣
- የመረጃ አቀባዮችን ፍላጎት በአስተርጓሚዬ በኩል በመረዳት ቀጠሮን ማስተካከልና የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት በመሞከር፣
- በተለያዩ ሕዝባዊ ስራዎች ምክንያት ያልታዩ ጉዳዮችን በግልና በአስተርጓሚዬ ክትትል ጥረት በአንድ ቀን ሁለት የቀላል ግጭት አፈታት ሂደትን ለመመልከት በመቻል፣ ወቅት ጠብቆ ሁለተኛውን የመስክ ጉዞ በማድረግም አንድ የከባድ ግጭት አፈታት ሂደትን በመመልከት መረጃውን ምሉዕ ለማድረግ በመሞከር፣
- መብራት በሚኖርበት ጊዜ ሌሊትን ጨምሮ የጽሁፍ ስራ በመስራት፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በተለይም በመስክ ቆይታዬ ከምኖርበት ቀበሌ ጎረቤቶች ጋር ቅርበት በመፍጠር ለጤንነቴ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አልፎ አልፎ እንዳገኝ በመመቻቸቱ፣ የአስጎብኚ ድርጅቶችን (Tour Guide) ቢሮን በቀን እንድገለገልበትና በመደበኛ የስልክ አገልግሎትም እንድጠቀም ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ለማግኘት በመቻል፣

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ጠቃሚ ተመክሮዎች

በመረጃ ስብሰባ ወቅት የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን አስመልክቶ ከመደበኛው ይልቅ ኢ-መደበኛ የሆነው መንገድ የበለጠ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት እንደሚያስችል የተረዳሁበት አጋጣሚ ነበር። ለአብነትም፡-

- በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ለመረጃ ሰጪዎች ጥያቄዎችን ሳቀርብ አጭር ወይም ከጥያቄው ጋር ያልተገናኘ መልስ የማግኘት ሁኔታ ገጥሞኛል፣ ይህ ያስተማረኝ ነገር ቢኖር ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ በብሔረሰቡ "ጨቃ" (ባህላዊ መጠጥ) በሚዘወተርባቸውና አብዛኛው የአካባቢው ሽማግሌዎች በሚሰበሰቡበት ስፍራ ተመሳስሎ በመቀመጥ እየተጫወቱ እግረ መንገድ የፈለጉትን ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ መሞከር ጥሩ አማራጭ መንገድ እንደሆነ የተረዳሁበት መሆኑ፣
- በሥራና በሌሎች አጋጣሚዎች የአካባቢና የግለሰቦች ቀደምት እውቀት መኖር በመረጃ ስብሰባ ወቅት ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ መሆኑና
- በመረጃ ስብሰባ ወቅት የማነሳቸው ጥያቄዎች መረጃ ሰጪዎችን ይበልጥ ስለ አካባቢያቸው እንዲመረምሩ፣ ሌሎች ያልተጠኑ ጉዳዮችን እንዲያነሱ እድል መፍጠሩ፣ ለአብነት ከአመጣጣቸው ጋር አያይዘው የሚያነሷቸውን የተለያዩ "ሚቶች"ን መጥቀስ ይቻላል።

ስለብሔረሰቡ በቀጣይ በምን ላይ ጥናት ወይንም ምርምር ማድረግ እንደሚቻል መነሻ የሚሆኑ ጋብቻና ሞትን መሰረት ያደረጉ ሀሳቦችን ማግኘት መቻሉ፣ ለመጥቀስ ያህል፡-

ጋብቻን በተመለከተ፡-

- በብሔረሰቡ ወንድ ልጅ ያልወለደ እንደሙሉ ሰው አይቆጠርም፣ እሱ ከሰው እኩል አይደለም ይባላል፣ በትዳር ህይወት ውስጥም ትልቅ ተፅእኖ አለው ለምሳሌ ወንድ ልጅ ካልወለደ ሀብት ንብረቱ በሙሉ ለጉሳው ወንድ ዘመድ ይሰጣል ይህን ከ'Gender' ጋር በማያያዝ እንደ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ማጥናት ይቻላል።
- በትዳር ላይ ባል ሲሞት የባል ታናሽ ወንድም የታላቅ ወንድሙን ሚስት ያገባል፣ ልጆቹንም ያሳድጋል በሚል የንብረቱ ባለቤት ይሆናል። ሴቷ ምንም ድርሻ

የላትም፣ የሞተው ታናሽ ወንድም ከሆነ ግን ታላቅ ወንድሙ የታናሽ ወንድሙን ሚስት አያገባም በባህሉ እንዲያገባት አይፈቀድም ይህም ሊጠና ይችላል።

- በብሔረሰቡ ሴት ልጅ ስትወለድ ወደ ሌላ ጐሳ በትዳር የምትሄድ ስለሆነች እንደቤተሰብ አባል አትቆጠርም፤ እንደወንዱ ክብር የላትም ይህም ሌላ ጉዳይ ነው።

ከሞት ጋር ተያይዞ፡-

- ያገባና ያላገባ፣ አግብቶ የወለደና ያልወለደ፣ ወንድ ልጅ የወለደና ያልወለደ ሕፃንና ሽማግሌ ሆኖ ሲሞት ሁሉም የየራሱ የአለቃቀስ ስርዓት አለው። በለቅሶ ስርዓቱ ትልቅ ልዩነት አለ፤ ይህም አንድ የጥናት ጉዳይ ሆኖ ሊታይ ይችላል።
- በብሔረሰቡ ወጣት ልጅ ከ15-18 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ሴትም ሆነ ወንድ ቤት ውስጥ ቢሞቱ ማንም ሰው ሳያይ ቤተሰብም ቢሆን ሌሊት ቀብሩ ይከናወናል፤ ውጭ ከሆነ ደግሞ የሟች ሬሳው መኖሪያ ቤት ሳይገባ በዚያው ወደ ቀብር ቦታ ይወሰድና ይቀበራል፤ በተጨማሪም አንድ ሰው ከመንደሩ ውጭ ሞቶ ሬሳው መገኘት ካልቻለ ወይ ከልብሱ አሊያም ከፀጉሩ ተፈልጐ መጥቶ በራሱ ቀብር ላይ ይቀመጥለታል። ይህም አንድ የጥናት ጉዳይ ሊሆኖ ይችላል።
- በብሔረሰቡ የጎሳ መሪ ከሞቱ በኋላ ለ9 ዓመት፣ ለ9ወር፣ ለ9ቀንና ለ9 ሰዓት አስከሬናቸው እቤት ቆይቶ ይቀበራሉ። በቆይታቸው በሕይወት እንዳሉ ተደርጎ ‹‹ታመዋል›› ‹‹ጉንፋን ይዟቸዋል›› ይባላል እንጂ ሞተዋል አይባልም። ከቀብሩ 9 ቀን በፊት መሞታቸው ታውጆ ለሳምንት ያህል ከበሮ እየተመታ እየተሞካሹ ይዘፈንላቸዋል። ባህላዊ ጭፈራው በብሔረሰቡ ‹መና› የሚባል ሲሆን ለፖቅላው (ለጎሳ መሪው) ብቻ የሚዘፈን ነው። ሀዘናቸውን በዘፈን መግለጻቸው የእሳቸውን ዕድሜ ይስጠን፣ እንደ እሳቸው ያኑረን የሚል እንድምታ አለው። ስለዚህ ሂደቱና ከ9 ቁጥሩ ጋር ተያይዞ አንድ የጥናት መነሻ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ እነዚህ በኢ-መደበኛ ውይይትና ጨዋታ የተገኙ በመሆናቸው ለምን በሚል ለጥናትና ምርምር መነሻ ሀሳብ ስለሚሆኑ እንደጠቃሚ ተመክሮ በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል።

# ምዕራፍ 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ የመስኩ ምሁራንን በማጣቀስ ከግጭት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽሁፎች ይዳሰሱበታል፡፡ በዋናነትም ስለግጭት ምንነት፣ ዓይነትና መንስኤዎች (የሚቀሰቀስባቸው መስኮች)፣ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች፣ የግጭት ፋይዳ፣ የግጭት አፈታትና ፎክሎር፣ በኢትዮጵያ የባህላዊና መደበኛው ግጭት አፈታት ስርዓት ቅኝት እንዲሁም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይቀርብበታል፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1.1 የግጭት ምንነት ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች

ግጭት ለሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተለያዩ ትንታኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ ለአብነት በደስታ ተክለወልድ ያማርኛ መዝገበ ቃላት (1962፣ 249) ግጭት መግጨት፣ መገጨት፣ ድንገተኛ ጥል፣ ዕለተ ጠብ፣ ያልታሰበ አደጋ የጊዜ ጦርነት ሲል ይገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል ግጭት የማህበራዊ ኑሮ ተጋሪ በሆኑ ቡድኖችና ሕዝቦች መካከል በሚኖር ተቃራኒ ፍላጐቶች፣ እሴቶች እና ግቦች ምክንያት በሚከሰቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ቁሳዊ መበላለጦች አማካይነት የሚከሰት ትግል እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይስማማሉ፡፡

> "*Conflict is the struggle over values or claims to status, power, and scarce resources, in which the aims of the groups or individuals involved are not only to obtain the desired values, but to also neutralize, injure, or eliminate rivals*" (Coser, in Porter, 1967: vii).

ደጀኔ (2004፡ 165) Douglas (1996) ን በመጥቀስ ግጭት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች ወይም ፓርቲዎች መካከል የተለያየ ፍላጎት መኖር ነው ሲል የገለጸ ሲሆን በሌላ በኩል Fisher (2000) ን በመጥቀስ ግጭት ማለት የማይጣጣም ወይም የማይገናኝ ግብ ያላቸው ወይም አለን ብለው የሚገምቱ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ፓርቲዎች መካከል ያለ ግንኙነት ነው ሲል ያስረዳል፡፡

ግጭት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩና በተደራጀ ሁኔታ መጠናት የጀመረው ከ20ኛው ክፍለዘመን ጀምሮ እንደሆነ፣ ጽንሰ ሀሳቡም የፊት ለፊት ውጊያ፣ ጦርነትና ትግል ተደርጎ ይቆጠር እንደ ነበርና ቀስ በቀስ ይህ አመለካከት እንደተቀየረ፤ በምትኩ ግጭት ለሚለው ጽንሰ

ሀሳብ አለመግባባት፣ በፍላጎት ወይም በሀሳብ ተቃራኒ ሆኖ መገኘት የሚለው ትንታኔ ተተካ ሲል ደጀኔ (2004፡ 165) patz (2000)ን በመጥቀስ ይገልጻል።

በተጨማሪም ግጭት ለቡድኖች መበላለጥ ምክንያት በሆነው ሰፊ ማህበረ-ባህላዊ ሥርዓት ላይ ትችት ከመሰንዘር ባለፈ ለመደብ ትግል መቀስቀስ መንስዔም ሊሆን እንደሚችል ምሁራን ያስረዳሉ።

> "*Social conflict is one of the most ubiquitous of events and encompasses a broad range of phenomena, including class, racial, religious, & community conflicts plus riots, rebellions, revolutions, strikes, marches, demonstration, & protest rallies*" (Oberschall, 1978: 291).

በሌላ በኩል ግጭት የላቀ ጠቀሜታ ያለውን የጥሬ ሀብት ክምችት ያለ ተጋሪ በባለቤትነት ለመቆጣጠር የሚደረግ ፍጥጫ መሆኑንም ያስረዳሉ።

> "*Conflict is a situation of competition in which parties are aware of the incompatibility of potentially future positions and in which each party wishes to occupy a position that is incompatible with the wishes of the other*" (Boulding, 1962: 4).

Simmel (1964) በ Porter (1987፡ 3-4) እንደተጠቀሰው የግጭት ጽንሰ ሀሳብ መገለጫ የሆኑ ሁለት ዓበይት ገጽታዎች እንዳሉ እነሱም Objective እና Subjective መሆናቸውን ያብራራል። የግጭቱ ተቀዳሚ ትኩረት ከተጨባጭ መስፈርቶች አንጻር መሟላት ያለበት ጉዳይ ወይም የግለሰቦች ማንነት ነጸብራቅ ሊሆን መቻሉ እንደሆነ ይጠቁማል። አያይዞም የቅድሚያ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ የሚፎካከሩት ወገኖች ፊት ለፊት ሲፋጠጡ በግል ሊያሳኩት የሚፈልጉትን ግብና የማሕበረሰቡን የጋራ ይሁንታ ባገኙ እሳቤዎች ላይ መሰረት ያደረጉ ውጤቶችን ለማምጣት በማሰብ እንደሆነ ይተነትናል። የግጭቶችን መንታ ገጽታ በውል ለመረዳት አገዛ የሚያደርግ ተጨባጭ ምሳሌም እንደሚከተለው ይጠቅሳል።

> *"If one fights with somebody to obtain his money, wife, or fame, one uses quite other forms and techniques than if one competes with him as to who is to channel the publics, money in to his pockets, who is to win a woman's favor, who, by deed or word, is to make a greater name for himself"* (Simmel,1964: 57).

ከላይ ከቀረበው ገለጻ መገንዘብ የሚቻለው ግጭት በአመለካከት የማይጣጣሙ፣ በአስተሳሰብ የማይግባቡ፣ በስራ የሚፎካከሩ በሀሳብ የሚለያዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት ለመቀዳጀት አሊያም አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ ወይም ለመጨቆን ሆን ብሎና አስቦ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚከሰት ሂደት መሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪ ለግጭት መከሰት እንደዋነኛ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉት የስልጣን ጥም፣ ሙሰኝነት፣ በአድልኦ ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ፣ ራስ ወዳድነት፣ ወገናዊነት፣ የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

ከትንታኔዎቹ መረዳት የሚቻለው በአብሮ መኖር ሂደት ግጭት አይቀሬ ክስተት ቢሆንም አንድ ወጥ የሆነና በቅድሚያ ተለይቶ የሚታወቅ ውጤት አለው ለማለት ግን በእጅጉ አዳጋች ነው፡፡

### 2.1.2 የግጭት አይነቶችና መንስኤዎች

በግጭት አፈታት ዙሪያ በተሰሩ ቀደምት ስራዎች ላይ ለተለያዩ የግጭት ዓይነቶች የተለያዩ መንስዔዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የተገለጸ ሲሆን፣ ከቀደምት ስራዎች ተዋሪ አንዱ የሆነው Katz (1965: 356) ግጭት ከመነሻ ምክንያቶቻቸው አንጻር በሶስት ይከፍላቸዋል። እነሱም፡- የኢኮኖሚ፣ የዕሴትና የስልጣን ግጭቶች ናቸው። ተዋሪው የገለጻቸው አጠቃላይ ጨመቅ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የኢኮኖሚ ግጭት፡-**

የኢኮኖሚ ግጭት የምንለው የላቀ ጠቀሜታ ያለውን ወይም ውስን የሆነ የጥሬ ሀብት ክምችትን ያለ ተጋሪ በግል ባለቤትነት ለመቆጣጠር ባለ ፍላጎት የሚከሰት ፍጥጫን ነው፡፡

**የዕሴት ግጭት፡-**

የዕሴት ግጭት በኃይማኖት፣ በርዕዮተ-ዓለም፣ በአስተሳሰብና በባህል ልዩነት ወዘተ ሳቢያ በሚፈጠር አለመግባባት የሚከሰት ልዩነት ወይም ግጭት ነው።

**የስልጣን ግጭት፡-**

የስልጣን ግጭት በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል በሚኖር ፖለቲካዊና ማህበራዊ አወቃቀር ውስጥ መንበረ ስልጣንን ለማቆየት ወይም ከፍ ለማድረግ በሚኖር ፍላጎት ምክንያት የሚቀሰቀስ ግጭት ነው፡፡

### 2.1.3 የግጭት አፈታት ዘዴዎች

ግጭት በአግባቡ ሳይፈታ ቀርቶ አንዴ ፈሩን ከለቀቀ አሳስፈላጊ ወደ ሆነና አደጋ ሊያስከትል ወደሚችልበት አስከፊ ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል። በተፃራሪው ግጭት በከፍተኛ ጥንቃቄና ብልሃት ከተፈታ አመርቂ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻልበትን አጋጣሚ መፍጠር ያስችላል። በመሆኑም ግጭትን በከፍተኛ ጥንቃቄና ብልሃት ለመፍታት የሚያስችል ዕውቀት መገብየትና ልምድ ማካበት የአብሮ መኖር ሂደትን ውጤታማ፣ የጋራ ስራን ስኬታማ በማድረግ ረገድ ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ያበረክታል።

የግጭት መፍቻ ዘዴ በዕድሜው የግጭት እኩያ ነው:: የተለያየ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ቢኖሩም ሁሉም በጠበኞች መካከል ዕርቅ በማውረድ ሙሉ በሙሉ ሰላም የሚሰፍንበት አጋጣሚ እንዲፈጠር ይረዳሉ። ሆኖም ግን  በሰው ልጆች የምዕተ ዓመታት ታሪክ ሰላም ሙሉ በሙሉ የሚሰፍንበት አጋጣሚ ባለመፈጠሩ ግጭትን በተገቢው መንገድ ለመፍታት እገዛ የሚያደርጉ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። Porter (1987: 19-34)፣ Simmel (1964)፣ Coser (1967) ና Boulding (1962) የተባሉ የዘርፉ ምሁራን በመጥቀስ ስምንት ዓይነት የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ። ዘዴዎቹም ገለል ማለት፣ በኃይል መርታት (ድል ማድረግ)፣ ማስተማርና ማቀራረብ፣ ቅጽበታዊ ሽሽት፣ ዕርቅ አፈላላጊ የግጭት መፍቻ፣ ግልግል፣ መደበኛ የብይን ስርዓት  እና ዕርቅ-ፈሪ መሆናቸውን ያብራራሉ።

**ገለል ማለት**

ገለል ማለት በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ዘዴ ግጭት ተወግዶ ዕርቅ የሚሰፍንበት ሳይሆን፣ በመሀከላቸው ለተከሰተው ግጭት የተሻለው አማራጭ የአንደኛው ወይም የሁለቱም ከቦታው ገለል በማለት የማቋረጥ እርምጃ ነው።

**በኃይል መርታት/ድል ማድረግ**

በኃይል መርታት በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ዘዴ ለግጭት የተዳረጉና በጸብ የሚፈላለጉ ወገኖች ፍልሚያ የሚገጥሙበት፣ በፍልሚያው ኃይሉ በርትቶ፣ ክንዱ ፈርጥሞ በለስ የቀናው ድል የሚያደርግበት፣ ኃይል አንሶት ክንዱ ዝሎበት ለሽንፈት የተዳረገው ወገን ሽንፈቱን በጸጋ ተቀብሎ፣ በይፋ የሚያምንበትና አሸናፊና ተሸናፊ በመሀከላቸው ሰላማዊ ግንኙነት የሚመሰርቱበት ሂደት ነው።

### ማስተማርና ማቀራረብ

ማስተማርና ማቀራረብ በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ዘዴ በዋናነት በጎሳዎች መካከል፣ ና/ወይም ለዘር መድልኦ በተጋለጡ ቡድኖች መካከል የሚቀሰቀስን ግጭት በፕሮፖጋንዳ መልኩ በሚሰጥ ትምህርት አዘል ቅስቀሳ ለግጭቱ ጊዜያዊ መፍትሄ የሚያስገኝ ስልት ነው። ይህ የመፍትሄ አቅጣጫ ከስር-ከመሰረቱ በመመርመር የማያዳግም መፍትሄ የሚያመጣ አይደለም። በመሆኑም ዘዴው ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የታሰበውን መፍትሄ እንጂ ያልታሰበ አደጋ አስከትሎ እንዳይመጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንደሚኖርበት በማህበራዊ-ስነ ልቡናዊ የጥናት መስክ የተሰማሩ ምሁራን ይመክራሉ (Porter, 1987: 22)::

### ቅጽበታዊ ሽሽት

ቅጽበታዊ ሽሽት በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ በውስጡ ኢ-አመክኖአዊ ባህርይ ያካተተና በአንጻራዊነት አዲስ ሊባል የሚችል ዘዴ ነው። ዘዴው በሁለት ወገኖች መካከል የተከሰተውን ግጭት በዕርቅ ለመጨረስ የተደረገው ተደጋጋሚ ጥረት ጉንጭ አልፋ ሆኖ መና በሚቀርበት ወቅት ተፋላሚዎችን ለማስታረቅ ሚዛን የሚደፋ የማግባቢያ ቃል ሲያጥር ፣ዕርቁ ሳይሳካ በእንዲህ ነህ፣ እንዲህ ነሽ የስሞታ፣ የወቀሳና የዘለፋ ጋጋታ የተጋጬ ግለሰቦች ክብር የባሰ እንዳይነካ ከተጋጩበት ቀዬ በቅጽበት በመሸሽ የግጭት ምዕራፍ እስከወዲያኛው የሚዘጋበት ስልት ነው (Porter, 1987: 23) ።

### ዕርቅ አፈላላጊ የግጭት መፍቻ

ዕርቅ አፈላላጊ የግጭት መፍቻ ዘዴ በውስጡ ሶስት ዓይነት ግጭት የማብረጃ፣ ዕርቀ-ሰላም የማውረጃ ዘዴዎችን ማካተቱን Porter (1987: 25-26) በመግለጽ ዘዴዎቹም የተፋላሚዎች ግለ-ዕርቅ ድርድር፣ የቤተ-ዘመድና የአገር ሽምግልና ዳኝነት መሆኑን ይጠቅሳሉ።

### ግለ-ዕርቅ ድርድር

በተፋላሚዎች ግለ-ዕርቅ ድርድር ግጭትን ለመፍታት የሚደረገው ሙከራ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሁለቱ ወገኖች በጠረጴዛ ዙሪያ የሚቀመጡበት፣ የግጭታቸውን መንስኤ በጽሞና የሚደማመጡበት፣ የችግሩን ስረ-መሰረት የሚያፈላልጉበት፣ በማያዳግም ሁኔታ የሁለትዮሽ ጠቀሜታ ያለው ዕርቀ- ሰላም የሚያወርዱበት ስልት ነው።

**የቤተ-ዘመድ ሽምግልና**

በቤተ-ዘመድ ሽምግልና ግጭትን የማብረድና ዕርቀ- ሰላም የማውረድ ሂደት በቀዳሚነት ከሁለቱ ወገኖች በፈቃደኝነት የተመረጡ የቤተሰብ ሽማግሌዎች የሚሰየሙበት ሂደት ነው፡፡ በመቀጠል የቤተሰብ ሽማግሌዎች ተፋላሚዎቹ በጽሞናና በእርጋታ የግጭታቸውን መንስኤ በይፋ እንዲገልጹ የሚያበረታቱበት፣ በይፋ ለተገለጸው የግጭት መንስኤ የመፍትሄ አማራጭ ከሁለቱ ወገኖች የሚቀበሉበት፣ ከቀረቡት የመፍትሄ አማራጮች ሁለቱን ወገኖች ያማከለና ግጭቱን ለማስወገድና ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ የተሻለ የሚሉትን የውሳኔ ሀሳብ የሚሰነዝሩበት የግጭት መፍቻ ሂደት ነው፡፡

**የአገር ሽምግልና ዳኝነት**

የአገር ሽምግልና ዳኝነት በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ዘዴ በዳኝነቱ የተሰየሙት ሽማግሌዎች ሁለቱ ወገኖች የጠባቸውን መንስኤና፣ የተሻለ የሚሉትን የመፍትሄ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ በማበረታታት ሳይወሰኑ እነሱም ሁለቱን ወገኖች ለማቀራረብና ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ የሚያስችል ብያኔ በመስጠት ሂደት በንቃት የሚሳተፉበት ስልት ነው፡፡

**ግልግል**

ግልግል በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ስርዓት ተፋላሚ ወገኖች በመሀከላቸው የተከሰተውን ግጭት መፍትሔ ለማፈላለግና ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ በጋራ በስምምነት በሚመርጡት አስተዋይና ገለልተኛ አስታራቂ አማካይነት የሚካሄድ ጠብ የማስወገጃና ዕርቀ- ሰላም የማውረጃ ስልት ነው፡፡

**መደበኛ የፍትህ ስርዓት**

መደበኛ የፍትህ ስርዓት በመባል የሚታወቀው ግጭት መፍቻ በሁለት ወገኖች መካከል ጸብ እንዲቀሰቀስና ግጭታቸው እንዲባባስ ያደረገው ምክንያት የተወሳሰበ በሚሆንበት ጊዜና በባህላዊው የሽምግልና ስርዓት የተወሳሰበውን ግጭት በማያዳግምና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ የሚያስችል ብያኔ መስጠት አዳጋች በሚሆንበት ሁኔታ የተወሳሰበውን ችግር ለፍትህ ስርዓቱ ማስፈጸሚያነት በተደነገጉት ህገ-ደንቦች በመታገዝ የሚፈታና ፍትሃዊ ብይን ለመስጠት የሚቻልበት ዘዴ መሆኑን Porter (1987፣ 33) ይገልጻሉ፡፡

### *ዕርቅ-ፈሪ*

*ዕርቅ-ፈሪ በመባል የሚታወቀው የግጭት መፍቻ ዘዴ የሁለቱን ወገኖች የግጭት መንስኤ ከስረ-መሰረቱ አብጠርጥሮ ለመለየት የተጀመረው ጥረት ከዳር ደርሶ ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ የሚያስችል ውሳኔ ለመስጠት ሳይበቃ በእንጥልጥል የሚቋረጥበት ስልት ነው። በዚህ መልኩ በእንጥልጥል የተቋረጠ የግጭት ማስወገድ ጥረት በመደበኛው የፍትህ ሰርዓት እገዛ ውሳኔ እንዲያገኝ ይመከራል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ በዕርቅ-ፈሪ ዘዴ የተነካካውና በእንጥልጥል የተቋረጠው ግጭት መፍትሄ ፍለጋ ያልታሰበ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ እንደሚገባው* Porter (1987፣ 33-34) የስጠነቅቃሉ፡፡

ከዚህ በላይ በርካታ የዘርፉ ምሁራን የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ምንነትና የአተገባበር ሂደት የዘረዘሩበት ትንታኔ ቀርቧል። ትንታኔው የኮንሶ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ዘዴ ምንነትን፣ የአተገባበር ቅደም ተከተልና ፋይዳ ለሚዳስስበት ለዚህ ጥናት የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው እሙን ነው፡፡

### 2.1.4 የግጭት ፋይዳ

ግጭት የሰው ልጆች የአብሮ መኖር መስተጋብር አንድ አካል ነው። ለግጭት መከሰት በዓቢይ ምክንያትነት የሚጠቀሰው ግለሰቦች በተናጠል የየራሳቸው የሆነ አስተሳሰብና አመለካከት ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ግለሰቦች የግላቸው በሆነ አስተሳሰብና በአመለካከታቸው ጉዳይ ከሌሎች ጋር ሊስማሙም ላይስማሙም ይችላሉ (Caplow, 1962: 488-493)፡፡ ግጭት የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ብክነት የሚያስከተል ክስተት መሆኑ ዕሙን ቢሆንም የተለያዩ ጠቀሜታዎች/አገልግሎቶች እንዳሉትም መገንዘብ ያስፈልጋል። ለአብነትም Simmel (1964፡ 14) በተባሉ የስነ-ሰብዕ ጥናት ዘርፍ ተመራማሪ ቀጥለው የተዘረዘሩት የግጭት ጠቃሚ አገልግሎቶች ተጠቅሰዋል ፡፡

1. Establish unity and cohesion.
2. Produce stabilizing & integrative elements.
3. Assertain the relative strength of antagonistic interests within the structure.
4. Constitute mechanisms for maintenance and/or readjustment of power balance.
5. Produce association and coalition.

6. Help reduce social isolation and unite individuals.
7. Maintain boundary lines between new associations/coalition.
8. Act as a “safety valve” to reduce frustration and aggression.
9. Produce situations for consensus.

ከላይ ከቀረበው ዝርዝር ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ግጭቶች ማህበረሰቡ ወደ ዕድገት ጉዳና የሚያደርገውን ጉዞ ለማሳካት አስፈላጊዎች ናቸው። በተጨማሪም የሰመረ ውህደት እና ልዩነት ለማህበረሰብ ዕድገት ተፈላጊ ሁነቶች ከመሆናቸው ባሻገር ማህበረሰቡ ወደማያቋርጥ የዕድገት ጉዳና እንዲያቀና በማድረግ ረገድ የላቀ ድርሻ እንዳላቸው ነው።

በሌላ መልኩ የግጭት መከሰትን ተከትሎ ግጭትን የመፍታትና ሰላምን የማስፈን ፍላጐት ይቀሰቀሳል። ተፃራሪ ቡድኖች፣ መደቦች ወይም ማህበረሰቦች ተቀራርበው ይመክራሉ። በየጊዜው የልዩነቶቻቸው መንስዔ ለሆኑ ጉዳዮች የማያዳግም ዕልባት የሚያስገኝ ውሳኔ ያሳርፋሉ። በዚህ ሁኔታ የግጭቶች መከሰትን ተከትሎ የልዩነት መንስኤዎች ይቀንሳሉ ወይም ጨርሶ ይወገዳሉ። ከዚህ አንጻር ግጭቶች ትብብርን ለማቀላጠፍ የጐላ ድርሻ ያበረክታሉ ለማለት ያስችለናል።

በተጨማሪም የግጭት መከሰት ሂደት ሲጠናቀቅ የመፍትሄ እርምጃ አንድ ብሎ ይጀምራል። የግጭት የመጨረሻ ምዕራፍ አዎንታዊ ለውጥች እንደሚያስገኝ በሀገራችን በመሬት ከበርቴዎችና በጭሰኞች መካከል ለተከሰተው ግጭት በ1967 ዓ.ም. የመሬት ለአራሹ አዋጅ መታወጁ በመፍትሔነት ሊጠቀስ ይችላል። በተጨማሪም ግጭት የተዛባን የኃይል ሚዛን በማቃናት ጠቃሚውን ለማመጣጠን ጎጂውን አፈራርሶ ለመስራት፣ የውህደትና የቅንጅት መንፈስ ለመፍጠር፣ ከማህበራዊ ህይወት መገለልንና ባይተዋርነትን በመቀነስ የግለሰቦችን ሕብረት ለማጠናከር፣ በአዲስ መልክ በሚመሰረቱ ውህደቶች ወይም ቅንጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅርበት ደረጃ የሚወስን (የሚጠቁም) ድንበር ለማበጀት፣ የቁጣ ገሞራን ለማስተንፈስ፣ የመንፈስ ጭንቀትን ለመቀነስና የጋራ መግባባትን ለመፍጠር ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ አለው።

### 2.1.5 የግጭት አፈታትና ፎክሎር

በሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወዘተ ያጋጥማቸውን ግጭት ለማብረድና በዘለቄታዊነት መፍትሄ ለማበጀት የሚያከናውኗቸው ሀገረሰባዊ

ልማዶች በሙሉ በፎክሎር የጥናት መስክ ሊታዩ የሚችሉ ጽንሰ ሀሳቦች ናቸው። ፎክሎር ከሌሎች ሰብዓዊ ሳይንሶች ጋር የሚጋራቸው ጉዳዮች ቢኖሩትም የራሱን የጥናት ትኩረትና አቅጣጫ የሚከተል መስክ ነው። ፎክሎር የማይዳስሰው ሰዋዊና ጥበባዊ ጉዳይ የለም። የሰው ልጆች ደግሞ ትናንት የኖሩበትን ዓለም ለመገምገም ዛሬና ነገ የሚኖሩበትን ለመግለፅና ለመቆጣጠር ፎክሎርን በመሳሪያነት ይጠቀማሉ። ይህ የፎክሎር ከሰው ልጆች የህይወት ዑደት ጋር አይነጠሌነት ለዘርፉ ፈርጀ ብዙነት መነሻ ሆኗል ሲል ተመስገን (2005፡ 11) ይጠቅሳል።

''ኦኩፔ ሁ'' የተባለው አፍሪካዊ የስነቃል ተመራማሪ የአንድ ሕዝብ ፎክሎር ሰዎች በልማድ ከሚናገሩት እና በልማድ ከሚተገብሩት እንደሚመነጭ ይናገራል ሲል ፈቃደ(1991፡ 16) ይጠቅሳል። በልማድ ከሚነገሩት ውስጥ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ አባባሎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወዘተ ተጠቃሽ ሲሆኑ በየብሔረሰቡ በሚከናወኑ ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት ትልቅ ሚና አላቸው። ለአብነት አስታራቂዎች ስርዓቱ ከጅምሩ ጀምሮ ጠበኞችን በአግባቡና በነጻነት ለመዳኘት ከማገዛቸው ባሻገር ዕርቁ እውን እንዲሆን በነጻነት ለመንቀሳቀስና አነጋገራቸውን ለማሳመር ብሎም ተቀባይነታቸውን ለመጨመር ይገለገሉበታል። ጠበኞችም ሆኑ ተሳታፊዎች በአስታራቂዎቹ ነገር አዋቂነትና ነገር አለዛቢነት ብዙ ይማሩበታል።

በሌላ በኩል ማንኛውም ማሕበረሰብ ከልምዳቸውና ከገጠመኞቻቸው በመነሳት የፈጠሯቸውና ያካበቷቸው እንዲሁም በዕለት ተዕለት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተራክቦ ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ስነቃላዊ ቅርጾች አሏቸው። እነዚህ ስነ ቃሎች ያለፈንና አሁን ያሉበትን የሕይወት ፍልስፍና በመግለጽ በኩል የጎላ ድርሻ አላቸው። በተለያዩ ዐውዶች፣ በውይይቶች፣ በስብሰባዎች፣ በፍርድ ስርዓት ጊዜ ነገርን በውል ለማስያዝ ስነ ቃሎች ትልቅ ስፍራ አላቸው። የስነ ቃሎች አስፈላጊነትን በመረዳት፣ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ጉልህ ድርሻ በመገንዘብ በኢሳዎች ዘንድ በግጭት እሳቤ፣ በግጭት መንስኤ፤ እንዲሁም በግጭት አፈታት ላይ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታዎች የሚገልጹ ስነ ቃሎች እንደሚንጸባረቁና በነዚህም ማህበረሰቡ ስለሕይወት ያለውን አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ እምነትና እሴቶቹን ከትውልድ ትውልድ እንደሚያስተላልፍ ደበበ (2001፡ 71) ይገልጻል። በተመሳሳይ በሸካቾ ብሔረሰብ ዘንድ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን አስመልክቶ አስታራቂ ሽማግሌዎች ተጋጪዎችን ወደዕርቅ ለማምጣት በሚጥሩበት ጊዜ

ለመታረቅ ፈቃደኛ የማይሆኑት ላይ ስነ-ልቡናዊ ጫና የሚፈጥሩት በብሔረሰቡ የተለያዩ ስነ ቃሎች አማካኝነት እንደሆነ ስለሺ (2002፡ 102) ይገልጻል፡፡ እነዚህ አስታራቂ ሽማግሌዎች የሚጠቀሟቸው ስነ ቃሎች የሚወሰኑት እንደተጋጪዎች የነገር አካሄድና እንደሚያሳዩት ፍላጎት እንደሆነም አያይዞ ያስረዳል፡፡ አስታራቂዎች የጠበኞችን የነገር አካሄድ ተመልክተው ከፎክሎር የጥናት መስኮች ስነቃል ላይ በማተኮር እንደተረት፣ ተረትና ምሳሌ፣ አባባል፣ ተረክ፣ ምርቃት ወዘተ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ይጠቁማል፡፡ እነዚህን ስነ ቃሎች የሚጠቀሙት ለተጋጩ ወገኖች ብቻ ሳይሆን ለአስታራቂ ሽማግሌዎች፣ ለምስክሮችና ለጠበኛ ወገኖችም ጭምር እንደሆነ አክሎ ይገልጻል፡፡ ከዚህ አኳያ ፎክሎር በግጭት አፈታት ወቅት ተጋጪዎችን ወደዕርቁ ለማምጣት ብቻ ሳይሆን የአስታራቂ ሽማግሌዎች አካሄድን በማስተካከል፣ የምስክሮችንና የጠበኛ ወገኖችንም ሁኔታ ወደትክክለኛው አቅጣጫና መስመር ለማስገባት ያለውን ሚና እነዚሁ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ፎክሎር በተለያዩ ብሔረሰቦች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት ለስርዓቱ ዕውን መሆን ቁልፍ መሳሪያ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡

### 2.1.6 የኢትዮጵያ ባህላዊና መደበኛ የግጭት አፈታት ሥርዓት ቅኝት

ኢትዮጵያ ለበርካታ ክፍለ ዘመናት ባህላዊ የግጭት መፍቻ የሽምግልና ሥርዓትን ጥቅም ላይ ማዋሏን የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ (Gowok 2008: 265) ለአብነትም የኦሮሞ ገዳ፣ የአማራ ሽማግሌ እና የተቀሩትን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የአስታራቂ ሽማግሌ ተቋማትን ይጠቅሳሉ፡፡ አያይዘውም የአስታራቂ ሽማግሌ ተቋማቱን በአማራጭ የግጭት መፍቻነት መጠቀም ስለሚቻልበት አግባብ የሚደነግጉ ጥቂት የህግ ትንታኔዎች በኢትዮጵያ የፍትህ ስርዓት ውስጥ መካተታቸውን ያብራራሉ፡፡ ለአስረጅነትም በሀገሪቱ የፍትህ ስርዓት ባህላዊው የሽምግልና ስርዓት ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር የተቀናጀበትንና በግለሰቦች ወይም በማህበረሰቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚያገለግለውን ፍትሐ-ነገስት የሚባለውን መጽሐፍ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ ኃይማኖተ-አበው ግጭት በመፍታት ሂደት እንደሚሳተፉ ይገልጻሉ፡፡

ምሁሩ በመቀጠል በኢትዮጵያ የፍትህ ስርዓት ውስጥ አማራጭ የግጭት መፍቻ ህገ ደንቦችን ለማካተት በፊር ቀዳጅነት የሚጠቀሰው ዘመናዊ ጥረት በ1952 ዓ.ም. የፍትሃ ብሄርና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በአዋጅ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉ እንደሆነ

ያብራራሉ። የህግ ድርሣናቱ ድንጋጌዎች የግጭት አፈታት ሂደት በዋነኛነት የሚያጠነጥነው በኮንትራት ወይም በህግ አግባብ በተመሰረተ ግንኙነት ላይ መሆኑን ይገልፃሉ። ገለፃቸውን በመቀጠል "ድርድር" ለሚለው ስያሜ በድንጋጌዎች ሰፊ የትኩረት አድማስ እንደሚሸፍንና ለተለዋጭ የግጭት አፈታት ስርዓት በአቻ ስያሜነት እንደሚያገለግል ያብራራሉ። ከላይ ከተዘረዘረው የህግ ድንጋጌ መንፈስ ድርድር በሁለት ወገኖች መካከል ለሚቀሰቀስ አለመግባባት/ግጭት ከፊል ወይም የተሟላ ዕልባት የማስገኘት ጥረት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል በ1953 ዓ.ም የወጣውን ህግ ለማሻሻል በ1958 ዓ.ም የወጣው የፍትሃ ብሔር ህግ መደበኛ ዳኝነትን ለግጭት ማስወገጃነት ለመጠቀም የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አካትቷል። ይህንን ጅምር ጥረት ወደተሻለ ደረጃ በማሸጋገር ረገድ መንግሥት፣ በፍትሕ ስርዓቱ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት ዳኞች፣ አቃቢያነ ህግና ጠበቆች የጎላ ሚና እንደሚጫወቱ ተገልጿል።

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ መደበኛ የፍትሃ ብሔርና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ተግባራዊ ቢደረግም በበርካታ የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ሀገር በቀል ቴክኒኮች ላይ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሄ በማፈላለግ ረገድ ለጠቀሜታ የማዋል የቆየ ልማድ አለ። በዚህ መነሻነት ከልማድ የቀሰመው፣ በሙያው የተካነው ወይም በልምድ ብዛት ያጎለበተው ዕውቀት ያለው ማንኛውም ግለሰብ በዳኝነት ሊሰማራና ግጭት የመፍታት ኃላፊነትን ለመወጣት ይችላል የሚል አቋም ያራምዳሉ። በዚህ ዘመን በባህላዊ ዳኝነት ግጭት የመፍታት ተግባር በሰፊው ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ ‹‹አቦ ገረብ›› የግጭት መፍቻ የዳኝነት ስልትን ይጠቅሳሉ።

### 2.1.7 ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት በኢትዮጵያ የሚኖረው አንድምታ

Gowok (2008, 283) የኢትዮጵያን የፍትህ ስርዓት አነሳስና ዕድገት እንዲሁም የተመራጭ ግጭት መፍቻ ስርዓት በዳሰሱበት ጥናታዊ ጽሁፍ ማጠቃለያ ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ ገጽታ ከተገቢው በላይ ማጋነን እንደማይቻል ይጠቁማሉ። ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት በሀገራችን በርካታ ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ወደ ከፍተኛ የግጭት ማስወገጃ ስርዓት ደረጃ እንዳላደገ፣ መደበኛ ፍ/ቤቶችም ግጭት የማስወገዱንና ዕርቀ-ሰላም የማውረዱን ኃላፊነትና ድርሻ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ብቻ መወጣት እንደማይችሉ መንግስት፣ ምሁራን፣ የፍትህ

አካላት፣ ማህበራዊና ሙያዊ ተቋማት እየተገነዘቡ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በዚህም ምክንያት አሁን በተለያዩ መስኮች ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓትን ተግባራዊ የማድረግ አዝማሚያ እየተስተዋለ መሆኑን ገልጸዋል። ለአብነትም በሰራተኞችና በየመ/ቤታቸው መካከል የሚነሳ አለመግባባትና ግጭትን በመደበኛው ፍ/ቤት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን ሁኔታ እንደሚያበረታታ በሰራተኛ መተዳደሪያ አዋጅ መደንገጉን ጠቅሰዋል።

ባህላዊ የግጭት አፈታት እንድምታዎች በሙሉ ለተከሰቱት ጉዳዮች ዳኝነት በመስጠት ዕርቅ ማውረድ ብቻ ሳይሆን ሰላምና መረጋጋት በሕብረተሰቡ ዘንድ ተመልሶ እንዲሰፍን ማድረግ ዋንኛ ዓላማው ነው። ይህ የሚገለጸው በግጭቱ ምክንያት የተሰናከለው ማሕበራዊ ግንኙነት ተመልሶ እንዲያንሰራራ ስለሚያደረግ ነው።

በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት የመፍጠርና አስፈጻሚ ተቋማትን የማዋቀር ጥረት በተለያዩ ተቋማት እየተከናወነ እንደሚገኝና ይህ ጥረትም እንዲቀጥል ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየተከናወነ እንደሆነና በዩኒቨርሲቲዎችም የስርዓተ ትምህርት ቀረጻ መካሄዱን እ.ኤ.አ Dec. 28 ቀን 2007 በተካሄደ የምክክር ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል[2]። ስለዚህ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ስርዓተ-ትምህርት መተግበርና ተለዋጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት እንደ አንድ ኮርስ ማስተማር መጀመር በነባሩ አሰራር ላይ የተወሰደ ስር ነቀል እርምጃ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በጉባኤው ባህላዊው የሽምግልና ስርዓት ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር መደጋገፉ የፍትህ ስርዓት ሂደቱን የማሳለጥ ጥቅም እንዳለውም ተገልጿል። በ1997 ምርጫ ለተቀሰቀሰው ግጭት በአገር ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብነት ፍትሃዊ ውሳኔ መሰጠት መቻሉን ለአብነት ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት መደበኛውን የፍትህ ስርዓት በአማራጭነት ለመተካት ይችላል ቢባል ስህተት አይደለም።

በአጠቃላይ ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት በመንግስት፣ በሲቪል ማህበረሰብ፣ በምሁራን፣ በህግ ባለሙያዎች እና በፍትህ አካላት ተቀባይነት አግኝቶ ጥቅም ላይ መዋል መጀመሩን በመጥቀስ ከላይ የተጠቀሱት ምሁር የጥናት ጽሁፋቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡

---

[2] በጉባኤው ላይ የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ አሰፋ ከሲቶ ባደረጉት ንግግር ተመራጭ የግጭት መፍቻ ስርዓት የመፍጠርና አስፈጻሚ ተቋማትን የማዋቀር ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስገንዝበዋል፡፡

## 2.2 ሀገረሰባዊ ጥናቶች በባህላዊ ግጭት አፈታት

በዚህ ክፍል ከባህላዊ የግጭት አፈታት ጋር በተያያዘ በሃገራችን ብሄረሰቦች ላይ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በቀረቡ ጥናቶች ተመስርቶ ዳሰሳ ይደረጋል፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሁለት የትምህርት ክፍሎች ማለትም በአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት (በቀድሞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል) እና የሶሲዮሎጂና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጥናትና ምርምር ቡድን የተሰሩ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ዋና ዓላማው በባህላዊ የግጭት አፈታት/እርቅ/ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ምን ያህል ናቸው? ከብሔረሰብስ አንጻር? የጥናት ትኩረታቸው ምን ይመስላል? በጥናታቸው ምን ምን አንስተዋል? የሚለውን በሚገባ በመፈተሽ ለዚህ ጥናት በቂ ግንዛቤ ይዞ መነሳትና ክፍተት ባለው ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናቱን ማካሄድ ነው፡፡

### 2.2.1. በአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የተጠኑ

ቀድሞ የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ-ጽሐፍ ትምህርት ክፍል ይባል በነበረውና አሁን የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በተባለው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ከ1997 ዓ.ም. እስከ 2005 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 9 (ዘጠኝ) ዓመታት ጊዜ ውስጥ 22 (ሀያ ሁለት) ጥናቶች በግጭት (እርቅ) ስርዓት ላይ ተሰርተዋል፡፡ ጥናቶቹ በአማራ፣ ኦሮሞ፣ አፋር፣ ኩናማ፣ ራያ አላማጣ፣ ጋሞ፣ መኤነት፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ አኝዋ፣ ኢሳ፣ ሸካቾ እና ማረቆ ብሔረሰቦች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከዓመት ዓመት የተለያየ ቁጥር /ብዛት/ ይኑራቸው እንጂ ስራዎቹ በአብዛኛው ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ብቻ ሳይሆን በጥናት ዘዴዎቻቸውና በአቀራረብ ረገድም ተቀራራቢነት እንዳላቸው በተደረገው ዳሰሳ መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 2.2.2. በሶሺዮሎጂና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ ትምህርት የተጠኑ

በተለያዩ የትምህርት መስኮች በእንግሊዚኛ ቋንቋ በርካታ ቁጥር ያላቸው ጥናቶች በግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ተሰርተዋል፡፡ ለዚህም (ፈቃደ፣ አሰፋና ገብሬ፣ 2004) "በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ላይ የተከናወኑ ጥናቶች ኑትት መዘርዝር" በሚል የሰሩት ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ጥናት የተዳሰሱት በሶሲዮሎጂና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ

ትምህርት እ.ኤ.አ ከ1995-2013 ድረስ በትምህርት ክፍሉ ቤተመጻህፍት ላይ የተገኙና በግጭት አፈታት ዙሪያ ላይ የተሰሩ 14 ያህል ጥናቶች ናቸው። ጥናቶቹን ከብሔረሰብ አንፃር ስናያቸው በኦሮሞ 8፣ በሶማሌ 2፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በትግራይና በአፋር በእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ጥናቶች ናቸው። በነዚህ ጥናቶችም በተደረገው ዳሰሳ ስለተጠኚው ብሔረሰብ ማንነት ከመረዳት ባለፈ በትምህርት ክፍሉ ስለኮንሶ በተለያየ ርዕሠ ጉዳይ ላይ የተሰሩ ስራዎች መኖራቸውን ለማወቅና ስለተሰሩት ስራዎች ምንነት ግንዛቤ ለመያዝ አስችሏል፤ በተጨማሪም ለዚህ ጥናት በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ላይ አለመሰራቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ አግዟል።

### 2.2.3. በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የተጠኑ

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክና ባህል ላይ የጥናትና ምርምር ስራ የሚሰራ በመሆኑ በብሔረሰቦች የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተሰሩ ጥናቶች አሉ። እነዚህን ስራዎች በዘርፉ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች የመነሻ ሀሳብ ለማግኘት ወይም ያገኙትን ለማጠናከር ጥሩ የመነሻ ግብዓት ሊሆኑ ይችላሉ። ለአብነትም ጌታቸው (1998) “ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በጉጂ ኦሮሞ” እና “ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት በጌድኦ” በሚል በተመሳሳይ ዓመት የሰራቸውና ደጄኔ (2004) “የቦረና ኦሮሞ የግጭት አፈታት ዘዴ” በሚል የሰራው ጥናት ይጠቀሳሉ።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በኮንሶ ብሔረሰብ ላይ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በመቃኘት ያልተዳሰሱ የጥናት አቅጣጫዎችን መለየትና የዚህን ጥናት አስፈላጊነት ማሳየት ነው። በመሆኑም ከዚህ በታች በተለያየ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስለኮንሶ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት ይዳሰሳል።

Herman (1984፤ 751-757) “History of Events and Internal Development: The Example of Burji-Konso Cluster” በሚል ርዕስ በጻፈው ስለቡርጂ- ኮንሶ ታሪክና ዕድገት፣ የቡርጂ-ኮንሶ የኢኮኖሚ መሰረት ስለሆነው የእርከን ስራና የእርከን ስራው ዛሬ ድረስ ባህል ሆኖ ስለመቀጠሉ፤ እንዲሁም በኮንሶዎች ዘንድ የማህበራዊ መስተጋብር መሰረት የሆነው የኃላፊነት ወሰንን የሚጠቁም የስልጣን እርከን መዋቀሩን በጥናቱ አሳይቷል። Lakew (1998) “Settlement and Clanship among the Konso” በሚል ርዕስ ባደረገው ጥናት ደግሞ የኮንሶ ማህበረሰብ የአሰፋፈር ሁኔታ ጉሳን መሠረት ያደረገ

መሆኑንና የአሰፋፈራቸውን ገጽታ የሚጠቁም ስራ ሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ Yilma (2002) “The Role and Status of Women in the Food system of the konso, south West Ethiopia” በሚል ርዕስ የኮንሶ ማህበራዊ አደረጃጀትን በማነፃፀሪያነት በመጠቀም የኮንሶ ሴቶች በማህበረሰቡ በስርዓተ ምግብ (በምግብ አመራረት፣ አስተዳደርና ግብይት ሂደት) ውስጥ ያላቸውን ድርሻና ማህበራዊ ደረጃ ትኩረት በመስጠት ጥናት አድርጓል፡፡ Mamitu (2002) በበኩሏ “Some Aspects of the Status of Women among the Konso of Southern Ethiopia” በሚል ርዕስ ባቀረበችው ጥናት የኮንሶ ሴቶችን የማንነት ገፅታ፣ የተሰማሩበትን የሙያ መስክ መሠረት በማድረግ የስራ ድርሻና ማህበራዊ ደረጃ በሦስት ክፍሎች እንደሚከፈልና እነሱም በግብርና ሙያ የተሰማሩ ሴቶች፣ የዕደ ጥበብ ሙያተኛ ሴቶች እና የመንፈሳዊ አባት ሚስቶች በመባል ሊፈረጁ እንደሚችሉ አመላክታለች፡፡ Kansite (2011) ደግሞ “Moora: A study of the public place and its multiple purposes among the Konso people of Southern Ethiopia” በሚል ርዕስ ባደረገው ጥናት የኮንሶ ማህበረሰብ አባላት ስለሞራ አጀማመር፣ ትንታኔና አገልግሎት ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃና የ“ሞራ” ግብዓቶች ጥቅምና አገልግሎት እንዲሁም ሞራ በአሁኑ ዘመን ያንዣበበበትን ለውጥ የዳሰሰ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ በሌላ በኩል Solomon (2012) “Konso Traditional Architecture and Housing” በሚል ርዕስ ባቀረበው መጣጥፍ የኮንሶ ዘመን-ዘለቅ (ነባር)መንደሮች የተከተሙበት በጋራና በሸንተረሮች አናት ላይ በሚገኙ አምባዎች ላይ መሆኑን በመጠቀም የኮንሶዎች የመንደር ምስረታ ልዩ የሚያደርገው ድንቅ የሆነ የኪነ-ህንጻ አሻራ ባረፈበት የድንጋይ ካብ መታጠሩ እንደሆነ በጽሁፉ አመላክቷል፡፡ አጸደ (2003) እንዲሁ “የኮንሶ ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ገላጭ-ተንታኝ ጥናት” በሚል ርዕስ ባቀረበችው ጥናት የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጦቹን የማህበረሰቡን የጸጉር አሰራር አካላዊ ገጽታ ትኩረት በማድረግ የአለባበስ ስርዓቱን እና አጋጣሚዎቹን በመግለጽ የአልባሳቱን እና የጌጣጌጦቹን ማህበረ-ጥበባዊ ፋይዳውን እንዲሁም በቁሶቹ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ ለውጦች ከነምክንያቱ አሳይታለች፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡ ጥናቶች ላይ በተደረገው ዳሰሳ በየብሔረሰቡና ስለኮንሶ በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተደረጉት ጥናቶች

- ብሔረሰቡን በማስተዋወቅና የተጠኑ ጥናቶች ብዛትን በማወቅ ረገድ የጎላ ድርሻ እንዳላቸው እሙን ነው፡፡ የአጥኚዋም እምነት ነው፡፡

- በየብሔረሰቡ ለግጭት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን፣ ግጭት የሚፈታባቸውን ዘዴዎች፣ ሂደቶች፣ የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታንና የትንተና ዘዴን እንዲሁም አጠቃላይ የጥናት አቀራረቡን ለመረዳት አግዟል፡፡
- ለዚህ ጥናት በተመረጠው የኮንሶ ብሔረሰብ ላይ በግጭት አፈታቱ ዙሪያ ጥናት አለመደረጉን ለማረጋገጥ አስችሏል፡፡ በዚህ ምክንያት ስለብሔረሰቡ የተጠኑትን ጉዳዮች ምሉዕ አያደርጋቸውም፡፡ በመሆኑም በርዕሰ ጉዳዩ የታየውን ክፍተት በከፊል በመሙላት ይህ ጥናት ጠቀሜታ ያለውና ከላይ ከቀረቡት ጥናቶችም የሚለይ ነው፡:

# ምዕራፍ 3. የኮንሶ ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ

በዚህ ምዕራፍ ስለኮንሶ ብሔረሰብ አመጣጥና ስያሜ፣ ስለወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና ስለብሔረሰቡ መተዳደሪያ፣ ቋንቋና ኃይማኖት እንዲሁም በብሔረሰቡ ውስጥ ስለሚገኙት ማህበራዊ ተቋማትና የባህላዊ አስተዳደሩ አደረጃጀት ቀርቧል።

## 3.1 ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ

የኮንሶ (xhonso) ብሔረሰብ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሰገን አካባቢ ሕዝቦች አስተዳደር ዞን በኮንሶ ልዩ ወረዳ በዋናነት የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ክልል በባስኬቶ ልዩ ወረዳ፣ በደቡብ ኦሞ ዞን በሰላማጎ ወረዳ፣ በአርባምንጭ እና በጂንካ ከተሞችም ይገኛል። ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመቀላቀል ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በተልተሌ እና በያቤሎ ወረዳዎችም ይገኛል።

ኮንሶ የሚለው ቃል የተወሰደው "ኮንሲታ" ከሚለው የኮንስኛ ቃል ሲሆን፣ ፍችውም ለም፣ ለምርት ተስማሚ "መሬት" ማለት ነው። በሌላ በኩል ሻኮ (2005፡ 6-7) ኮንሶ የሚለው ቃል "xhonso" ከሚለው በአነባበብ ችግር የመጣ እንደሆነ ይገልጻል። "xhonso" በጣሊያንኛ "khonso" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። "xho" የሚለው ድምጽና ፊደሉ በትግሪኛ ያለ ሲሆን፣ በአማርኛና በእንግሊዚኛ ግን የሉም። በመሆኑም በአማርኛ "ኮንሶ" በእንግሊዝኛ "konso" በሚለው አነባበብ ብሔረሰቡ የሚታወቅበት ስም ሆኗል።

በኮንሶ ብሔረሰብ ዘንድ የሚነገር ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ፣ ሲያያዝ የመጣ ስለልዩ ልዩ ባህላዊ ገጽታዎቻቸው፣ ስለዝርያዎቻቸው ወደ አካባቢው መፍለስ፣ ስለአካሄዷቸው ጦርነቶች፣ ስለተፈጥሮአዊ ክስተቶች፣ ስለታሪኮቻቸው ወዘተ የሚያወሱ አፈታሪኮች አሏቸው። ኮንሶዎች እነዚህን መሰል ይዘት ያላቸው አፈታሪኮች እውነተኛ የታሪኮቻቸው አካል መሆናቸውን ያምናሉ (የቅርስ ኢንቬንተሪ፣ 2001፡ 21)፡፡ ኮንሶዎች የአመጣጥ ታሪካቸውን በተመለከተ ከጸሀይ መውጫ በኩል ከምስራቅ የኦሮሞ ክፍል ከቦረና ኦሮሞ የሊበን ቦረናዎች ይኖሩበት ከነበረው ቦታ ፈልሰው እንደመጡ ይናገራሉ። የፈለሱት በአንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ ማለትም ከብት ይዘው ከቦታ ቦታ በመዘዋወር በተለይ ወደምዕራቡ አቅጣጫ በመጓዝ እንደሆነም ይገልጻሉ።

የኮንሶ ሕዝብ ታሪካዊ አመጣጥ በግምት ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ሲሆን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት (ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ) ምክር ቤት የባህል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም (2001፣ 153) እና ዲኖቴ (2004፣ 11) ከምስራቅ አቅጣጫ መጡ በማለት መነሻቸውም ከሊበን ቦረና እና ቡርጂ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን Metasebia (2012፡ 27) ደግሞ ከምዕራብ አቅጣጫ እንደመጡና ከደራሼ፣ ማሻሌ፣ ገዋዳና ፀማይ አካባቢዎች ተነስተው ለብዙ ዓመታት ያህል በኮንሶ ተራራማ አካባቢዎች ከሰፈሩ በኋላ ቀስ በቀስ አሁን ወዳሉበት ቦታ መጥተው መስፈራቸውን ይናገራሉ። ሻኮ (2005፡7)[3] ''የኮንሶ ብሔረሰብና ማንነቱ'' በሚለው ጽሁፉ Black (1973) እና Hallpike (1972) ን በመጥቀስ እንደጻፈው እንደ ኮንሶ እምነት ጥንታዊ ኮንሶ ኮማይቲ (ከኮንሶ በሰሜን ምስራቅ በቡርጂ አቅጣጫ የሚገኝ ጫካ) ከሚሉት አካባቢ በአይሎታ (የቶክመሌታ ጎሳ የሆኑ ኮንሶዎች የሚኖሩበት) ምድር ተወልዶ ከተባዛ ወዲህ በታሪካዊ ምክንያቶች ቢያንስ በደቡባዊ ኢትዮጵያ ከመዘዋወሩም ባሻገር ከአይሎታ በስተምስራቅ፣ በስተምዕራብና በስተሰሜን ምዕራብ ሊሰፍር ተገድዷል። እነዚህ ጥንታዊ ሰፈራዎች ኋላ ላይ በአዳዲስ የትውልድ ሀረጎቻቸው ፍልሰት ተጠናክረዋል። ይህም የፍልሰት ዝምድና በማህበራዊ ታሪኩ፣ በቋንቋው፣ በአጠቃላይም በባህሉ ይገለጻል ሲል ይጠቅሳል። በሌላ በኩል በአፈ-ታሪክ ደረጃ ያለውን ዲኖቴ፡-

> *‹‹ታላቅና ታናሽ ሆነው ከቆላማው ቦረና ክፍል ከብት እያገዱ ወደገላን (ሰገን) ወንዝ አካባቢ ደረሱ። ታላቅ ታናሽየውን መኖ ወዳለበት ቅኝት አደርጋለሁ ብሎ ሰገን ወንዝን በመሻገር ኮንሶ ወደሚባለው ጋራ አቅንቶ ቃኝቶ ሲመለስ ሰገን ወንዝ ሞላ። በዚያም ማዶ ከብት የሚያግድ ታናሽ ወንድሙን በመሰናበት ኮንሶ በመምጣት እዚያው ኮንሶ ጋራ (ተራራ) አካባቢ በመስፈር ከሌሎች ጋር ተቀላቅሎ በመጋባትና በመዋለድ ዛሬ ላለበት ደረጃ ደረሰ››*
> (በደንገልቱ፣ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣31) ሲሉ ይገልጻሉ።

## 3.2 የወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ


የኮንሶ ልዩ ወረዳ በ41 የገጠር ቀበሌዎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው። ወረዳው በሰሜን የደራሼ ልዩ ወረዳ፣ በደቡብ የኦሮሚያ ክልልና በምዕራብ የቡርጂ እና

---

[3] በጽሁፉ May 2013 ብሎ ያስቀመጠው አቆጣጠሩ በዓመተ ምህረት ተለውጧል።

የአማሮ ልዩ ወረዳዎች፤ እንዲሁም በምስራቅ የደቡብ ኦሞ ዞን ያዋስኑታል (የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ምክር ቤት የባህል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፣ 2001፡ 152)። የኮንሶ ወረዳ ዋና ከተማ ‹‹ካራት›› ስያሜውን ያገኘው "ካራታ" (በካራታ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች) ከሚለው የአካባቢው መጠሪያ ሲሆን፣ ከተማው ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ሀዋሳ በ361 ኪ.ሜ ርቀት ላይ፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ በ595 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የቆዳ ስፋቱ 2500 ካሬ ሜትር ሲሆን፣ ከባህር ጠለል በላይ ከ1400 - 2000 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል።


የኮንሶ ልዩ ወረዳ ካርታ በገላጭ ስዕል 1 እንዲሁም የወረዳው አቀማመጥ በኢትዮጵያ ካርታ ላይ በገላጭ ስዕል 2 ተመልክቷል።




ገላጭ ስዕል 1 የኮንሶ ልዩ ወረዳ ካርታ

የልዩ ወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በአብዛኛው ተራራማ፣ ድንጋያማ፣ ገደላማና ወጣገባ የበዛበት ሲሆን፣ በከፍተኛ ደረጃ የተሸረሸሩና የተቆራረጡ ሸለቆዎች እንዲሁም መጠነኛ ሜዳዎች ይገኙበታል። በልዩ ወረዳው በአማካኝ ከ650 ሚ.ሊ. በታች የዝናብ መጠን ሲኖር፣ ከአጠቃላይ መሬቱ 40.96% ለእርሻ፣ 33.23% ለግጦሽ፣ 1.8% በደን፣ 16.78% በሌሎች የተሸፈነና 7.23% ደግሞ ሊለማ የማይችል መሬት እንደሆነ ይገመታል። ኮንሶዎች ድንጋያማ፣ ገደላማና ድርቅ የሚያጠቃው አካባቢያቸውን ለህይወት

ተስማሚ ሆኖ ማህበረሰቡን እንዳቀፈ እንዲቆይ ከተፈጥሮ ጋር ባደረጉት የረጅም ዓመታት ጥረት መልክዓ ምድሩንም ሆነ ማህበረሰባቸውን የሚጠብቁበትና የሚያስተዳድሩበት ባህላዊና ትውፊታዊ ስርዓት ያላቸው ሲሆን፣ በዚህ በካበተ ባህልና ድንቅ ጥበብ በመጠቀም በተፈጥሮው ለሰው ልጅ ኑሮ አስቸጋሪ የነበረውን የመሬት የአየር ንብረት በጥረታቸው በመቀየር ለኑሮ ምቹ ማድረግ ችለዋል፡፡




ገላጭ ስዕል 2 የኮንሶ ልዩ ወረዳ አቀማመጥ በኢትዮጵያ ካርታ ላይ

ይህ ጥረታቸው ከጁን 19-29/2011 በፓሪስ በተካሄደው 35ተኛው የአለም አቀፍ የቅርስ ኮሚቴ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የኮንሶን ባህላዊ መልክዓ ምድር በዓለም አቀፍ ቅርስነት ዘጠነኛ አድርጎ ለማስመዝገብ አስችሏል፡፡ መልክዓ ምድሩ 23000 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ በውስጡም የተለያዩ በባህላዊ ዘዴ የተሰሩ እርከኖች፣ በካብ የታጠሩ መንደሮች፣ ሞራ የተባሉ ባህላዊ ጎጆዎች፣ ጥብቅና ቅዱስ ደኖች፣ ዋካ የሚባሉ የእንጨት ሀውልቶችና ዳጋ ዳሩማ የተባሉ የድንጋይ ሀውልቶች እንዲሁም ሀርዳ የሚባሉ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ባህላዊ ኩሬዎችን አካትቶ ይዟል፡፡ ከነዚህ የሚዳሰሱ ቅርሶች ጋር አብረው የሚከወኑ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ይገኙበታል (Yonas 2012: 21-25)፡፡

በኮንሶ አካባቢ ሁለት የተለመዱ የዝናብ ወቅቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም ከየካቲት ግማሽ እስከ ሚያዚያ ያለው በኮንሶኛ “ሮባ ፓራ” ተብሎ የሚጠራውና ሁለተኛው ወቅት ደግሞ ከነሐሴ እስከ ጥቅምት አጋማሽ ያለውን ይሸፍናል፡፡ ይህ ወቅትም “ሮባ ሀገይታ” ተብሎ በአካባቢው ይታወቃል፡፡ ከነዚህ ወቅቶች ውጭ ያሉት ወራቶች ደረቅ ሆነው ያሳልፋሉ፡፡ አካባቢው በአብዛኛው ሞቃታማና የዝናብ እጥረት የሚያጋጥመው ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከ650 ሚሊ ሊትር በታች መሆኑንም መረጃዎች ይጠቁማሉ (የደ/ብ/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ም/ቤት የባህል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፣ 2001፡ 154)፡፡ ለኮንሶ ብሔረሰብ ዝናብ ከዕለታዊ ጥቅሙ ባሻገር ከእምነታዊ ገጽታው ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ በባህላዊ እምነቱ መሠረት ዝናቡ ማህበረሰቡ ከአምላኩ ወይም “ዋቃ” ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገነዘብበት ሲሆን ይህም ማለት በማህበረሰቡ ውስጥ የእርስ በርስ ግጭትና አለመረዳዳት ካለ “ዋቃ” የሚቀጣበት አንደኛው መንገድ ዝናብ ማሳጣት ነው (Hallpike 2008፡ 23)፡፡

የኮንሶ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የቀን አቆጣጠር ያለው ሲሆን፣ ይህም በሰላሳ ቀናት የተከፋፈሉ አስራ ሁለት ወራትን የያዘ ነው፡፡ በዚህ የቀን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያው ወር ጥር ሲሆን ታህሳስ አስራ ሁለተኛ ወር ነው (ዲኖቴ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 31) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ የአስራ ሁለቱ ወራት በመገኛ ቋንቋና በአማርኛ እንዲሁም ወቅቶቹ በ ሠንጠረዥ 1 ተገልጿል፡፡

ሠንጠረዥ 1 በኮንሶ ብሔረሰብ የወራትና ወቅቶች ሥያሜ

| ወር | ወራት በመገኛ ቋንቋ | ወራት በአማርኛ | ወቅቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦይባ | ጥር | ፀሐያማ |
| 2 | ሳጋኖጋማ | የካቲት | “ሮባ ፓራ” ዝናባማ |
| 3 | ሙሬኖ | መጋቢት | |
| 4 | ፓላሎ | ሚያዝያ | |
| 5 | ሃሪ | ግንቦት | ፀሐያማ |
| 6 | ቶላ | ሰኔ | ›› |
| 7 | ኦርሃልሳ | ሐምሌ | ›› |
| 8 | ሴሳይሳ | ነሐሴ | “ሮባ ሀገይታ” ዝናባማ |
| 9 | ፓርቱካታ | መስከረም | |
| 10 | ኪሳ | ጥቅምት | |
| 11 | ሁሊንዳላ | ህዳር | ፀሐያማ |
| 12 | ፓሪንጋ | ታህሳስ | ›› |

በአጠቃላይ ኮንሶዎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት ከመሆናቸው ባሻገር እነዚህን ቅርሶች ጠብቀውና ተንከባክበው ለትውልድ በማቆየት ረገድ የጠንካራ ማህበረሰብ ተምሳሌት መሆን የቻሉ ናቸው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

## 3.3 የኢኮኖሚ መሠረት

የሰው ልጆች ኢኮኖሚያዊ መሰረታቸውን እንደሚኖሩበት አካባቢ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና አየር ጸባይ ይመርጣሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የአኗኗር ዘይቤና የመኖሪያ አካባቢ መረጣ በአገራችን የታሪክ ጉዞ የነበረና አሁንም ያለ መሆኑን ተመስገን (2005፡ 23) ይገልጻል፡፡ የኮንሶ ብሔረሰብ አሰፋፈሩም ሆነ የኢኮኖሚ መሰረቱ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የአካባቢውን መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የአየር ጸባይ መሰረት ያደረገ ሲሆን የብሔረሰቡ አባላት ዋነኛ መተዳደሪያው ግብርና ነው፡፡ አብዛኛው የብሔረሰቡ አባላት ሰብል አምራች ሲሆኑ ከፊሉ ደግሞ የእንስሳትና የንብ እርባታን ያከናውናሉ፡፡ በተወሰነ ደረጃ በንግድ ስራም ይሰማራሉ፡፡ በግብርና የሚተዳደረው የብሔረሰብ ክፍል "ኤታንታ" ሲባል፣ በንግድ፣ በሸክላ ስራ፣ በሽመና፣ በብረታብረት ስራና በሉካንዳ አራጅነት የሚተዳደሩት ደግሞ "ኻውዳ" በመባል ይታወቃሉ፡፡

## 3.4 ቋንቋና ኃይማኖት

የኮንሶ ብሔረሰብ የሕዝብ ብዛትን አስመልክቶ በኢትዮጵያና በጥንት በፍልሰት ከአገር የወጡ ውጭ የሚኖሩ ትውልድ ሀረጋቸውን ከኮንሶ የሚመዙ በርካቶች መሆናቸውን በመግለጽ (Hallpike 2008; Watson 1998; ሻኮ፣ 2005) የተለያየ አሀዝ አስፍረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን በመጥቀስ (Metasebia 2012፡ 26) እ.ኤ.አ በ2011 በተደረገ የሕዝብ ቆጠራ የኮንሶ ሕዝብ ብዛት 262,993 መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይሁንና የኮንሶ ሕዝብ ብዛት ግማሽ ሚሊዮን አካባቢ ሊደርስ እንደሚችል እምነት ያለ መሆኑ ተገልጿል (ሻኮ 2005፡ 4)፡፡ ይህ ሕዝብ የተለያዩ ቋንቋዎችን እየተጠቀመ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን ይመራል፡፡ የኮንሶ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የመግባቢያ ቋንቋ አለው፡፡ ቋንቋው "አፋን ኾንሶ" በመባል ይታወቃል፡፡ የቋንቋ ሊቃውንት አፋን ኾንሶን ከምስራቅ ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ ከኦሮማዊ ቡድን እንደሆነ Bender (1971); Black (1973) ን በመጥቀስ ይገልጻሉ (ሻኮ 2005፡ 16-17)፡፡ ሊቃውንት "የአፋን ኾንሶ" ቋንቋ በተለይ ከኦሮምኛ ቋንቋ ጋር የሚያመሳስሉት ብዙ ነገሮች እንዳሉት Hallpike

(2008) መግለጻቸው የሁለቱ ቋንቋዎች መመሳሰል የኮንሶ ብሔረሰብ ጥንተ-አመጣጥ ከኦሮሚያ አካባቢ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ያጠናክራል (አፀደ፣ 2003፡ 26)። አፋን ኾንሶ ከ1980ዎቹ ጀምሮ የጽሁፍ ቋንቋ ለመሆን በመብቃቱ ለስራና ለትምህርት መስጫነት በማገልገል ላይ ይገኛል። ብሔረሰቡ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው በተጨማሪ ኦሮምኛን፣ አማርኛንና ዶባስኛን በተለያየ ደረጃ ይናገራል። በግጭት አፈታት ስርዓቱ የሚጠቀሙት አፋን ኾንሶን ነው። ኃይማኖትን በተመለከተ የኮንሶ ብሔረሰብ የፕሮቴስታንት፣ የባህላዊ እምነትና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሲሆን፣ ለባህላዊ የዕርቅ ስርዓቱ አስታራቂ ሽማግሌዎች ባህላዊ ዕምነታቸውን መሰረት ያደርጋሉ፤ በዚህም ከኃይማኖታዊ ገጽታው ይልቅ ባህላዊው ይጎላል።

## 3.5 ማህበራዊ ተቋማት

የኮንሶ ማሕበረሰብ አባላት በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እርስ በርስ የሚገናኙባቸውና የሚቀራረቡባቸው የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት አሏቸው። ተቋማቱ ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ሲሆኑ አሳታፊነታቸው ጾታንና ዕድሜን አይለይም። ከነዚህ ውስጥ ዕቁብ፣ ዕድር፣ የቡድን (ደቦ) ስራና የመሳሰሉት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ዕቁብን ብንወስድ በብሔረሰቡ አጠራር "ቆቁቤታ" ይባላል። ዕቁብ አቻ የሆኑ የኢኮኖሚ ደረጃ ያላቸው ሰዎች በአቅማቸው ራሳቸው በራሳቸው ወስነው በቀን፣ በሳምንትና በወር፣ ብር 100፣ 200፣ 1,000 ወዘተ... በሚል መነሻ ገንዘብ እያሰባሰቡ የተለያዩ ችግሮቻቸውን የሚቀርፉበት፣ የተለያዩ ጉዳዮቻቸውን የሚከውኑበትና የሚገናኙበት ትልቅ ተቋም ነው። በዚህ ተቋም አባል የሆነ ማንኛውም ሰው ዕቁቡን በመጀመሪያ ከፈለገ እንደሚሰጠው ከዚያ በዕጣ መሠረት ሁሉም እንዲደርሰው ከተደረገ በኋላ ሲያልቅ መጨረሻ ላይ ገንዘብ ያዋጡና ሁለት በሬ አርደው ከባህላዊ መጠጥ ደግሞ "ጨቃ" አዘጋጅተው የዕቁቡን ማጠናቀቂያ የሚያውጁበት ስርዓት አላቸው።

የዕቁብ ማጠናቀቂያ የሚታወጅበት ስርዓት ዝግጅቱ በሰብሳቢው ቤት የሚከናወን ሲሆን ለ2 ቀናት ያህል ይቆያል፡፡ የመጀመሪያው ቀን እርድና በቅርጫ መልክ ስጋ በመከፋፈል ከዚሁ ጋር የጨቃ መጠጥና ከሁሉም ድርሻ ላይ በማስቀረት ጥሬ ስጋ በመብላትና በመጨዋወት ያልፋል። የሁለተኛው ቀን ግን በዕቁቡ ወቅት ስለአጋጠመ ችግር፣ ዕቁቡ በአዲስ መልክ ስለሚጀመርበት ሁኔታ፣ የክፍያ ሁኔታ (መጨመር መቀነስ) አጠቃላይ አካሄዱን

አስመልክቶ ሰፊ ውይይትና ምክክር ተደርጐ ቀጣዩ እቁብ መቼ፣ በምን ያህል ብር፣ በምን ያህል ሰው ይጀመር የሚለውን የሚወስኑበት፣ ነባር የዕቁብ አባል በልዩ ልዩ ምክንያት በአቅም ማነስ ወዘተ… ከማህበሩ እንዳይለይ፣ ግንኙነቱ እንዳይቋረጥ ሲባል በዚህ ጉዳይ አባላቱ ተወያይተውና መክረው አባሉ በግማሽ ተቀማጭ መዋጮም ቢሆን የሚቀጥልበትን ሁኔታ አመቻችተው የሚለያዩበት ቀን ነው፡፡ በዚህ ተቋም ከተለያዩ ቀበሌያት በርካታ አባላት የሚሳተፉበት ስለሆነ ማህበራዊ ግንኙነቱን በማጠናከር ረገድም ሆነ ስለአካባቢው ሁኔታ መረጃ ለመለዋወጥ በማስቻል በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ነው፡፡ በጐሳዎች መካከል በተመሳሳይ ዕቁብ ያለ ሲሆን፣ በዚህ ዕቁብ በዋናነት ዕርድ የሚከናወነው በሀዘን፣ በሰርግ ወዘተ ጊዜ ለመተጋገዝ በሚል አገልግሎት ላይ የሚውል ነው፡፡

ዕድርን ብንወስድ ዕድር በብሔረሰቡ አጠራር "ኢቲሬታ" ይባላል፡፡ ዕድር በከንታ (ንዑስ መንደር ደረጃ)፣ በፓሌታ ደረጃ፣ በጐሳ ደረጃም አለ፡፡ በነዚህ ደረጃዎች የሚሰበሰበው የዕድር ገንዘብ በዋናነት አገልግሎቱ በሀዘን ጊዜ ወይም ከባድ ህመም ሲያጋጥም፣ አሊያም ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ ጉዳይ ሲኖር ከዚያ ገንዘብ ወስነው በመውሰድ ለችግራቸው የሚያውሉት ነው፡፡ በግልም የሚያዋጡበት ሁኔታ አለ፡፡ ከገንዘብ ዕርዳታው በተጨማሪ በሀዘን ወቅት ሀዘንተኛው/ዋ ቤት የዕድሩን አባላት በመመደብ ለቀስተኞችን የመቀበል፣ የማስተናገድ፣ ከማህበረሰቡ የሚቀርቡትን ምግብና መጠጥ የመቀበል፣ ቤተሰቡን የማፅናናት፣ በሽተኛ ካለ ወደህክምና የመውሰድ፣ የእርሻ ስራ እንዳይስተጓጐል ሳር በማጨድ፣ ከብቶችን ከበረት በማስወጣትና ወደ ግጦሽና ውሀ በማሰማራት ማገዝ፣ የቤትም ስራ እንዳይበደል (እንዳይጐድል) ውኃ በመቅዳት፣ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት በማከናወን የሀዘንተኛው ቤተሰብ ህይወት የሚቀጥልበትን ሁኔታ የዕድሩ አባላት ያመቻቻሉ፤ ያግዛሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በሰርግ ወቅት ዝግጅትም በብሔረሰቡ አጠራር "ሳርጌታ" የዕድሩ አባላት የሆኑ ሴቶች በሙያቸው የሴት ስራዎችን በመስራት፣ ወንዶችም በሚመለከታቸው ጉዳይ ማለትም ዕቃ በማቅረብ አስፈላጊ ስራዎችን በመስራት ያግዛሉ፡፡ ድግሱ ሲጠናቀቅ ዕቃ የመመለስ፣ የጐደለ ካለ የመተካት፣ ለቤተሰቡ የተሰጠ ገንዘብ ካለ በማስረከብ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ይወጣሉ፡፡

ከዚህ ሌላ የሚጠቀሰው የቡድን ስራ ወይም "ደቦ" ሲሆን ይህም በተለያየ መልኩ ይገለፃል፡፡ የመጀመሪያው "የደቦ" ስራ በብሔረሰቡ አጠራር "ኡጋንዳ" ተብሎ የሚጠራው ተቋም ነው፡፡ "ኡጋንዳ" የዕለት ስራ ነው፡፡ ይህ ስራ አንድ ቤተሰብ እህል ከማሳ ለማስመጣት

አሊያም ሳር ከርቀት ለማስመጣት ወይንም እንጨት ለማሸከም ፈልገው ነገር ግን በአንድ ጊዜ፣ በቀላሉ ለሠራተኛ ከፍለው ለማሰራት የኢኮኖሚ አቅማቸው የማይፈቅድላቸው በሚሆኑበት ጊዜ አካባቢው ማሕበረሰብ ለዕለት ስራ እገዛ ይጠይቃሉ፡፡ በዕለት ስራ ከሴቱም፣ ከወንዱም፣ በዕድሜ ገፋ ካለውም እንደሙያቸው በመጥራት ያሰራሉ፡፡ ለዚህ የዕለት ስራ ከቤተሰቡ የሚጠበቀው ቤት ያፈራውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት ብቻ ይሆናል፡፡ ክፍያ አይኖረውም፡፡

ሁለተኛው የቡድን (ደቦ) ስራ በብሔረሰቡ አጠራር "ፓርካ" የሚባል ሲሆን በሁለት መልኩ ይገለጻል፡፡ የመጀመሪያው የሴቶች (እህቶች) ቡድን ሲሆን፣ ሁለተኛው የወንዶች ቡድን ነው፡፡ ሆኖም ግን ሴቶቹም ያለ ወንድም እገዛ ስራው አይሳካም በሚል ቢያንስ ሁለት ወይንም ሦስት ወንዶች የሚጨምሩበት ሁኔታ ሲኖር፣ በተመሳሳይ ወንዶችም ያለ እህት በሚል ሁለት ወይንም ሦስት ሴቶችን (እህቶችን) የሚጨምሩበት ሁኔታ አለ፡፡

የጾታ ስብጥሩ ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ከወንዱም ከሴቱም በእኩል መጠን ተውጣጥተው የሚሰባሰቡበትና በየተራ ለእያንዳንዳቸው እርሻ የሚወጡበት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሰባሰቡት የደቦ አባላት የደቦው አባል ላልሆኑ ሰዎች ደግሞ ስራ ለመስራት ሲወጡ ገንዘብ የሚጠይቁበት ሁኔታ አለ፡፡ የገንዘቡ አከፋፈል ሁኔታ በተለያየ መልኩ የሚተመን ሲሆን በሰው አርባ አርባ ወይም ሃምሳ ሃምሳ ብር አሊያም በጥቅሉ አምስት መቶ ብር ወይም አንድ ሺህ ብር ብሎ በመተመን እንደሰው ብዛት ስራ ወጥተው ገንዘብ የሚያገኙበት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚያገኙትን ገንዘብ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለበሬ መግዣ አውለው እራሳቸውን ያዝናኑበታል፤ ቀሪውን ገንዘብ ተከፋፍለው ለተለያዩ ለግል ጉዳዮቻቸው ያውላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ቀደም ባሉት ጊዜያት የሚፈፀመው በታህሳስና ጥር ወር ሲሆን በዚያ ወቅት "ኦሎሎታ" የሚባል ባህላዊ ዘፈን እየዘፈኑ፣ እየጨፈሩ ያከብሩት ነበር፡፡ በዚያ የጭፈራ ወቅት የበሬውን ሞራ አንገታቸው ላይ በማጥለቅ የበሬውን ስብነት ለማሳየትና ለመግለጽ ይዞሩ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ሴቶቹ ሲጨፍሩ የአንገት ጨሌያቸውን በማድረግ ተውበውና የዱላ ጉማጆችን አዘጋጅተው እየመቱ ነበር፡፡ በጭፈራው ወቅት የግል ጥንካሬ፣ ብቃት እና/ወይም በስራ ሂደት ያጋጠማቸውን ስኬት በማነሳሳት ያሞጋግሱ ነበር፡፡

ይህ ስርዓት አሁን የሚከናወነው መስከረም ላይ በመስቀል በዓል ወቅት ሆኗል፡፡ መስቀል በኮንሶ የተለመደ ባይሆንም ስርዓቱ ወደ መስከረም የተለወጠበትን እንደምክንያት ሲናገሩ የመጀመሪያው የክርስትና እምነት በአካባቢው መስፋፋት፣ ሁለተኛው ዘመናዊነት

(ትምህርት) መስፋፋት፣ በተጨማሪም መስከረም እሸት የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ መስከረም ዞሮ በመስቀል በዓል ወቅት የሚከናወን መሆኑን በመስክ ቆይታ የአጥኚዋ ጊዜያዊ ማረፊያ በነበረው በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር በወ/ሮ ሀገያ ሶካ መኖሪያ ቤት በተካሄደው የዕቁብ ማጠናቀቂያ ስነ ስርዓት ላይ ከተለያዩ የብሔረሰቡ ተወላጅ  ተሳታፊዎች ጋር በተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት የተገኘው መረጃ ያመለክታል (ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም)።

ከዚህ በተጨማሪ አስቸኳይ የቀን ስራ ይጠቀሳል። ይህ በብሔረሰቡ አጠራር "ሉዱማዳ" ይባላል። "ሉዱማዳ" አንድ ሰው በሆነ አጋጣሚ አንድ አስቸኳይ ስራ ኖሮት ስራውን እዚያው አሠርቶ  ለስራው ተመጣጣኝ ክፍያ የሚፈጽምበት የስራ ዓይነት ነው። የክፍያ መጠን እንደስራው ሁኔታ ይወሰናል። የቀን ሠራተኞቹም እዚያው የሰሩበትን ተከፋፍለው የዕለት ጉርሳቸውን (የሚፈልጉትን) የሚያደርጉበት ነው። በዚህም ስራ ፆታና ዕድሜ አይለይም። ሁሉንም ያሳትፋል።

በሌላ በኩል አብሮነታቸውንና መደጋገፋቸውን ለመግለጽ በብሔረሰቡ አባባል ‹‹ኾራ ካሌ ካፋ ዳኒ›› ይባላል። ይህም ማለት በአጋጣሚም ይሁን ታስቦበት የአንድ ሰው ሕይወት ቢጠፋ የነፍስ ዋጋ ‹‹ጉማ›› ከፋዩ ካፋው (ጎሳው) ነው፤ ጎሳው ይተባበራል።

እነዚህ ሁሉ ማህበራዊ ተቋማት በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን የጠነከረ ማህበራዊ መስተጋብርና ግንኙነት በእጅጉ የሚገልጹና የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ውስጥ እነዚህን መሠል ተቋማት መኖራቸው ማህበረሰቡን በዕለት ተዕለት ህይወቱ የሚያገናኙ፣ የሚያቀራርቡ በመሆናቸው ለማህበረሰቡ መልካም ግንኙነት ወይም ማህበራዊ ትስስርና አኗኗር ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል።

## 3.6 ባህላዊ አስተዳደር

### 3.6.1. ፓሌታዊ አደረጃጀት

የኮንሶ ብሔረሰብ የሚኖረው ከተማ መሰል በሆኑ ፓሌታዎች(መንደሮች) ነው። ፓሌታዎቹ ችምችም ብለውና ተጠጋግተው በተሰሩ ቤቶች የተሞሉ ሲሆኑ፣ አደረጃጀታቸውን በተመለከተ በ5 (አምስት) አገልግሎቶች ሆኖ በ41 (አርባ አንድ) የገጠር ቀበሌ ማህበራት የተመሰረተ ነው። የአገልግሎቱ አደረጃጀት እንደሴክተር (ወረዳ) ሆኖ በስሩ ቀበሌያት

(መንደሮች) እንዲይዝ ተደርጎ የተዋቀረ ነው፡፡ አደረጃጀቱ የካራት፣ ፋሻ፣ ቱሮ፣ ኮልሜና ጉማይዴ አገልግሎቶች በሚል ሲሆን፣ እነዚህም በካራት አገልግሎት ስር ጃርሶ፣ ደራ፣ አባሮባ፣ ናላያ ሰገን፣ ዱራይቴ፣ ዶካቱ፣ ጋሞሌ፣ መጨሎ፣ ቡሶ፣ ጎጫ፣ ሶሮቦ፣ ብአይዴና ፋጬጫ የተባሉ 13 ቀበሌያትን (መንደሮችን)፤ በቱሮ አገልግሎት ገላቦ፣ ተሽመሌ፣ አርፋይዴና ለሀይቴ የተባሉ ቀበሌዎችን፤ በኮልሜ አገልግሎት ቦርቃራ፣ ጉኛራ፣ ማደሪያና ግዛባ፣ ገልገላና ቆልማሌ፣ ጠበላና ቁጫሌ፣ እንዲሁም ማሶያ በድምሩ 6 ቀበሌዎችን በመጨረሻም በጉማይዴ አገልግሎት ሉልቶ፣ ከርከሳ፣ አይሎታዶካቱ፣ አዲስገበሬ፣ ባቾ፣ መላካ ና ዱካያ፣ ሰገን ገነትና ገርጬ በጥቅሉ 8 ቀበሌዎችን እንዲይዝ ተደርጎ የተደራጀ ነው፡፡ በኮንሲታ "ፓሌታ'' መንደር ተብሎ ይታወቃል፡፡ አንድ "ፓሌታ" በብዙ ንዑስ መንደሮች የተከፋፈለና ይህም "ከንታ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ አንድ ከንታ ብዙ ቶላ (ቲካ) ዎችን ይይዛል፡፡ ቶላ (ቲካ) ማለት አንድ አባወራ ወይም ቤተሰብ ማለት ነው፡፡ የኮንሶ ሕዝብ የመኖሪያ አሰፋፈር እንደሰፈራ ጣቢያ ወይም እንደከተማ በተለያዩ ቦታዎች ጥቅጥቅ ባለ ቤት የተሞላ በመሆኑ አንዱ ሰፈራ ጣቢያ ወይም አንዱ ከተማ "ፓሌታ" ወይም የቀበሌ አስተዳደር ተብሎም ይጠራል፡፡ ፓሌታዎች በየራሳቸው የተሟላ አስተዳዳራዊና የዳኝነት ሥርዓት እንዲሁም የየራሳቸውም መሪ ያላቸው ናቸው፡፡ መሪያቸውም አፓ-ቲንባ ይባላል፡፡ ስለዚህ በባህላዊም ሆነ በፖለቲካ አስተዳደር በራሳቸው ምሉዕ ናቸው፡፡ ማንኛውንም ጉዳይ በራሳቸው ይወስናሉ፡፡ ፍርድም ይሰጣሉ፡፡ ይሁንና መንግስት ነክ ጉዳዮችን ግን በቀጥታ ወደሚመለከተው አካል ያስተላልፋሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለአብነት ከቀበሌ ሊቃነመናብርት፣ ከማህበራዊ ፍርድ ሸንጎ አባላት፣ ከጥበቃ ጓዶችና ከሚመለከታቸው የአመራር አካላት አስተዳደር ጋር ጉዳዮችን በጋራ እንደሚያዩና ግጭቶችን በመቀናጀት እንደሚፈቱ አጥኚዋ በመስክ ቆይታዋ ከአንዳንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች ጋር በነበራት ኢ-መደበኛ ውይይት ለመረዳት ችላለች (በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

### 3.6.2 ጐሣዊ አደረጃጀት

የኮንሶ ብሔረሰብ አንድ ወጥ ብሔረሰብ ቢሆንም በዘጠኝ ጎሳዎች የተደራጀና እያንዳንዱ ጉሳ የራሱ መሪ ያለው ነው፡፡ ዘጠኙ ጎሳዎች እሻላይታ፣ ከርቲታ፣ ፓሳንታ፣ ሳውዳታ፣ ማሐሌታ፣ ኤላይታ፣ አርጋማይታ፣ ቶክማሌታ፣ እና ትክሳይታ ይባላሉ፡፡ እነዚህ ጉሣዎች እያንዳንዳቸው ''ፖቅላ ቱማ'' የሚል የማዕረግ መጠሪያ ያላቸው የጎሳ መሪዎች አሏቸው

(የደ/ብ/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ም/ቤት የባህል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፣ 2001: 153)፡፡ ዘጠኙም ጕሳዎች የራሳቸው የሆኑ አርማዎች አሏቸው። እንደመረጃ አቀባዩ ዲኖቴ አገላለጽ፡-

> *‹‹አርማ ስንል የሚታይና የሚጨበጥ ማለት አይደለም ፤ቀዳሚው ጎሳ ከተከታዩ ወይም ከአዲሱ ትውልድ ጋር ግንኙነት የሚፈጥርበት መለያ እንደማለት ነው፤ ለአብነትም አርጋማይታ የተባለው ጎሳ የግመል ስጋ አይቀምስም መለያው ነው፤ ስለዚህ በዚህ መለያው የአርጋማይታ ጎሳ መሆኑ ይታወቃል ፤እሻላይታ ጎሳ ደግሞ ኩይሳን ያከብራል ከዚህ ወጣን ይላል ፤ስለዚህ ይህ መሊያ አርማው ነው ማለት ነው፤ በተጨማሪም የሳውደታ ጎሳ ዝንጀሮ ያከብራል ለዝንጀሮ ልዩ ክብር አለው ይህ መለያው ነው፤ ስለዚህ በዚህ መሰረት ሁሉም ጎሳ ተለይቶ የሚታወቅበት የየራሱ መለያዎች አሉት››* (በደንገልቱ[4]፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 31[5]) በማለት ያሰረዳሉ፡፡

የእያንዳንዱ የጕሳ መሪና የተሰጠው መጠሪያ በመገኛ ቋንቋው በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2 የኮንሶ ጕሳ መሪና መጠሪያ

| | ጕሳዎች (ካፋዎች) | የጕሳ መሪዎች መጠሪያ (ፖቅላ) |
|---|---|---|
| 1 | እሻላይታ | አፋርታ ፖቅላ |
| 2 | ከርቲታ | ካላ ›› |
| 3 | ማሐሌታ | ኮርጂባ ›› |
| 4 | ሣውደታ | ማቶ ›› |
| 5 | ፓሣንታ | ሎኾባ ›› |
| 6 | ኤላይታ | ባሕሞ ›› |
| 7 | ትክሳይታ | ኦርጌታ ›› |
| 8 | አርጋማይታ | ባማሌ ›› |
| 9 | ቶክማሌታ | አይሎ ›› |

---

[4] በደንገልቱ በዱራይቴ ቀበሌ የሚገኝ ነዑስ መንደር ነው፡፡

[5] በጥናቱ ውስጥ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡ የገጽ ጥቅሶች (ጥቅስማዎች) በአባሪ ላይ የቀረቡና በስክርብ ውስጥ በተመሳሳይ ገጽ ላይ ያሉ ናቸው፡፡


እነዚህ የጎሳ መሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የአመራር እና የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ሲሆን፣ ይህ ስልጣን በዘር ሀረግ የሚተላለፍና የዕድሜ ልክ ነው። የኮንሶ የዘር ሀረግ የሚተላለፈው በአባት ዘር ሲሆን የአንድ ጐሣ አባላት የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን እንደ እህትና ወንድም ይቆጥራሉ። በዚህም የተነሳ የአንድ ጎሳ አባላት በሆኑ ግለሰቦች መካከል የእርስ በርስ ጋብቻ የተከለከለና በመካከላቸው የሚፈጠር የግብረ ስጋ ግንኙነትም የተወገዘ ነው፡፡

በሁሉም የኮንሶ መንደሮች (ፓሌታዎች) ውስጥ የዘጠኙም ጐሣ አባላት ተቀላቅለው ወይም በስብጥር በጋራ ይኖራሉ። ዋና ዋና የጐሣ መሪዎች ወይም ፖቅላዎችና ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ተለይተው በአካባቢዎች ብቻ ተወስነው ወይም በየራሳቸው ማዕከል ይኖራሉ። በኮንሶዎች አባባል “ፖቃላ ላኪ ኦልቃራ ኩትኒንቻን” ይባላል፡፡ ይህም ማለት ሁለት ፖቅላዎች በአንድ አካባቢ አይቀመጡም እንደማለት ነው። ከዚህ የተነሳ እየተሽጋሸጉ ወደተለያዩ አካባቢዎች ሄደው በመስፈር መኖሪያ ግቢያቸውንና ጫካዎቻቸውን እንደሚመስርቱ በነበረ ኢ-መደበኛ ውይይት ለመረዳት ተችሏል (በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

በኮንሶ ብሔረሰብ የጐሳ መሪዎች እንደ ኃይማኖት መሪዎች የሚቆጠሩ ሲሆን፣ ሕዝቡን የመባረክና የመምከር እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትን የማድረግ ስልጣን አላቸው። ዋና ተግባራቸው ለጐሳውና ለአጠቃላይ ለኮንሶ ሕዝብ እንዲሁም ለሀገርና ለዓለም ሰላምና ደህንነት ፀሎት ማድረግ፣ የጐሳው አባላት የግንኙነት ሁኔታ እንዲዳብርና እንዲጠናከር የሚያስችሉ ስራዎች መስራትና የጐሳው አባላት ጉዳዮችን በበላይነት የማከናወን፣ አለመግባባቶችን መዳኘትና ግጭቶችን መፍታት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የጎሳ መሪ የራሱን የጎሳ አባላት ግንኙነት፣ ደህንነትና ሠላም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡ መሪው በጣም የሚከበርና የሚወደድ ሰው ሲሆን አኗኗሩም ብሔረሰቡ የ“ንጽህናና የክብር” መገለጫዎች የሚላቸውን ጉዳዮች በመጠበቅ ይሆናል። እንደ አብነትም ከቤቱ ውጪ የተሰራ ምግብ አይበላም። ፀጉሩን አይላጭም። ለቅሶና ሠርግ አይሄድም። ከኮንሶ ውጪ ሲወጣም አፈሩን ዘግኖ ይዞ ነው፡፡ ይህም በሄደበት ቦታ ሁሉ ከነሙሉ ክብሩ በኮንሶ ምድር እንዳለ ለማመልከትና ለማሰብ ነው።

ከዚሁ “ከፖቅላ ቱማው” በታች ፖቃላ ሙግላ ወይም ቱራይታ፣ ሣራ የተሰኙ የተለያዩ የስልጣን ደረጃዎች ያሏቸው ሹማምንቶችም አሉ። እነዚህም ፖቃላ ሙግላ ወይም ቱራይታ የሚባሉት “የፖቅላ ቱማው” ምክትል ሆነው የሚሰሩ ሲሆኑ፣ “ሣራ” የሚባሉት

ደግሞ የመሪውን ትዕዛዝ ተቀብለው ወደታችኛው የማህበረሰብ ክፍል በማድረስ የመልዕክተኛነት ተግባርን የሚያከናውኑ ናቸው፡፡ ይኸው መዋቅር በስዕል 3 ይታያል፡፡




ገላጭ ስዕል 3 የጎሳዊ አደረጃጀት መዋቅር

# ምዕራፍ 4. ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኮንሶ ብሔረሰብ

ማንኛውም ሰው ለመኖርና ህይወቱን ለመምራት በሚያደርገው ውጣ ውረድ አንድም ከራሱ አንድም ከቤተሰቡ አንድም ከጓደኛው ጋር በፍላጎት አለመጣጣም፣ እና/ወይም በሀሳብ ልዩነት ግጭት ውስጥ የሚገባበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በተመሳሳይ  ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል በፍላጎቶች አለመጣጣም ወይም በጥቅም ግጭት ሳቢያ አለመግባባት ይከሰታል፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች ከባድ ወይም ቀላል ግጭቶችን ሲጭሩ ይስተዋላል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ምዕራፍ ግጭት ለኮንሶ ህዝብ ምን ማለት እንደሆነ፣ ዓይነትና መንስኤዎቹ ምን እንደሆኑ፣ የግጭት መፍቻ ተቋማት የአደረጃጀት ሁኔታ ምን እንደሚመስል፣ የአስታራቂዎች ሚናና መምረጫ መስፈርት ምን እንደሆነ፣ ባህላዊ ዳኝነት የሚሰጥባቸው ቦታዎች የት እንደሆኑ፣ በየደረጃው ያሉ የግጭት አፈታት ሂደት የተለያዩ ኬዞችንና ሂደቶችን በተለያዩ ማሳያነት ለመተንተን ጥረት ይደረጋል፤ እንዲሁም በባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች በአብነቶች ተደግፎ ይቀርብበታል፡፡

## 4.1 የግጭት ጽንሰ ሀሳብ በኮንሶ ብሔረሰብ

የኮንሶ ብሔረሰብ በስራ ወዳድነቱ፣ በታታሪነቱ፣ በባህላዊ ዕውቀት አክባሪነቱና ተጠቃሚነቱ ዓለም አቀፍ ዕውቅና አግኝቷል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ከአበው የወረሱትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዕውቀት እንደአስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ጋር በማቀናጀት ግጭትን ለማስወገድ፣ በዳይን ለማስተማር፣ ተበዳይን ለመካስና ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ ይጠቀሙበታል፤ ተንከባክበው በመጠበቅ ለተተኪው ትውልድ ያስተላልፉታል፡፡ ባህላዊውን የግጭት መፍቻ ዕውቀት በመጠቀም ዕርቀ-ሰላም የማውረድ ጥረት ለመጀመር በቀዳሚነት በግለሰቦች እና/ወይም በቡድኖች መካከል የነበረ ሰላም መደፍረስ፣ የጠብ አጫሪነት መንፈስ መባባስ፣ የንብረት ይገባኛል ውዝግብ መፈጠር እና ቀላል ወይም ከባድ ተብሎ ሊፈረጅ የሚችል ግጭት መቀስቀስ ይኖርበታል፡፡

በዚህ የጥናቱ ክፍል የኮንሶ ማሕበረሰብ ‹‹ግጭት›› ለሚለው የአማርኛ ቃል በብሔረሰቡ ቋንቋ የሚሰጠው አቻ ስያሜ አለው ወይ? ግጭት በብሔረሰቡ ሁልጊዜ የሚከሰትስ ነውወይ? መነሻ ምክንያቶቹ ምንድናቸው? እንዴትስ መፍትሔ ያገኛሉ? በሚል በዝርዝር

ለቀረቡት ጥያቄዎች የኮንሶ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት በሚከናወንበት ዐውድ በመገኘት በሚደረግ ምልከታና በግጭት አፈታት ስርዓቱ ውስጥ ዋነኛ ተዋናዮች ከሆኑ አውራ መረጃ አቀባዮች በሚገኘው መረጃ በመታገዝ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ግጭት ለሚለው ቃል አቻ የብሔረሰቡ ስያሜ አለው ወይ በሚል ለከርቲታ ጎሳ መሪ ለቀረበችላቸው ጥያቄ፡-

> *‹‹ግጭት በብሔረሰቡ ቋንቋ ‹ኦል ዳብ› በመባል ይታወቃል ‹ፔቃ ›ጥል ‹ኦል ካሌታ ዳቤታ ›ወይም አለመስማማት የሚል አቻ ትርጓሜዎች አሉት፤ ‹ኦል ኬላ ዳባይታ› በሀሳብ መለያየት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ በተጨማሪም ግጭት ‹ኦል ዳቤታ ዲኣና›ተብሎ ይጠራል››* (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ[6]፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 1[7]) በማለት ሲገልጹ፡

አቶ ዲኖቴ ኩስያ በተመሳሳይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ከላይ በጎሳ መሪው የተጠቀሱት ስለመሆናቸው ያለልዩነት፡-

> *‹‹በብሔረሰቡ ግጭት ‹ኦል ዳብ› ይባላል ‹ኦል ካሌታ ዳቤታ› አለመስማማት የሚልም ትርጓሜዎች ይኖሩታል ‹ኦል ኬላ ዳባይታ› በሀሳብ አንድ አለመሆን መለያየት ተብሎም ሊገለፅ ይችላል በአጠቃላይ ግጭት ‹ኦል ዳቤታ ዲኣና› ተብሎ ይጠራል››* (በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 22) ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አቶ ኪሮስ ጃርሶ በበኩላቸው ስለ ግጭት አቻ ስያሜ መኖር ሲገልጹ፡-

> *‹‹ግጭት በኮንሶ ብሔረሰብ ዲሃይታ ወይም ፒያቃ ይባላል››* (በደንገልቱ፣ ጥር7፣ 2006 ዓ.ም፣ 31) ይላሉ፡፡

ከዚህ በላይ ስለግጭት ምንነት በተለያዩ የመረጃ አቀባዮች የተሰጠው የተለያየ ሀሳብ በተለያየ መልክና ቃላት ይገለጽ እንጂ አለመስማማት የሚለውን ሀሳብ አጉልቶ እንደሚያሳይ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ በብሔረሰቡ የግጭት መከሰቻ መንገዶች ምንድናቸው በሚል አቶ አያኖ በተመሳሳይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

---

[6] በጋሞሌ ቀበሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው፡፡

[7] ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች በተመሳሳይ ቦታና ዕለት የተደረገ ቃለመጠይቅ ሲሆን በቅንፍ ውስጥ ያሉቁጥሮች በስክርብ ውስጥ ያሉ ና በስምቅደም ተከተላቸው መሰረት የተቀመጡ መሆኑን ያመለክታል፡፡

*‹‹ግጭት በኮንሶ ሕዝቦች ዘንድ ብዙ ጊዜ የሚከሰት አይደለም፤ ይሁን እንጂ በብሔረሰቡ አባላት መካከል ግለሰቦች በትንሽ ነገር ተነስተው ትንሿን ነገር ወደ ትልቅ እየተረጐሙ ወደ ሕዝብ እያሸጋገሩ የዚህ ሕዝብ እኮ እንደዚህ ብሏል፤‹እከሌ እኮ እንዲህ አለ› ብሎ የማይሆንና ያልተባለን ነገር በመናገር በዚሁ መነሻ የሚፈጠር ቅራኔ ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 42) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል ካላ ገዛኸኝ ፡-

*‹‹ግጭት በኮንሶ በአብዛኛው ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ናቸው ፤ለዚህ መሰሉ ግጭት መንስኤ ከሚሆኑት ለመጥቀስ ያህል መሬት በኪራይ ወስዶ ባለመሬቱ መሬቱን ሲፈልግና ሲጠይቅ መካካድ ሲኖር ነው››* (ጋሞሌ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 1) በማለት ሲገልጹ፣

አቶ ዲኖቴ በበኩላቸው፡-

*‹‹ግጭት በኮንሶ በአብዛኛው ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዞ ይፈጠራል፤ ለዚህ ዓይነት ግጭቶች ደግሞ መንስኤ ሆነው የሚጠቀሱት መሬት በኪራይ ወይም በፊርማና ያለፊርማ ከአንድ ቤተሰብ ወስዶ ባለመሬቱ ወይም ባለይዞታው ሲፈልግ መካካድ ሲኖር፣ ሲመጣ፣ ሌላው ድንበር በመግፋት ማለትም አንዱ የሌላውን ድንበር ገፍቶ ሲገኝ ነው ››* (በደንገልቱ፣ ጥር 7፣ 2006 ዓ.ም፣ 22) በማለት ይገልጻሉ ፡፡

ይሁን እንጂ ግጭቶች በአካባቢው በተለያዩ ጉዳዮች መነሻነት እንደሚከሰቱ ሁሉም መረጃ አቀባዮች ይስማማሉ፡፡

ግጭቶች ሲከሰቱ ከመፍትሔ አወሳሰድ ጋር ተያይዞ ለቀረበ ጥያቄ አቶ ኪሮስ፡-

*‹‹ግጭቶች ሲፈጠሩ እኛ በአቅራቢያው ያለን ሽማግሌዎች ስለሆንን በቀጥታ ግጭቶች ወደኛ ሲመጡ አብዛኛውን ግጭቶች በእርቅ እንጨርሳለን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እስከ ቅጣት ውሳኔ እናደርሳለን››* (በደንገልቱ፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 31) ሲሉ ይጠቅሳሉ፡፡

በተመሳሳይ አቶ ካምብሮ፡-

*‹‹እኔ ግጭት በአካባቢው ሲከሰት እንደክስ መስራች ነኝ ብዬ ብል አልሳሳትም፤ ለምን ማንም ተበዳይ በቅድሚያ እኔ ጋ ይመጣል፤ እከሌ በደለኝ ይለኛል፤ ከዚያ በደሉን ሳይዘረዝር የኸራታ ገንዘብ እንዲይዝ ወይም እንዲያስይዝ አደርጋለሁ፤ ገንዘቡን ካስያዘ በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር በጋራ ሆነን በዳዩን እስከምንጠይቅ ድረስ ጊዜ እንሰጠዋለን፤ ከዚያ ቀነ ቀጠሮ ይዘን በዳዩን ገንዘብ እንዲያሲዝ አድርገን ሁለቱን በማቀራረብ በሞራዎች አግባብ ለማስታረቅ እንሞክራለን፤ አብዛኛውን ጊዜ በእርቅ እንዲያልቅ እንዲተማመኑና ይቅር እንዲባባሉ እናደርጋለን፤ አይ ተበዳይ በጣም ተጐድቻለሁ የሚል ከሆነ አስመስክረን እስከማስቀጣት እንደርሳለን››* (በደንገልቱ፣ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 37) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

## 4.2. የግጭት ዓይነቶችና መንስኤዎቻቸው

በኮንሶ ብሔረሰብ የሚቀሰቀሱት ግጭቶች ስንት ዓይነት ናቸው? ለግጭቶቹ መቀስቀስ በዋነኛነት የሚጠቀሱት መንስዔዎች ምን ምን ናቸው? በሚል ለአውራ መረጃ አቀባዮቹ በተደረገ ቃለ መጠይቅ ዓይነቶቹን በተመለከተ ካላ ገዛኸኝ ፡-

> *‹‹በኮንሶ ብሔረሰብ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች በዋናነት ስድስት ይሆናሉ በስድስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ እነዚህም በግለሰብ ደረጃ የሚፈጠር አለ በቤተሰብ፣ በጐረቤት፣ በቡድን ደረጃ መንደር ከመንደር ህብረት እየፈጠሩ፤ እንዲሁም በንብረት የሚፈጠረውንና ወንጀልን መጥቀስ ይቻላል፤ እነዚህን ግጭቶች ቀላልና ከባድ በማለት ልናያቸው እንችላለን›* (ጋሞሌ፣ጥር 10፣2006 ዓ.ም፣ 1) በማለት ሲገልጹ፣

ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ካምብሮና አያኖ በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንኑ ሀሳብ በተለያየ አገላለጽ ይናገራሉ (በደንገልቱ፣ ጥር10፣ 2006 ዓ፣ም፣ 22-23፣ 32፣ 38፣ 42)፡፡

በዚህ መሰረት በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር አውራ መረጃ አቀባዮቹ በ6 የከፈሏቸው የግጭት ዓይነቶች የመንስኤ ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.2.1. የግለሰብ ግጭት

እንደ አውራ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ የግለሰብ ግጭት በተለያየ ደረጃ በቅርብ ወዳጆች፣ በጓደኛማቾች ወዘተ መካከል ሊከሰት ይችላል፡፡ መንስኤውን አስመልክተው ዲኖቴ፡-

> *‹‹አፍእልፊት ፣መካካድ ፣አድልኦ መፈጸም፣ መናናቅ፣ በመጠጥ ሀይል በመገፋፋት ተገቢ ያልሆነ ቃላት ማውጣት ናቸው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 23) በማለት ሲገልጹ፣

ካላ ገዛኸኝ በበኩላቸው፡-

> *‹‹ለግለሰብ ግጭቶች ሰበቦቻቸው የተለያዩ ናቸው ፤እንደመጠጥ አፍ እላፊ ንግግር፣ ንቀት ተገቢ ያልሆነ ቃላት መወራወር፣ ክህደትና የገንዘብ ብድር ወስዶ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆን ሀይለኛ መሆን ፣በተለይ በሴቶች ከውኃ ወረፋ ጋር በተያያዘ አድሎ ናቸው። በፊት በቅርብ ወዳጆችና ጓደኞች ሊፈቱ የሚችሉበት አግባብ አለ በቅርብ ወዳጆችና ጓደኞች መፈታት ያልቻሉ ከሆኑ ኸራታ ይያዛል፤ኸራታ ማለት የክስ መክፈቻ ማለት ነው፤ ስለዚህ ይህ ኸራታ ይያዝና በሞራ ከንታ ደረጃ እንዲታይ ይደረጋል፤ በዚህ ደረጃ መፍትሄ ከሌለ ወደሞራፓሌታ ተላልፎ በዚያ ደረጃ ይታያል››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 1) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

አቶ ኪሮስ በተመሳሳይ ፡-

> *‹‹የግለሰብ ግጭቶች ዋና ሰበቦች በመጠጥ ሀይል አፍአልፌት፣ ንቀት፣ ሀይለኛ መሆን በተለይ ሴቶች ውኃ ከምንጭ ለመቅዳት በሚሄዱበት ጊዜ በወረፋ ምክንያት ብዙ ይደርሳሉ፤ የግለሰብ ግጭቶች ቀላል ግጭቶች ስለሆኑ በሞራ አግባብ በሞራ ከንታ ደረጃ ይፈታሉ፤ ከዚያ ከፍ ሲል በሞራ ፓሌታ ደረጃ ይቀርባሉ››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 32) በማለት ያብራራሉ፡፡

አቶ ካምብሮ እንዲሁ፡-

> *‹‹ተገቢ ያልሆነ ቃላት መወራወር ዘለፋ፣ ክህደት፣ ንቀት፣ በመጠጥ ሃይል መገፋፋት፣ መዘላለፍና አድሎ ናቸው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 38) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

አቶ አያኖ ደግሞ፡-

> *‹‹ብዙ ጊዜ ለግለሰብ ግጭት መነሻ ሰበቦቹ አፍ እልፌት፣ መጠጥ ጠጥቶ ተገቢ ያልሆነ ነገር መናገር፣ ሀይለኛ መሆን ከሁኔታና መናናቅ ለግለሰቦች ግጭቶች መነሻ ሰበቦች ይሆናል››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 42) ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች መረዳት እንደሚቻለው በብሔረሰቡ ለሚከሰቱ የግለሰብ ግጭቶች መነሻ ሰበቦቻቸውም ሆኑ መንስኤዎቻቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ እንደአብዛኞቹ ገለጻ ከሆነ መጠጥ ቀዳሚው ነው፡፡ በመጠጥ ኃይል አፍ እላፊና ተገቢ ያልሆነ ንግግር፣ ዘለፋና ስድብ፣ ንቀት፣ የቅናት መንፈስ (መቀናናት)፣ ተገቢ ያልሆነ ቃላት በመወራወር አንዱ ባንዱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣ ክህደት፣ ገንዘብ በብድር ወስዶ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ሰበብ እየፈጠሩ ጊዜ ማራዘም፣ ኃይለኝነት፣ በወፍጮ ቤትና በምንጭ ውኃ ቦታ በወረፋ ምክንያት (በሴቶች) የሚፈጠሩ ግጭቶች ከመሰዳደብ አልፎ እቃ እስከመስበር መድረስ፣ የግለሰቦችን ስሜት የሚነኩ ቀልዶች፣ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አድልኦ መፈፀምና የመሳሰሉት እንደሆኑ ከጠቅላላው ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.2.2. የቤተሰብ ግጭት

መረጃ አቀባዮቹ ካላ ገዛኸኝ፣ ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ካምብሮና አያኖ የቤተሰብ ግጭት የሚባለውን ሲገልጹ፡-

> *‹‹በቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠር ሆኖ በዋናነት በባልና ሚስት፣ በአባትና ልጅ በእናትና ልጅ ወይም ከቤተሰቡ አባላት ጋር ተጠግቶ ከሚኖር ሰው ጋር ተያይዞ የሚፈጠር አለመግባባት ነው››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣1፤ በደንገልቱ፣ ጥር10 ቀን 2006 ዓ.ም፣ 23፣ 32፣ 38፣ 42) በማለት ያብራራሉ፡፡

ለቤተሰብ ግጭቶች መንሰኤ የሚሆኑትን አስመልክተው ዲኖቴ ሲገልጹ፡-

> *‹‹መነሻ ሰበቡ ብዙ ጊዜ የቤተሰቡ የዕለት ተዕለት ስራ እንከን ሲገጥመው ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006 ዓ.ም፣ 23) ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ካምብሮ፡-

> *‹‹መንስኤው የቤተሰቡ የዕለት ተዕለት ተግባራት ሲጓደሉ፣ ሳይሟሉ ሲቀሩና ልጆች አለመታዘዝ ናቸው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 38) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ካላ ገዛኸኝ በበኩላቸው፡-

> *‹‹መንስኤያቸው እንግዲህ የኮንሶ ህዝብ የሚተዳደረው በእርሻ፣ ከብት በማርባትና ቀፎ በመስቀል ነው፤ እነዚህ የቤተሰቡ የዕለት ተዕለት ስራዎች ሲስተጓጎሉ የሚፈጠርነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 1) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች መረዳት እንደተቻለው ለቤተሰብ ግጭት መነሻ ሰበቦቹ የኮንሶ ማህበረሰብ የሚተዳደረው በእርሻ፣ በከብት ርቢ እንዲሁም ቀፎ በመስቀልና ማር በማምረት መሆኑን በመጥቀስ የቤተሰቡም የዕለት ተዕለት ተግባር በዚሁ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እነዚህ የተጠቀሱ ተግባራት እንከን ሲገጥማቸውና በልጆች ትዕዛዝ አለመፈጸም ሳቢያ የየዕለት ስራዎች ሲስተጓጎሉ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በነዚህ በተጠቀሱት ጉዳዮች የሚቀሰቀሰው ግጭት ከአፍ እላፊ አልፎ እስከድብደባ የሚደርሱበት ጊዜ ያለ መሆኑን መረጃ አቀባዩ ዲኖቴ ሲያስረዱ፡-

> *‹‹ከአፍ እልፊት ያለፈ ድብደባ ይኖረዋል፤ ድብደባ ደግሞ ተከትሎት የሚመጣ ደም የማፍሰስ ሁኔታ አለው፤ የተወገዘ ድርጊት ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 23) ሲሉ፣

ቦንሳ በበኩሏ፡-

> *‹‹ድብደባ ይኖራል፤ ድብደባ በማህበረሰቡ አብሮት ተከትሎት የሚፈጠር ደም የማፍሰስ ሁኔታ ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታሰብ በጣም የተወገዘ ድርጊትና ከባድ ቅጣት የሚጣልበት ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 52) በማለት ትገልጻለች፡፡

እነዚህ ግጭቶች ከቀላል የግጭት ዓይነቶች የሚመደቡ በመሆናቸው፡-

*‹‹በቅርብ ቤተዘመድ በአባወራው ታይተው ይፈታሉ፤ ከቅርብ ቤተዘመድና ከአባወራ አቅም በላይ ከሆኑ ደግሞ በሞራ ከንታ ደረጃ እልባት ይሰጣቸዋል፤ ከዚህም ሲያልፍ ወደሞራፓሌታ ተሸጋግረው ይፈታሉ››* (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 1) በማለት ይገልጻሉ።

### 4.2.3. የጉረቤት ግጭት

እንደመረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ የጉረቤት ግጭት ሲባል ጉረቤት ከጉረቤት አሊያም አንድ ከንታ (ንዑስ መንደር) ከሌላ ከንታ (ንዑስ መንደር) ጋር የሚፈጥረው አለመግባባት ነው። በዚህ ደረጃ ለሚፈጠሩ ወይም ለሚከሰቱ ግጭቶች መነሻ ሰበቦች ወይንም መንስኤዎቻቸው፡-

*‹‹የጉረቤትን ሰላም የሚነሳ ጩኸት ወይንም ከፍተኛ ድምፅ፣ የሞሪንጋ ዛፍ ቅርንጫፍ መዝመምና የጉረቤት ጣራን መንካት፣ ባለንብረቶች ዛፉን እንዲቆርጡ ተጠይቀው ለመቁረጥ ፍቃደኛ አለመሆን፣ የአጥር መዝመምና የጉረቤት ይዞታን መንካት ወይም ማለፍ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የከብቶችና የህፃናት ጥፋት ለግጭት መቀስቀስ መንስዔ መሆኑን ያመለክታሉ፤ ለአብነትም የተሰጣን እህል የእርሻና የማሳ እህልና ሳርን በከብቶች ማስበላት፣ በልጆች ጨዋታ የተሰጣ እህል መበተን፣ ዕቃ መስበር፣ ባለማወቅ ዕቃ መውሰድና መደባደብ ወዘተ ይጠቀሳሉ፤በዚህ ደረጃ የሚከሰተውም ግጭት በሞራ ከንታ ደረጃ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ እንዲፈቱ ተደርጎ ከዚህ ደረጃ በላይ ከሆነ ወደ ሞራፓሌታ በማሸጋገር እንዲፈታ ይደረጋል››* (ካላ ገዛኸኝ፣ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 2፤ ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ካምብሮና አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 23፣ 32፣ 38፣ 42-43) ይላሉ።

### 4.2.4. የቡድን ግጭት

የቡድን ግጭት ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው መንደር ከመንደር (ፓሌታ ከፓሌታ)፣ እንዲሁም ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ያለልዩነት ይገልጻሉ። ዲኖቴ ለግጭቱ መንስኤ ሆኖ የሚጠቀሰውን ሲያስረዱ፡-

*‹‹በኮንሶ እያንዳንዱ ፓሌታ ወይም ቀበሌ የየራሱ ድንበር አለው ቀበሌውም ወረዳውም ሆነ አቅራቢያ ብሄረሰቦች ድንበሮቻቸው እንዲነኩ አይሹም፤ አይፈልጉም››* (በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 23) በማለት ሲገልጹ፡-

*ኪሮስ በበኩላቸው፡-*

*‹‹ዋናው ለቡድን ግጭት ለቡድን ጠብ ምክንያቱ ድንበር ነው፤ እያንዳንዱ ቀበሌም ሆነ አቅራቢያ ብሔረሰብ ድንበሮቻቸው እንዲጣሱ ፈጽመው አይፈቅዱም፤ ስለዚህ ይህ በተነካ*

*ቁጥር ድንበር በተገፋ ጊዜ የቡድን ግጭቱ አንዱ መንደር ከሌላ መንደር ከባድ ግጭት ውስጥ ይገባል›› *(በደንገልቱ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 32) በማለት ያስረዳሉ።

ሌሎች የመረጃ አቀባዮችም ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ሀሳባቸውን በተመሳሳይ ይገልጻሉ (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 2፤ ካምብሮና አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 38፣ 43)፡፡

ከላይ ከመረጃ አቀባዮቹ ሀሳብ ያለልዩነት መረዳት የተቻለው ለቡድን ግጭት መንስኤ ሆኖ የሚጠቀሰው የድንበር ጉዳይ መሆኑ ነው። ከድንበር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። ድንበሬን ገፋህ ገፋሽ፣ የይዞታ ክርክርም ይኖራል። በኮንሶ እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደርም ሆነ ወረዳው የራሱ የሆነ አራቱንም ማዕዘናት ያጣቀሰ ድንበር ያለው እንደመሆኑ ቀበሌውም ሆነ አቅራቢያ ብሔረሰቦች ድንበሮቻቸው እንዲጣሱ ወይም እንዲደፈሩ አይፈልጉም። ስለዚህ እነዚህ በተነኩ ቁጥር ለግጭት መቀስቀስ ምክንያት እንደሆኑ የመረጃ አቀባዮቹ ገለጻ አስረጂ ሆነው ቀርበዋል።

ምክንያቱን ዲኖቴ፡-

> *‹‹መሬቱን ለልዩ ልዩ አገልግሎት ይጠቀሙበታል፤ ቀፎ ይሰቅሉበታል፤ ለእርሻ ናለግጦሽ ይፈልጉታል፤ ስለዚህ እዚህ ተደፍረው ከተገኙ በዚህ ሳቢያ ግጭት ውስጥ ይገባሉ»* (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 23) በማለት ሲገልጹ፣

መንበረ ስልጣንን የመቆናጠጥ ፍላጎትም ለግጭት መከሰት በምክንያትነት እንደሚጠቀስ ካላ ገዛኸኝ፡-

> *‹‹አዲስ የወጣት ትውልድ ሽግግር ወይም የኼላ ስልጣንን ለመውሰድ አንድ ጀብዱ መስራትና በትውልድ ዘመኑ ጀብዱው እንዲወሳ ከመፈለግ የተነሳ ግጭቱ ይከሰታል፤ ይህም ዞሮ ዞሮ ወደ ድንበር ግጭት ቢያመራም መነሻው ግን ስልጣን መሻት ነው፤ ለአብነት የጕረቤቱን ድንበር ገፍቶ ወደራሱ የማድረግ፣ ይሄ ድሮ የኛ ድንበር ወይም መሬት ነበር በማለት ነገር ቆስቁሶ በዚያ ሳቢያ መንደር ከመንደር በቡድን እንዲጋጭ የማድረግ፣ በዚህ ሁኔታ የሚከሰት ግጭት እስከነፍስ ግድያ የሚያደርስ ሲሆን፣ በዚህ ሳቢያ ከየመንደሩ ሰው ሲሞት ይህ የትውልዱ ጉብዝና እንደጀብዱ ስለሚወሳ ይህንን ከመሻት አንጻር የቡድን ግጭቱ ይከሰታል››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 2) ሲሉ ይገልጻሉ።

በእነዚህ መነሻነት የሚፈጠሩ ግጭቶች ከከባድ የግጭት ዓይነቶች ተመድበው የሚታዩ መሆናቸውን ዲኖቴ ሲገልጹ፡-

‹‹*የቡድን ግጭት ከባድ ግጭት ነው፤መንስኤው የድንበር ጥያቄ ነው፤ የቡድን ግጭት በብሔረሰቡ ብዙ ጊዜ የሰው ነፍስ እስከማጥፋት ይደርሳል፤ በቡድን ግጭት ወቅት ለጠፋ ነፍስ አይለቀስለትም፤ የሞተውም ሞተ አይባልም*›› (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 24) በማለት ያስረዳሉ፡፡

ለምን እንደማይለቀስ ካላ ገዛኸኝ ሲገልጹም፡-

‹‹*በዚህ ዓይነቱ ግጭት ለሞተ ሰው ለድንበሩ ሞተ ለመሬቱ ሞተ ስለሚባል አይለቀስለትም፤ እንዲያውም ጭፈራ ነው የሚሆነው፤ ድንበሩን ላለማስነካት ሲል ሞተ ተብሎ እንደ ጀግና ይጨፈርለታል፤ ይወደሳል፤ ስለዚህ የሰው ህይወት የሚጠፋበት በመሆኑ በከባድ ግጭትነት ተፈርጆ የሚታይ ነው*›› (ጋሞሌ፣ ጥር 10 ቀን 2006፣ 2-3) ሲሉ፣

ዲኖቴ በበኩላቸው፡-

‹‹*ለድንበሩ ለሞተ ሰው ለቅሶ ሳይሆን እንደጀግና ጭፈራ ይደረግለታል ይወደሳል*›› (በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 24) በማለት ይገልጹታል፡፡

### 4.2.5. ከሀብት ንብረት ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ግጭት

ሀብትና ንብረት ሲባል ብዙ ጉዳዮችን ማንሳት መቻሉን መረጃ አቀባዮቹ ካላገዛኸኝና ዲኖቴ በተመሳሳይ ዕለትና ቦታ በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት ይናገራሉ (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 3፣ 24)፡፡

በብሔረሰቡ ሀብትና ንብረት የግጭት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ሲያስረዱም፡-

‹‹*የብሔረሰቡ የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመሬት ጥበት መፈጠሩ ነው፤ ስለሆነም መሬት በቀዳሚነት ይጠቀሳል፤ መሬት ስንል የግጦሽ፣ የእርሻ እንዲሁም ከባለቤትነት ጋር ተያይዞ የሚመጣም ነው*›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 3፤ ዲኖቴ፣ ኪሮስ ና አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 10፣2006 ዓ.ም፣ 24፣ 33፣ 43) ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ከባለቤትነት ጋር ተያይዞ ስለሚመጣው ጉዳይ ካላገዛኸኝ ሲገልጹ፡-

‹‹*ለምሳሌ የዛፍ አበቃቀል ሁኔታን ብናነሳ ዛፉ የበቀለው በኔ መሬት ላይ ነው ስለዚህ የማር ቀፎ መስቀልና መጠቀም አትችልም እችላለሁ በሚል የዛፉ ጥላ አዝመራዬን ከልሎታልና የማር ቀፎ የተሰቀለበትን ዛፍ እቆርጣለሁ አትቆርጥም በሚል የተነሳ ጠብ ውስጥ ይገባል*›› (ጋሞሌ፣ ጥር10፣ 2006 ዓ.ም፣ 3) ሲሉ ያብራራሉ፡፡

የይዞታ ጉዳይን አስመልክተው ሲያስረዱም፡-

*‹‹የቤት አጥር መንካት ወይንም መግፋት፣ የሰውን ንብረት ለልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎት ለለቅሶ ና ለሰርግ ተጠቅሞ ባግባቡ ንብረቱን ወይንም ዕቃውን አለመመለስ፣ የተሰበረ ካለ ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆን ሲሆን፣ ከውኃ ጋር በተያያዘ የምንጭ ውኃ የሕዝብ የጋራ ሀብት ነው፤ ከአጠቃቀም ጋር በተያያዘ እንዲሁም ስርቆት ከጥቃቅን ነገር ተነስቶ እስከ ከባድ ንብረቶች መውሰድ፣ ሆን ብሎ የራስንም የጐረቤቶችንም ቤት ለማቃጠል መሞከር ወይም አቃጥላለሁ ብሎ መዛት በራሱና አንዱ የአንዱን ሚስት በማባበል ወይም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከትዳር አፈናቅሎ ያገባ እንደሆነ ለግጭቶቹ መፈጠር ዋነኛ መንስኤዎች ናቸው››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10 ቀን 2006 ዓ.ም፣ 3) በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ በመረጃ አቀባዮቹ ከተገለጹት ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በተዘረዘሩት መነሻዎች የሚፈጠሩ ግጭቶች ከከባድ የግጭት ዓይነቶች የሚመደቡ መሆናቸውን ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ መሬት ለኮንሶዎች የደም ስር የሕይወት ጉዳይ ነውና፡፡ በመሬት ጉዳይ ቀልድ የለም ስርቆትና ቤት ማቃጠል በብሔረሰቡ የተወገዙ ወንጀሎች ናቸው፤ ከትዳር አፈናቅሎ የሌላን ሰው ሚስት ማግባት ከጎሳ አባል መጨመርና መቀነስ ጋር ስለሚያያይዙት ሴትየዋ ከዚህ በኂላ የምትወልደው ወንድ ልጅ የኛ ጎሳ አባል አይደለም የሌላ ጎሳ አባል ነው፡፡ ቁጥራችን ተቀነሰ የሚለውን ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን አመለካከት መነሻ በማድረግ ለከፋ ግጭት እንደሚዳረጉ ከሰጡት ማብራሪያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከትዳሯ አፈናቅሎ ያገባው ባልም የመጀመሪያ ባልዋ ለወላጆችዋ የጣለውን ጥሎሽ አራትና አምስት እጅ ጥሎ ሴትየዋ ምንም ንብረት ሳትካፈል በክብር ወደአዲሱ ጎጆዋ ተጠቃልላ እንድትገባ የሚደረግ መሆኑን በቃለመጠይቁ ወቅት በአግረመንገድ ጥያቄዎች ግንዛቤ የተገኘበት ነው፡፡ ንብረት ለምን እንደማትካፈል ለመረጃ አቀባዮቹ በቀረበ ቃለ መጠይቅ ዲኖቴ ኮጫኔና ሳጎያ ያለልዩነት፡-

*‹‹በኮንሶ ባህል ሴት ልጅ ከእናት ጌጣ ጌጥ ከአባት ደግሞ በሕይወት ዘመንዋ ብቻ በተለይም ከትዳር ሕይወቷ በፊት በወላጆቿ ቤት እያለች የምትጠቀምበትን አንድ የእርሻ መሬት ወይም አንድ የሽፈራው ዛፍ ተክል የሚሰጣት ሲሆን፣ በዚህ መልኩ የነበራት ንብረት ወደ አዲሱ ትዳሯ ስትገባ ንብረትነቱ ለወላጆቿ የሚመለስ ይሆናል››* (ቡርቁዳ[8]፣ ጥር 12፣ 2006 ዓ.ም፣ 45፣ 47) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

### 4.2.6. ወንጀል

እንደመረጃ አቀባዮቹ ካላ ገዛኸኝ፣ዲኖቴ፣ኪሮስ፣ዲኖቴ ኮጫኔና ሳጎያ አገላለጽ፡-

---

[8] ቡርቁዳ በዶካቶ ቀበሌ የሚገኝ ንዑስ መንደር ነው፡፡

*‹‹በብሔረሰቡ ወንጀል ተብለው የሚጠሩት የተወገዙ ድርጊቶችና ጥፋቶች ሲሆኑ፣ ለከፍተኛ ቅጣት የሚያደርሱም ናቸው፤ ወንጀሎች ብለን የምንጠራቸው ድብደባ መፈፀም፣ ድብደባው ደም መፍሰስ ያለበት ከሆነ እንዲሁም ‹ደም› ብሎ ቃሉን መጥራት፣ ተደጋጋሚ ስርቆት መፈፀም ፣ድንገተኛ ነፍስ ግድያ ፣ሴቶችን ከትዳራቸው ማስኮብለል፣ ማባለግ፣ መድፈርና አካል ማጉደል እንዲሁም በብሔረሰቡ ውጉዝ የተባሉ ጋብቻዎችን መፈፀም ናቸው››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 4፤ በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 24፣ 33፣ 45፣ 47) በማለት ሲገልጹ፣

ለነዚህ ወንጀሎች መነሻቸውን አስመልክተው ካላ ገዛኸኝ፣ዲኖቴ ኮጫኔና ሳጎያ ሲናገሩ፡-

*‹‹ድንገተኛ ፀብ ፣ልማደኛ መሆን፣ የስርቆት አመል፣ ችግርና ማጣት ድንገተኛ አደጋ የሞተር ሳይክልና የመኪና፣ ለባህላዊ ስርዓቱ ተገዢ አለመሆን፣ ንቀትና የተመሳሳይ ጎሳ ጋብቻ መፈፀም ናቸው››* (ጋሞሌ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 4፤ ቡርቁዳ፣ ጥር 10 ቀን 2006 ዓ.ም፣ 45፣ 48) ሲሉ ይጠቅሳሉ፡፡

## 4.3 የግጭት መፍቻ ተቋማት አደረጃጀት፣ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት

### 4.3.1. የተቋማቱ አደረጃጀትና አስታራቂዎች

በብሔረሰቡ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ሁኔታ እንደዳኝነት ስፍራ (ሞራው) የተለያዩ ናቸው (ካላ ገዛኸኝ፣ጋሞሌ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 8፤ ዲኖቴ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 25) ሲሉ፣ በዚሁ መነሻነት በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በየደረጃው ያሉ የግጭት መፍቻ ተቋማት የአደረጃጀት ሁኔታ፣ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርቱ እንደሚከተለው የቀረበ ሲሆን ዝርዝሩ ከሠንጠረዥ 3-5 ተመልክቷል፡፡

#### 4.3.1.1. ሞራ- ከንታ

በብሔረሰቡ ከንታ ማለት ንዑስ መንደር ወይንም ሰፈር እንደማለት ነው፡፡ ከንታ በፓሌታ ስር ያለ የአነስተኛ መንደሮች መጠሪያ ነው፡፡ በኮንስኛ ፓሌታ በአማርኛ ቀበሌ (መንደር) ማለት ሲሆን፣ እያንዳንዱ ፓሌታ (መንደር) በስሩ ከ2-10 የሚደርሱ ከንታዎች (ንዑስ መንደሮች) አሉት፡፡ እነዚህ ንዑስ መንደሮች (ከንታዎች) የየራሳቸው ባህላዊ የዳኝነት ስፍራ (ሞራ) አላቸው፡፡ ይህ 'ሞራ" ሞራ-ከንታ ተብሎ ይጠራል፡፡ በሞራ-ከንታ ደረጃ ባህላዊ የግጭት መፍታት ሂደት ለማከናወን የሚቀመጡት የስርዓቱ አስታራቂዎች ፖርሺታ፣ አፓ-ከንታ (የከንታ አባት)፣ ቂሞታ-ከንታ (የከንታ ሽማግሌ) እና ኸሊታ-ከንታ (የወጣት

ትውልድ ቡድን አባል) ናቸው። እነዚህ አካላት በዚህ ደረጃ የሚቀርቡ ቀላል ግጭቶችን በመፍታት ረገድ የየራሳቸው ተግባር ወይንም ኃላፊነት አላቸው።

#### 4.3.1.2. ሞራ -ፓሌታ

በኮንሶ ብሔረሰብ ፓሌታ አሮጌ ከተማ ወይንም አምባ መንደራት እንደማለትም ነው። ፓሌታ ከከንታ ከፍ ያለ፣ ሰፊና በርካታ አገልግሎት መስጠት የሚችል ነው፡፡ ኮንሶዎች ሞራ-ፓሌታን "ካርሞቴ" ይሉታል። ትልቁ ሞራ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ሞራ የሚታዩት ግጭቶች በሞራ-ከንታ ደረጃ መፈታት ያልቻሉና በዚህ ደረጃ እንዲታዩ ተላልፈው የመጡ ቀላል ና ከባድ ግጭቶች እንደ ድብደባ፣ (ደም መፍሰስ ካለበትና ደም በማለት ቃሉን መጥራት ከሆነ)፤ እንዲሁም ሴቶችን ማስኮብለልና ማባለግ፣ መድፈር ናቸው። በዚህ ደረጃ የግጭት መንስኤ የሆነውን ጉዳይ ለማየትና ዕርቀ-ሰላም ለማውረድ የሚቀመጡት ቂሞታ-ፓሌታ (የፓሌታ ሽማግሌ ከየትኛውም ከንታ ሊሆን ይችላል)፣ ኸሊታ-ፓሌታ (ከየትኛውም ከንታ ሊሆን ይችላል የወጣት ትውልድ ቡድን አባል)፣ ሰንቀሊታ (የወጣት ትውልድ ቡድን መሪ)፣ አፓ-ቲንባ (የከበሮ አባት) ወይንም የፓሌታው የበላይ መሪ፣ ዳውራ (መንፈሳዊ አባት)፣ ሳራዎች (የጐሳ መሪ መልዕክተኞች)፣ ፖቃላ ሙግላ (ቱራይታ) የዋናው ጐሳ መሪ ምክትል ናቸው። በዚህ ደረጃ የሚቀርቡ ግጭቶች ከባድ የግጭት ዓይነቶች በመሆናቸው በግጭት አፈታት ስርዓቱ ወቅት እነዚህ አካላት የየራሳቸው ኃላፊነትና ተግባር አላቸው። በሞራ-ፓሌታ ደረጃ መፈታት ያልቻሉ ግጭቶች በፖቅላ ደረጃ እንዲታዩ ወደፖቅላ ይተላለፋሉ።

#### 4.3.1.3. ፖቅላ

በኮንስኛ ፖቅላ የሚለው ስያሜ ለጎሳ መሪዎች የሚሰጥ የማዕረግ ስምን ያመለክታል። ጉዳዩ ወደ ፖቅላ ተላለፈ ማለት በጐሳ መሪ ደረጃ ዳኝነት የሚሰጥበት ማለት ነው። በዚህ ደረጃ የሚታዩት ጉዳዮች በየደረጃው በሞራ-ከንታ ደረጃ ታይተው እልባት ያላገኙ፣ ወደ ሞራ-ፓሌታ ደረጃም ተሸጋግረው መፈታት ያልቻሉ ጠንከር ያሉ ጉዳዮች (ከባድ ግጭቶች) እና ወንጀሎች ናቸው። በዚህ ደረጃ ጉዳይ ለማየት የሚቀመጡት አፓ-ካፋ (የጐሳው /የቤተሰቡ አባት)፣ ቂሞታ-ካፋ (ከጐሳው በዕድሜ ከፍ ያለ ሽማግሌ)፣ ፖቃላ ሙግላ (ቱራይታ) የጐሳ መሪው ምክትልና ፖቅላ ቱማው (ዋናው የጐሳ መሪ) በመሆን ጉዳዩን በጋራ ይመለከታሉ። በዚህ ደረጃ እነዚህ አካላት የየራሳቸው ድርሻና ኃላፊነት አላቸው።

በዚህ ደረጃ የሚቀርቡ ጉዳዮች በሞራ-ፖሌታ ደረጃ ታይተው እልባት ያላገኙና ተደጋጋሚ ስርቆት መፈጸም፣ አካል ማጉደል፣ ድንገተኛ ነፍስ ግድያ፣ ውጉዝ ጋብቻና መረጃ የሌላቸው ጉዳዮች በቀጥታ በፖቅላ ደረጃ ታይተው የሚፈቱ ሲሆን በድርድር አይታዩም። ማስረጃም ሆነ ምስክር አይጠየቅም። ጉዳዩ በልዩ ዘዴ ይጣራና የመጨረሻ ውሳኔ ያገኛል። ከዚህ ካለፈና መተማመን ካልተቻለ ወደ "ሞራ-ኻኻ" ተሸጋግሮ እልባት ያገኛሉ፡፡

### 4.3.1.4 "ኻኻ" ወይም የመሀላ ስርዓት

ከላይ ከተገለጹት በኮንሶ ብሔረሰብ የባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ደረጃ በደረጃ በተለይም በፖቅላ ያልተፈቱ ጉዳዮች የሚፈቱት "ኻኻ" ወይም የመሀላ ስርዓት በመፈጸም ነው። ‹‹ወደ መሀላ የሚያስኬዱ ጉዳዮች ዋነኛ ምክንያት ዕውነታ ፍለጋ ሲሆን አንድን ጉዳይ አጣርቶና አስመስክሮ ውሳኔ ለመስጠት ወይም መንስኤያቸው የማይታወቁ ወይንም ደግሞ በምስጢር የተፈጸሙ ድርጊቶች ለምሳሌ የእርሻ መሬት ክርክር የድንበር የንብረት መካካድና ስውር ደባዎች ሲፈጸሙና መረጃ የማይገኙላቸው ጉዳዮች ሲከሰቱ እንዲውጣጡ ለማድረግ ነው›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 7፤ ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ካምብሮና አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 24፣ 33፣ 39፣ 43) በማለት ያስረዳሉ።

የመሀላ ስነ ስርዓቱ በሚፈጸምበት ቦታ ላይ በመገኘት መሀላውን የሚያስፈጽሙት በብሔረሰቡ ‹‹አፓ-ኻኻ›› ይባላሉ። የመሀላ ስነስርዓቱ የሚፈጸሙባቸው ቦታዎች በየሞራዎች ላይ የሚተከሉ የትልልቅ ድርጊቶች ማስታወሻ ትክል ድንጋዮች ዳጋ ዳሩማዎች በየፖቅላ ወይም ቱራይታ መኖሪያ ግቢዎች ውስጥ በተለይ እናቶች ሲወልዱ የሚታረሱበት ቤት መሰል ሆኖ አክታ በመባል የሚታወቅ ፖቅላዎች ወይም ቱራይታዎች ባህላዊ የእምነት ስርዓቶች የሚያከናውኑባቸው ቤቶች እንደሆኑ ከመረጃ አቀባዮቹ ካላ ገዛኸኝ፣ ዲኖቴና ኪሮስ በአብነት ለመረዳት ተችሏል (ጋሞሌ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 8፤ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 25፣ 33)።

#### አብነት

*"በባልና በሚስት መካከል የግብረስጋ ግንኙነት መካካድ ሲኖር ባል በሚስቱ ጭን ተራምዶ እንዲያልፍ አሊያም በሁለት እጆቹ የሚስቱን ጭኖች በመንካት የሚፈጽመው የመሀላ ዓይነት ይጠቀሳል ጭን ተራምዶ የመንካቱ ምሳሌነት አልነካሁሽም ጭንሽ መሀል አልገባሁም አልተገናኘሁሽም እንደማለት ነው፤ በእርሻ መሬት ድንበርተኞች በድንበር ሲጋጩ በአኩታ የመሀላ ዓይነት ይማማላሉ ድርጊቱም አንዱ ባንዱ ላይ አፈር ብናኝ በመበተን የሚፈጸም ነው፤ አፈር*

*የመበተኑ ምሳሌነት የራስህ ያልሆነ ነገር የራስህ አደረግህ ስለዚህ እንደዚህ አፈር ሁን እንደማለት ነው ፤ውጤቱም ከአንዱ ቤተሰብ የቤተሰብ አባል በሞት ሲለይ የእሳት አደጋ ሲፈጠርና የመብረቅ አደጋ ሲከሰት ይህ ድርጊት የሚያሳየው ተከራካሪ ወገን መረታቱን ነው ይላሉ፤ የጥፋተኛው የመረታት ምልክቶች ናቸው በሚልም ሽማግሌዎች እንደማረጋገጫ በመያዝ ከስምምነት እንዲደርሱ ያደርጋሉ"* (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 7)።

### 4.3.2. የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት

በኮንሶ ብሔረሰብ በየደረጃው በሚከናወነው የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የተለያዩ አስታራቂዎች ይሳተፋሉ። በዚህ ንዑስ ርዕስ ስርም የእነዚሁ አስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 4.3.2.1 በሞራ-ከንታ ደረጃ

በሞራ-ከንታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርትን አስመልክቶ በመስክ ቆይታ ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት በስርዓቱ ያሉ አስታራቂዎች አራት እንደሆኑ (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 17፣ 2006 ዓ.ም፣ 8፤ ዲኖቴና አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 17፣ 2006 ዓ.ም 25፣ 43) ገልጸዋል። የእያንዳንዱ ትርጉም፣ የአስታራቂው ሚና/ዋና ተግባሩ፣ የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ በ ሠንጠረዥ 3 ተመልክቷል።

*ሠንጠረዥ 3 በሞራ-ከንታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት*

| የሞራ-ከንታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| ፖርሺታ | የከንታው ቀስቃሽ ወይም አስተባባሪ ሆኖ የሚሰራ ነው።<br><br>እያንዳንዱ ከንታ ሁለት ፖርሺታዎች ይኖሩታል። | ከሳሽና ተከሳሽን ማቅረብ፣ ለቂሞታ-ከንታዎች (ለከንታ ሽማግሌዎች) በጕረቤት፣ በአቅራቢያ አካባቢ የተፈጠረ ችግር ካለ መጠቆም፣ ሰዎች እርሻ ሄደው ቢደከሙ፣ ቢታመሙ ወዘተ ለከንታ ሽማግሌዎችና ለኸሊታ-ከንታው የሚነግርና ጉዳዩን ተከታትሎ የሚያቀርብ ሲሆን፣ በሞራ-ከንታ ደረጃ በሚካሄደው የዳኝነት ስርዓት ላይ ሊቀመጥም ላይቀመጥም ይችላል። | በአካባቢው ነዋሪዎች በሥነ-ምግባሩና በስራ ቅልጥፍናው ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመኑ ሁለት ዓመት ሆኖ በስራው ላይ ድክመት ካሳየ ግን በአንድ አመቱ ሊሻር ይችላል። |
| | | አንድ ግጭት ሲከሰት | እያንዳንዱ ከንታ የራሱ የሆነ |

| የሞራ-ከንታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| **አፓ-ከንታ** | የከንታ አባት ወይም የከንታ ተወካይ እንደማለት ነው። | የመጀመሪያ ክስ ለመመስረት የክስ መመስረቻ "ኸራታ" ወይንም ገዝብ የሚቀበል ነው፤ ከዚህ በተጨማሪ ለከንታው ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተወክሎ የሚሰራ ነው እንደ ለቅሶ፣ ቀብር ወዘተ... ሲኖር ማለት ነው። | ተወካይ አፓ-ከንታ አለው። አመራረጡ ባለው ስነ ምግባርና ታዛዥነት በማህበረሰቡ ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመኑ ከንታውን ወክሎ መስራት እስከቻለና አቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ ይሆናል። |
| **ቂሞታ- ከንታ** | የከንታ ሽማግሌዎች ማለት ነው። | በግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት በብሔረሰቡ አጠራር "ለማይዳ" ይባላል በአማላጅነት ከመላክ ጀምሮ፣ የዕርቅ ድርድር ስርዓቱን በፀሎት ወይንም በቡራኬ የመክፈትና ጠበኞችን አደራድሮ እስከማስታረቅ የደረሰ ሚና አላቸው። | በአካባቢያቸው ባላቸው የማደራደር ብቃት፣ ችሎታና ልምድ እንዲሁም ተሰሚነትና ተደማጭነት የሚሰየሙ ናቸው። የስራ ዘመናቸው ገደብ የለውም። አገልግሎታቸው እግራቸው ከቦታ ቦታ ለመሄድና ያለችግር መራመድ እስከቻሉ፣ ታማኝነታቸውና ችሎታቸው ብቁ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ይሰራሉ። ችግር ያለበት ግን በየጊዜው በሚካሄዱ ሕዝባዊ መድረኮች ተገምግሞ በሌላ የመተካት ዕድሉ አለ። |
| **ኸሊታ-ከንታ** ለነጠላ (ለብዙኼለታዎች) | የኼላው (በመሪነት ላይ ያለው የወጣት ትውልድ ቡድን አባል) የሆነ ማለት ነው። በብሔረሰቡ የወጣት ትውልድ ስልጣን ሽግግር የሚጀመረው ከ19-25 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ጀምሮ ያሉ ወጣቶች ስልጣኑን ከያዘው አካል ጋር ለቀጣይ 18 ዓመት ከመሪው ጋር የትውልዱ አባል ሆነው ይዘልቃሉ። | በዳኝነት ስርዓቱ ላይ አልቀርብ ያለ ተከሳሽ ካለ ይዞ ማቅረብ፣ የቅጣት ውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ለሽማግሌዎች መላላክ፣ የጉልበት ስራ ካለ ማገዝና ስርዓቱን በሚገባ መከታተል ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ከዳኝነት ስራው ባሻገር በከንታው የሕዝብ ስራ ላይ ያልተገኘን የከንታ አባል መቀጮ ከተጣለበት መቀጮውን መሰብሰብ ሌላው ተግባሩ ነው። | የአገልግሎት ዘመንን በተመለከተ ለወጣት ትውልዱ የስልጣን ሽግግር ጊዜ በተቀመጠው ዕድሜ ይገደባል። |

#### 4.3.2.2 በሞራ-ፓሌታ ደረጃ

በሞራ-ፓሌታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርትን ስንመለከት ደግሞ ቂሞታ-ፓሌታ የመጀመሪያው ነው፡፡ በተመሳሳይ በየደረጃው በስርዓቱ ያሉ አስታራቂዎች ሰባትእንደሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች ገለጻ መረዳት የተቻለ ሲሆን የእያንዳንዱ ትርጉም፣ የአሰታራቂው ሚና/ዋና ተግባሩ፣ የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ በ ሠንጠረዥ 4 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4 በሞራ-ፓሌታ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት

| የሞራ-ፓሌታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| ቂሞታ -ፓሌታ | የፓሌታ ሽማግሌዎች ማለት ነው፡፡ | የእርቅ ድርድር ስርዓቱን በዕደሜ ቅደም ተከተል መሠረት በቡራኬና በፀሎት ማስጀመር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ በከሳሽና በተከሳሽ የቀረበውን ጉዳይ የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም የእርቅ ድርድሩን መስመር ማስያዝ፣ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች የማድረግና የከሳሽና የተከሳሽ ሀሳብን በሚገባ በማዳመጥ የተደረሰበትን ሀሳብ ለዳውራዎች አሊያም ለኸሊታዎች ለውሳኔ ማቅረብ ነው፡፡ ከማደራደር ባለፈ አይወስኑም፡፡ ውሳኔም አያስተላልፉም፡፡ | ባላቸው የማደራደር ብቃት፣ ችሎታና ስነ-ምግባር ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመናቸው የእድሜ ልክ ነው፡፡ በጤንነት ምክንያት ካልሆነ በቀር፡፡ በዚህ ደረጃ የሚቀመጡት ቂሞታ ፓሌታዎች ከየትኛውም ከንታ ባላቸው የተሻለ የማደራደር ብቃት ተመርጠው ነው፡፡ |
| ኸሊታ- ፓሌታ | አንድ ፓሌታ (መንደር) ከ2-10 የሚደርሱ ከንታዎች (ንዑስ መንደሮች) አሉት፡፡ ስለዚህ ኸሊታ-ፓሌታው | ስርዓቱን የመከታተል፣ ለሽማግሌዎች መታዘዝና መላላክ፣ የጉልበት ስራ መስራት፣ የቅጣት ውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ይጠቀሳሉ፡፡ | አመራረጡን በተመለከተ በዚያው በትውልዱ የቡድኑ አባል ሆኖ በፓሌታ ደረጃ በአነጋገርም ሆነ በስራ የተሻለ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ የአገልግሎት ዘመንን በተመለከተ ከትውልዱ የስልጣን ሽግግር ጋር አብሮ |

| የሞራ-ፓሌታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | ከየትኛውም ከንታ ሊሆን ይችላል የሚቀመጠው (የሚሰየመው)፡፡ | | አገልግሎቱ ያከትማል፡፡ |
| **ሰንቀሊታ (ኬላ)** | በስልጣን ላይ የሚገኘው የወጣቱ ትውልድ መሪ ማለት ነው፡፡ ሥርዓቱ "ኸልታ" ይባላል፡፡ ሥልጣን የተረከበው ትውልድ ደግሞ "ኬላ" ተብሎ ይታወቃል፡፡<br>ከዚህ በተጨማሪ ሰንቀሊታው ካለው ሚና አንጻር አፓ-ሊሻ፣ አፓ-ኩማና ኢፓ-ቢላ ተብሎ ይጠራል፡፡ | ማስተባበር፣ በሕዝብ ውይይትና ዳኝነት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠትና መደመደም ነው፡፡ | የዚህ ትውልድ ስልጣን መሪ የሚሆነው ከጥንት ጀምሮ ሰንቀሊታዎች ከሚመረጡባቸው<br>ቤተሰቦችና ከ19-25 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ በጨዋነቱ፣ በአስተዋይነቱ፣ በጠንቃቃነቱ እንዲሁም በስነ-ምግባሩ በማህበረሰቡ በጥንቃቄ የሚመረጥ ሆኖ፣ የስልጣን ዘመኑ አስራ ስምንት አመት ነው፡፡ |
| **አፓ-ቲንባ** | የከበሮ አባት ማለት ነው፡፡ ከበሮ ስንል ተራ ከበሮ ሳይሆን በትረ ስልጣን ያለው እንደ ማለት ነው፡፡ አፓ- ቲንባ የፓሌታው የበላይ መሪ ነው፡፡ በዳኝነት ስርዓቱ ላይ ወደኋላ በመሄድ በህይወት ያሉ የየኬላው (የየትውልዱን) ተወካዮች በመያዝ የሚቀመጥ ነው፡፡ | በፓሌታ ደረጃ እንዲታዩ የቀረቡ ግጭቶችን በራሱ ቤት አሊያም በደጃፉ ላይ ከሌሎች ጋር በጋራ በመሆን ጉዳዩን በማየት የሚፈታ ነው፡፡ በፓሌታ ደረጃ ስርዓቱን የሚመራም ነው፡፡ በዚህ ደረጃ መፈታት ያልቻሉትን ጉዳዮች በፖቅላ ደረጃ እንዲታዩ ወደ ኀላ መሪው የሚመራ ፣ ጉዳዩን የሚልክ ትልቅ ኃላፊነት ያለው ነው፡፡ | በየሶስት ዓመቱ በብዙ ብልሃትና ጥንቃቄ ሕዝብ ሳያውቅ በምስጢር በፖቅላዎች፣ የከንታ መሪዎች፣ ኸሊታዎች፣ ሀዮታዎች (ነገር አዋቂዎች) በመወያየትና በመመካከር ይመረጣል፣ ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡ ሹመቱ በዘር አይተላለፍም፡፡ የአፓ-ቲንባው የስራ ዘመን ሊጠናቀቅ የወራት ጊዜ ሲቀረው ጀምረው ከላይ የተጠቀሱት የሕዝብ መሪዎች በምስጢር በመገናኘት ቀጣዩ አፓ-ቲንባ ማን ይሁን? በሚለው ጉዳይ ላይ ይወያያሉ፡፡ ይህ ምስጢራዊ ውይይት ማድረጊያ |

| የሞራ-ፓሌታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | | | ‹ቲጋ-ቃዋ› ተብሎ ይጠራል፡፡ ድብቅ ቦታ (ቤት)፣ ሚስጥር የሚነገርበት እንደማለት ነው፡፡ አፓ-ቲንባ ስልጣኑን የሚያጣባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ እነርሱም ሚናውን መወጣት ሲያቅተው ለአብነት ከኃላፊነቶች መካከል የመንደር ካብ ሲፈርስ፣ የጉድጓድ ውሀ መስኖና ኩሬ ሲሰራ ስራውን ማስጀመር፣ በፓሌታ አባላት መሀከል የመሬት ድንበር ግጭት ሲከሰት በአጭር ጊዜ ወይም በፍጥነት መፍታት ምክንያቱም የድንበር ግጭት ዝናብን ያጠፋል፤ ድርቅን ያመጣል፤ ረሀብን ይስባል ተብሎ ይታመናልና፡፡ በሌላ በኩል በቤቱ ውስጥ በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሰው ሲኖር፣ አፓ-ቲንባው በሰው ተፈንክቶ ሲደማ፣ የሽግግር ጊዜው ባይደርስም ቲንባው ለሌላ ሰው ይተላለፋል፡፡ ይህም የሚሆነው ደምና ሞት በአፓ-ቲንባው ቤት ከታየ ለሕዝቡ የሚበጅ ነገር እንደማይኖርና አስፈሪ ነገር እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡ የተፈነከተውም አፓ-ቲንባ ቲንባው እስኪወጣ ድረስ ወደቤቱ አይገባም፡፡ |
| **ዳውራ** | መንፈሳዊ አባት ወይንም ባህላዊ ቄስ እንደማለት ነው፡፡ | በሽማግሌዎች አደራዳሪነት የተደረሰበትን የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ጉዳዮች ሲከሰቱ በእርቅ ድርድሩ ይሳተፋሉ፡፡ ለአብነት የደኖች መነካት፣ | ከቤተሰቦቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣና በሚነገርላቸው ጨዋነት ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ በኮንሶ የዳውራ ሥራዎችንና ተግባራቸውን የሚያከናውኑ 3 ፓሌታዎች (አምባ መንደሮች) አሉ፡፡ እነርሱም ሌሃይቴ፣ |

| የሞራ-ፓሌታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | | የምንጮች መድረቅ፣ የዝናብ መጥፋት፣ የወረርሽኝ መኖር ወዘተ.. ሲኖር፣ በዋናነት ግን በግጭት ወቅት ደም ሲፈስ ግጭቱን ለማብረድ ደም የፈሰሰበትን አካባቢ በማንፃት ሂደት ዋነኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ | ሶሮቦና አያይቴ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ከነዚህ መንደሮች ውስጥ የተወሰኑ ቤተሰቦች የዚህ ሥልጣንና ማዕረግ አላቸው፡፡ ማዕረጉን ያገኙበትን መንገድ በተለያየ መልኩ ይተርኩታል፡፡ ለምሳሌ የሌሃይቴ ዳውራዎች የዳውራነትን መቀባት ያገኑት ካልማሌ ፖቅላ(አንዳንድ ጎሳዎች ከአንድ በላይ የጎሳ መሪ አላቸው) ተብለው ከሚጠሩ የጃርሶ አካባቢ አጠቃላይ መሪ ከነበሩት የቶክመሌታ ጐሳ ተወላጅ እንደሆነ አዛውንቶች ያስረዳሉ ሲሉ መረጃ አቀባዮቹ ይገልጻሉ፡፡ በብሔረሰቡ ዳውራዎች ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ሲሆኑ፣ የአገልግሎት ዘመናቸው የዕድሜ ልክ ነው፡፡ በስልጣን ቆይታቸው ጥንቃቄ የሚወስዱባቸው ሁኔታዎች አሉ። ለአብነት ጸጉራቸውን አይላጩም፣ ድንገት በሰዎች በአጋጣሚ ቢፈነከቱና ደማቸው ቢፈስ ‹‹ጥቁር ሴት በግ ታርዳ በአካባቢው ደም እንዲረጭ ይደረጋል፡፡ ይህም በዳውራዎች ደም መፍሰስ የረከሰው አካባቢ በበጓ ደም መረጨት መንጻቱን ማረጋገጫ ነው፡፡ ዳውራዎች ለቅሶ ቤት አይደርሱም፡፡ በተለይ የሟች ሬሳ (አስክሬን) ከቤት ተሸኝቶ እስከ አልወጣ ድረስ በአካባቢው ዝር አይሉም፡፡ በዕርቅ ድርድር ወቅት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭ አካል እንደመሆናቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የተከበሩና |

| የሞራ-ፓሌታ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | | | የሚታመኑ፣ በፍፁም ከአድሎ የራቁና ቅድስና የተላበሱ ናቸውም ይላሉ። |
| **ሳራዎች** (ሳራ) በነጠላ ሳራዎች (ለብዙ) | መልዕክተኞች ማለት ነው። መልዕክተኝነታቸው ም ለዋናው የጐሳ መሪ ለፖቅላ ቱማው እና ለምክትሉ ለፖ ቃላሙግላ (ቱራይታው) ነው። | በዳኝነት ስርዓቱ ላይ አስተያየት መስጠትና መልዕክት ማድረስ ነው። በፓሌታ ደረጃ የተወሰኑ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ። | አመራረጣቸው በኀሳው ባላቸው ሥነ-ምግባርና በስራ ቅልጥፍናቸው ሆኖ፣ የአገልግሎት ዘመናቸው የዕድሜ ልክ ነው። |
| **ፖ ቃላ ሙግላ (ቱራይታ)** | የዋናው ጐሳ መሪ ተጠሪዎች (ምክትሎች) ሆነው የሚሰሩ ማለት ናቸው። | በፓሌታ ደረጃ የሚታዩ ጉዳዮች ወደ ዋናው ጐሳ ወደ ፖቅላ ከመድረሱ በፊት የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ግጭቶቹ እንዲፈቱ የሚሰሩ ናቸው። | አመራረጣቸውም ሆነ የአገልግሎት ዘመናቸው ከዚያው ከጐሳው ከአባት ወደ ታላቅ ልጅ በሚል በትረ ስልጣኑን በዘር ሀረግ የሚያገኙት በመሆኑ የዕድሜ ልክ ነው። |

### 4.3.2.3 በፖቅላ ደረጃ

በፖቅላ ደረጃ የሚቀርቡ ግጭቶችን ለመፍታት የተቋማቱ ሚናና የመምረጫ መስፈርትን እንዲሁም አመራረጣቸውና የአገልግሎት ዘመናቸውን ስንመለከት በጐሳ ደረጃ ከሆነ ስልጣኑ በዘር ሀረግ የሚመጣ በመሆኑ አገልግሎታቸው የዕድሜ ልክ ነው። በዚህ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርትን ስንመለከት ደግሞ አፓ-ካፋ የመጀመሪያው ነው። በተመሳሳይ በዚህ ደረጃ በስርዓቱ ያሉ አስታራቂዎች አራት ሲሆኑ (ዲኖቴ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 25) የእያንዳንዱ ትርጉም፣ የአስታራቂው ሚና/ዋና ተግባሩ፣ የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ በ ሠንጠረዥ 5 ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 5 በፖቅላ ደረጃ የአስታራቂዎች ሚናና የመምረጫ መስፈርት

| የፖቅላ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| **አፓ-ካፋ** | አፓ ማለት አባት ማለት ነው። ካፋ ስንል ደግሞ | ከካፋ ሳራዎች (ከጐሳው | ስልጣኑ በዘር ሀረግ የሚመጣ በመሆኑ |

| የፖቅላ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | ጐሳ ማለታችን ነው። በብሔረሰቡ የአንድ ጐሳ አባላት እንደ አንድ ቤተሰብ ይታያሉ። ስለሆነም አፓኳፋ ስንል የጐሳው (የቤተሰቡ) አባት እንደ ማለት ነው። | መልዕክተኞች) ጋር በመሆን በጐሳ አባላትና በቤተሰብ መሀከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን (ግጭቶችን) ይፈታሉ። | አገልግሎታቸው የዕድሜ ልክ ነው። |
| **ቂሞታኳፋ** | ከጎሳው በዕድሜ ከፍ ያለው(የጐሳ ሽማግሌ) ወይም በጐሳ ደረጃ ለሚታይ ጉዳይ እንደሽማግሌ የሚቀመጥ ማለት ነው። | ቀደም ብሎ በሌሎቹ እንደተገለፀው በዕድሜ ቅደም ተከተል የዳኝነት ስርዓቱን በቡራኬና በፀሎት ማስጀመር ነው። | ስልጣኑ ከጎሳው/ከቤተሰቡ የሚመጣ በመሆኑ አገልግሎታቸው የዕድሜ ልክ ነው። አመራረጣቸው ስርዓቱን ባግባቡ የማስጀመር ብቃት ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ የሚቀመጡት ቂሞታኳፋዎች (ሽማግሌዎች) ይህንኑ ይተገብራሉ። |
| ***ፖቃላ ሙግላ*** **(ቱራይታ)** | የጐሳው መሪ ተጠሪ (ምክትል) የሆኑ ናቸው። | ከላይ ጠንከር ብለው የመጡ ጉዳዮችን በቀጥታ ወደ ፖቅላው(ዋናው የጎሳ መሪው ዘንድ) ሳይደርስ ከአፓኳፋና ከቂሞታ ካፋው ጋር በጋራ በመሆን ለመፍታት የሚሞክሩ ናቸው። | በብሔረሰቡ ጎሳዎቹ በየቀበሌያቱ (በየፓሌታው) ተቀላቅለው እንደመኖራቸው ዘጠኝ ቱራይታዎች (ፖቃላ ሙግላዎች) አሉ። ተጠሪነታቸውም ለጎሳው መሪ "ለፖቅላ ቱማው" ሲሆን፣ በቁጥር አምስት የሆኑ ከጥቁር ብረት የተሰሩ ‹ሙግላ› በመባል የሚታወቁ ከአባት ወደ ታላቅ ልጅ ከበትረ ስልጣን ጋር የሚተላለፍ በቀኝ እጅ ላይ የሚታሰሩ ቀጠን ቀጠን ያሉ የብረት አምባሮችን የሚያደርጉ ናቸው። |
| ***ፖቅላ ቱማ*** | የኮንሶ ብሔረሰብ በዘጠኝ ጎሳዎች የተደራጀ እንደመሆኑ ዘጠኝ የጎሳ መሪዎች አሏቸው። የእያንዳንዱ ጎሳ መሪ | በዚህ ደረጃ ፖቅላ ቱማው (የጐሳ መሪው) ከላይ ከ3(ሦስቱ) በጐሳ ደረጃ ያለፈውን ጉዳይና | ስልጣኑን ከአባቱ የሚረከብ ነው። ከብር የተሰራ የብር አምባር በቀኝ እጁ የሚያስር ነው። |

| የፖቅላ አስታራቂዎች | ትርጉም | ሚና/ዋና ተግባሩ | የመምረጫ መስፈርትና የአገልግሎት ዘመኑ |
|---|---|---|---|
| | መጠሪያውም ‹‹ፖቅላ ቱማ›› በሚል ይታወቃል፡፡ ከኮንሶ አምባ መንደሮች ወጣ ብሎ በሚሠራለት ባህላዊ ቤተ መንግስት ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር የሚኖር ከዘጠኙ ዋና ዋና የጎሳ መሪዎች አንዱ የሆነ ማለት ነው፡፡ | በፓሌታ ደረጃ ያልተፈታውን ይዞ በዋናነት ራሱ በመቀጠል የከንታ፣ ፓሌታና የሚመለከታቸው የጐሳው አባላት በተገኙበት ከላይ የተጠቀሱትን ይዞ ግጭቶቹን ይፈታል፡፡ የጎሳ መሪዎች በብሔረሰቡ የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ይታወቃሉ፡፡ ሁሉንም ግጭቶች ወይም ቅራኔዎች እንደቅለቱና ክብደቱ ይፈታሉ፡፡ የመጨረሻ ውሳኔዎችን ይሰጣሉ፤ ውሳኔ በጋራ እንዲሰጥም ያደርጋሉ፡፡ ይሁንና ይህ ሁሉ ሲሆን የጎሳ መሪዎቹ ግጭቱ ወደተነሳበት መሬት/ቦታ አይሄዱም፣ በግለሰብ መሬትም ሆነ በቀበሌ የድንበር ግጭት ስፍራ አይሄዱም፤ አይደርሱም፡፡ | |

ከላይ እንደተገለጸው በኮንሶ ብሔረሰብ በየደረጃው በሚከናወነው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተለያዩ አስታራቂዎች ይሳተፋሉ፡፡ ማህበረሰቡ (ነዋሪው) በራሱ ለባህላዊ ስርዓቱ ዕውን መሆን የሚኖረውን ሚና ስንመለከት በውስጣቸው የተፈጠረውን ችግር ከማሳወቅ ጀምሮ ለባህላዊ ስርዓቱ ውሳኔ ተገዢ ያልሆኑ ሰዎችን ተከታትሎ በማጋለጥ

ረገድ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ማጋለጡ ከቤተሰብ እና ከቤተ ዘመድ ማለትም አባት ወይም እናት ልጃቸውንም ቢሆን ከዚሁ እንደሚጀምሩ ሀገያ፣ ኦተያና ቦንሳ (በደንገልቱ፣ ጥር 12፣ 2006 ዓ.ም፣ 50፣ 51) ያስረዳሉ፡፡

ለዕርቅ ስርዓቱ ተፈጻሚነት ብሎም ዕውን መሆን ተጋጪዎች (ጠበኞች) ከፍተኛ ሚና ያላቸው ሲሆን፣ ጠበኞች በአስታራቂዎች ዘንድ ፍትሀዊ በሆነ መልኩ እንደሚዳኙ ስለሚያውቁ በስርዓቱ ወቅት በሁሉቱም ጎራ ያሉ ጠበኞች ራሳቸውን ጥፋተኛ ላለማድረግ ጥረት እንደማያደርጉና የአስታራቂዎችም ቃል እንደሚከበር በዚህም ሁለቱም ወገኖች ሳይዋሹ እንደሚናገሩ፣ ከአንድ ጊዜ በላይም እንዲመላለሱ እድል እንደማይሰጣቸው ለመረዳት ተችሏል (ኪሮስ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም፣ 35፤ ዲኖቴ ኮጫኤና ሳጎያ፣ ቡርቂዳ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም፣ 48፣ 50)፡፡ ይህንኑ ሐሳብ በማጠናከር ካምብሮና ሽሬ በበኩላቸው ጠበኞች የአስታራቂዎችን ሀሳብ ብቻ በመቀበል ለዕርቅ ስርዓቱ ዕውን መሆን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ የሚያደርጉ እንደሆነ ያረጋግጣሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም፣ 39፣ 49)፡፡

በባህላዊ ስርዓቱ የሴቶችን ሚና በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ በተመሳሳይ የቃለመጠይቅ ወቅት ዲኖቴ ኮጫኤና ሽሬ በተመሳሳይ ሀሳባቸውን ሲያብራሩ፡-

> ***‹‹ሴቶች በብሔረሰቡ በባህላዊ ዳኝነት ላይ አይሳተፉም ፤ተከሰውም ሆነ ከስሰው ወደ ሞራ ሸንጎ ሲቀርቡ በግልጽ በአደባባዩ ላይ አይቀመጡም፤ ዞር ብለው አጥር ተጠግተው ምላሻቸውን ይሰጣሉ፤ እንጂ የወር አበባ በታያቸው ወቅትም በአንዳንድ ዋና ዋና ሞራዎች ወይም የባህል ስርዓቶች በሚፈጸምባቸው ቦታዎች እንዲያልፉ አይፈቀድላቸውም፤ በባህላዊ እምነቱም ንጹህ አለመሆናቸውን ያመለክታል***›› (በደንገልቱ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም፣ 46፣ 50) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ይሁንና የሴቶችን ተሳትፎ አስመልክቶ ከሌሎች መረጃ ሰጪዎች ጋር በነበረ ቃለመጠይቅ ተሳትፎ አላቸው የላቸውም የሚል አሻሚ ሀሳቦች ስለነበሩ የብዙሃኑን ሀሳብ ለማግኘት የቡድን ውይይት ተካሄዷል፡፡ በዚህም የቡድን ውይይት ተወያዮች አቶ ፈረንጨታ፣ ኃይሉና ወ/ሮ ቲንፋ ሲያስረዱ ማንኛውም በአካባቢው የሚፈጠሩ ቅራኔዎች ወይም ግጭቶች ከትንሽ እስከ ትልቅ በሞራ-ከንታ ደረጃ አሊያም በሞራ-ፓሌታ ደረጃ ይፈታሉ፡፡ በዚህ የሞራ ስርዓት (የግጭት አፈታት ላይ) ከጥንት ጀምሮ ሴቶች እንዲገኙ ወይም በሞራ ላይ እንዲቀመጡ አይፈቀድም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሴትና ሴት ወይንም ወንድና ወንድ

ተጋጭተው ግጭቱ በሞራ ላይ በሚፈታበት ጊዜ ሴቶቹ ከሞራ ውጭ ሆነው ጉዳያቸውን ያስረዳሉ አሊያም በአጥር ውስጥ ሆነው ይናገራሉ እንጂ እንደወንዶቹ ሞራ መሀል ገብተው ጉዳያቸውን አያስረዱም። ይሁንና በዚህ መልኩ በዳኝነት ላይ አይቀመጡ፣ ቀጥተኛ ተሳትፎም አይኑራቸው እንጂ በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮችና ጨቃ ቤቶች ላይ ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የሚያነሷቸው ጠቃሚ ሀሳቦች በተዘዋዋሪ መንገድ ሞራ ላይ ይነሳሉ። ከዚህ በመነሳት በቤታቸው ውስጥም ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር፣ በጨቃ ቤትም ከተለያዩ ሽምግልና ከሚቀመጡ ሰዎች ጋር ስለሚገናኙ የመነጋገርና ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ አለ፤ በዚህ ኢ-መደበኛ መልኩ የተገኙ ሀሳቦች በተዘዋዋሪ መንገድ ሞራ ላይ ይነሳሉ፤ ስለዚህ ኢ-ቀጥተኛ ተሳትፎ አላቸው የሚለው አስተሳሰብ እንደሚያስማማቸው ይገልጻሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም)።

## 4.4 ባህላዊ ስርዓቱ የሚከወንባቸው የዳኝነት ቦታዎች

### 4.4.1 ፓሌታዊ የዳኝነት ቦታዎች (ሞራዎች)

በኮንሶ ብሔረሰብ ሞራዎች በዋናነት የሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ ሲሆኑ፣ በስፍራው በቅርበት እንደማረፊያና ማደሪያ የሚያገለግሉ ከድንጋይ ካብና እንጨት የተሰሩ ትልልቅ የሳር ክዳን ያላቸው ባለቆጥ ቤቶችን አካተው የያዙ ናቸው። እነዚህ ቤቶች በብሔረሰቡ አጠራር "ፓፍታ" ይባላሉ። ሞራዎች ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ባህላዊ አገልግሎቶች አሏቸው። ሞራዎች በፓሌታ አደረጃጀት የችሎት ቦታዎች ናቸው። አሰራራቸው ከፓሌታ (ከመንደሩ) ቤቶች የተለየ ነው። ከመረጃ አቀባዮቹ ሳጎያና ሽሬ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ በአንድ ፓሌታ ውስጥ ብዙ ሞራዎች የሚገኙና ከአገልግሎት አንጻር በአራት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል (ቡርቁዳ፣ ጥር 17፣ 2006 ዓ.ም፣ 48፣ 50) ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በዚሁ መነሻነት እነዚሁ አራት ሞራዎች እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

#### 4.4.1.1 ሞራ-ከንታ

ሞራ-ከንታ (የንዑስ መንደሩ ሞራ) ከቤተሰብ፣ ከጎሳ አባላት፣ እንደዚሁም ከቅርብ ጎረቤት ነዋሪዎችና ከዘመድ አዝማድ ብሎም ከጓደኞች የዘለቀ ቀለል ያሉ ቅራኔዎች በከንታ ሽማግሌዎች አቅም የሚፈታበትና የመጨረሻ ውሳኔዎች የሚሰጡበት ሲሆን፣ በከንታ ደረጃ ማለቅ (መፈታት) ያልቻሉትን ወደ ሞራ-ፓሌታ በማሸጋገር የሚሰሩ የመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ የችሎት ቦታዎች ናቸው።

ከንታ ስንል ንዑስ መንደር ማለት ነው። በአንድ ፓሌታ (መንደር) ውስጥ ከ2-10 ሊደርሱ የሚችሉ ሞራ-ከንታዎች ሲኖሩ እያንዳንዱ ሞራ-ከንታ ከ50-300 ሜትር ባለ ርቀት ላይ የተገነባ ነው። ሞራ-ከንታዎቹ አገልግሎታቸው ሰፊ የሆነና ለአካባቢው ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ከመሆኑ የተነሳ ሕብረተሰቡ በቀላሉ በቅርበት ያገኛቸዋል። ከአገልግሎታቸው መካከል የሽማግሌዎች የመዝናኛ ማዕከልነት፣ የልጆች መጫወቻ ቦታነት፣ የመንገደኛ ማረፊያነት፣ በስራ የደከመው ጊዜያዊ ዕረፍት የሚያገኝበት፣ የህብረተሰቡ የባህል መሪዎች መወያያና መመካከሪያ መድረክነት፣ ወጣት ወንዶችና ሚስቱ የወለደች አባወራ ለተወሰነ ጊዜ ማደሪያነት የሚያገለግል ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ያለው ነው።

#### 4.4.1.2 ሞራ-ፓሌታ

ሞራ-ፓሌታ ዋናው ሞራ ወይንም ትልቁ ሞራ በመባል ይታወቃል። በስፋቱም የፓሌታውን ሕዝብ የመያዝ አቅም አለው። በሞራ-ከንታ ደረጃ መፈታት ያልቻሉ ልዩ ልዩ ግጭቶች በዋናው ሞራ ይፈታሉ። ከዚህ ባሻገር የሕዝብ መሰብሰቢያዎች የኼላ (የወጣቶች የስልጣን ሽግግር) ስነ ስርዓቶችና የስልጣን ሽግግሩ ምልክት የሆኑ ትልልቅ የዕንጨት ምሰሶዎች (ኦላ ሂታ) የሚተከሉበት፣ በፓሌታ ደረጃ የተከናወኑ ታላላቅ ጀብዱዎች ምልክት የሆኑ ትልልቅ ጥርብ ድንጋዮች (ዳጋ ዳሩማዎች) የሚተከሉበት ቦታ ነው። እንዲሁም ለከባድ ግጭቶች ያለድርድር የመጨረሻና የማያዳግም ውሳኔ የሚተላለፍበት ሲሆን፣ ከፓሌታው አቅም በላይ የሆኑትን ወደ ፖቅላ ደረጃ በማሸጋገር የሚሰራና በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ የብሔረሰቡ ዋነኛው ባህላዊ የዳኝነት ቦታ ነው።

#### 4.4.1.3 ሞራ-ኪርባ

ሞራ-ኪርባ በዋናው ሞራ ውስጥ ሆኖ የአውጫጭኝ ጉዳዮች ሲኖሩና ጉዳዮቹ በምስጢር የሚታዩበት ሞራ ነው። ከዚህ ባሻገር ልዩ ልዩ ባህላዊ ጭፈራዎችና የብዙሃን ስፖርት ትርዒት የሚካሄዱበትም ነው።

#### 4.4.1.4 ሞራ-ኻኻ

ሞራ-ኻኻ አንዳንድ ጊዜ ሞራ -ዳውራ በማለት ይጠሩታል። ‹‹ኻኻ›› ማለት መሀላ (ቃለ መሀላ) ማለት ሲሆን፣ ሞራ-ኻኻ ማለት ደግሞ መሀላ ወይም ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት

የሚፈጸምበት ሞራ ማለት ነው። የተለያዩ ግጭቶች በየደረጃው ባሉ ሞራዎች ታይተው መፈታት ካልቻሉ፣ መካካድ ሲኖርና መተማመን ሲጠፋ የመጨረሻው ስርዓት 'ኻኻ ይፍረድ" በሚል የመሀላ ስርዓት ይከናወኑበታል። ጥቃቅን ጉዳዮች ወደ ሞራ-ኻኻ አይደርሱም። ስርዓቱን የሚያስፈጽሙት ደግሞ አፓ-ኻኻ ይባላሉ። እነዚህን በማከናወን ረገድ በአፓ-ኻኻ ማዕረግ መንፈሳዊ አባቶች ወይንም ዳውራዎች ዋነኞቹ ናቸው። በብሔረሰቡ ኻኻ (መሀላ) መፈጸም ይፈራል፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ችግሮች ‹‹ኻኻ›› ላይ ሳይደረስ በየደረጃው ባሉ ሞራዎች እልባት ያገኛሉ። ‹‹ኻኻ›› መፈጸም የመጨረሻው ስርዓት ነው። እያንዳንዱ ፓሌታ የራሱ የሆነ አንድ ወይ ሁለት እንደሁኔታው በመንደሩ (በፓሌታው) ውስጥ ወይም ከመንደሩ ካብ ውጪም ሊከለሉ የሚችሉ ሞራ-ኻኻዎች (ሞራ-ዳውራዎች) ይኖሩታል።

### 4.4.2 ጎሳዊ የዳኝነት ቦታዎች

ሞራዎች ሕዝባዊ መድረኮች በመሆናቸው አገልግሎታቸው ለፓሌታ ጉዳዮች ብቻ ነው። በፖቅላ (በጎሳ መሪ) ደረጃ የሚታዩ ጉዳዮች የቤተሰብ ጉዳይ ተደርገው ስለሚታሰቡ በሕዝባዊ ቦታዎች አይታዩም። በመሆኑም የጎሳ አባቶችና አባላት ግቢ የጎሳ (የቤተሰብ) ጉዳዮች የዳኝነት ቦታዎች ሆነው ያገለግላሉ። በዋናነት ደግሞ የፖቅላ ቱማው (የጎሳ መሪው) እና የፖቃላ ሙግላው (የምክትሉ) ቅጥር ግቢዎች ዋነኛ የጎሳ ዳኝነት ማዕከላት ናቸው።

## 4.5. የግጭት አፈታት ሂደት

የኮንሶ ብሔረሰብ የተለያዩ ግጭቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ሲከሰት ግጭቶቹን የሚያበርድበት ወይም የሚፈታበት የራሱ የሆነ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት አለው። ይህ ስርዓት በአካባቢው ቋንቋ ‹‹ዴኻ-አራራ›› በሚል ስያሜ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህም ‹ዴኻ› ድርድር፣ ‹አራራ› እርቅ ‹‹ዴኻ -አራራ›› ማለት ደግሞ የዕርቅ ድርድር ስርዓት የሚለውን ይወክላል። ስርዓቱ ሶስት ዓይነት አደረጃጀት አለው፡፡ ይኸውም በፓሌታዊ አደረጃጀት (ሞራ-ከንታና ሞራ-ፓሌታ)፣ በጐሳዊ አደረጃጀት ፖቅላ ናቸው። እነዚህ ሶስት ዓይነት አደረጃጀቶች በስራቸው የየራሳቸው አወቃቀር አላቸው። የዳኝነት ቦታቸውም ከላይ እንደተገለጸው እንደየአወቃቀራቸው የተለያየ ነው።

በብሔረሰቡ አንድ ግጭት እንደተከሰተ ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ከአነሳሱ እስከ ውሳኔው የሚኬድበት የራሱ የሆነ መዋቅር አለው፡፡ ይህ አካሄድ እንደተፈጠረው የግጭት ዓይነት ክብደትና ቅለት፤ እንዲሁም የተፈጠሩት ግጭቶች እንደሚዳኙበት መዋቅር የሚታይ ሆኖ፣ ግጭቱ (ጠቡ) እንደተከሰተ በየደረጃው የሚሄዱበት አግባብ አላቸው፡፡ በባህላዊ ስርዓቱ ለተለያዩ የግጭት ዓይነቶች በየደረጃው የሚካሄደው የድርድር ሂደት የራሱ ስያሜ ያለው ሲሆን፣ የእርቅ አፈጻጸም ሁኔታውም የየራሱ ስርዓቶችና ስያሜዎች አሉት፡፡ ለምሳሌ በከንታ ደረጃ የሚካሄደው ድርድር ዴኻ-ከንታ፣ በፓሌታ ደረጃ የሚካሄደው ድርድር ዴኻ-ፓሌታ፣ እንዲሁም በፖቅላ ደረጃ የሚደረገው ስርዓት ዴኻ-ካፋ ይባላል፡፡ ከአፈጻጸም ጋር ተያይዞ ደግሞ በይቅርታ ወይንም ይቅር በመባባል፣ በቅጣት፣ በእርድና በመሀላ የሚፈቱ የግጭት ዓይነቶች አሉ፡፡ ስርዓቶቹ በአጠቃላይ ‹አራራ› ሲባሉ በስያሜ ረገድ ግን ይለያያሉ፡፡ ይኸውም በይቅርታ ወይንም ይቅር በመባባል የሚፈታው የግጭት ዓይነት ስርዓት ዴኻ-ዴባይታ ይባላል፡፡ በቅጣት የሚፈቱ (የሚደመደሙ) ዴኻ-ኾራ፣ በእርድ (የሚፈጸሙ) የሚፈቱ ‹ኮዴታ› ቃልኪዳን ነውና፣ እንዲሁም በተለያየ የመሀላ ዓይነት የሚፈቱት ሬቃ-ኾርባይታና አኩታ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ‹‹ጠበኞች ያለሽማግሌ ጣልቃገብነት በራሳቸው ሰላም የሚፈጥሩበት ስርዓትም አለ ይህ ስርዓት በብሔረሰቡ አጠራር ‹ቱታ› በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሰኔ አጋማሽ ላይ  የሚከናወን ነው ይህ ወቅት እሸት የሚደርስበት እንደመሆኑ የብሔረሰቡ ተወላጆች በጋራ ተሰባስበው እሸት በእንኩቶ መልክ እየጠበሱ በመብላት የሚያከብሩት ትልቅ ስርዓት ነው በዚህ ስርዓት ጠበኞች በተለይ ባልና ሚስቶች ሚስትም ፊት ወይም ጋለሞታ ላለመባል ባልም የቀደመ ክብሩን ላለማጣት ሲል ለማንም ሳያሰሙ ሽማግሌም ሳያስገቡ በራሳቸው ሰላም የሚወርዱበት ወቅትና ስርዓት አለ›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 21) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የግጭት አፈታት ስርዓትን በተመለከተ በብሔረሰቡ አንድ ግጭት ምንም ይሁን ምን ሲከሰት ጉዳዩ የሚታይበት ወይም የዕርቅ ስርዓቱ የሚከናወንበት የተለየ ስፍራ ወይንም ቦታ አለው፡፡ የዕርቅ ስርዓቱ ቦታዎች በአብዛኛው ገለልተኛ ስፍራዎች ሲሆኑ፣ እነዚህም የአፓ-ቲንባ ቤት፣ ሰንቀሊታ ቤት፣ የታዋቂ አገር ሽማግሌ ቤት፣ የፖቅላ ቤት፣ ወይም ‹ፓላ› ሞራ ሳይሆን በሞራ -ከንታ ውስጥ ጠፍጣፋ ድንጋዮች ብቻ ያሉበት መቀመጫ ያለው ነው፡፡

ወደ ሞራ በተለይ ወደሞራ-ከንታም ሆነ ወደ ሞራ-ፓሌታ በቀጥታ የሚቀርቡ ጉዳዮች ህዝብ ነክ ጉዳዮች ናቸው። ለምሳሌ የወጣት ትውልድ መሪ (ኼላዎች)ን መስደብ፣ ባህሉን መስደብ ወይንም ማንቋሸሽ፣ የኃይማኖት አባቶችን፣ ሽማግሌዎችን፣ ዳውራዎችን እና ፓቅላ ቱማዎችን መስደብ፣ አንድን ከንታ አሊያም አንድን ጎሳ መስደብ፣ በአጠቃላይ ሰብዕናንና ክብረ-ጎሊናን የሚነኩ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ከዚህ ባሻገር አውጫጭኝ ነገሮች ሲፈጠሩ በዋናው ሞራ ደረጃ በሞራ-ፓሌታ ሞራ-ኪርባ ላይ ይታያሉ። ስርዓቱ የሚካሄድባቸው የጊዜ ሁኔታን በተመለከተ በብሔረሰቡ ቋሚ የጉዳይ ማያ ቀናት ያሉ ቢሆንም የሞራ ላይ ጉዳዮች ግን ብዙ ጊዜ ልዩ የሆነ ክስተት ሲፈጠር ለምሳሌ ጩኸት ሲኖር፣ በአካባቢው ላይ ልዩ የሆነ ብጥብጥ ወይንም ሁከት ሲነሳ፣ በመንደሩ ሌባ ገብቶና አምልጦ የሄደ ዓይነት ከሆነ፣ ቃጠሎ ከተነሳ፣ የሆነ ቦታ ሰው ተገድሎ ቢሆንና ገዳዩ ያልታወቀ ሲሆን፣ የምንጭ ውኃ ቦታ ያልሆነ ነገር ተደርጎ ከሆነ በዚህ ጊዜ በማንኛውም ጊዜ ስርዓቱ ይደረጋል። ሌላው ‹‹በኮንሶ ከየካቲት ግማሽ እስከ ሚያዚያ እንዲሁም ከነሀሴ እስከ ጥቅምት ያሉት ወራት የዝናብ ወቅቶች ናቸው ስለሆነም መሬቱ ዝናብ እየዘነበበት እየለመለመ አረንጓዴ ከሆነ የመሬት ድንበር ጉዳይ ለማየት ወደቦታው አይኬድም የመሬት ጉዳዮች እህል እየተዘራ አይታዩም ምክንያቱም እህል ወይም አዝመራ በብሔረሰቡ ዘንድ ትልቅ ክብር አለው በመደበኛ ህግ ካልሆነ በስተቀር በባህላዊ ዳኝነት ስርዓት አይታይም ነገር ግን እገዳ ይደረጋል ማናቸውም እንዳይደርሱበት በተለይ ተዘርቶበት ከሆነ ይህ እገዳ ይኖራል›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 12፣ 2006 ዓ.ም፣ 8) ሲሉ ያስረዳሉ። ይሁንና ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ሞራ ከመቅረቡ በፊት በዳዩ ያጠፋው ጥፋት ተሰምቶት ሽማግሌዎች ዘንድ ሄዶ ተበዳይን እንዲለምኑለት ሊያደርግ ይችላል። አጥፍቻለሁ፣ ሞቅ ብሎኝ ነው ወዘተ ይቅርታ ጠይቁልኝ ብሎ አማላጅነት ሊልክ ይችላል። ሽማግሌዎቹም ወደተበዳይ ሄደው በዳይ ጥፋቱን አምኗል። ‹እውነት ጊደር ናት ትወልዳለች› በማለት አማላጅነታቸውን ይናገራሉ። ይህ ማለት በዳይህ ስለእውነት ብሎ አንተ ጋር ስለመጣ ይቅር በለው እንደማለት ነው ይላሉ። በዚህ ሁኔታ ተበዳይ ይቅር ካለ ጉዳዩ ወደሞራ ሳይሄድ በሽማግሌዎች አማላጅነት ብቻ ይቋጫል። ሽማግሌዎች በአብዛኛው የሚይዙት የምልጃ ጉዳይን ነው። በእርግጥ ምልጃ በየደረጃው ሁሉም ይሄዳል። ዋናውም የጎሳ መሪ (ፖቅላውም) ይሄዳል። እንደወንጀሉ ሁኔታ ለምሳሌ ግድያ ከሆነ፣ የአካል ድብደባ፣ ድብደባው ደም ማፍሰስ ካለበት፣ አካል መጉደል ወዘተ ከሆነ በብሔረሰቡ እንደንጉስ የሚታዩት ፖቅላዎችና ዳውራዎች ይሄዳሉ። ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎች እጅ የገባ ነገር በዕርቅ ድርድር የሚፈታ ነው። ጉዳዩን ያቀረበው

በደል ያደረሰው አካል ከሆነ ግለሰቡ በደሉንና ጥፋቱን አውቆ ይቅር ብሎ የመጣ፣ የሚወሰንበትን የቅጣት ውሳኔ ለመቀበል የመጣ ነውና ቀጣይ ቤተሰባዊ፣ ወዳጃዊና ዘመዳዊ ኑሮ የሚፈልግ አካል ስለሆነ ሽማግሌዎቹ፣ ዳውራውና ፖቅላው በበዳይ ቦታ ሆነው ይቅርታ ለመጠየቅ እንደሚሄዱ ከላይ የተጠቀሱት መረጃ አቀባይ ይገልጻሉ፡፡ የተበዳይ ቤተሰብ ይሁንታ እስኪሰጥ ድረስም ይመላለሳሉ፡፡ በቃ ለድርድር እሺ ካላችሁ ከናንተ ቃል የትም መውጣት ስለማይቻል ይህን ያህል በደል ስለደረሰብኝ ጉዳዩን እናንተ ተመልከቱልን ብለው ይሁንታ ሲሰጡ ገለልተኛ ቦታ ይወሰንና እዚያ ቦታ ድርድሩ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ጠበኞች ድርድሩን የሚበታትን ቃላት እንዳይጠቀሙ በአደራዳሪዎች ይታዘዛሉ፡፡ በድርድሩ ወቅት የዕርቅ ድርድር ከተጀመረ በኋላ ጠበኞች ስርዓቱን ጥለው መውጣት (ጨርሶ መሄድ) አይችሉም፡፡ እንደችሎት መድፈር ስለሚቆጠር ያስቀጣል፡፡ አደራዳሪዎችን መናቅ፣ ባህሉንና ስርዓቱን መናቅ እንደሆነ ስለሚገመት ያስቀጣል ማዕቀብም ይጣላል፡፡ ምናልባት ጠበኞች ስሜት ውስጥ ገብተው የወጡ እንደሆነ ግን ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ቢያንስ ለ3 ቀናት ቢበዛ ለሁለት ሳምንታት ያህል፤ ይሁንና አንዳንድ ጊዜ በዳይ ቅጣቱ እንዲቀልለት፣ የከፋ ነገር እንዳይያዝበትና ነገሩን ለማድበስበስ ሲፈልግ ወጣ ገባ ሊል ይችላል፡፡ በተለይ የድርድሩ ሁኔታ ሳያምር ሲቀር፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የአገላለጽ ሁኔታው ሳይመች ሲቀርና ተግሳጽ በመሀል የማይገባ ከሆነ እንዲሁም ጠበኞች ሳይረጋጉ ወይንም መረጋጋት የማይታይባቸው ከሆነ ሁለቱም ሊወጡ እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡ ካለመረጋጋት ጋር ተያይዞ ከሆነ ለድርድር ስለማይመች መርገብ ይኖርበታል በሚል ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ በባህል ህጉ መሰረት አንድ ድርድር ከተጀመረ ጊዜ ተወስዶና ተብላልቶ እስከሚሄድ ይሄዳል እንጂ ማቋረጥ አይቻልም፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አደራዳሪዎቹ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ጠበኞች ከሄዱ በኋላ አንመለስም የሚሉ ከሆነ ማዕቀብ ይጣልባቸዋል በማዕቀቡ መሰረት መጥተው የማዕቀብ ማንሻ እስከ 20 ብር ድረስ ይከፍሉና ከዚያ በኋላ ወደ ድርድሩ እንደገና እንዲገቡ ይደረጋሉ (ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ አያኖ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 25፣ 34፣ 44፤ ሳጎያ፣ ቡርቂዳ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 48) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ከሽማግሌዎቹ ምልጃ በላይ ከሆነ የተበደለ ሰው ወይንም ተበዳይ መጀመሪያ ወደ ሞራ-ከንታ በመሄድ ለከንታ መሪው (ለአፓ-ከንታው) ክስ መመስረቻ ወይንም ፋይል ማስከፈቻ የ‹ኾራታ› ገንዘብ ያስይዛል፡፡ የ‹ኾራታ› ገንዘብ በተበዳይ አሊያም በሁለቱም ሊያዝ ይችላል፡፡ በሞራ-ከንታ ደረጃ በተበዳይ የሚያዘው

የገንዘብ መጠን ትንሹ 10 ብር ከፍ ሲል 20 እያለ 100 ና 200 ድረስም እንደጉዳዩ ክብደትና ቅለት ይሆናል፡፡ በበዳይ ግን በኪሱ ያለውን ሆኖ ትንሹ መስያዣ ከተበዳይ በመጠኑም ቢሆን ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ ይህ እንደመነሻ የክስ መመስረቻ ወይንም ፋይል ማስከፈቻ ከተያዘ በኋላ በሳምንት በዋናነት 3(ሶስት) ቀናት ማለትም ማክሰኞ፣ አርብና እሁድ አልፎ አልፎ እሮብ ጠዋት ላይ የሽማግሌዎች የጉዳይ ማያ ወይንም የችሎት ቀናት ሆነው ይውላሉ፡፡ በነዚህ ቀናት ጉዳዮች ይታያሉ፡፡ ሰኞና ሀሙስ የገበያ ቀናት ስለሆኑ ጉዳይ የሚታይባቸው ቀናት አይደሉም፡፡ ቅዳሜ ሁሉም የየግል ተግባሩን የሚያከናውንበት ስለሆነ ቅዳሜም የጉዳይ ማያ ቀን አይደለም፡፡ ሽማግሌዎችም አይቀመጡም፡፡ ማክሰኞ፣ አርብና እሁድ የጉዳይ ማያ ሆነው የተመረጡበት ምክንያት መረጃ አቀባዮቹ ካምብሮ፣ ሽሬ፣ ሀገያና ኦተያ ሲያብራሩ፡-

> *‹‹ማክሰኞና አርብ የገበያ ማግስት በመሆናቸውና ለኸራታ ማስያዣ ገንዘብ ያጡ ሰዎች ያላቸውን ሸጠው የሚያሲዙትን ገንዘብ የሚያገኙት በነዚህ ቀናት በመሆኑ ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 39፣ 50፣ 51) በማለት ያለልዩነት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ካምብሮ የአፈታት ሂደቱን፡-

> *‹‹የኾራታ ገንዘብ ለአፓ ከንታው ከተያዘ የሚታይ ጉዳይ አለ ማለት ነው ጉዳይ ካለ ደግሞ በየደረጃው ጉዳዩን የሚመለከቱ አካላት ይኖራሉ በተጠቀሱት ቀናት በችሎቱ ይገኛሉ በዳይና ተበዳይም ችሎቱ ላይ በተጠቀሱት ቀናት በፖርሺታው አማካኝነት በመቅረብ ነው የስርዓቱን አጀማመር በተመለከተ በሽማግሌዎች ቡራኬና ጸሎት ሆኖ በቅድሚያ ከችሎቱ መሀል በዕድሜ ገፋ ባሉ ሽማግሌ ከዚያም እሳቸውን ተከትለው በዕድሜ ቅደም ተከተል ሁለት ሽማግሌዎች አንድ ላይ በሶስት ሽማግሌዎች ንግግር ይጀመራል ሽማግሌዎቹ በንግግራቸው እግዚአብሄር በሰላም አሳድሮናል ለዚህም ዕለት አብቅቶናል በማለት ይጀምራሉ ነገሩን ሲጀምሩ ፈጣሪ አንደበታችንን አንድ ያድርገው እዚህ ቦታ የተገኘነው መልካም ለሆነ ነገር ለማስታረቅ ነውና በጎ በጎውን ያናግረን ክፉ የሆነውን ነገር ፈጣሪ ከውስጣችን ያውጣ መልካም የሆነውን ነገር እንድንናገር ያድርገን በማለት ስርዓቱን ይከፍታሉ በዳኝነት ስርዓቱ የሽማግሌዎች ዋና ተግባር ስርዓቱን በጸሎትና በቡራኬ መክፈት ጉዳዩን ወደ ዕርቅ ለማምጣት ማደራደር እንጂ የውሳኔ ሀሳብ አያቀርቡም አያስተላልፉም ሽማግሌዎች ስርዓቱን በንግግር ከከፈቱ በኋላ ጠበኞች በየተራ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ዕድል ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም ድርድሩ ሲጀመር ጠበኞችን የምን ቁጭ ብድግ ነው ቁጭ ብድግ መፍትሄ ይሆናል እንዴ እያሉ በመካከል ጣልቃ እየገቡ ነገሩን በምሳሌያዊ ንግግር የማለሳለስ፣ እያለሳለሱም ጉዳዩን ለውሳኔ እንዲመች የማስተካከልና በመጨረሻ በድርድሩ የተመለከቱትን ይዘው እንግዲህ ይህን አይተናል በዚህ መሰረት እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል የውሳኔ ሀሳቡን በተመለከተ ከውሳኔ ሰጪዎች አንደበት እንድትሰሙ እንጠይቃችኋል በማለት ይሆናል ከዚያም በውሳኔ ሰጪው አንደበት በባህሉ መሰረት ሶስት ሰዎች በዕድሜ ቅደም ተከተል ይነሱና እንግዲህ የተባለውን ሰምታችኋል ብቻ በማለት*

*ሊጀምሩ ይችላሉ ነገሩን ላለመደጋገም ምክንያቱም ዋናውን የውሳኔ ሀሳብ ላለመናገር ማለት ነው ከዚያ የመጨረሻውንና ዋናውን የውሳኔ ሀሳብ ኽሊታው ወይም ሰንቀሊታው አሊያም የጎሳ መሪው ወይምፖቅላው በየደረጃው እንዲያቀርቡ ይደረጋል በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች የቅጣት ውሳኔው ከፍ ካለና የበዛ ከመሰላቸው ቅጣቱ እንዲሻሻል ውሳኔ ሰጪዎቹን ሊጠይቁ ይችላሉ በውሳኔው የተስማሙበት ከሆነ ደግሞ በዚያው አጽድቀው ችሎቱን ይደመድማሉ››* (በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 41) ሲሉ ይገልጻሉ።

እዚህ ላይ እያንዳንዱ የግጭት ዓይነት እንደየችሎቱ የደረጃ ሁኔታና እንደግጭቱ ቅለትና ክብደት የየራሱ የሆነ የአፈታት ሂደትና የአፈጻጸም ስርዓት ያለው ሲሆን፣ ይህ ከላይ የቀረበው አካሄድ በሞራ ደረጃ ለሚታዩት መንደርደሪያ ሆኖ የቀረበ ነው። ከላይ የቀረበውን የመንደርደሪያ ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በየደረጃው ያሉ ችሎቶች የሚያዩዋቸው የግጭት ዓይነቶችና የአፈታት ሂደታቸው በቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 4.5.1. በሞራ-ክንታ ደረጃ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው

በክንታ ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች ብዙ ጊዜ ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ እነዚህም የግለሰብ፣ የቤተሰብና የጉረቤት ግጭቶች በሚል በቀላል ግጭትነት ተፈርጀው የሚታዩ መሆናቸው ከላይ ተጠቅሷል። እነዚህ ግጭቶች እንደተከሰቱ በቀናት እጅግ ቢበዛ በሳምንት ውስጥ ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ። የአፈታት ሂደቱን በተመለከተ ከዚህ በላይ የቀረቡ የግጭት ዓይነቶች እንደተከሰቱ ጉዳዮቹ እልባት አግኝተው ወደቀደመው ሰላም እንዲመለሱ በመጀመሪያ ለአፓ-ክንታው (ለክንታው-መሪው) "ኾራታ" በማስያዝ የክስ ሂደቱ ይጀመራል። "ኾራታ" ማለት በብሔረሰቡ አጠራር  የክስ መመስረቻ ገንዘብ ማስያዝ ማለት ሲሆን፣ ባጭሩ "ኾራታ" ማለት ክስ መመስረት አሊያም በዘመናዊው አገላለፅ የክስ ፋይል መክፈት ማለት ነው። የ"ኾራታ" ገንዘብ የሚያዘው በተበዳይ አሊያም በሁለቱም (በበዳይና ተበዳይ) ሲሆን፣ የገንዘብ መጠኑም 10 ከፍ ሲል 20፣ 100 ና 200 ብር ድረስ ይሆናል። ለአንድ ጉዳይ (ግጭት) "ኾራታ" ከተያዘ የተለያዩ ሕዝብ ነክ የጋራ ስራዎች እንደ ሞራ (ዋና የዳኝነት ቦታ) ጥገና ስራና ምረቃ ዓይነት ካልገጠመ በቀር ጉዳዩ በሁለትና በሦስት ቀናት ውስጥ እጅግ ቢበዛ በሳምንት ጊዜ ውስጥ ይታያል። የስርዓቱ አፈፃፀም የጊዜ (ሰዓት) ዕለትና ቦታ እንዲሁም የአፈታት ሂደቱን አስመልክቶ ጊዜና ሰዓቱን በተመለከተ ሁል ጊዜም ጠዋት (ማለዳ) ከ12፡00 ጀምሮ ሽማግሌዎች የሰላም ምልክት የሆነውን የ‹ሀንሳቢታ›

(ሀረግ መሰል) ቅጠል በመያዝ፣ ፊታቸውን ሳይታጠቡ፣ እህል ሳይቀምሱ ይሆናል፡፡ ይህም ሁኔታ በብሔረሰቡ አጠራር "ማዳኮታ" ይባላል፡፡ ማለዳ የሚመረጥበት ዋና ምክንያትን አስመልክቶ ዲኖቴና ካምብሮ፡-

> *‹‹ሰው እህል ሳይቀምስ የሚናገረው ነገር ሁሉ እውነትን መሠረት ያደረገ፣ መደማመጥ፣ መስማማትና መከባበር ያለበት ይሆናል የሚል ትልቅ ዕምነት በማህበረሰቡ ውስጥ በመኖሩነው ››* (በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 25፣ 39) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

እንደ መረጃ አቀባዩ ሽሬ ገለጻ ከሆነ፡-

> *‹‹ዕለቱን ወይም ቀናቱን አስመልክቶ ማክሰኞ አልፎ አልፎ ሮብ አርብና እሁድ ጉዳይ ማያ ናቸው፤ እነዚህ ቀናት ይመረጣሉ፤ እነዚህ ቀናት የሚመረጡበት ምክንያት ማክሰኞና አርብ የሰኞና የሀሙስ የገበያ ቀን ማግስት በመሆናቸውና ብዙ ጊዜ ዕዳ ያለባቸው ሰዎች በነዚህ ቀናት ይከፍላሉ በሚል ሲሆን፣ ሌላው የኾራታ ገንዘብ ማስያዣ ማግኘት የሚቻለው በገበያ ቀናት ያላቸውን ሻሽጠው በሚያገኙት ገንዘብ በመሆኑ ነው፤ እሁድ ደግሞ የእረፍት ቀን በመሆኑ አብዛኛውን የማህበረሰቡን ክፍል ለማግኘት ምቹ በመሆኑ ቀናቱ ተመርጠዋል፤ ቅዳሜ ቀን ሁሉም የአካባቢው ነዋሪ የየግል ስራውን የሚያከናውንበት እርሻ ያለው እርሻውን ሌላ ማህበራዊ ጉዳይ ያለበት ማህበራዊ ጉዳዩን የሚያከናውንበት በመሆኑ የጉዳይ ማያ ቀን አይደለም››* (በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 50)፡፡

የዕርቅ ስርዓቱ መፈጸሚያ ቦታውን በተመለከተ እንደ አመቺነቱ በከንታው ወይም በንዑስ መንደሮቹ ከሚገኙ ሞራዎች ባንዱ ሞራ ከንታ ሊሆን ይችላል፡፡ የአፈታት ሂደቱን በተመለከተ በመጀመሪያ የኾራታ ገንዘብ ይያዛል በተበዳይ አሊያም እንደሁኔታው በሁለቱም ከዚያም በሞራ ከንታ ደረጃ ነገር ለማየት የሚቀመጡ አካላት (ተቋማት) ማለትም ፖርሺታ፣ አፓ-ከንታ ቂሞታ -ከንታና ኸሊታ- ከንታ እንዲሁም በዳይና ተበዳይ ወይንም ከሳሽና ተከሳሽ በመደበኛው የችሎት ቦታ ወይም ሞራ -ከንታ በተጠቀሰው ቀን በተለመደው ሰዓት ይገኛሉ፡፡ ሌሎችም መሳተፍ የሚፈልጉ መገኘት እንደሚችሉ ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች ለመረዳት ተችሏል፡፡

የእርቅ ድርድር (ዴኻ) ስርዓቱ የሚጀመረው በቡራኬ ወይም በፀሎት ሲሆን ይህን የሚያስጀምሩት በሞራው ከተገኙትና በዕድሜ ከፍ ካሉት ሽማግሌ ወይም ቂማያ ሆኖ እሳቸውን ተከትሎ በዕድሜ ቅደም ተከተል ሁለት ሽማግሌዎች ፀሎቱን በማጠናከር በንግግር እንደሆነ ኪሮስና አያኖ ገልጸዋል (በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 34፣ 44)፡፡ የዕርቅ አፈጻጸም ስርዓቱንና ዐውዱን በተመለከተ ዲኖቴ፡-

‹‹በሽምግልና ስርዓቱ የሽማግሌዎች የአቀማመጥ ሁኔታ አንድ ቦታ ላይ የተወሰነ ሳይሆን ተቀራራቢ ሆኖ እንደተመቻቸው የሚቀመጡ ናቸው፤ በዳይና ተበዳይም ወይም ከሳሽና ተከሳሽም  በተለያየ አቅጣጫ ተራርቀው በመቀመጥ ነው፤ በስርዓቱ ወቅት ሽማግሌዎች የሰላም ምልክት የሆነውን የሀንሳቢታ ቅጠል ይይዛሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ኸሊታ ከንታው ወረቀት በእጁ ይይዛል፣ አገልግሎቱም በዳይና ተበዳይ ጉዳያቸው በማስረጃ የሚጣራ ሆኖ ከተገኘ ማስረጃ የሚያቀርቡ ሰዎችን ለይቶ ለመያዝ ያገለግላል፤ የግጭት አፈታት ስርዓቱ በሽማግሌዎች ቡራኬ ሲጀመር አይቆሙም፣ በተቀመጡበት በዕድሜ ቅደም ተከተላቸው እከሌ ጀምር እከሌ ቀጥል ሳይባባሉ ንግግራቸውን ያደርጋሉ፤ በንግግራቸው ወቅት መጣላትም ሆነ መጋጨት ያለና አዲስ እንዳልሆነ ይገልፁና አሁን የቀረቡ ተጋጪዎች ወይም ጠበኞች የተጋጩበትን ጉዳይ ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ እግዚአብሔርን ፈርተው እውነትን አግኝተው ወደየመጡበት በሰላም እንዲመለሱ የተደረገውንና የሆነውን ብቻ እውነትን በመመርኰዝ እንዲናገሩ በማሳሰብ ተበዳዩ ሁኔታውን አጠር አድርጐ እንዲናገር የመጀመሪያውን እድል በመስጠት ያስጀምራሉ፤ በዚህ ስርዓት በዳይና ተበዳይ በደላቸውን በተቀመጡበት የሚገልጹ ሲሆን ተበዳይ በደሉን ተናግሮ ሲያበቃ ለበዳይ በተመሳሳይ ዕድሉን ይሰጡና ሀሳቡን በዝርዝር እንዲያቀርብ ያደርጋሉ፤ ከዚያ በኋላ ተበዳዩ የተረሳ ወይንም ያለአግባብ የተነገረ ካለ ተጨማሪ ዕድል ተሰጥቶት እንዲናገር ይደረጋል፤ በዚህ ሁኔታ ሽማግሌዎች በጥሞና የሁለቱንም ሀሳብ ወይም አስተያየት ይከታተላሉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለበዳዩም ተጨማሪ ዕድል ይሰጣሉ፤ በዚህ ሁኔታ የሁለቱንም ሀሳብ ሽማግሌዎች ካደመጡ በኋላ የነገሩን ጭብጥ ወይም ዋና ጉዳይ ይለያሉ፤ ወደማስረጃ ከመሄዳቸው በፊት የሰሙትን ጭብጥ መሠረት አድርገው ከታዘቡት በመነሳት እዚያው ይቅር እንዲባባሉ ይቅርታ እንዲደራረጉ ይጠይቃሉ፤ እርቅም እንዲወርድ ለማደራደር ይሞክራሉ፤ ይሁንና ለይቅርታውም ሆነ ለዕርቁ ፈቃደኛ ካልሆኑ የአንዱ ወይንም የሁለቱም ጉዳይ በማስረጃ እንዲጣራ ይደረጋል፤ ሽማግሌዎችም ምስክር በማስጠራት ከምስክር ቃል ይቀበላሉ ፤በዚህ ጊዜ ኸሊታ ከንታው በሽማግሌዎች ታዞ ሦስት ምስክሮችን እንዲጠራ ይደረጋል፤ ምስክሮችም ብዙውን ጊዜ በአቅራቢያ ስለሚገኙ ይህንን ያደርጋል፤ ምስክሮች አንድ ላይ አይገቡም፤ በየተራ እየተጠሩ በመግባት ቀርበው ያዩትንና የሰሙትን በባህሉ መሠረት ለሽማግሌዎች ቃለ መሀላ ፈጽመው ይመሰክራሉ፤ በዚህ የምስክር ወቅት ሁለት ሰዎች ከመሰከሩ ሦስተኛው አይገደድም ሽማግሌዎች ማን እንዳጠፋ በሚገባ ስለሚረዱ አሁንም በዳይና ተበዳይን ይቅርታ እንዲደራረጉ ይቅርታቸውን ይጠይቃሉ፤ ይለምናሉ፤ በዚህ ሁኔታም ተበዳይ ይቅርታ አላደርግም ካለ ሽማግሌዎች እንደ ግጭቱ ሁኔታ በበዳይ ቅጣት እንዲጣልበት ያደርጋሉ፤ ቅጣቱንም ኸሊታዎች እንዲወስኑ ወይም የቅጣት ጣራውን እንዲናገሩ ዕድል ይሰጣሉ፤ በዚህ ደረጃ የሚወሰነው ቅጣት ብዙ ጊዜ የገንዘብ ቅጣት ሲሆን መጠኑን በተመለከተ ለኾራታ ከሚያስይዙት ገንዘብ ብዙም የሚጨምር አይደለም በዚህ ጊዜ አንዱ ኸሊታ እንደነገሩ ክብደትና ቅለት ይህን ያህል ቢሆን ብሎ ቅጣቱን ይናገራል ሽማግሌዎቹ ቅጣቱ የበዛ ከመሰላቸው የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በማቅረብ ኸሊታውን በድጋሚ እንዲቀንስ ይለምናሉ ኸሊታው አሁንም በዚህ ሁኔታ ሽማግሌዎች ሲለምኑ ሊቀንስ ይችላል አለበለዚያ መጀመሪያ ኸሊታው በወሰነው ውሳኔ ሽማግሌዎች ካመኑበት ቅጣቱ እንዲፀና ያደርጋሉ ይህን የቅጣት ውሳኔ በዳይ ካልተቀበለውና ግጭቱ መፈታት ካልቻለ ጉዳዩ በሞራ ፓሌታ ወይም በዋናው ሞራ ደረጃ እንዲታይ ያስተላልፉታል ነገር ግን በቅጣቱ ከተስማማ በዳይ ያስያዘው ገንዘብ ከቅጣቱ ጋር

*ተመጣጣኝ ከሆነ ተነስቶ ወደ ውጭ ወጥቶ ይቆያል፤ የቅጣቱ ገንዘብ እሱ ካስያዘው በታች ከሆነ እንዲጨምር ይደረጋል፤ የቅጣቱ ገንዘብ እሱ ካሲያዘው በላይ ከሆነ ትርፉ ይመለስለታል በመጨረሻም በዚህ ሁኔታ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሽማግሌዎች ሁለቱን ጸበኞችን አንድ ላይ በማድረግ ይህን መሰሉን ነገር ሁለተኛ እንዳንሰማ በሚል ያስጠነቅቃሉ፤ ብንሰማም አንዳኝውም ጉዳዩንም ወደ ሞራ ፓሌታ እናስተላልፈዋልን ስለዚህ እናንተ ከዚህ በኋላ ወንድማማቾች ናችሁ ሰላም ወርዷል ባላችሁበት ተጢያየቁ በሚል እርስ በርስ አጨባብጠውና አሳስመው ችሎቱን በዚህ ደምድመው ያሰናቧታሉ፤ በዚህ መልኩ የተፈፀመው የእርቅ ስርዓት በቅጣት የተደመደመ በመሆኑ ስርዓቱ ዴኻ ኾራ ይባላል፤ ይሁንና ጠበኞች በይቅርታ ከተላለፉ ስርዓቱ ዴኻ ዴባይታ ይባላል፤ በዚህ መልኩ ዕርቁ ከተደመደመ ጠበኞች የኾራታ ገንዘባቸው ተመልሶላቸው በመጨባበጥ ወይንም እጆቻቸውን ወደላይ እያነሱ ሰላም ወርዷል በቃ በማለት እያወዛወዙ በተለያየ አቅጣጫ ይወጣሉ፤ በተለያየ አቅጣጫ መውጣታቸው ሰላም የመውረዱ ምልክት ነው፤ በተለያየ መንገድ ቢሄዱም በሚሄዱበት መንገድ ሁሉ እግዚአብሄር ይከተላል››* (በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 25-27) እንደማለት መሆኑን ይገልጻሉ።

በዚህ የሞራ-ከንታ ደረጃ የተከሰቱ ቀላል ግጭቶችን ጥር 18 ቀን 2006 ዓ.ም ሁለት በቀላል ግጭቶች የሚፈረጁ የግለሰብና የጎረቤት ግጭቶች ቀርበው ሙሉ ስርዓታቸውንና ዐውዱን ጭምር በቦታው በአካል በመገኘት ሙሉ ስርዓቱንና ዐውዳዊ ክዋኔውን ማየት የተቻለባቸው ሁለት ኬዞች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ኬዝ አንድ**

የመጀመሪያው የወ/ሮ ሻካያ ሴንዴኮ ከዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር በኦተንቲታ ሞራ-ከንታ ላይ የእርሻ ላይ እህል በጎረቤት ከብቶች በመበላቱ ያስያዙት ‹ኾራታ› (የክስ ጉዳይ) ነው። በዕለቱ ባህላዊ ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት አጥኚዋ በቦታው አስቀድማ ጠዋት 12፡00 ሰዓት ተገኝታለች። ፖርሺታው፣ አፓ-ከንታው፣ ቂሞታ-ከንታ (የከንታ ሽማግሌዎች)፣ ኼለታዎች (ኸሊታ-ከንታው)፣ ከሳሽና ተከሳሽ እንዲሁም ሌሎች ከሁለቱም ወገኖች የሆኑና ያልሆኑ ተሳታፊዎች በሞራ-ከንታው (ችሎት) የተገኙ ሲሆን ከጠዋቱ 12፡00 ጀምሮ እስከ 12፡30 ድረስ ተሰባስበው ጉዳዩ ታይቷል።

ለወትሮው የኮንሶ አየር ንብረት እጅግ ሞቃታማ ቢሆንም በወቅቱ በዚያን ሰዓት የነበረው አየር በጣም ቀዝቃዛና ነፋሻማ ነበር። የሞራ-ከንታው አካባቢ ለመቀመጫነት የሚያገለግልና ለሁሉ ማረፊያ የሚሆን ዙሪያውን ጠፍጣፋ የድንጋይ ካብ በብሔረሰቡ አጠራር ‹ፓላ› ያለበት፣ የዕለቱም ጉዳዮች የታዩበት፣ የተቀራረቡ ቤቶችና ዘመም ያሉ በአሮጌ እንጨት የታጠሩ አጥሮች ያሉበት፣ በአራት አቅጣጫ ቀጫጭን የእግር መተላለፊያ መንገዶች

ያሉት፣ ከድንጋይ ውጭ ሳር የማይታይበትና በሳር የተሸፈነ የወጣቶች ማደሪያ ጎጆ ቤት (ፓፍታ) ያለው ነው። ከአንዲት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ከሳሽ ሴት በስተቀር በችሎት ቦታው የተገኙት ሁሉም ወንዶች ናቸው። በችሎቱ ከ40 የማያንሱ ሰዎች ተሳትፈዋል። በዕድሜ ደረጃ ሲታዩ ከ25-60ና በላይ የሚገመቱ ሲሆን አለባበሳቸው እጅግ የተዘበራረቀ ነው። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ የወጣት ቡድን አባላት (ኼለታዎች) ሲሆኑ፣ በህብረቀለማት ያሸበረቀ ጀለቢያ፣ ግማሾቹ በትከሻቸው ላይ ጣል ያደረጉ፣ የተወሰኑት ደግሞ ሙሉውን የለበሱ ናቸው። ቀሪዎቹ ደግሞ በዕድሜ ገፋ ያሉት ቂሞታ ከንታዎች (የከንታ ሽማግሌዎች) ሲሆኑ ጋቢ የለበሱ፣ የተወሰኑት ደግሞ ባዶኣቸውን ያለተጨማሪ ልብስ በዘወትር ልብሳቸው የመጡ ናቸው።

ከሳሽ ወ/ሮ ሻካያ አቀማመጣቸው እንደወንዶቹ ተዝናንተው ሳይሆን ጉዳያቸውን ለማስረዳት ከወንዶቹ ፊንጠር ብለው አጥር ስር ጭብጥ በማለት ነበር። ወንዶቹ እንደአመጣጣቸው ባገኙበት ቦታ የተቀመጡ ሲሆን፣ ሲመጡ ሰላምታ አልተለዋወጡም። የሁሉም አቀማመጥ የአራቱን ቀጫጭን መስቀለኛ መተላለፊያ መንገድን ይዞ ፊት ለፊት በመተያየት ነበር። በዚህ ሁኔታ የተሰባሰቡ ሰዎች መሟላታቸውን ከተረዱ በኋላ ‹ኸሊታ-ከንታው› ጎርነን ባለ ድምጽ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ስነ ስርዓቱን ለመጀመር ችሎቱ የተሟላ መሆኑን ገለጹ። ስነ- ስርዓቱ በኸሊታ-ከንታው ሲጀመር ሁሉም የጎንዮሽ ወሬውን አቁሞ በአካባቢው ጸጥታ ሰፍኗል። በዚህ ስርዓት አፓ-ከንታዎች (የከንታ አባቶች) እና ፖርሺታዎች (ከሳሽና ተከሳሽን) እንዲቀርቡ የሚያደርጉ፣ ጉዳይ የሚከታተሉና የሚቀሰቅሱ በመሆናቸው ይህንኑ አከናውነዋል።

በምልከታ ወቅት መረዳት የተቻለው ነገር በባህላዊ ችሎቱ ሽማግሌዎችና ኸሊታ ከንታው የሚከበሩ መሆናቸውን ነው። እነሱ ንግግር ሲጀምሩ የሚያወራ የለም ሁሉም የሚከታተል እንጂ። በዕለቱ የቀረበውን ጉዳይ ለመፍታት በመጀመሪያ 3 (ሶስት) ሽማግሌዎች (ቂሞታ-ከንታዎች) እከሌ ጀምር እከሌ ቀጥል ሳይባባሉ በዕድሜ ቅደም ተከተላቸው ችሎቱን በቡራኬና በጸሎት በንግግር ከፍተዋል። በንግግራቸው ወቅት የሽማግሌዎቹ አቀማመጥ አንድ መደዳ ሳይሆን የተለያየ ቦታ ነበር። በዚህም ንግግራቸውን ከተለያየ አቅጣጫ አይንን እያዘዋወሩ መከታተል የግድ ነበር። በቀዳሚነትም አቶ ጉደታ ሎኮ የተባሉ አረጋዊ በዕድሜ ደረጃ በጸሎት ከፍተዋል። እሳቸውን ተከትሎ አቶ ቱሬ ሀምቢሮ ቀጥለው ተናግረዋል። በንግግራቸው ‹ሰላም ያሳደረን ሰላም ያውለን፣ ሰላም ያናግረን፣ ከሀቅ እንዳንወጣ ያድርገን፣

ምህረት ያውርድልን መቼም እግዚአብሄር በሁሉ ነገር ይጠራል። ሲበላም፣ ሰጠጣም ሲተኛም አሁንም ሰላም ያውለን፣ ዳኝነታችንንም ቀና ያድርገው› በማለት የዳኝነት ሥርዓቱን ለመጀመር የሚያስችል የቡራኬ ጸሎትና የምርቃት ሥነ ስርዓት አከናውነዋል። ከዚያ ቀጥለው አቶ ኪሮስ ጃርሶ ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ተናግረዋል። በዋናነት ይህንን ጉዳይ ይመራ የነበረው ኸሊታ-ከንታው አቶ ሸሬ ጮልታ ነበር። ይህ መሪ ከሳሽና ተከሳሽ ሀሳባቸውን ከማቅረባቸው በፊት የጥፋቶቹን ሁኔታ ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ እንዲናገሩ፣ አንዱ ሲናገር ሌላው በጥሞና እንዲከታተል፣ እንዲያዳምጥና ለመልስ እንዲዘጋጅ፣ ይህ ሞራ የተቀደሰ እንደመሆኑ፣ እግዚአብሄርም አጠገባችን ሆኖ የምንሰራውንና የምናደርገውን የሚከታተል እንደመሆኑ እውነትን ተመርኩዘን ቅጣትን ሳናስብ፣ ጎረቤት ይቀጣናል፣ ብራችንን ይወስድብናል ሳንል፣ ይህንንም ሀሳብ ከውስጣችን አውጥተን የተከሰተውን ወይንም የተደረገውን እውነት ብቻ በሰውና በእግዚአብሄር ፊት እንድትናገሩ አሳስባለሁ ካለ በኋላ ከሳሽ ወ/ሮ ሻካያ የተበደሉትን እንዲናገሩ እድል ተሰጥቷቸዋል። ወ/ሮ ሻካያም የአቶ ገለቦ አንጎኖ እና የአቶ ገልገሎ ገለቦ ከብቶች በእርሻዬ ያለውን እህሌንና ሳር በሉብኝ፣ አበላላቸው ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ነው። ሆኖም ‹ቀባይታ› አላገኘሁም። ‹ቀባይታ› ማለት በብሔረሰቡ አጠራር ይቅርታም አልተጠየቅሁም እንደማለት መሆኑን ከአስተርጓሚ ዲኖቴ ኩስያ ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ ሁኔታው ስላስከፋኝ፣ አይዞሽ ተበደልሽ ባይ ስላጣሁ ቅሬታዬን አቤት ብያለሁ። ክስ መስርቻለሁ በማለት ሀሳባቸውን ዘርዝረው አቅርበዋል። ከዚያም የሳቸውን ሀሳብ ተከትሎ አንደኛው በዳይ (ተከሳሽ) አቶ ገለቦ አንጎኖ ከብቶቹ በርግጥ ሄደው እርሻ ላይ ገብተው ንብረት ማጥፋታቸውን አረጋግጫለሁ፤ ሆኖም በከሳሽ ተጋኖ እንደተነገረው አይደለም፤ ከብት ጠባቂ ልጆች ይዋሻሉ። ብዙ ጊዜ ጥፋታቸውን ለመደበቅ ሲሉ ያጋጩናል፡፡ ያደረጉትን አላደረግንም ይላሉ። በመሆኑም በወቅቱ አማላጅ የሚሆን ሽማግሌ አለመላኬ ሊያስወቅሰኝ አይገባም፤ ምክንያቱም ቀደም ሲል የወ/ሮ ሻካያ ከብቶች በተደጋጋሚ ማሳዬን ጎድተዋል፡፡ እኔም በተለያየ አጋጣሚ ወ/ሮ ሻካያ የደረሰብኝን ጉዳት እንዲያውቁት አድርጌያለሁ፡፡ ዛሬ ግን እሳቸው መቻል ሲገባቸው ክስ ለመመስረት በቅተዋል፤ እንዲያውም ከብቶቹ እርሻ ማሳ ላይ ሲገቡ አንዲት እርጉዝ በግ አጉል አመታት ተመትታ ይሄው እቤት ውስጥ እያጣጣረች ትገኛለች። ስለዚህ በጥፋቱ መሠረት እኔ ልቀጣና ለተበደልኩበት ደግሞ እኔ በተራዬ ክስ ላቅርብ በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ወ/ሮ ሻካያም እኔ ከብቱን አልጐዳሁም በወቅቱም ማሳዬ ሲበላ እኔም አልነበርኩም። ሌሎች ናቸው ከብቶቹን ከማሳዬ ያስወጡት፤ ስለዚህ ከብቱን አልጐዳሁም። በባህሉ መሠረት

ከብትና ልጅ ቢያጠፋም ከቁጣ ባሻገር ለጉዳት የሚያደርስ ቅጣት አይፈፀምባቸውም፤ ስለዚህ እኔ የተባለውን ነገር አልፈፀምኩም፤ ለመከላከል የሚያቀርበው ሀሳብ እንጂ እውነት አይደለም በማለት ድጋሚ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተከሳሹም ይህንኑ በማጠናከር እንደገና ተናግረዋል፡፡ በወቅቱ በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ይካሄድ የነበረው ምልልስ ብዙም የከረረ አልነበረምና ኸሊታ-ከንታው የሁለቱን ሀሳብ መሠረት በማድረግ አንደኛ ከንታ በእናንተ ገንዘብ አይበለፅግም፤ የእናንተንም ገንዘብ በልቶ አይጠቀምም፡፡ በወቅቱ ከብትና ልጅ ያጠፋል፤ ይቅርታ መደራረግም ያለ ነው፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያት የነገሩ መዘግየት ለዚህ ቢያበቃችሁም ተውት፣ ይቅርታም ተደራረጉ፡፡ ተበዳይም አንቺም ከብት አለሽ በተለያየ ጊዜ የአንቺም ከብቶች ጥፋት ማድረሳቸውን በዚህ መድረክ ሰምተናል፡፡ ስለዚህ አንቺም ተረጋጊ እናም ነገሩን ሁለታችሁም ለማቀዝቀዝ ሞክሩ፡፡ ይቅርታም ተደራረጉ በዚህ ሀሳብ ቅር የሚለው ካለ ይናገር በማለት ጠይቀዋል፡፡ አቶ አያኖ ከንዳ ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ተውት ይቅርታ ተደራረጉ ኾራታችሁን ውሰዱ ገንዘባችሁን ተረከቡ ብለው ሲናገሩ ምላሽ የሰጠ አልነበረም፡፡ ከሳሽም ተከሳሽም፣ ሽማግሌዎችም ጭምር ዝም ነበር ያሉት ይህ የሚያሳየው እርቁን መቀበልና የሽማግሌዎቹን ቃል አክብረው መስማማታቸውን ነው ሲሉ አስተርጓሚ ዲኖቴ ተናግረዋል፡፡ ከዚያም ኸሊታ ከንታው ለከንታ መሪው ጸበኞች (ከሳሽና ተከሳሽ) ያሲያዙትን የኾራታ ገንዘብ መልስላቸው በማለቱ አቶ ካምቢሮ ጉኞ (የከንታ መሪው) ገንዘባቸውን በመመለስ ጉዳዩ በይቅርታ ታልፎ በሰላም ወደየቤታቸው እንዲሄዱ በማድረግ የመጀመሪያውን ጉዳይ በዚህ ደምድመዋል፡፡ ይህ የእርቅ ስርዓት ያለቅጣት በይቅርታ የተደመደመ በመሆኑ ስርዓቱ ዴኻ- ዴባይታ ይባላል፡፡ በዚህ የምልከታ ወቅት የግጭቱ ሁኔታ የጠነከረና ብዙ ማስረጃ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ በእርቅ ስርዓቱ ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት ተከሳሾች ቢቀርቡም የተለየ ሀሳብ እንደሌላቸው በመናገራቸው ሁለቱም ቀርበዋል፤ ነገር ግን ሁለቱም አልተናገሩም፡፡ በዚህ ወቅት የጠበኞች የዕርቅ ሁኔታ በይቅርታ የታለፈ በመሆኑ ጠበኞች ያስያዙት የኾራታ ገንዘብ ተመልሶላቸው ተጨባብጠው በተለያየ አቅጣጫ እጆቻቸውን በማውለብለብ ከችሎቱ ተሰናብተዋል፡፡በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያው ችሎት ተደምድሟል፡፡ በዕለቱ ጥናት አድራጊዋ ከዕርቅ በኋላ የተበኞቹን ስሜት ለመረዳት ባደረገችው ጥረት ‹ቂሞታ ዋቃ› በማለት ይጀምራሉ፡፡ ቂሞታዎች (ሽማግሌዎች) እንደ እግዚአብሄር ይቆጠራሉ፡፡ ‹ቂሞታ ኡታ ናማዳ ሚኒ› (ሽማግሌዎች አር ያጎርሳሉ/ያበላሉ) እንደማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ሽማግሌዎች የሚሉትን ሁሉ መቀበል ግዴታ ነው፡፡ ከነሱ ቃል መውጣት ማለት ከእግዚአብሄር ቃል መውጣት

ስለሚሆን የተባለውን አሜን ብለናል፡፡ በዕርቁም ሰላም በመውረዱ ተደስተናል፡፡ አብረን የምንኖር፣ በደስታና በሀዘን ጊዜ የማንለያይ በመሆናችን በዚህ ሁኔታ ብንለያይ ማህበራዊ ህይወታችን ጥሩ ስለማይሆን ሰላም መውረዱ በጣም አስደስቶናል ሲሉ መግለጻቸውን በአስተርጓሚ ዲኖቴ አማካኝነት ስሜታቸውን መረዳት ተችሏል፤ ሌላው በዚሁ ችሎት ከለውጥ ጋር ተያይዞ በቃለመጠይቅ ወቅት ከአንዳንድ መረጃ አቀባዮች ለመረዳት እንደተሞከረው የሴቶችና የህጻናት በችሎት ወቅት ያለ ሁኔታ በከፊል እንደለውጥ የተስተዋለ ነበር፡፡

**ኬዝ ሁለት**

ሁለተኛው ኬዝ ደግሞ ከገንዲማ ቀበሌ (መንደር) የመጣ ተበዳይ አቶ ጉይታ ገለቦ የገዛሁትን ፍየል አቶ አወቀ ዲኖቴ የተባለው የገበሬ ነጋዴ ወሰደብኝ፣ ከራሱ ፍየሎች ጋር ቀላቅሎ የኔ ነው አለኝ በሚል ያቀረበው ክስ (ያስያዘው ኾራታ) ነው፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ ቀደም ብሎ ችሎቱ በሦስት ሽማግሌዎች በንግግር ስለተከፈተ በዚህ ክስ ተበዳይ ሀሳቡን ከማቅረቡ በፊት አቶ አያኖ ከነዳና ኸሊታ ሽሬ ጮልታ ለችሎቱ የመንደርደሪያ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች በመንደርደሪያ ንግግራቸው (ከሳሽና ተከሳሽን) የእናንተ ጉዳይ በመተማመን የሚያልቅ ካልሆነ በማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ ይህም አጥፊው የጠፋውን የፍየል ዋጋ ከመክፈል ባሻገር ለከንታው ይቀጣል፡፡ ይህን ሁኔታ ለሚያጠሩ ሽማግሌዎችም ሆነ የአካባቢ ወጣቶች (ኼለታዎች) አበል ይከፍላል፡፡ ቀጥሎም ኸሊታ ሽሬ ጮልታ ከላይ በተገለፀው መሠረት ጉዳዩ በግልጽ ተጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል እንጂ በባህል “አኩታ” የሚያስኬድ አይደለም፡፡ “አኩታ” ከአስተርጓሚ ዲኖቴ መረዳት እንደተቻለው መሀላ ማለት ነው (የመሀላ ዓይነት) ነው፡፡ መሀላ የሚያስኬድ ስላልሆነ ይህንን ከግንዛቤ አስገብታችሁ የተፈፀመውን ዝርዝር ሁኔታ እንድታቀርቡ እንፈቅድላችኋለን በማለት የማስጠንቀቂያ ያህል ተናግረዋል፡፡ ከዚያም ከሳሽ ከገንዲማ ቀበሌ ገ/ማህበር አቶ ጉይታ ገለቦ ቁመቱ ረጅም፣ ጠይም መልክ ያለው፣ ወጣትና ቀጭን ሲሆን፣ እንዲሁም ተከሳሽ አቶ አወቀ ደኖቴ ከዱራይቴ ቀበሌ መልኩ ጥቁር፣ መካከለኛ ቁመት ያለው ወጣት ከተለያዩ ቀበሌ የመጡ ቢሆንም ጉዳዩ በከንታ ደረጃ ታይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ጉዳዩ የመንደር ወይንም የብዙሃን ጉዳይ ሳይሆን የግለሰቦች ግጭት በመሆኑ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መልኩ በግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ ማንኛውም ግጭቶች የሚዳኙት በበዳዩ ከንታ ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት

የበዳይ ከንታ ጥፋቱን ከስር ተከታትሎ እውነትና ውሸቱን ለይቶ ትክክለኛውን ውሳኔ መስጠት ስላለበት ነው፡፡ ውሳኔውም ከአድልኦ ፈፅሞ የራቀ መሆን አለበት፡፡ የበዳዩ ጥፋቶች የዕለቱን ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ያሉ ጥፋቶች ካሉም ዘርዝሮ መግለጽ አለበት፡፡ ይህም የሚሆነው የተበዳይ ወገኖች ከሌላ መንደር ስለሚመጡ ሁኔታውንም ስለሚከታተሉ ትክክለኛ ውሳኔና ፍርድ መሰጠቱን ለማረጋገጥ ወደ ቀበሌያቸውም ሲሄዱ የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ነበር፤ ትምህርታዊ ነበር እንዲሉና ያለአድሎ ትክክለኛ ፍርድ እንዲሰጥ ስለሚፈለግ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በንግግሮቹም ወቅት ከሌላ ቀበሌ የመጡ ሰዎችን (የተበዳይ ወገኖችን) በማክበር፣ ምንም ቅሬታ ሳይሰማቸው እንዲሄዱ በማለት አስተያየት ያላቸው ሁሉ በነፃነት እንዲናገሩ እድል ሲሰጥ ነበር፡፡ ይናገሩም ነበር፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ከሌላ ቀበሌ የመጣን ተበዳይ የማክበር ስርዓት በባህሉ በመኖሩ መሆኑን ከአስተርጓሚው መረዳት ተችሏል፡፡ የዳኝነታቸውን ትክክለኛነት ለማስመስከርም ዝናም ለማግኘት ጭምር ሲሉ እንደሚያደርጉት ተገልጿል፡፡ በምልከታ ወቅት የግጭት አፈታት ሂደቱን በተመለከተ ተበዳይ አቶ ጉይታ ገለቦ የገንዲማ ቀበሌ ነዋሪ አቶ አወቀ ዲኖቴ በደንገልቱ ነዋሪ የሆነው ከኮልሜ ገበያ በብር 410 የገዛሁትን መልኩ ጥቁር፣ ከግንባሩ ላይ ነጭ፣ ከግራ የፊት እግሩ ስር ነጭ፣ ቀንዱ መጠነኛ የሆነ ፍየል ከራሱ ፍየሎች ጋር ቀላቅሎ ከወሰደብኝ አንድ ወር አለፈ፡፡ በተለያየ ጊዜ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም በመሆኑም ባለኝ ማስረጃ መሠረት የከንታው ሽማግሌዎች አጣርተው ውሳኔ እንዲሰጡኝ ስል የዛሬ 15 ቀን ብር 200 የ"ኾራታ" ገንዘብ ያስያዝኩት በማለት ሀሳቡን አቅርቧል፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ ሁለቱም የፍየል ነጋዴዎች ሲሆኑ ተከሳሽ አቶ አወቀ ዲኖቴ እኔ የአንተን ፍየል አልወሰድኩም የራሴ ፍየል ነው፡፡ የኔ ፍየል ካንተ ፍየሎች ጋር አንተ ሠፈር ወደ "ፎራ" /የከብቶች ማደሪያ/ ሄደ፡፡ እኔም ፍየል ጠባቂዬን ሂድና አምጣ ብዬ ልኬው አመጣልኝ፡፡ የእኔን እንጂ የአንተን አይደለም፡፡ አንተ የራስህን ፍየል ፈልግ የአንተን ፍየል አልወሰድኩም ብሎ ክዷል፡፡ ከሳሽ በተጨማሪም ፍየሉን ስገዛ የነበረ ሰው፣ 410 ብር ስቆጥር ያየ ሰው ወደዚህ አካባቢ ስመጣ ከማን ፍየሎች ጋር እንዳመጣሁ የሚያውቅልኝ አለ ብሎ ሲናገር ሽማግሌዎች ከሁለቱም የተሰጡትን ሀሳብ በጥሞና ተከታትለው አማራጭ ሰጥቷቸው፡፡ ሁለታችሁም ነጋዴዎች ናችሁ፡፡ ገንዘብ ቢጎድልባችሁ የምትበዳደሩ ናችሁ፤ ፍየል ቢጠፋባችሁ አብራችሁ በመተጋገዝ የምትፈልጉ ናችሁ፡፡ ስለዚህ አሁንም እኛ አንዱን ክፍል ክፍያውን ተቀበል አንልም፡፡ ስለዚህ ከሽማግሌዎች መሀል አንደኛው "ኮሮፍታ ሳሳ ኬሳኤ ተርሳሚ" በማለት ተናገሩ፡፡ ይህ ማለት ጥፋቱ

ከሁለት አንዳችሁ ጋር ነው ያለው ከናንተ አልወጣም ስለዚህ አስቡና የፍየሉን ዋጋ ለሁለት ተካፈሉ። ተበዳይ ነኝ የሚል ከበዳይ ግማሹን ገንዘብ ይቀበል። እሱም ግማሽ ይጣ (ይተው) በማለት ነገሩን ለማለዘብ ሞከሩ። ከዚያም እኛ ይኸን ብለናል እናንተስ ምን ትላላችሁ በማለት ድጋሚ ጠይቀዋል። ተበዳይ ነኝ ባይ ለዚህ ሁሉ ማስረጃ አለኝ አቀርባለሁ ብሎ ሲናገር በዳይ ደግሞ ማስረጃ መሆን የሚችለው እኔ ስገዛ ያየ ሰው ነው መሆን ያለበት እንጂ እሱ ሲገዛ ያየ አይደለም መሆን ያለበት በማለት ሀሳብ አቅርቧል። በዚህ ጊዜ የተለያዩ ሰዎች ተጨማሪ አስተያየት ለመስጠት ቢሞክሩም በዳይና ተበዳይ ፈፅሞ ሊስማሙና ሊግባቡ አልቻሉም። ጠንከር ያለ ምልልሶችም ያደርጉ ነበር። በመሆኑም ኸሊታ ከንታው አቶ ሽሬ ጮልታ ከተበዳይ በኩል አንድ ሰው፣ ከበዳይ በኩል አንድሰው፣ ከከንታ በኩል አንድ ሰው እንመድባለን በማለት መደቡ ስማቸውንም በወረቀት እንዲሰፍር አደረጉ። እነዚህም ሰዎች በደንቡ መሠረት ማስረጃ መቁጠር የሚችለው ተበዳይ ነኝ ባይ እንጂ በዳይ አለመሆኑን እናረጋግጣለን። ስለዚህ ማስረጃ የሚቆጥረው ተበዳይ ነው ሲል ተናግሯል። በዚህ መሠረት ሦስት/3/ ሰዎች ተመርጠው ማስረጃ ወዳለበት ተያይዘው እንዲሄዱ ተደርጓል። እዚያም ሄደው የማስረጃውን ቃል ሰምተው መጥተው ለዚሁ ችሎት እንዲያቀርቡና ከዚያ በመነሳት ውሳኔ ለመስጠት እንዲያመች ከ3 (ሦስት) ቀናት በኋላ ለ20/05/06 ማክሰኞ ቀን በቀጠሮ የተለያዩበትን ችሎት በአካል መመልከት ተችሏል።

### 4.5.2. በሞራ-ፓሌታ ደረጃ የሚፈቱ ግጭቶችና የአፈታት ሂደታቸው

#### 4.5.2.1. የቀላል ግጭቶች አፈታት ሂደት

በፓሌታ ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች በአብዛኛው መነሻቸው በማህበራዊ ጉዳዮችና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሳቢያ ሆኖ ቀላልና ከባድ በሚል ተፈርጀው የሚታዩ መሆናቸው የግጭት አይነቶችና መንስኤዎቻቸው በሚል ከላይ ተጠቅሷል። በዚህ ደረጃ እንደቀላል ግጭት የሚታዩት በሞራ-ከንታ ደረጃ መፈታት ያልቻሉና ተፈፃሚነት ያላገኙ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ እነዚህ ግጭቶች በከንታ ደረጃ በአፈታት ሂደት ውስጥ ቡድንተኝነት፣ ማዳላት ሲኖርና ጉዳዩ ሳይቋጭ ሲቀር፣ በዳይና ተበዳይ (ከሳሽና ተከሳሽ) በዳኝነት ሂደቱ ላይ ሳይጣጣሙ ሲቀሩና ለከንታው ለውሳኔ አሰጣጥ ሳይመች ሲቀር፤ እንዲሁም ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ሳይጣል ሲቀርና ከሁለቱ አንዱ ለከንታው ስልጣን ተገዢ ባለመሆን ሳቢያ ጉዳዩ ወደፓሌታ ደረጃ የተላለፈው ነው። ግጭቶቹን የሚያዩት ቂሞታ-ፓሌታ፣ ኸሊታ-ፓሌታ፣ ሰንቀሊታ፣ አፓ-ቲንባ፣ ዳውራዎች፣ ሳራዎች እና ፖቃላ ሙግላ (ቱራይታ) ናቸው። በዚህ ደረጃ

የሚታዩት ጉዳዮች የጊዜ (የሰዓት) ሁኔታን በተመለከተ ከሞራ-ከንታው የተለየ አይደለም። ግጭቱ እንደተከሰተ ወይንም ጉዳዩ እንደተላለፈ በ3 (ሦስት) ቀናት ውስጥ መታየት ይጀምራል። ጉዳዩ የሚታየው ብዙ ጊዜ ማለዳና የገበያ ዕለት ሰኞና ሐሙስ ባልሆኑ ቀናት ይሆናል። ጉዳዩ በቅድሚያ የሚታየው በአፓ-ቲንባው መሪነት በአፓ-ቲንባው ቤት ወይንም ደጃፍ ላይ ሞራ ያልሆነ ይሆናል፡፡ ጉዳዩ ጠንከር ብሎ ከዚህ ካለፈ በሞራ ላይ ሞራ-ፓሌታ ላይ የሚታይ ይሆናል። ሞራ-ፓሌታ ሰፊና ብዙ አገልግሎቶች ያሉት ነው። የፓሌታውን ሕዝብ የመያዝ አቅም ያለው ነው፡፡ የወጣት ትውልድ ሽግግር ምልክት “ኦላ ሂታ” የሚቆምበት እንዲሁም ሌሎች የትውልዱ የጀብዱ ስራ እንደጦርነት ማሸነፍ ሊሆን ይችላል። “ዳጋ ዳሩማ” /ትክል ድንጋይ/ የሚቆምበት፣ መጨፈሪያ ቦታ ያለው፣ ፓፍታ /የወጣቶች ማደሪያና የእንግዶች ማረፊያ እንዲሁም መቀመጫ ያለው ነው። በነዚህ በርካታ አገልግሎቶቹ ከሞራ-ከንታ ይለያል። የግጭት አፈታት ሂደቱን ስንመለከት እንደሞራ-ከንታው መጀመሪያ “ኾራታ” በተበዳይ አሊያም በሁለቱም ይያዛል። “ኾራታ” የሚያዘው ከሞራ -ከንታ ለተላለፉ ግጭቶች ነው። የኾራታ ገንዘቡ ድጋሚ የሚቀርብ ሲሆን፣ መጠኑ ከሞራ-ከንታው ከፍ ይላል፡፡ በሞራ-ፓሌታ የኾራታ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የቅጣት ሁኔታውም እንደደረጃው ከፍተኛ ነው። በሞራ-ከንታ ከ 10-200 የሚደርስ የኾራታ ገንዘብ የሚያዝ ሲሆን፣ በሞራ-ፓሌታ ደረጃ እንደጉዳዩ ሁኔታ ከ 50-1000 ብር ሊደርስ ይችላል። በዚህ መልኩ የ‹‹ኾራታ›› ገንዘቡ ከተያዘ በሦስት ቀናት ውስጥ በተጠቀሱት ቀናት፣ ጊዜና ሰዓት እንዲሁም ቦታ ችሎቱ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ስርዓት በቅድሚያ በዳኝነቱ ላይ የሚመለከታቸው አካላት ይቀርባሉ። ጠበቆቹም ይገኛሉ። ችሎቱ የተሟላ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ችሎቱ ከተሟላ በኋላ ስርዓቱ በ3 /ሦስት/ ሽማግሌዎች ይጀመራል።

ጥር 14 ቀን 2006 በነበረው የቡድን ውይይት ወቅት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ በባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ላይ ስነ-ስርዓቱ በ3 /ሦስት/ ሽማግሌዎች በቅደም ተከተል የመጀመሩ ተምሳሌትነት ብዙ ጊዜ “ሞራ” ላይ በሽምግልና ደረጃ ዳኝነት የሚቀመጡት አካላት የመጀመሪያ ትውልድ የሆነ አያት ወይም በብሔረሰቡ አጠራር “ጫብሳ”፣ ተከታይ ትውልድ አባት ወይም በብሔረሰቡ አጠራር “ቃዋሻ” ቀጥሎ በኃላፊነት ላይ ያለው ወጣቱ ትውልድ /ልጅ/ በብሔረሰቡ አጠራር “ካይሎላ” በመጨረሻ ታዳጊው ወይም ቀጣይ ተረካቢ /እጬ/ ወይም በብሔረሰቡ አጠራር “ማቃይሳ” ሊኖር ይችላል ይላሉ ስለዚህ “ሞራ” ላይ

ማንኛውም እርቅ /ባህላዊ ዳኝነት/ ሲካሄድ እነዚህ አካላት ይገኛሉ፡፡ በዋናነት እና በአብዛኛው የመጀመሪያዎቹ 3ቱ /ሦስቱ/ ይገኛሉ፡፡

በመጀመሪያ ከተገኙት መካከል በዕድሜ አንጋፋ የሆኑት ሽማግሌ አያት /የትውልዱ መጀመሪያ/ ይሆናሉ፡፡ ስርዓቱን በቡራኬና በፀሎት ይጀምራሉ፡፡ “ፈጣሪ በሰላም አሳድሮ በሰላም አሰባስቦናል፡፡ በዚህ ስፍራ የመጣነው መልካም ነገር ለመፍጠር ነው ፈጣሪ መልካም መልካሙን ያናግረን፣ እንድንስማማ ይርዳን፣ ክፉ የሆነውን መንፈስ ከኛ ያርቀው ዕውነቱን ብቻ ያናግረን፣ ጠበኞችም ልቦና ይስጣችሁ፣ ቀናውን ተናገሩ በሰው ላይ አታስቀምጡ የሆነውን ብቻ፣ ያያችሁትን ተናገሩ፡፡ እኛ በዕድሜ ገፍተናል፤ በዕድሜያችን ብዙ አይተናል፡፡ ሞትም ቢመጣ ከኛ ይጀምር፣ ከኛ በላይ ያለው ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተ ተተኪ ናችሁና ሀቅን ተናገሩ ከኛም ተማሩ“ ይላሉ፡፡ እሳቸውን ተከትሎ በዕድሜ ቅደም ተከተል ሁለተኛ ትውልድ /አባት/ ከመጀመሪያው ተናጋሪ የተዘለለ፣ የቀረ፣ የሚጨመር ካለ ያክላል ቀጥሎ ኸሊታው ይናገራል፡፡

ይህ አሠራር የነበረ፣ አሁንም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል በሁሉም መንደር በ”ሞራ” የዳኝነት ስራ ላይ እንደ “ቀመር” የሚያገለግል ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ሽማግሌዎቹ ንግግራቸውን ሲደመድሙ ጠበኞች /ባለ ጉዳዮቹ/ ንግግራቸውን በየተራ አንዱ ሲናገር በማስጨረስ ጣልቃ ባለመግባት እንዲናገሩ ቅድመ ስርዓት በማስቀመጥ የእርቅ ድርድሩን ያስጀምራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተጀመረው ድርድር /ዴኻ/ ተበዳይ በደሉን እንዲናገር ይደረጋል፡፡ እሱ ከጨረሰ በኋላ በዳይም በተመሳሳይ እንዲናገር እድል ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ተበዳይ ከበዳይ ንግግር በኋላ ያልተነሱ ነጥቦች አሊያም ያልታመኑ ሀሳቦች ካሉ በድጋሚ ማብራሪያ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በዳይም በተመሳሳይ እንዲናገር እድል ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረቡት ሀሳቦች በሙሉ የሚታመኑ ከሆኑ ሽማግሌዎች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ሀሳባችሁ አንድ ነው ስለዚህ እናንተ ምን ይሁን ትላላችሁ በማለት የተለያዩ ምሳሌዎችን፣ ከአሁን ቀደም የተከሰቱ ጉዳዮችን እያነሱ የተሰጡ ውሳኔዎችን እያጣቀሱ ያነሳሉ፡፡ ከዚያ የነሱን ሀሳብ ይዘው አንደኛው ከሌላኛው ምን እያነሱ እንደሆነ፣ ማን በማን ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ እንደሆነ አዝማሚያውን በምሳሌ እያዋዙ ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ጠበኞቹ ወደ ይቅር መባባሉ፣ ወደመካካሱ እንዲሄዱ ይገፋፋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ይቅር መባባሉ ካለ ዕርቁ በጠበኞች የጋራ ሀሳብ ይደመደማል፡፡ ሲደመደም ለሽማግሌዎች ደረቅ እህል /ማሽላ/ ይቀርባል፡፡ ሽማግሌዎቹም ማሽላውን

በጥርሳቸው ይፈነክቱና ይተፋሉ። ይህ ከሌለም “ጨቃ” የብሔረሰቡን ባህላዊ መጠጥ ጠጥተው ይተፋሉ። ይህ የእርቅ ማፅኛ ነው። ምሳሌነቱም በእርቁ ላይ ከኛ ጋር ያልሆነ እኛ የማናየው የታላላቅ አባቶች ሙት መንፈስ አለ። እሱም ሳይቀር ይቅር ማለቱን ማሳያ ምልክት ነው። በዕርቅ አፈጻጸም ወቅት የዕርቅ ማጽኛ እህል መቅመስና መትፋት የሚኖረው የዕርቅ ድርድሩ በቤት፣ በቅጥር ግቢ ውስጥ ሲሆን ነው። በሞራ-ከንታም ሆነ በሞራ-ፓሌታ ደረጃ አይሆንም፡፡ በዚህ መልኩ ሰርዓቱ በመደምደሙ ጠበኞች ለ”ኾራታ” ካስያዙት ገንዘብ አንድ አንድ ብር ብቻ እንደ ደንብ ለምርቃት ማከናወኛ ይነሳለትና ገንዘባቸው ይመለስላቸዋል። ከዚህ ባሻገር ሽማግሌዎች አደራድረው በምርቃት ላስታረቁበት ጠበኞች በራሳቸው ፍላጐት ያሰቡትንና የፈቀዱትን የ”ጨቃ” መጠጥ መጠጫ ሊሆን ይችላል መስጠት ይችላሉ። በአጠቃላይ ይህ የግጭት አፈታት ስርዓት ያለቅጣት በይቅርታ የተደመደመ በመሆኑ ስርዓቱ ዴኻ-ዴባይታ እንደሚባል ከላይ ተገልጿል።

### 4.5.2.2. የከባድ ግጭቶች አፈታት ሂደት

በፓሌታ ደረጃ ከባድ ግጭት ሆነው የሚፈረጁት የአካል ጉዳት ያለበት ድብደባ/ማቁሰልና ደም መፍሰስ/ እንዲሁም ደም ብሎ መጠራቱ፣ ሴት ልጅን መድፈር፣ ማባለግ፣ ቤት ማቃጠል፣ የመሬት ግጭት፣ ስርቆትና በሀሰት መመስከር /መዋሸት/፣ የእርሻ ድንበር መግፋት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው ከላይ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ ደረጃ ከባድ ግጭቶች እጅግ ቢበዛ እስከ 3 /ሦስት/ ሳምንት ባለ ጊዜ ውስጥ ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ። ከባድ ግጭቶች እንደወንጀል ስለሚቆጠሩ በአፈታት ሂደታቸው “ኾራታ” አይያዝበትም፣ ድርድር አያስፈልገውም። ለአብነት ድብደባ፣ ድብደባው/ማቁሰልና ደም ማፍሰስ ካለበት/ አሊያም ደም ብሎ ቃሉን መጥራት በብሔረሰቡ ከባድ ወንጀል ነው። በእነዚህ ወንጀሎች ሳቢያ መጥፎ መናፍስት በአካባቢው በመግባት ወረርሽኝ ያስከትላል፣ ይህ ደግሞ ለብዙ ሰዎች ግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡ የዝናብ መጥፋትን፣ የሰላም መናጋትን፣ ረሀብና ጦርነትን ያስከትላል ተብሎ በባህል ስለሚታመን እንደወንጀል ይታያሉ። ከዚህም አልፎ ተርፎ ደም ፈሰሰም አልፈሰሰም ደም ብሎ መጥራቱም አካባቢው እንደረከሰ፣ ሁለተኛ ዝናብ የማይዘንብበት፣ ሰላም የማይገኝበት፣ ሞት የሚነግስበት ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ህብረተሰቡ ጉዳዩን ይዞ ሁኔታዎቹ በተከሰቱበት ወይም ከመንደር ውጭ ያጣራሉ።

*‹‹የሰው ልጅ የተሰራውም ሆነ የተፈጠረው ከተከበረው ደም ነው፤ ስለዚህ ቃሉ በከንቱ መጠራት የለበትም በሚል እንደወንጀል ይቆጠራል››* (ዲኖቴ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 27) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ከዚያም ወንጀለኛ ወይም አጥፊ ሆኖ የተገኘው ሰው ለዓመት ያህል ከሚኖርበት ቀዬ እንዲሰደድ ይደረጋል፡፡ ደም አፍሳሹ ከቀዬው እንዲሰደድ ሲወሰን የመንደሩ ዳውራዎች /መንፈሳዊ አባቶች/ ደም ለፈሰሰበት ቦታ የሚገባውን በማህበረሰቡ ተባባሪነት የሚቀርብ በግ ወይም ፍየል እንዳስፈላጊነቱ አርደው ደሙን ረጭተው አካባቢውን ያነጻሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት በቦታው ደም ሲፈስ አካባቢው ረክሷል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የረከሰውን ቦታ ደም በማፍሰስ መንጻት አለበት ይላሉ፡፡ አለበለዚያ በዚህ ምክንያት ዝናብ ይጠፋል፣ ወረርሽኝ ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡ የታረደውን በግ /ፍየል/ ስጋ ደግሞ የተወሰነውን ከየብልቱ ትንሽ ትንሽ ቆርጠው ይጥሉና (ይህን ማድረጋቸው በአካባቢው ዙሪያውን ያለ መንፈስም ከእኛ ጋር ይቋደስ  ማለት ነው) የቀረውን ግን ከመንደር ውጭ የሚመለከታቸው ባህላዊ ቦታዎች ላይ የነበሩ ሰዎች በሙሉ በጋራ ጠብሰው ይበላሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ የተሰደደው ሰው በአጋጣሚ ዘመዶቹን እንኳ ቢያገኝ ሰላምታ አይሰጥም፣ የመንደሩንም ሰዎች አያናግርም፣ አያያቸውም፣ ከእጃቻቸው አይቀምስም፣ አይበላም ይህ ወንጀል ከባድ በመሆኑ በሽምግልና ድርድር አይካሄድበትም፣ አይታይም፡፡ አጥፊው የቅጣት ጊዜውን ጨርሶ ወደመንደሩ ሲመለስ የፓሌታው ኼላ /የወጣት ትውልድ ቡድኑ/ አባላት በፓሌታው መግቢያ በር ላይ እሳት አንድደው ረመጡን ረግጦ ወደ መንደሩ እንዲገባ ያደርጉታል፡፡ እሳት ተምሳሌትነቱ እርኩስ መንፈስ ሁሉ ይውጣ፣ ተራግፎ ይግባ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሲገባ ወይንም ሲመለስ በወቅቱ የነበረው ኼላ /የትውልዱ ቡድን/ ጋሻና ጦር ይዞ ይቀበለዋል፡፡ ጋሻና ጦር ከለላ መሆኑን ያሳያል፣ ከለላህና መከታህ ነን፡፡ ጊዜህን ጨርሰህ ወደ ህብረተሰቡ ተመልሰሀልና እንኳን በሰላም መጣህ ማለት ነው፡፡

ከዚያ ይህን ሰው ወደዋና ሞራ በማስገባት አብረው "ኾራ" የተባለውን ባህላዊ ጨዋታ በጋራ እየዘፈኑ ይጨፍራሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚከናወነው ጠዋት ማለዳ ላይ ነው፡፡ ከዚያም ይህ ሰው ወደቤተሰቦቹና ዘመዶቹ ሄዶ ይቀላቀላል፡፡ በዚህ ጊዜ ቅጣቶቻቸውን ጨርሰው የሚገቡ የሳምንት፣ የወራት ጊዜ ቆይታ ያላቸው ሌሎችም ወንጀለኞች ሊኖሩ ስለሚችሉ ስርዓቱ በጋራ ይፈፀማል፡፡ ይህን አስመልክቶ በቡድን ውይይት ወቅት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በኮንሶ በአዲስ አመት መጀመሪያ ወር ጥር ወንጀለኞች መግባታቸው

ወሩ እህል የሚገባበትና እህል የሚሰበሰብበት በመሆኑ በአዲስ መንፈስ እንደገቡና እንደተመለሱ ስለሚታሰብ ይህ ወር የተለየ ሆኖ ይታሰባል ፤ ይሁንና ይህ ማለት ሁልጊዜ ወንጀለኞች የሚወጡትና የሚመለሱት በጥር ነው ማለት አይደለም። እንደአብነት አንድ ወንጀለኛ በጥር ወጥቶ ለመጪው ዓመት ጥር በዓመቱ ሲመለስ በዚህ መሀል የተፈጠሩ ወንጀለኞች በሳምንታቸውም ይሁን በወር አመት ሞልቶት ከሚመለሰው ሰው ጋር አብረው ይመለሳሉ ይህም አጋጣሚ ነው። በዚህ ጊዜ መመለሳቸው ግን ከአዲስ አመት ጋር ተያይዞ እንደተለየ ወቅት የሚታይ መሆኑን ከቡድን ውይይቱ መረዳት ተችሏል።

የነዚህ ሰዎች የመመለሻ ጊዜያቸው ከሳምንት በፊት በጥሩምባ በይፋ ለማህበረሰቡ ይገለጻል። ማህበረሰቡም ያ ቀን የ"ኾራ" ባህላዊ ጨዋታ ቀን መሆኑን ስለሚያውቁ "ጨቃ" የብሔረሰቡን ባህላዊ መጠጥ አዘጋጅተው ይጠብቃሉ። ዘመድ አዝማድ ከተለያየ መንደር መጥቶ ስነ-ስርዓቱን ይከታተላል "ይጨፍራል" ጨቃ ይጠጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቀኑን ሙሉ በመዋል ስርዓቱ በዚያው ቀን ይጠናቀቃል። ሰዎቹም ወደነበሩበት ሕይወት ወይም ማህበረሰብ ገብተው ኑሮአቸውን እንደቀድሞው ይቀጥላሉ ሲሉ (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 12፤ ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ካምብሮና ሳጎያ፣ በደንገልቱ፣ 30፣ 34፣ 39፣ 48) ይገልጻሉ።

ሴት ልጅን መድፈር በተመለከተ በድሮ ጊዜ ከ100 ዓመት በፊት በብሔረሰቡ ከባድ ወንጀል ሆኖ ጥብቅ ቅጣት ይጣልበት የነበረ፣ ዛሬም ድረስ ከባድ ወንጀል ተብሎ የሚጠራ ነው። ይህ ወንጀል ብዙ ጊዜ የሚከሠተው ሴት ልጅ ብቻዋን ስትሄድ ከተገኘች፣ ወይም በአንድ አካባቢ ብቸኛ ሆና ስትዘዋወርና ሲከታተል በቆየ ግለሰብ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ የሚከሠት ነው። ይህም ቢሆን ፎራ በሚባሉ ገጠራማ ቦታዎች/የከብቶች መጠበቂያ ስፍራዎች አካባቢ/፣ ራቅ ያሉ ማሳዎች ላይ፤ እንዲሁም ኮንሶ ካራት ከተማ ውስጥ አልፎ አልፎ ይከሠታል። ይህ ዓይነቱ ወንጀል ብዙ ጊዜ የሚታየው ወንጀሉ እንደተከሰተ ሲሆን፣ በዳይ ወንጀሉን እንደፈፀመ ወዲያው በሕዝብ ትብብር በቁጥጥር ስር እንዲውል ይደረጋል። በኮንሶ ማህበረሰቡ ወንጀለኛን በማጋለጥ፣ አውጥቶ በመስጠት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ሕዝቡ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን በማጋለጥ ዙሪያ ፍፁም ተባባሪ ነው። ትብብሩ ከራስ ቤተሰብ ይጀምራል፣ የራስን ልጅም ቢሆን አጋልጦ እስከመስጠት ይደርሳል። ምክንያቱም ይላሉ ለአካባቢው፣ ለሕዝቡ የማይበጅ ለቤተሰብ ደህንነትም አደጋ ነው ይላሉ ይህን በተመለከተ በቡድን ውይይት ወቅት የተገኘው መረጃም የማህበረሰቡን ተባባሪነት ይበልጥ

የሚያጠናክርና የሁሉም አባላት አስተያየት እንደሆነ ማረጋገጥ የተቻለበት ነው፡፡ በተጨማሪም የቡድኑ አባላት ወንጀል ብዙ ዓይነት እንደሆነ ገልጸው እንደ ስርቆት መፈጸም፣ ሴትን ማባለግ ድብደባ ወዘተ ይሉና በብሔረሰቡ ይህን ወንጀል ፈጽሞ ከማህበረሰቡ ፈጽሞ መሸሽግም ሆነ መሠወር አይቻልም ይላሉ፡፡ በኮንሶ ማህበረሰቡ ወንጀልን አይወድም፡፡ ጥፋትን አይደግፍም፡፡ የአንድ ግለሰብ ጥፋተኛ መሆን ለአካባቢው ደህነነት መጥፎ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ወንጀለኞች አይወደዱም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ተደጋጋሚ ወንጀል በተለይ የሚታዩ ወንጀሎችን ለአብነት እንደስርቆት፣ ሕዝብ ነክ ወንጀሎችን/የሰውን ንብረት ማበላሸት፣ ባህልን ማጉደፍ፣ የባህል መሪዎችን አለማክበር፣ እህል መስበር ወዘተ ፈፅመው ሲገኙ የአካባቢው ማህበረሰብ ወንዱም ሴቱም ወንጀለኞችን በማጋለጥ በሞራ ላይ እንዲዳኙ ያደርጓቸዋል፡፡ በዳኝነቱ ጊዜ የሚገኙት ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶችም፣ ወንዶችም ይሆናሉ፡፡ ወንጀለኛውም በዋናው ሞራ/ሞራ-ፓሌታ/ላይ ኦላ ሂታ ስር እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ኦላ ሂታ ስር መቀመጡ ሁሉም እንዲያየው እንደመቀጣጫ ጭምር ነው፡፡ የወንጀል ድርጊት ዋነኛው ተጠቂ ህብረተሰቡ በመሆኑ ተጠርጣሪው በፍርድ ሂደት ወንጀሉን መፈጸሙ ሲረጋገጥ ወንጀሉ ሕዝብ ነክ በመሆኑ ሁሉም በግልጽ እንዲመለከተው በሚያስችል ቦታ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ላይ ሴቶች መገኘታቸውም ጉዳዩ ወንጀልና ሕዝብ ነክ በመሆኑ ነው፡፡ ወንጀለኛው በዚህ መልክ ከተቀመጠ በኋላ ወንጀሉን ሲፈጽም የተመለከቱ ሁሉ ወንድ፣ ሴት፣ ዘመድ ወዳጅ ሳይቀር እንዲመሰክሩበት፣ እንዲዘረዘሩበት ይደረጋል፡፡ ለመካድ እንኳ ቢሞክር ግርፋት ይከተለዋል፡፡ በማህበረሰቡ መጋለጡ ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆንና ሌላውም ወንጀል ሰርቶ መሸሽግ እንደማይችል እንዲማርበትም ጭምር ነው በማለት የቡድኑ አባላት በውይይቱ ወቅት አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዱ ወንጀሉን በፈፀመ ሙሉ ፓሌታው ስለሚሰደብ ለመንደራቸው /ለፓሌታቸው/ ክብር ሲሉ ያጋልጣሉ፣ ሌላው በተለይ ኼላው /የወጣት ትውልድ ቡድን አባላት/በኛ የኃላፊነት ዘመን ይህ መከሰቱ ኃላፊነት ያስረከበን ማህበረሰብ ምን ይለናል አትጠብቁም፣ ወንጀለኞችን አትከታተሉም፤ አታዩም እንባላለን ስለሚሉ ያጋልጣሉ፡፡ ተገቢውን ርምጃም ይወስዳሉ፡፡ በሕዝቡም ያስወስዳሉ በማለት በቡድን ውይይት ወቅት አባላት ሀሳባቸውን አጠናክረው የገለጹበት ነው (በደንገልቱ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

እንደአባባልም "ከፊታ ሆራ ቃራ ዳኒማ ቃራ ኤኒንጃን" ይላሉ። ይህ ማለት ‹‹ወንድምን በገንዘብ እንጂ በማዳላት አይረዱትም›› እንደማለት ነው። ወንድም ሆነ እህት በስራው መጋለጥ አለበት ይላሉ፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ ሴት ልጅን ደፍሮ የተገኘ በሕዝብ ትብብር ይያዛል፤ እንደተያዘም በቀበሌው ጊዜያዊ ማቆያ ቤት እንዲያድር ይደረግና በማግስቱ ሞራ ላይ በፓሌታው አመራር በፓሌታው ባሉ የመንግስት የፍትህ አካላት አማካኝነት እንዲቀርብ ይደረጋል። ከዚያም የአውጫጭኝ ስርዓትና መረጃ የማጠናከር ስራዎች በጋራ ይሠራሉ። በመጨረሻም በባህላዊ መዋቅሩና በቀበሌው የመንግስት አካላት በሸኚ ደበዳቤና የድጋፍ መረጃ አማካኝነት ለወረዳው የፍትህ አካላት ይተላለፋል። ከዚያም የሰው ምስክሮች ይዘጋጅና የፍርድ ሂደቱ ይቀጥላል፡፡ በህጉ መሠረት ፍ/ቤት ውሳኔ ይሠጣል። ቀደም ሲል ግን ከ100 ዓመት በፊት ይሠራበት የነበረ ዛሬም እንደ ማስተማሪያ የሚጠቀሙበት ስርዓት እንደሚያሳየው በሚል እንደቡድን አባላቱ ገለጻ ከሆነ በጊዜው ሴት ልጅ አስገድዶ የደፈረ ከተረጋገጠበት ያለድርድር በቁሙ ከአንገቱ በታች ይቀበራል፡፡ በቅሎና ፈረስ ጋላቢዎች እንዲጋልቡበት ይደረጋል። በድንጋይም ይወገራል።ይሁንና ‹‹አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ወንጀል የፈጸመ በማህበረሰቡ ትብብር ተይዞ ለመደበኛው ፍ/ቤት ይቀርባል እዚያም የፍርድ ውሳኔውን እንዲያገኝ ይደረጋል ከዚያ ወንጀለኛ በመሆኑ ወደመንደሩ አይመለስም ስርዓቱ በዚህ መልኩ ተለውጧል›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 8-9፤ ኪሮስ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 35-36) ሲሉ ይገልጻሉ።

ሴቶችን ማባለግ በተመለከተ ብዙም በአካባቢው የተለመደ ባይሆንም አልፎ አልፎ ሴቶች በልዩ ልዩ ምክንያት መውለድ ሳይችሉ ሲቀሩና ወንዶቹ ልጅ መውለድ ሲፈልጉ፤ እንዲሁም ወንዶቹ በአንዳንድ አጋጣሚ ሚስቶቻቸውን ጥለው ሌላ ቦታ በስራም በሌላም አጋጣሚ ሲሄዱ ከሌሎች ወንዶች ጋር በመቀራረብና በመላመድ ይከሠታል። ይህ ወንጀል በፓሌታው የጉሳ አባላት በሽምግልና የሚታይ ሲሆን፣ የአፈታት ሂደቱ በመጀመሪያ አግባብ ያላቸው የፓሌታ ሽማግሌዎች ይመረጣሉ። ቁጥሩ እንደሁኔታው ሁለትና ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል። ይህም ጉዳይ ያልተለመደና እንደወንጀል ስለሚቆጠር "ኾራታ" አይያዝም። እነዚህ ሽማግሌዎች የድርጊቱን ሁኔታ ያረጋግጡና ትክክል ከሆነ ለቀድሞ ባል "ማሳ" ወይም የሞራል ካሳ ክፍያ ...የመጀመሪያ ባሏ ለቤተሰቦቿ ከከፈለው ጥሎሽ አስር እጅ እንዲከፍል ይደረጋል ሴትየዋንም አግብቶ ይወስዳል ይህ ወጪ አሁን ባለው ሁኔታ እስከ 8 ሺህ ብር እና በላይ ደርሷል ማሳ ይከፈላል አነሰ ቢባል 4 ሺህ ብር ይከፍላል ድሮ

ግን ከ 400-800 ብር ይከፈል እንደነበር ይገልጻሉ (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 13፤ ዲኖቴ ኮጫኔ፣ ቡርቁዳ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 46)፡፡ በዚህ ሁኔታ አጥፊው "ማሳ" ወይም የሞራል ካሳ ክፍያ ሲጠየቅ የጉሳ አባላቱ ጉሳውን ጨመረ በሚል ወጪውን ይጋሩታል፡፡ ደስተኛም ይሆናል፡፡ ስርዓቱም በዚሁ ይደመደማል፡፡

ይሁንና የመጀመሪያ ባል ምንም እንኳ ሚስቱ ብትጠፋም ወይም ብትባልግም ሚስቴን እፈልጋለሁ ካለና አስቀጥቶም ቢሆን ከፈለጋት እሷም ምህረት እንደሚያደርግላትና እንደማይበቀላት ካመነች በባህሉ መሠረት በመጀመሪያ ባሏ አማካኝነት በፖቃላ ሙግላ/በጉሳ መሪው ምክትል/ ቤት ቀርባ "ላጋንዳ" እና "ዳሃንታ" /ቅጠል እና ድፍን የደረቀ ቅል/ ቀርቦ ቅሉን በመሰንጠቅ እንደከበት /በግ/ በማድረግ ከውስጥ ያለውን ፍሬና የተለያዩ ነገሮች አውጥቶ ከ"ቁርበታ" /በማለዳ የተቀዳ ቅዱስ የምንጭ ውኃ/ ጋር ይደባለቅና ይረጭባታል፡፡ ይህ የመረጨቱ ተምሳሌትነት እንደንሰሀ መንፃትን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በኋላ ታደሰች ማለት ነው፡፡ ባሏም አይጠረጥራትም፡፡ እሷም ከጥፋቷ ተማረች በሚል ሰርዓቱ ይደመደማል፡፡

ይህ ስርዓት ከተደረገ በኋላ "ፖቃቃ" የሚባል የቃልኪዳን ስነ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ ይህ ስርዓት ባልም ሚስቱን እንደማይበቀል፣ ሚስትም ባሏ ላይ ከእንግዲህ ክፉ ነገር እንደማትሰራ ቃል ማስገቢያ ነው፡፡ የስርዓቱ አፈጻጸም "ቁርበታ" ወይም ቅዱስ ውኃ እየቀመሱ ሶስት ጊዜ ወደመሬት መትፋት ሲሆን፣ የሦስት ቁጥር ተምሳሌትነት ከትዳር ህይወት፣ ከሦስት ጉልቻ ጋር ይያያዛል፣ እንደገና ማር፣ ጤፍ እና ጨቃ /ባህላዊ መጠጥ/ አንድ ላይ ቀላቅሎ ሦስት ጊዜ መዋጥ ነው፡፡ እንደዚህ መደረጉም እህል ውሃችሁ ትዳራችሁ ይስመር፣ እንደ ቃል ኪዳን የሚወሰድ ነው፡፡

እነዚህ  አቀራረባቸው አዲስ በደረቀ ቅል ለሁለት ተሰንጥቆ በአንዱ ቅዱስ ውኃ፣ በአንደኛው ደግሞ እንደተጠቀሰው የተደባለቀ ማር፣ ጤፍና ጨቃ ቅደም ተከተሉም ቅዱስ ውኃ፣ ከዚያኛው ወደ ውስጥ የሚዋጠው ማር ጤፍና ጨቃ ናቸው፡፡ ከዚያ ባልና ሚስቶቹ ከላይ የተጠቀሰውን ስርዓት ፈጽመው ተሳስመውና ተጨባብጠው ሰርዓቱ ይደመደማል፡፡ ሌላው በብሔረሰቡ ከፍተኛ ወንጀል ሆኖ የሚታየው የመሬት ግጭት ነው፡፡

የመሬት ግጭት በግለሰብ፣ በፓሌታ በቡድን ደረጃ /መንደር ከመንደር/ ይከሰታል፡፡ የግጭቶቹ መንስኤ የድንበር መገፋት፣ የእርሻ መሬት ለ3ተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት

አለዚያም መካድ፣ የሰው የግጦሽ መሬት አላግባብ መጠቀም ወዘተ ሲሆን፣ በዚህ መነሻነት የሚከሰቱ ግጭቶች በፓሌታው አፓ-ቲንባ ቤት ወይንም ደጃፍ ከዚያ ካለፈና ጠንከር ካለ በሞራ /ሞራ-ፓሌታ/ ላይ ይታያል፡፡ ይህንን ግጭት የሚያዩት ቂሞታ-ፓሌታ፣ ኸሊታ-ፓሌታ /ኬለታዎች/፣ ሰንቀሊታ፣ አፓ-ቲንባ /የየኼላ ተወካዮችን ወደ ኂላ በሕይወት ያሉትን በመያዝ/፣ ፖቃላ ሙግላ /ቱራይታ ካፋ/ና ሳራዎች የሚሳተፉበት ሲሆን፣ የአፈታት ሂደቱ ወንጀል በመሆኑ "ኾራታ" አይኖርም፣ አይያዝም፡፡

በ3 /ሦስት/ ሽማግሌዎች በእድሜ ቅደም ተከተል በቡራኬና በፀሎት ይጀመራል፡፡ ከዚያም ከሳሽና ተከሳሽ/በዳይና ተበዳይ/ የመናገር ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ በችሎቱ የተገኙ አካላት ዋና ተግባርም ጉዳዩን በጥሞና መከታተል ይሆናል፡፡ ጊዜውን በተመለከተ ወቅቱ የዝናብ ወቅት ከሆነ በአካባቢው የዝናብ ወቅቶች ሁለት ሲሆኑ፣ የመጀመሪያው ከየካቲት ግማሽ እስከ ሚያዝያ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከነሐሴ እስከጥቅምት አጋማሽ ያለው ነው፡፡ በነዚህ ጊዜያት የእርሻ መሬት ጉዳይ ፈፅሞ አይታይም፡፡ ነገር ግን ከእርሻ ነክ፣ ድንበር ነክ ጉዳዮች የተለየ ከሆነ ይታያሉ፡፡

የእርሻ መሬትም ቢሆን ቦታው (ድንበሩ) ላይ አይኬድም እንጂ ጉዳዩ ታይቶ እስኪወሰን ድረስ ጠበኞች እንዳይደርሱበት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ በከንታ፣ በፓሌታም ሆነ በፖቅላ ደረጃ በዚህ መልክ ያሉ ጉዳዮች ከዝናብ ወቅቶች ውጭ ባሉት ጊዜያት ለማስረጃነት ቦታው ድረስ በመሄድ አጣርቶ ድንበሩን የማስከበርና የመሬት ይዞታን የመከለል ስራ ይሰራሉ፡፡ አስፈላጊው ውሳኔም በስፍራው ይሰጣል፡፡ በቦታው ውሳኔ የማይቀበል አካል ካለ ወደላከው ወደ አፓ-ቲንባው ቤት ተወካዩ ይመለስና የደረሰበትን ሪፖርት ያቀርባል፡፡ በቀረበው ሪፖርት መሠረት አፓ-ቲንባው ጽኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውን የማይቀበል ካለ ወደ "መሀላ" ይሄዳሉ፡፡ መሀላውም እዚያው ድንበር የተገፋበት ቦታ ላይ ሲሆን፣ ይሄ የኔ ነው በማለት መሬቱን ይመታሉ ወይንም አፈሩን ዘግነው ይበትናሉ፡፡

ይህን የማድረጋቸው ተምሳሌትነት ድንበር አልገፋሁም፤ ገፍቼ ከሆነ እንደዚህ እንደአፈር ብን ያድርገኝ ማለት መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ ከዚያ በኂላ ሁለቱም ያንን ቦታ አይደርሱበትም፡፡ ከዚያ ሞት፣ ጉርፍ፣ መብረቅ፣ እሳት…ከተሚጋቾች በአንዱ ቤት ሲከሰት ሽማግሌዎች ጉዳዩን የሚከታተሉት ስለሚሆን አንዱ እንደተረታ ያውቃሉ፡፡አስጠርተው ቅጣትና የካደውን ወደ ቦታው እንዲመልስ ተደርጎ የስርዓቱ ፍፃሜ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ በንብረት መካካድ ከሆነም በመሀላ ሞራው መሀላ ፈጻሚዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል። መሀላ አስፈጻሚው ‹‹አፓ -ኻኻ››ው የሰላም ምልክት የሆነውን የሀንሳቢታ ቅጠል በመያዝ ይቀርባል። በሁለት እጆቹም መሀላ ፈጻሚዎቹን የመሀላ ድንጋይ ያስጨብጣል፤ ቀኝ እጆቹንም በእጆቻቸው ላይ በመጫን ንብረታችሁ አይበርክት፣ ልጆቻችሁ አይደጉ፣ ክፉ ነገር ይድረስባችሁ በማለት ይረግማል። መሀላ ፈጻሚዎቹም በተራቸው መሀላ አስፈጻሚው ያለውን በመድገም መሐላውን ይፈጽማሉ። በመጨረሻም መሀላ አስፈጻሚው ቃቃዋ (መብረቅ)፣ አቢታ(እሳት)፣ ቶታ(ሞት) ይምጣ ብሎ ትቷቸው ይሄዳል። መሀላ ፈጻሚዎቹም በተለያየ አቅጣጫ ይሄዳሉ። ከዚያን ቀን ጀምሮ መሀላ አስፈጻሚውና የአቅራቢያ ሰዎች መሀላ የገቡ ሰዎችን መሀላ መፈጸማቸውን ከሰሙ በኋላ ይከታተሏቸዋል። በአንዳቸውም ቤት እሳት ቢነሳ፣ ሰው ቢሞት…ይህ የተከሰተበት ግለሰብ ጥፋተኛ (የተረታ) መሆኑ ይታወቅና ወዲያው መሀላ አስፈጻሚው ተረቺውን ወደ መሀላ ሞራው አስጠርቶ ዋቃ ምልክቱን አሳይቷል፣ ጥፋትህን ተረድተህ ንብረቱን መልስ ይባላል። ዋቃ ይቅር ይበልህ በማለትም ቦታው ይታጠብ ይባልና አንድ ብር ተረቺው እንዲከፍል ይደረጋል። ሽማግሌዎችም ከባህላዊ መጠጥ ‹‹ጨቃ›› ቀምሰው በመትፋት ቦታው እንዲፀዳ ተደርጎ ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡ በመስክ ቆይታ ከጎሳ መሪው ካላ ገዛኸኝ ጋር ጋሞሌ ቀበሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በተደረገ ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው ብዙ ጊዜ በዚህ መልኩ የሚፈፀም መሀላ እንደሚደርስ የሚከተለውን አብነት በማንሳት ይገልጻሉ (ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 5-7)።

## አብነት አንድ

*"በ1991 ዓ.ም አካባቢ ነው አባቴ ካላ ወልደዳዊት በኃላፊነት ላይ በነበሩ ጊዜ በቱሮ አገልግሎት አካባቢ የተከሰተ ክስተት ነበር ይሄ ክስተት አንድ ሴት አባወራዋ እያሉ በግቢ ውስጥ ጓደኛቸው አብረው የሚበሉና የሚጠጡ ሌሊት አባወራው ወጣ ብሎ እዚያው እግቢው ውስጥ ተኝተው እያሉ ክራር በመምታት እየተጫወቱና እየጠጡ ሌሎች ሰዎችም ሳሉ አንድ እልፍኝ ቤት ውስጥ እሳት ሲጠፋ ያኛው ሰውዬ እሳት ስለጠፋ ጨለመና ወጣ ይላሉ ሲወጡ ጨኸቷን በመልቀቅ ደፈረኝ ብላ ትላለች ፤በዚህ የተነሳ በአካባቢው በፓሌታ ባሉ ሽማግሌዎች አፓ ቲንባዎች ዳውራዎችና በኬላ አማካኝነት የማጣራት ስራ ተካሄደ መተማመን አልቻሉም በኋላ ጉዳዩ ከከንታ አልፎ ወደፓሌታ ደረሰ፣ ከፓሌታም አልፎ በአካባቢው የቱሮ አገልግሎት ገላቦ ሌሀይቴ አርፋይዴና ተሸመሌ ቀበሌዎችን የያዘ አካባቢ ከአራዮ ወንዝ መልስ የሚባል አለ ይሄ እስከ ሌሀይቴ ቀበሌ ከብአይዴ ፓሌታ መንደር ጋር ያደርሰዋል እዚያ ክልል ውስጥ የሚታይ ነው እዚያም ሊዩተው ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው ወደ ጐሳ መሪው ካላ ከርቲታ ቤት ወደ መሀላ እንዲተላለፍ ይባልና ጉዳዩ በአባትና ከእርሱ ጋር ባሉ ሰዎች ከላይም ከሌሀይቴ ቀበሌ በአጠቃላይ ከአራዮ ወንዝ መልስ በተወከሉ ሽማግሌዎች አማካኝነት እንደገና እዚህ ጉዳዩን ሲመለከቱ ምንም ዓይነት መግባባትና መተማመን*

*ላይ ሳይደርሱ ሲቀሩ ከሦስት ወራት ቆይታ በኋላ መሀላው ተፈጽሚል፤ እዚህ ላይ መሀላው ለሦስት ወራት የቆየበት ምክንያት ሰዎቹ አስበው ሳለመማልና ወደ እውነታው ተመልሰው ወደመተማመን ይሄዳሉ በሚል ሀሳብ ነበር ነገር ግን አልተሳካም፤ በመጨረሻ ላይ እንዲምሉ ነው የተደረገው በባህሉ መሠረት እንግዲህ ከመሀላ በፊት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ ቅድመ ሁኔታዎቹ የሁለቱም ተሟጋች አካላት ዘመዶቻቸው፣ ጐሳዎቻቸው፣ የቅርብ ጓደኞቻቸው በሙሉ በመሀላው ማመን ይኖርባቸዋል መሀላው መደረግ አለበት ብለው መወሰን አለባቸው፤ ቤተሰቦቻቸውም ሊስማሙበት ይገባል ስለዚህ እንደገና ለዚህም የምክር ጊዜ ሦስት ሳምንት ያህል ተሰጥቷቸው እነሱም በትክክል አለማድረጋቸውን እንዲያጣሩ ተደርጐ እንዲታይ ተደርጓል እንዲያም ሆኖ እውነቱን ለመናገር የፈቀደ አልነበረም፤ በመጨረሻ ላይ የመሀላውን ስነስርዓት ለመፈፀም አሁንም ቅድመ ሁኔታዎች አሉ መቀጮ ይወሰናል፤ ስለዚህም ለቱሮ አገልግሎት አካባቢና ለቀበሌ ወይም ለፓሌታቸው አምስት መቶ አምስት መቶ ብር እንደሚከፍሉ ከዚህ ባሻገር መሀላ ማስቆሚያ ጊደር ከነቃጭሉ ባንገቷ ላይ ያስሩና ለምርቃት ሥርዓት ማከናወኛ የሚውል ከ 1.50 ጋር አብረው ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል የተረታ ሰው ይህንን ይዞ እንዲመጣ ይደረጋል፤ ጊደር ከነቃጭሉ በአንገቷ ማሰር ተምሳሌትነቱ ጊደር ያልወለደች በመሆኗ ችግር ያላየች በመሆኑ ሕይወትን እንዳዲስ እንዲኖሩ ለማመልከትና ለማሳየት ነው፤ ይህ ከተገለፀላቸው በኋላ መሀላ የመፈፀም ስነ ስርዓቱ ይከናወናል ይኸውም በብሔረሰቡ አጠራር ሬቃኻኻ ይባላል ባለ አንድ ፎቅ ጐጆ የመሀላ መፈፀሚያ ነው በዚህ ውስጥ ወንዱ በሴቷ እግር ላይ በመሻገር የሚፈጽመው የመሀላ ዓይነት ነው ይህ ስርዓት ሬቃ ኾርባይታ ይባላል አፈፃፀሙ ሴትየዋ ሬቃ-ኻኻ ውስጥ ገብታ ፊቷን ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በማዞር መሬት ላይ ተቀምጣ እግሯን በመዘርጋት ወንድየው ከደጃፉ ወደሬቃው ከሬቃው ወደ ውጭ ሦስቴ ይሻገራል ሦስቴ የመሻገሩ ተምሳሌትነት ከትዳር ህይወት ጋር ይያያዛል ከዚያ የእግሯን ጭን ነክቶ ነክቼሽ አላውቅም ደፍሬሽ አላውቅም አድርጌው ከሆነ ፈጣሪ ክፉውን ነገር ያምጣብኝ ብሎ በዋናው በር ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የጐሳ መሪው ካላ ትልቁና ዋናው በር በኩል እንዲወጣ በስርዓቱ መሠረት ተደረገ፤ ምዕራብ የጸሀይ መጥለቂያ በመሆኑ ሳይመሽ ያጋልጠኝ እንደማለት ነው፤ ሴትየዋ ደግሞ በምስራቅ በኩል ባለው የእህቶች በር በሚባለው እንድትወጣ ተደረገ ምስራቅ የጸሀይ መውጫ በመሆኑ ሀቁ ይውጣ እንደማለት ነው፤ ከዚህን ጊዜ በኋላ እንግዲህ አንዳች ነገር እስኪከሰት ድረስ አይገናኙም፤ በቅድሚያ ግን የተደረገው ነገር ገንዘብ ተበዳድረው ስለነበር ገንዘቡን እንዲመላለሱ ተደረገ፤ ደፈረ ተብሎ የተጠረጠረው ግለሰብ በዚያ በተጠረጠረበት ቤተሰብ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሀለኮ ሞሪንጋ ዛፍ ስላለው የዚያ ቤተሰብ ግቢ ባለቤት የዚያን የሀለኮ ሞሪንጋ ዛፍ ዋጋ እንዲከፍሉ ነው የተደረገው፤ ይህ የተደረገበት ምክንያት የሀለኮ የሞሪንጋ ቅጠል ረጋፊ ነው ድንገት ረግፎ በነሱ ምግብ ወይም እህል ውስጥ እንዳይገ በተሰጣ እህል ውስጥ ከገባ የሌላውን ንብረት እንደተጠቀሙ ስለሚታይ ከዚያ ጋር ተያይዞ ሌላ ነገር እንዳይታሰብ በማሰብ ነው፤ ይህ ከተደረገ በኋላ መሀላው ተፈፀመ፤ ነገር ግን እንደተመለሱ ተደፈርኩ ብላ ያለችው ሴትዮ በሳምንቱ አስወረዳት ይህን በዚያው አድበስብሰው ለማስቀረት እንደቻሉ የመጨረሻው ክስተት ሲከሰት እዚህ በውይይት ወቅት ለመግለጽ ችለው ነበር፤ በሁለተኛው ሳምንት ላም ጉድጓድ ውስጥ ገብታ ሞተችባቸው ይሄንንም አድበስብሰውት በሶስተኛው ጊዜ የባሏ አባት ይሞታሉ በዚህ ጊዜ ደፈረ የተባለው ግለሰብ ቤተሰብና ዘመዶች ይሄንንስ ምን ትሉታላችሁ ብለው ያዟቸው በዚህ ጊዜ እዚሁ ካላ ቤት አቀረቧቸው፤ እነዚያም በዚያው እንግዲህ መረታታችሁን ስታውቁ የደንቡን ያው 1.50 ሳንቲም ና ጊደር ቃጭል ባንገቷ አስራችሁ ይዛችሁ መምጣት አለባችሁ ተባሉ በዚህ መሠረት ይዘው መጡ አሳድረው በማለዳ ያው አመኑ የተከሰተውን ሁሉ ተናገሩ ሴትየዋ ይህን ያደረገችበትን ምክንያት ተጠየቀች ቀደም ሲል ባልሆነ*

*አጋጣሚ እንዳስቀጣቸውና ለመበቀል ያዘጋጁት ስልት እንደሆነ ተናገሩ ከዚያ በኋላ ይህንንም ቢሆን ወዲያው ያላመኑበት ምክንያት የተቀመጠ ውሳኔ ስላስፈራቸው እንደሆነ ምናልባትም እንደገና ውሸት ተናግረናልና በህብረተሰቡ መካከል ክብርም ላይኖረን ይችላል በሚልና ይህንኑ በመፍራት እስከ መጨረሻው የመጣው ይምጣ በሚልና እውነታው አይታወቅብንም የሚል ግምት እንደነበራቸው ገለፁ፤ በመጨረሻም በካላ ቤተሰብ ደረጃ ምክር ተሰጣቸው በዚህ የምክር ወቅት ሴትየዋ ወዲያው እንዳስወረዳት ቀጣዩን ማስቆም ይችሉ እንደነበረ ተገለፀላቸው መጀመሪያ እንዳስወረዳት ብታምኑ ኖሮ ላሟ ጉድጓድ ውስጥ ገብታ አትሞትም ነበር ከዚያም የባሏን አባት ማትረፍ ትችል እንደነበር ተገልፆላቸው ከእንግዲህ ከእንደዚህ ዓይነት ጥፋት እንዲቆጠቡ በሚል ምክር ተሰጣቸው፤ በመጨረሻም እህል አብረው እንዲበሉ ተደረገ በዚያውም የቅድመ ቅጣት ውሳኔ አምስት መቶ አምስት መቶ ብር ሊከፍሉ ቃል የገቡበትና በስማቸው የተጻፈና የፈረሙበት ደብዳቤ መኖሩ ተገለጸላቸው፤ በፊርማቸው መሰረት ያንን እዚያው ከፍለው ሽማግሌዎቹም የደንቡን 1.50 ልከው የተገባው ቃል በዚህ መልኩ ተከናውኗል። ይህ የ1.50 ገንዘብ ጉዳይ 1.00 ብሩ ለካላ ቤት ሽማግሌዎች ለምርቃት ሥርዓት ማከናወኛ የሚሰጥ ሲሆን 50 ሳንቲሙ ካላ ቤት ለጨው መግዣና የቡና ቅጠል ሻይ የሚዘጋጅበት ነው፤ መሀላዎች ሲፈፀሙ በዚህ መልኩ እውነቱ ይጣራል እዚህ ላይ ግን ይላሉ መረጃ አቀባዩ በሁለቱ መካከል ቀደም ሲል የቆየና ያልተፈታ ችግር ካለ ግዴታ ቅድሚያ የቆየው መፈታት አለበት፤ ምክንያቱም በየትኛው እውነታ እንደሚጀመር ፈጣሪም በየትኛውም ሁኔታ እንደሚጀምር ስለማይታወቅ ይላሉ፤ ስለዚህ የቀደመ ችግር ካለ መፈታት ይኖርበታል መሀላዎችም በጣም አልፎ አልፎ የሚፈፀሙ እንደመሆናቸው አንዳንድ ጉዳዮች ለመሀላ የሚገፉ ከሆነ ከመሀላ በፊት ለሰዎቹ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የማሰላሰያ ጊዜ ይሰጣቸውና አቋማቸው ያው ከሆነ ነው መሀላውን የሚፈፅሙት"።*

ስለዚህ ይህን መሰሉን ማንሳት እንደሚቻል በተመሳሳይ ዕለት ከመረጃ አቀባዩ ጋር በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት መረዳት ተችሏል።

በዚህ ደረጃ ሌላው ከባድ ግጭት ሆኖ የሚታየው ስርቆት ወይም ሌብነት ነው ። በብሔረሰቡ ስርቆት የተለመደ አይደለም፤ በጣም የተወገዘ ተግባር ነው፤ ስርቆት የሚፈጸመው የከብት፣ የፍየል፣ የበግ፣ የቀፎ ማር ወዘተ ነው። በዚህ የተነሳ የተፈጠረው ግጭት ብዙውን ጊዜ የሚፈታው በአውጫጭኝ እና በማጣራት ነው። የአውጫጭኝ ቦታው በሞራ ፓሌታ ውስጥ ሞራ ኪርባ በተባለው የጭፈራ ቦታ ነው፤ ይህ ቦታ የሚመረጠው ሰው በነፃነት ሀሳቡን ለመግለጽ የሚችልበት ሰፊ ቦታ አደባባይ ስለሆነ ነው።

የአፈታት ሂደቱ ተጠርጣሪዎች በኬላው በወጣት ትውልድ ቡድን አባላት አማካይነት የኬላው አባላት ይሰማራሉ፤ ተጠርጣሪዎችም ተይዘው ይቀርባሉ። ፍተሻም ይደረግባቸዋል አፓ ሊሻው የአለንጋው አባት ይቀርባል አለንጋውም ይቀርባል ግርፋት ከመጀመሩ በፊት ከስነ ልቡና አንፃር ብዙ የማውጣጣት ሥራ ያከናውናሉ። የሚያምኑ ከሆነ ለድርድሩ ወደ አፓ ቲንባው ቤት ይሄዳሉ ከዚያም ንብረቱን ለባለቤቱ የሚመልስበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ

የተሰረቀው ንብረት ሕይወት ያለው ከሆነና ስርቆቱ በሚጣራበት ወቅትም በሕይወት ካለ ከነነፍሱ እንዲመለስ የተሸጠ ወይንም የታረደ ከሆነ ደግሞ ግምቱ በእጥፍ እንዲከፈል ይወስናሉ ውሳኔው ባለው መዋቅር መሠረት ይከናወናል ከዚያም በኂላ የተሰረቀው እንዲመለስ ይደረጋል የፓሌታውን ስም ስላጠፉ እንዲያምኑ ይገደዳሉ፤ ወዳጅ ዘመዶቹም አስቀድመው ከግርፋቱ በፊት እንዲያምን ያደርጋሉ፤ ካመነ ቅጣቱን ብቻ ይፈጽማል ማሩኝ ብሎ ከለመነ ከተጸጸተም ቅጣቱ ሊቀልለት በግማሽም ሊቀነስለት ወይም እንደንብረቱ ሁኔታ ያለቅጣት በነጻ የሚለቀቅበትም ሁኔታ ይኖራል፤ ነገር ግን ተለምኖም፣ ተረጋግጦበትም፣ ተገርፎም እምቢተኛ ከሆነ ከፓሌታው ከመንደሩ ሙሉ በሙሉ እንዲባረር ይደረጋል። ስለ ሰውየው ሁኔታ መረጃው ለኮንሶ ፓሌታዎች ወይም መንደሮች ለባህላዊ መሪዎች ይበተናል፤ ማንም እንዳያስጠጋው ይደረጋል፤ ትልቅ ማዕቀብ ይጣልበታል።

ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ግለሰብ ሌብነቱ ተረጋግጦ አደባባይ ወጥቶ ከታወቀ በሰላሙም ጊዜ ሆነ በሌላ የቅርብ እህቶቹም ሆነ ወንድሞቹ ወይም ዘመዶቹ ሁሉ የሌባ ዘመድ እህት ወንድም እየተባሉ በአጋጣሚው ሁሉ ስለሚተቹ ስርቆት ወይም ሌብነት በብሔረሰቡ ትልቅ ወንጀልና እንደነውር የሚቆጠር ሕልውናን ዝቅ የሚያደርግ ተግባር መሆኑን ካላ ገዛኸኝና ዲኖቴ የተባሉት መረጃ አቀባዮች በካላ መኖሪያ የእንግዳ ማረፊያ በተደረገ የቃለመጠይቅ ወቅት የሚከተለውን አብነት በማንሳት ይገልጻሉ (ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 14፣ 27) ።

## አብነት

*"በድሮ ጊዜ በጣም አስቸጋሪና ልማደኛ ሌባ በየጊዜው እየተቀጣም የማይማርና የማያስተካክል ከሆነ በኬና አካባቢ ቱርካማናማ መካነ መቃብር በሚባለው ሸለቆ ውስጥ ተገፍትሮ ይጣልና እንዲሞት ይደረግ ነበር፤ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ጥቅጥቅ ያለ ደን አለ ባሁኑ ጊዜ ግን የለም ሬቃ ባለ አንድ ፎቅ ትልቅ ጒጆ እንደ ፓፍታ የወጣቶች ማደሪያ ቤት ያሉ ቤቶች አሉ አንድ ደረጃ ፎቅ ያላቸው እዚያ ውስጥ ተሸካሚው ላይ ተሸጋጋሪውን እንጨት በማንሳት ሕዝብ ተሰብስቦ እጁን እዚያ ውስጥ በማስገባትና እጁ ላይ በማስቀመጥ እዚያ ደን ውስጥ እየጮኸ እንዲሞት ይደረግ ነበር የሚል አፈ ታሪክ እንዳለ ይነገራል ። ይህ የዛሬ 500 ዓመት አብነት ነው። ከዚህ አንፃር ነው በኮንሶ ብዙም ሌብነት ያልተለመደ የሆነው ይላሉ ፤ቀደም ሲል የነበረው ቅጣት በአሁኑ ጊዜ ሰውን ማስተማሪያ ሆኗል ማለትም ይቻላል፤ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ቅጣት ነበር ስለሚባል ይላሉ፤ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በኮንሶ ወረዳ ካራት ከተማ ሁለት የገበያ ቀናት ሰኞና ሐሙስ የሚውልባቸው አሉ በነዚህ ቀናት ብዙ ገበያተኛ ነው የሚመጣው እናም በዚህ ቦታ እንደአጋጣሚ ኪስ ሲያወልቅ ወይም ሲሰርቅ የታየ ሰው በግልጽ ይመታል፤ አላፊ አግዳሚው ሁሉ ይመታዋል፤ በዚህ ጊዜ ፖሊስ ሊገላግል እንኳ ቢገባ አብሮ ይመታል፤ ይህ ሁሉ የሚያሳየው የኮንሶ ሕዝብ*

*የሌብነትን ተግባር ምን ያህል እንደሚጸየፍ በጉልህ ማሳያ ነው"* (ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 9፣ 28) ሲሉ ይገልጻሉ ።

በፓሌታ ደረጃ እንደ ከባድ ወንጀል የሚታየውና የሚጠቀሰው ሌላው ቤት ማቃጠል ነው። ቤት ማቃጠል የሚከሰተው በድንገት ወይም በአጋጣሚ በቸልተኝነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በኮንሶ ፓሌታ ምን ይደረጋል የኮንሶ ባህላዊ አምባ መንደሮች ወይንም ቤቶች እጅግ የተጠጋጉ በመሆናቸው በጋ ሲደርስ ‹‹በብሔረሰቡ አጠራር አፓ-ሰሌታ አዋጅ ነጋሪ የሚባል አለ ይህ ሰው በየሞራው ማታ ማታ እየዞረ ሰሌ ወይም አዋጅ አዳምጡ አሁን በጋ ነው ቦና ደርሷል እሳት ለመጫር በገል ልጅ አትላኩ ከጎረቤት እሳት በክብት ቀንድ ጫሩ በሚል ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይናገራል ለቅድመ ጥንቃቄ ያውጃል›› (ዲኖቴ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም፣ 30) ሲሉ ያስረዳሉ።

ማንኛውም ፓሌታ ወይንም መንደር ይህን ጥንቃቄ ያደርጋል። የእሳት አደጋ ሊከሰቱ የሚችሉት በጥንቃቄ ጉድለት ሲሆን ይህም በኮንሶ "አቢታ ቶላ ገላ ዳንዴ" ይባላል። ይህ ማለት ከቤተሰብ ያመለጠና ድንገት የተከሰተ ነው እንደማለት ነው። የኮንሶ ብሔረሰብ መንደሮቹ /ቤቶቹ/ የተሰሩት ከሳርና ከእንጨት ሲሆን፣ የቤቶቹ አሰራርም እጅግ የተቀራረቡና መኖርያውንም፣ መኝታውንም፣ መመገቢያውንም፣ ምግብ ማብሰያውንም ሁሉንም ባንድ ላይ የያዘ ሆኖ ነው። በአጋጣሚም ሆነ፤ ሆን ተብሎ የእሳት አደጋ ቢከሰት አንድ ቤት ብቻ ሳይሆን የሚቃጠለው መንደሩን በሙሉ ሊያጠፋ ይችላል።

በዚህም ምክንያት የኮንሶ መንደሮች ዙሪያቸውን በቅንጭብ የታጠሩ ናቸው። የእሳት አደጋ በመንደሩ ሲከሰት ማንም ሰው እቤት ውስጥ ያለውን ፈሳሽ ነገር የሚጠጣውን ውኃ ሆነ፣ ጨቃ ይዞ እሳቱን ለማጥፋት ይረባረባል። በይበልጥ ግን አቅም ያለው ማንኛውም የመንደሩ አባል ከሌላ መንደርም ቢሆን ቅንጭብ ቆርጦ ወደ እሳቱ ይመጣል። ቅንጭብ የሚመረጥበት ምክንያት እሳት በማጥፋት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው መሆኑን በዚያው የቃለመጠይቅ ወቅት ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ አቀባዮች አማካኝነት መረዳት ተችሏል።

በዚያ መንደር የተተከለን ቅንጭብ አላግባብ የቆረጠ፣ የሕዝብ ንብረት እንደቆረጠ ተቆጥሮ ቅጣት ይጠብቀዋል። በከንታ ደረጃ የፖርሺታ ዋና ተግባር ይህን መቆጣጠር ነው። የቆረጠውን አቅርቦ በከንታ ደረጃ ማስቀጣት፣ ከውስጥ የደረቁ ካሉም በጣም የደከሙና ጧሪ የሌላቸው አሮጊቶች ሰብረው እንዲጠቀሙ የማድረግና የመፍቀድ ስልጣን አለው።

በዚህ ደረጃ ይህ እንዳለ ሆኖ አንድ ሰው ሆን ብሎ ቤት ማቃጠል ብቻ ሳይሆን ቤትህን /ቤትሽን/ቤቴን/ በጥቅሉ ቤት አቃጥላለሁ ካለ ከባድ ቅጣት ይቀጣል። ይህ የወንጀል ሂደት በሞራ-ፓሌታ የሚታይ ሆኖ ጉዳዩን የሚመለከቱት ቂሞታ-ፓሌታ፣ ኸሊታ-ፓሌታ፣ ሰንቀሊታ፣ አፓ-ቲንባ፣ ሳራዎች፣ ዳውራውና ፖቃላ ሙግላ /ቱራይታ/ ናቸው። ጊዜውን በተመለከተ ማለዳ ጠዋት ከ12:00 ጀምሮ ከገበያ ቀናት ሰኞና ሀሙስ ውጪ ሲሆን ማለዳ የሚመረጥበት ዋና ምክንያት ማለዳ ፊትን ሳይታጠቡ እህል ሳይቀምሱና ቡና ሳይጠጡ የሚደረግ ዳኝነት በንፁህ ልቦና ላይ የተመሰረተ መደማመጥ ያለበት ይሆናል ከሚልና ከረፈደ ሁሉም ወደ የግል ስራው የሚሄድ በመሆኑ ጭምር መሆኑን በቃለመጠይቅ ወቅት ለመረዳት ተችሏል (ዲኖቴና ካምብሮ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 25፣ 39)። ስለዚህ አንድ ሰው ሆን ብሎ እሳት ለኩሶ ቤት ሲያቃጥል ከታየ በድሮ ጊዜ ከ50 እና 60 ዓመት በፊት ሰው ሁሉ በተሰበሰበበት እሳቱን ለማጥፋት እየተረባረበ ባለበት ሰዓት ወንጀለኛውን በብሔረሰቡ አጠራር በ‹‹ቃበሌታ›› ማለትም ባላ ባለው እንጨት ወንጀለኛውን ወደ እሳት ውስጥ በመግፋት እንዲቃጠል ይደረግ ነበር፡፡

ይሁንና ወንጀለኛው ሲያቃጥል ባይታይና ጥርጣሬው በትክክል በሱ ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ በማግስቱ የፓሌታው (መንደሩ) ሕዝብ በተሰበሰበበት፣ የፓሌታው የበላይ አመራሮች በተገኙበት፣ በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ቂታሳ›› የእድሜ ልክ ቅጣት እንዲቀጣ ይወሰናል። ይኸውም የቤተሰቡን የመኖሪያ ቤት ጉልቻ ያጋጫሉ። ጉልቻ ተምሳሌትነቱ ከኑሮና ከትዳር ሕይወት ጋር ይያያዛል።ጉልቻ ተጋጨ ማለት ደግሞ ሰው እዚያ ቦታ እህል አያበስልም። ማንም አይኖርም ማለት ነው። ሳር ቤቶቻቸውን በአፉ ይደፋሉ። በአፉ ይገለብጣሉ። መኖሪያ የነበረው፣ ኑሮ የተመሠረተበት ቤት ዳግም ሕይወት የለውም፤ ለመኖሪያም አይሆንም በማለት ይገለብጡና በአፉ ይደፉታል፡፡ ወንጀለኛውም ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ እዚያው እንዲቀበርና እንዲበሰብስ ያደርጋሉ። ይህን የሚያደርገው የተሰበሰበው ሕዝብ ነው። ይህ ከተፈፀመ በኋላ ወንጀለኛው ከነቤተሰቡ /እናት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ አያት፣ ከብት ወዘተ/ ይዞ ከመንደር እንዲወጣ ይደረጋል።

ቤተሰቡ በዚህ መልኩ ሲወጡ ሕዝቡ ቅንጭብ በመያዝ መንደሩ ዋና መግቢያና መውጫ ድረስ አጅበው ይወስዷቸዋል፡፡ መንደሩን ሲወጡ ቅንጭቡን መሬት ይመታሉ። ቅንጭብ እሳትን ማጥፋት የሚችል ኃይል ያለው ተክል ነው፤ መሬት በቅንጭብ መምታታቸው ‹ርግማን› ነው። አይመልስህ አጥፍተሃልና ያጥፋህ ማለት ነው። ከዚያ ‹ኡ› ብለው ድምፅ

ያሰማሉ። ‹ኡ› ማለታቸው ጩኸቱ ‹ውግዘት› ነው። አይመልስህ ማለት ነው። የአንድ ነገር ወይም በሕብረት የተሰራ ነገር ፍፃሜን የማብሰሪያ ምልክት ነው። ሕዝቡም በዚህ ሁኔታ ወንጀለኛውን ካስወጣ በኋላ ወደ መንደሩ ይመለሳል። ወንጀለኛውና ቤተሰቡ እንዲሁ እንደተያያዙ ወደኋላቸው ሳይመለከቱ ወደፊት ብቻ በመሄድ ከመንደሩ ይወጣሉ። እድሜ ልካቸውንም አይመለሱም። የልጅ ልጅ እንኳ ተመልሶ መጥቶ በቦታው አይኖርበትም። ይህ ቅጣት ኢህአዴግ እስከገባበት እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ተፈፃሚ ነበር ኢህአዴግ ከገባ ወዲህ የኢሰፓ አባላት በተለይ የቀበሌ አመራር የነበሩ ከላይ እንደተጠቀሰው ወንጀሉን የፈጸሙ ግለሰቦች ከቀበሌያቸው በቅንጭብ ተባረው በሌላ ቀበሌ የሚኖሩ አሁንም እንዳሉ ከጎሳ መሪው ካላ ገዛኸኝና ዲኖቴ ጋር በካላ ገዛኸኝ መኖሪያ የእንግዳ ማረፊያ በተደረገ የቃለመጠይቅ ወቅት ግንዛቤ ተወስዷል (ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 15፣ 29)።

አብዛኞቹ በሕይወት አሉ ይህ ቅጣት /የዳኝነት ሥርዓት/ በዚህ መልኩ መፈፀሙ የቀረው ኢህአዴግ ከገባ በአካባቢው ነዋሪ የብሔረሰቡ አባላት በሆኑና በኢሰፓ አባላት ላይ ሆኖ ከዓመት በኋላ ማለት ይቻላል። አሁን ባለው ሁኔታ ይህን መሰሉ ድርጊት እንደተከሰተ ወንጀለኛውን በመያዝ ለመደበኛ የፍትህ አካላት የመንደሩ ነዋሪ የማቅረብና መረጃ በማጠናከር በዚያ ውሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል። ከዚያ ቅጣቱን በፍ/ቤት ከተቀበለ በኋላ ወደነበረበት መንደር አይመለስም። ምክንያቱም ቤት በማቃጠሉ የሕዝብ ጠላት ነው ተብሎ ስለሚገለል ተመልሶ ወደ መንደሩ አይሄድም። የመንደሩ ነዋሪ ቢያገኘው እንኳ አብሮ አይበላም። አብሮ አይጠጣም።

በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ቀደም ሲል የነበረው ቅጣት ከባድ መሆኑ ባሉ ሕዝባዊ መድረኮች ስለሚነገሩ፣ ስለሚነሱ ሕዝቡ ሆን ብሎና አቅዶ ቤቶችን ለማቃጠል አይነሳሳም። መንደር ከመንደር ጋር እንኳ ሆን ብለውና አቅደው እየተጋጩና እየተጣሉ ባለበት ሁኔታ እንኳ ቢሆን መንደር ሲቃጠል እሳቱን ለማጥፋት ግንባር ይፈጥራሉ ሲሉ ከላይ የተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች በተመሳሳይ ቀን በተካሄደው ቃለመጠይቅ ያብራራሉ።

**ኬዝ**

በኮንሶ ብሔረሰብ ድብደባ መፈጸም በተጎጂዎች ላይ የማይታይ የአካል ጉዳት ከማድረስ ባሻገር የአካባቢን ሰላም ከማወክና ጸጥታን ከማድፍረስ ጋር ስለሚያያዝ ጊዜ የማይሰጠው ከባድ ወንጀል ሆኖ እንደሚጠቀስ ተገልጿል። በዚህ መሰረት ሚያዚያ 5 ቀን 2006 ዓ.ም

በኮንሶ ጋሞሌ ቀበሌ ድብደባ ተፈጽሟል በሚል በባህላዊ ዳኝነት ስርዓት ጉዳዩን ለማየት በአፓ-ቲንባው ቤት የተከናወነውን የዕርቅ ስርዓት በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ የዕርቅ አፈጻጸም ስርዓቱንና ዐውዱን መመልከት ተችሏል።

በዕለቱ ለዕርቅ ድርድር የቀረበው ጉዳይ በጋሞሌ ቀበሌ የተለያዩ ጎሳዎች ሆነው ነገር ግን በአንድ ከንታ በሚኖሩና ቤተሰቦቻቸው ጎረቤታሞች በሆኑ የ 18ና የ10 ዓመት ልጆች መካከል የተፈጠረ ድብደባን መሰረት ያደረገ ሲሆን፣ በዕለቱ ለድርድሩ የቀረቡት የሁለቱም ወገን ወላጆች ነበሩ። ጉዳዩ ከባድ ወንጀል ሆኖ እያለ ጉዳዩ እንደተከሰተ ሁለቱ ቤተሰቦችና ልጆቻቸው በቤተዘመድ የሽምግልና ደረጃ ዕርቅ ፈጽመዋል። ይሁንና ዕርቁን ተበዳይም ሆነ በዳይ ከልባቸው ባለመቀበላቸው፣ በዳይም መሀላ እንዲፈጽም በመጠየቁ ጉዳዩ በአፓ-ቲንባ ቤት እንዲታይ ተብሎ የቀረበ መሆኑን በምልከታው ወቅት ተሳታፊዎች ከተናገሩት ለመረዳት ተችሏል።

በስርዓቱ ከ50 የማያንሱ ሰዎች ተገኝተው የተሳተፉ ሲሆን ሁሉም ወንዶች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የከንታውና የፓሌታው ኸሊታዎች (የወጣት ቡድን ተወካዮች) ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የአካባቢ ሽማግሌ፣ አስታራቂዎችና ሰንቀሊታው (የኼላው መሪ) ናቸው። የተሳታፊዎቹ የአቀማመጥ ሁኔታ በአፓ-ቲንባው ቤት ደጃፍ ባሉ ጠፍጣፋ ድንጋዮች ላይ ክብ በመስራት ነበር። የአለባበስ ሁኔታቸው የዕለቱ የአየር ሁኔታ በጣም ሞቃታማ ስለነበር ያለተጨማሪ ልብስ የወትሮ ልብሳቸውን እንደለበሱ ተገኝተዋል።

የዕርቅ ድርድር ስርዓቱም በዳይና ተበዳይም ሆኑ ሌሎች ተሳታፊዎች በተቀመጡበት የተካሄደ ሲሆን በስርዓቱ ለአደራዳሪዎችም ሆነ ለበዳይና ተበዳይ የተለየ ስፍራ አልነበረም። እንደ አመጣጣቸው ባገኙበት በመቀመጥ የተካሄደ ነበር። በዚህ መሰረት ስርዓቱ ሲጀመር ጉዳዩ ቀደም ብሎ በቤተዘመድ የሽምግልና ደረጃ የታየ በመሆኑ በቀጥታ የተጎዳ ቤተሰብ የሆነው አቶ ገደኖ በዶ ሃሳቡን በማቅረብ ጀምሯል። በዚህም ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ለበዳይ ቤተሰብ ለአቶ ለሚታ በወቅቱ አሞት ስለነበር ችግሩን እንዲፈታ በሽማግሌዎች ልኮበት እንደነበር ገልጿል። ነገር ግን አቶ ለሚታና ቤተሰቡ ጉዳዩን እንደልጅ ነገር አድርገውት እንዳስቀሩት ተናግሯል። ይሁንና ዛሬ ሚያዚያ 5 ቀን 2006 ዓ.ም በማለዳ ከቤታቸው አስጠርተዋቸው በጉዳዩ ላይ ተነጋግረውበት ችግሩን እንደፈቱ ነገር ግን የተያዘ ኾራታ ስላለ እሱ እንዲመለስ መፈለጋቸውን ጠይቀዋል።

የአካባቢ ሽማግሌ አቶ አያኖ ከንቶ በበኩላቸው ስለጉዳዩ ሲናገሩ “ጉዳዩ ወደባህላዊ ዳኝነቱ ተሸጋግሮ ከመታየቱ በፊት በቤተዘመድ የሽምግልና ደረጃ በማየት ተፈቷል” ሲታረቁም በቦታው እንደነበሩና እንዳዩ እጅ ለእጅም መጨባበጣቸውን ተናግረዋል፡፡ አቶ ኪሮስ ገሀኖ በበኩላቸው “መልካም ነው ዘመዳሞች ነበራችሁ አንድ ናችሁ በሽማግሌ መፍታታችሁ ይደገፋል ችግር መፍታት ይደገፋል እንጂ አይናቅም በዳይ (ልጁም) ጥፋተኛ ነኝ ካለና መካዱን ከተወ መልካም ነው” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ከልካለው ደነቦ ደግሞ አቶ ለሚታ ኾራታ ለባህላዊ ዳኝነቱ ሲያሲዙና መጥተው እዚህ እንዲነጋገሩ ሲጠየቁ “ልጃችን ታስሯል፤ ስለዚህ እሱ ይምጣ” ብለው ነበር የተጎዲው እናት ደግሞ “ልጄ ተጎድቶ በህግ ታጣቂ ተሸክመው ወደ ህክምና ወስደውልኝ ነገሩ ህግ ላይ እያለ እንዴት እዚህ ኾራታ ይያዛል” ብላ ስትጠይቅ የበዳይ ቤተሰብ “ልጁ መጀመሪያ ክዶ ነበር የሆኖ ሆኖ መሀላ እንገባለን ልጃችን አልነቃም ብላችሁ ስለነበር  ወደ መሀላ ልንልካችሁ ነበር የነበረው እንዴት በጎን ሄዳችሁ ተደራድረን ፈታን ትላላችሁ ማነው ከዚህ በግል እንድትታረቁ ያደረገው እንዴት ባህላዊ ዳኝነቱን ትታችሁ በጎን ጨረሳችሁ ግልጽ አድርጉልን አስታረቅን ብቻ በቂ አይመስለኝም” ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አቶ ገረመው ኩሴ ደግሞ “ችግሩን መፍታት ጥሩ ነው ነገርግን በወቅቱ አካባቢው ተሸብሮ ነበርና መቀጫ ያስፈልጋል ሁለታችሁም ትቀጣላችሁ ልጁ ቢሞት ኖሮ ሰላም ይናጋ ነበር” ሲሉ ኸሊታ-ፓሌታ ለሚታ ገልገሎ በበኩላቸው “በባህላዊ ህግ አልጠየቅም ያለው የበዳይ ወላጅ አቶ ለሚታ ጎዳን ሲሆን በህግ ይጣራ የሀኪም ማስረጃ ያቅርቡ አለበለዚያ ልጃችን አልነቃም የሚል ነገር ሲያነሱ የተመታው ልጅ እናት ደግሞ በህግ ለመከራከር አቅም የለኝም የተፈነከተና የቆሰለ ነገርም የለውም ልጁ በወቅቱ በተመታ ጊዜ ግን ራሱን ስቶ ነበር ስለዚህ እውነቱ በባህላዊ ህጉ ተጣርቶ ወይ ይመኑ ወይ ይካዱ ብላ ነበር የባህላዊ ህጉ ደንብም የተሰወሩ ነገሮችን፣ የሚካዱ ነገሮችን የማውጣጣት ስራ ነው የሚሰራው ህጉ ለሕዝብ እውነትን ለማውጣት እየሰራ ያለ ነው የሆኖ ሆኖ አሁን አስተካክለናል እያሉ ነው ካስተካከሉ መልካም ነው ቢሆንም ሕዝብ ሁለት ቀን በጉዳዩ ላይ ውሎ ተነጋግሮ ስለቆየ የደንብና አካባቢ ያወካችሁበትን መቀጫ ትከፍላላችሁ” በማለት ተናግረዋል፡፡

የበዳይ ወላጅ አቶ ለሚታ ጎዳን ደግሞ “ጉዳዩን አንድ ቀን ነው ያየነው ብዙም አላጉላላናቸውም ልጁ በወቅቱ  አላመነም ስለዚህ በመሀላ ይፈታ ብለን ነበር የሚደጋገም ነገር አይኖርም ከካደ ወደመሀላ መሄዳችሁ ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ የመሀላው ቀን እስኪደርስ

ድረስ ታላላቆቻችሁን፣ አባቶቻችሁን ጠይቁ ከዚያ መልስ ይዛችሁ ኑ አሏቸው፡፡ እኛም ስንመክርበት ቆየን ልጁንም አስጠርተን ቱራይታ ካፋችን ጋር ወስደን ምክር ሰጥተን ተመካክረን ነገሩን ፈታን የፈታንበት መንገድ መሀላ ከመግባት ማመን ነው የሚሻለው በማለት ነበር፤ ይህን ተቀብለን ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ሆነን የመታውንና የተመታውን ሁለቱንም አስጠርተን እንዲያምኑልን አድርገናቸው ተማመኑ ፈታን" በማለት አስረድተዋል፡፡

አቶ አሌ ኦቶማ በበኩላቸው "ማስታረቃችሁ ጥሩ ነው ግን ማነው ጥፋተኛ ሆኖ ያገኛችሁት ይህ መለየትና መታወቅ አለበት እሱን ግልጽ አድርጉልን መሀላ እንዳይሆን ለማስቀረት አደራድራችኋል ጥሩ ነው የሕዝብ ስርዓትና ደንብ የሚከበርበትና የሚፈራበት ቦታ ላይ ነው እየተነጋገርን ያለነው ሕዝቡንም ድርጊታችሁንም ከዳችሁ ነበር ስለዚህ ማነው ጥፋተኛው ግልጽ አድርጉልን መሀላ ሲባል ሰው እንዳይሞት ፈርታችሁ ተማምናችሁ ከሆነና ከፈታችሁ ጥሩ ነው ግን ማነው ጥፋተኛ በምንስ መልኩ እንዳመነ ግልጽ ይደረግ ካሉ በኋላ በዚህ መሰረት የተበዳይ ቤተሰብ ለባህላዊ ዳኝነቱ ምንም መክፈል የለበትም ጥፋተኛው የበዳይ ቤተሰብ ነው ተጠያቂ መሆን ያለበት" ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል ሌሎች ተሳታፊዎች የሚቀጡት ሁለቱም መሆን አለባቸው ብለዋል ለምን ማስታረቃችሁ ጥሩ ሆኖ ከባህላዊ ዳኝነቱ ሳይመራ መሆኑ ተገቢ አልነበረም፡፡

በስርዓቱ በተበዳይና በበዳይ ቤተሰብ መካከል የተጀመረው ምልልስ ከሁለቱም ወገን በመጡ የኼላውና የአካባቢ ሽማግሌ ክርክር ተጠናክሮ የተንሸራሸሩ በርካታ ሀሳቦች በነጻነት ከተደመጡ በኋላ በተሰጡት ሀሳቦች ላይ ተመስርተው አስታራቂ ሽማግሌዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህም አቶ ገልግሎ ካምብሮ ሲናገሩ "እዚህ ለባህላዊ ዳኝነቱ የተቀመጥንበት ምክንያት የሚካድ ነገር፣ በድብቅ የተሰራውን ስራ ለማውጣጣት ብለን ነው፡፡

በባህላዊ ዳኝነቱ አንድ ሰው ሌላውን አለአግባብ ሰድቦና ዘልፎ የካደ እንደሆነ መሀላ ይገባል መሀላ የማይደፍር ከሆነ ጥፋተኛ ነው" በማለት ሲገልጹ ኸሊታ-ፓሌታው (የኼላው ተወካይ) አቶ ገልሾ ገለቦ በበኩሉ "ሽማግሌዎች መጀመሪያ በንግግር ከፍታችኋል፡፡ የእናንተን ንግግር ተከትለው ባለጉዳዮች (የበዳይና ተበዳይ) ቤተሰቦች ቀጥለዋል፣ ምርቃትና ምክርም ከፖቅላው ሰምተናል፡፡

በዚህ ላይ የመጨረሻ ንግግር ማድረግ የሚገባቸው ወጣቶች ናቸው” ካሉ በኋላ ሀሳባቸውን አቅርበው የተበዳይና የበዳይ ወላጆች ቅሬታቸውን እንዲያነሱ ጠይቀዋል፡ በዚህም በዳይና ተበዳይ በዕርቅ መውረዱ በመስማማታቸው በቅድሚያ ሽማግሌዎች በዕድሜ ቅደም ተከተላቸው እህል ከቀመሱና ከተፉ በኋላ የበዳይና የተበዳይ ወላጆች ደግሞ ተጨባብጠው፣ አንዱ ላንዱ እህል በመስጠት በጋራ ቀምሰው ስርዓቱን ፈጽመዋል፡፡

ጠበኞች መጨባበጣቸውና በጋራ እህል መቅመሳቸው የዕርቁ ማጽኛ ምልክት ሲሆን፣ ሽማግሌዎችም እህል ቀምሰው መትፋታቸውም ዕርቁን በአካባቢው ያለ ሙት መንፈስ ሳይቀር መቀበሉን ለማመልከትና የዕርቁ ማጽኛ ሆኖ ማገልገሉን መረዳት ተችሏል።

### 4.5.3. በፖቅላ ደረጃ የሚፈቱ ወንጀሎችና የአፈታት ሂደታቸው

በፖቅላ ወይንም በጐሳ መሪ ደረጃ የሚታዩ ግጭቶች በአብዛኛው ከበድ ያሉ ከሕብረተሰቡ ባህልና ስርዓት ጋር የማይሄዱ ከባድ ወንጀሎች ናቸው። እነዚህ ወንጀሎች እንደ ውጉዝ ጋብቻ፣ ተደጋጋሚ የሆነ ስርቆት፣ ድንገተኛ ነፍስ ግድያ፣ አካል ማጉደል /እጅ መስበር፣ ዓይን ማጥፋት፣ ጥርስ ማውለቅ ወዘተ፣ መረጃ የሌላቸው ማናቸውም ጉዳዮች እና ለመሀላ የሚቀርቡ ጉዳዮች ናቸው። ለነዚህ ግጭቶች መከሰት ዋና ሰበቦች ከውጉዝ ጋብቻ ጋር ተያይዞ ከዘመድ ጋር ጋብቻ መፈፀም ለምሳሌ ከእህት ልጅ፣ ከወንድም ልጅ፣ አልፎ አልፎ ከጎሳ ጋር ጋብቻ መፈፀም ይህም አንድ ጎሳ እንደ አንድ ቤተሰብ ስለሚታይ የቤተሰብ ጋብቻ ፈፅሞ ክልክል በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮች የሚያዩት በዋናነት አፓ-ካፋ፣ ቂሞታ-ካፋ፣ ፖቃላ ሙግላ/ቱራይታ/ እና ፖቅላ ቱማው /የጎሳ መሪው/ ሲሆኑ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ዳውራዎች /መንፈሳዊ አባቶች/ እና ሳራዎች/ የጎሳው መልዕክተኞች/ ሊገኙ ይችላሉ።

በዚህ ደረጃ ለሚቀርብ ወንጀል ኾራታ የለም። ምስክርም አይጠራም። ማስረጃ አያስፈልግም፤ ጉዳዩ በየደረጃው ታይቶ የመጣ በመሆኑ ድርድር የለም፡፡ ወንጀለኞች ማመን ወይንም አለማመን ብቻ ነው የሚጠበቅባቸው። በትክክል ጉዳዩ መፈፀሙን ማረጋገጥ ብቻ ነው። ካረጋገጡ በኋላ ሁለቱም ተጋቢዎች /ሴቷንም ወንዱንም/ ከኮንሶ ምድር እንዲባረሩ /እንዲወጡ/ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ወንጀል ምንም ድርድር የለም።

ይህ መዋቅር አሁን ባለበት ሁኔታ እየተሰራበት ያለና ተፈፃሚነት ያለው ደንብና ስርዓት ነው። የአፈታት ሂደቱን በተመለከተ ወንጀሉን ፈፃሚዎች በጎሳውና በአካባቢው “ኬላ”

አማካኝነት በሕዝብ ሞራ /ሞራ-ፓሌታ/ አሊያም በፖቅላ ቱማው ቅጥር ግቢ እንዲቀርቡ ይደረጋል። ከዚያም ለጥያቄ የቀረቡ አካላት የፈፀሙትን እንዲናገሩ እድል ይሰጣል። አብዛኛውን ጊዜ ድርጊቱን መፈፀማቸውን ያምናሉ፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ መፈፀሙ መጠርጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ጥብቅ ክትትል ስለሚደረግባቸው ነው። ስለዚህ ድርጊቱን ከማመን ውጭ አማራጭ አይኖራቸውም።

እስካሁን ባለው ሁኔታ በዚህ ደረጃ ይህን ፈፅመው አይክዱም ዕጣ ፈንታቸውም ጉዳዩ ተረጋግጦ ከቀዬው ወይም ከኮንሶ ምድር መባረር ብቻ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዩ ካላ ገዛኸኝ ጋር ጋሞሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በተካሄደ ቃለ መጠይቅ መረዳት ተችሏል (ጥር 24፣ 2006 ዓ.ም፣ 16)፡፡

ተደጋጋሚ ስርቆት መፈፀምን አስመልክቶ በብሔረሰቡ ይህም ከባድ ወንጀል ነው። ለዚህ ወንጀል መፈፀም መነሻ ሰበቦቹ ልማደኛ መሆን፣ ለባህል ስርዓቱ ክብር አለመስጠት፣ ችግር /ማጣት/ ሲሆን፣ ይህ ድርጊት በፓሌታ ደረጃ በቱራይታ ካፋዎች ታይቶ ሊታረም ያልቻለ ከሆነ ለመጨረሻ ውሳኔ በፖቅላ ደረጃ ቀርቦ ከቀዬው /አካባቢው/ መባረር እንደሚሆን በተመሳሳይ እለት ከመረጃ አቀባዩ መገንዘብ ተችሏል። ይህንን ወንጀል በተመሳሳይ የሚመለከቱት ከላይ የተጠቀሱት አካላት /መዋቅር/ ሲሆኑ፣ የጉዳይ ማያ ጊዜው ወይንም ዕለት በከንታና በፓሌታ ደረጃ እንደሚታየው ይሆናል።

የአፈታት ሂደቱን በተመለከተ ወንጀለኛው በመጀመሪያ በኼላው በራሱ የጎሳ አባል አማካኝነት ወደ ችሎቱ ማለትም ወደ ፓሌታው አሊያም ወደ ፖቅላ ቱማው እንዲቀርብ ይደረጋል። በሚቀርብበት ጊዜ ልማድህን ፈፅመሃል በሚል በቂሞታ-ካፋ /ሽማግሌዎች/ አማካኝነት ጥያቄ ይቀርብለታል። እናም ምን ይሻለኛል ትላለህ የሚሻለውን ነገር ተናገር ይባላል። ከዚያም መረጃ ቀድሞ የተሰባሰበበት በመሆኑ መካድ አይችልምና ያምናል። አላምን ካለ ግርፊያ ስለሚኖር ሳይወድ በግድ ያምናል። በዚህ ሁኔታ በሕዝብ ፊት እንዲያምን ከተደረገ በኋላ የወሰደውን ንብረት እንዲመልስ ይደረጋል። የጠፋም ከሆነ መኖሪያ ቤቱ ያለው ንብረት ተሸጦ እንዲመልስ ይደረግና ከአካባቢው /ከመኖሪያ ቀዬው እንዲወጣ/ ወይንም እንዲባረር ይደረጋል። በዚህ ጉዳይ ምንም ድርድር የለም።

ይህ መዋቅር አሁንም ድረስ በተጨባጭ እየተሰራበትና እየተተገበረ ያለ ስለመሆኑ በቃለመጠይቁ ወቅት ታውቋል። ‹‹ማንኛውም ሰው በባህሉ መሰረት ከአካባቢው ከባድ

ወንጀል ተብለው ከተፈረጁት አንደኛውን ፈጽሞ እንዲወጣ ከተደረገ በምንም መልኩ ቢሆን መመለስ አይችልም በፅሁፍም ባይኖር የባህል ስርዓቱ ወይም ደንቡ የሚያዘው ወይም የደነገገው ነው ይላሉ እንደ ባህል እነዚህ ከአካባቢው ወይም ቀዬው እንዲወጡ የሚደረጉ ሰዎች ወይም ወንጀለኞች ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ ናቸው ስለሚባል ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው በማናቸውም ሁኔታ ተሳታፊ ሊሆኑ አይችሉም›› (ካሳ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 24፣ 2006 ዓ.ም፣ 17) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ይህን ሁሉ በመፍራት ከአካባቢው የተባረረ ሰው ወደ ቀዬው አይመለስም፡፡ ዕድሜም አይኖረውም በማለት ይገልጻሉ፡፡

ድንገተኛ የነፍስ ግድያን በተመለከተ በብሔረሰቡ ከባድ ወንጀል ተብሎ የሚፈረጅ ነው፡፡ ለዚህ ወንጀል መከሰት ሰበብ ሆኖ የሚነሳው በዕለት ግጭት /ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት ጠብ በሌላቸው ሰዎች መካከል /ጠበኞችን ለመገላገል ሲሞክር በመሀል ሰለባ የመሆን፣ የተሽከርካሪ ድንገተኛ አደጋ /የመኪና መገልበጥ፣ የሞተር ሳይክል አደጋ/ጋር ተያይዞ የሚከሰት ነው፡፡ እነዚህን ወንጀሎች የሚፈቱት ወይንም ጉዳዩን የሚያዩት ከላይ በዚህ ደረጃ የተቀመጡ አካላት/መዋቅር ሲሆኑ፣ ጉዳዩ የሚታይበት ወቅት /ጊዜና ሰዓት/ን አስመልክቶ ህይወት መጥፋት በመሆኑ ጊዜ የሚሰጠው አይደለም፡፡ የገበያ ቀናት ወዘተ አይባልም፡፡ ስለዚህ ችግሩ እንደተከሰተና እንደተሰማ የመበቃቀል ነገር እንዳይኖር /በርግጥ በኮንሶ በቀል የለም/ የማረጋጋት ስራ ሳራዎች ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን ይሰራሉ፡፡

የአፈታት ሂደቱን በተመለከተ በመጀመሪያ የተከሰተው ወንጀል በሳራዎች አማካኝነት ለጎሳ መሪዎች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ በዚህ በክስተቱ ስፍራ የቱራይታ ካፋ ሳራዎች፣ የፖቅላ ቱማው ሳራዎች፣ ሰንቀሊታዎች፣ ሽማግሌዎች በጋራ ተገኝተው ሁኔታውን ያረጋጋሉ፡፡ በምን መልኩ መሄድ እንዳለበት ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተበዳይና የበዳይ ቤተሰብ እንደተረጋጉ የበዳይ ቤተሰብ ሽማግሌዎችን ይዞ ወደ ፖቅላ ቱማው /የጐሳ መሪው/ ቤት ይመጣል፡፡ ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎች የአማላጅነት ሥራ ስለሚሰሩ አማልዱን ተብለው ይመጣሉ፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ለፖቅላ ቱማው ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዋናው ፖቅላ ቱማው ለቅሶውን ስለማይደርስ የራሱን ሳራዎች ለቅሶውን እንዲደርሱ አድርጐ እግረ መንገዱን ቤተሰቡ እንዲጽናና፣ እንደዚህ ዓይነት ክስተት ፈጣሪ ዳግመኛ እንዳያመጣ ፀልየው መክረውና ገስፀው እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡

በዚህ ሁኔታ በተበዳይ ቤተሰብ ያለውን ሁኔታ፣ ድባቡን በመረዳት ለፖቅላ ቱማው ያለውን ሁኔታ ያስረዳሉ፡፡ ከዚያም ለቅሶ በደረሱ በሶስተኛው ቀን ከሌሎች ሽማግሌዎች፣ ከዳውራዎች ጋር በመሆን ወደ ሟች ቤተሰብ ያለቀጠሮ[9] ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ በድርጊቱ በጣም አሳዛኝነት ይጀምሩና ቀስ በቀስ የሆነው ሆኗል እንግዲህ ምን ይደረግ ምን እያሰባችሁ ነው ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ አሳዛኝነት ይጀምሩና ቀስ በቀስ የሆነው ሆኗል እንግዲህ ምን ይደረግ ምን እያሰባችሁ ነው ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

ይሄ ጉዳይ በሽማግሌ በድርድር ቢያዝ ምን ትላላችሁ ብለውም ይጠይቃሉ፡፡ የወንጀሉ ድንገተኛ መሆንና ያልታሰበ ክስተት መሆንን እያስተዛዘኑ በማስረዳት ይገልፃሉ፡፡ የበዳይ ወገንም ይቅርታ መጠየቅ እንደሚፈልጉ ይገልጹላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የተበዳይ ወገኖች እስኪ እንምከርበት ይላሉ፡፡ ቀጠሮ ይይዙና ብዙ ጊዜ በሁለት ቢበዛ በሶስት ቀናት ውስጥ ምላሻቸውን ያሳውቃሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ካልተፈፀመ ግን የተበዳይ ወገን ተናቅን ‹ልጃችንን ከውሻም አልቆጠሩትም› ብለው በስሜት ሊነሳሱ ይችላሉ፡፡

ይሁንና ይህ ሽምግልና የተበዳይ ወገኖች ቢፈቅዱም ባይፈቅዱም ነገሮችን ለማብረድና ለማቃለል ይጠቅማል፡፡ ስለዚህ በቀጠሮው ዕለት ከበዳይ ወገን አንድ ሰው ይዞ ወደ ተበዳይ ቤት ሊኬድ ይችላል፡፡ የድርድር ቦታው ይወሰናል፡፡ በፖቅላ ቱማው ቤት አሊያም ገለልተኛ በሆነ አቅራቢያ ግቢ ሊሆን ይችላል፡፡ እጅግ የከረረ ጉዳይ ሲሆን በፖቅላ ቱማው ግቢ ይታያል፡፡ ይህን መሰሉ ወንጀል እጅግ ቢበዛ በ3 /ሶስት/ ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያገኛል፡፡ ውሳኔውም ይቅር እንዲባባሉ ማድረግና ቃልኪዳን የሚገቡበትን መንገድ ማመቻቸት ይሆናል፡፡

ቃል ኪዳኑ ሁለተኛ ላይደራረሱ ‹ዳውራ› እንሁን / እንደ አንድ ጉሳ እንተያይ /ከሌላ ጉሳም ቢሆኑ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ቃል ኪዳን ጋብቻ አይኖርም፣ ከብቶቻቸውም እንዳይጠቃቁ፣ እንዳይገናኙ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ከብቶቻቸው የሚሰማሩበትን ቦታ ሳይቀር ያራርቃሉ፡፡ ድንገት ተቀላቅለው ከብቶቻቸው ሲጠቃቁ ቢያዩ እንኳ ‹ኩማና ኩማና› ይላሉ፣ ሚዳቋ ሚዳቋ ማለት ነው፡፡ በቃ እነዚህ የዱር እንስሳት ናቸው ብለው ያልፏቸዋል፡፡

---

[9] ያለ ቀጠሮ መምጣታቸው ሐዘኑ ትኩስ ነው የትም አይሄዱም በሚል ዕምነት መሆኑን በቃለ መጠይቁ ወቅት ያገኘሁት መረጃ ነው፡፡

በዚህም ጊዜ በእንስሳቱ ላይ ምንም ዓይነት ሁኔታ አይፈጠርም፤ አለበለዚያም ደም ሊሸኑ ይችላሉ ተብሎ በብሔረሰቡ በባህል ይታመናልና ሲሉ ከመረጃ አቀባዩ ካላ ገዛኸኝ ጋር ጋሞሌ ቀበሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በነበረ ቃለመጠይቅ መረዳት ተችሏል (ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 18)፡፡

በመጨረሻ በዚህ መልኩ የእርቅ ስርዓቱ ከተፈፀመ በኋላ የበዳይና ተበዳይ ቤተሰብ ይመራረቃሉ፡፡ እህልም አብረው ይቀምሳሉ፡፡ በአንድ ቅል ጨቃ ይጠጣሉ፡፡ በዚህ የእርቅ ስርዓት ለእርቅ ማፅኛው እርድ ይኖራል፡፡

እርድ የሚካሄድባቸው ሁኔታዎች ለየት ይላሉ፡፡ ጦርነት ነክ፣ ነፍስ ግድያና የሰው ደም መፍሰስ ናቸው፡፡ በእርድ አካባቢው መንፃት አለበት ይባላል፡፡ እዚህ ላይ አንደበት ትልቅ ስራ እንደሚሠራ መረጃ አቀባዩ ካላ ገዛኸኝ በተመሳሳይ ዕለት በነበረ ቃለመጠይቅ ያስረዳሉ፡፡ በተለይ የነፍስ ግድያ ካልሆነ አይ ጉዳዩ ቀላል ነው፤ ብዙ የከፋ አይደለም ትንሽ ነው ከተባለ በዕፀዋት ብቻ ሊደረግ ይችላል፡፡ በቅዱስ ውኃና በቅዱስ ዕፀዋት ብቻ ይደረጋል፡፡

ቅዱስ ውኃ /ጠዋት ማለዳ ማንም ሰው ሳይቀዳ የተቀዳ የምንጭ ውኃ/ ሲሆን፣ ቅዱስ ዕፅዋት ደግሞ እንደ ‹‹ሳጋንታ›› እና ‹‹ላጋንታ›› /ዳማከሴ መሠልና ሀረግ መሰል ቅጠል/፣ እንደ ብልሻ ውኃ /የጉድጓድ ውኃ/ ተቀድቶ ‹‹ማካሮታ›› የሚባል ቅል መሠል የሀረግ ፍሬ አለ፣ እሱን እንደበግና ፍየል በመውሰድና እንደእርድ ለሁለት ከፍሎ በመፈፀም በዚያ በቀላሉ ማጽዳት ይቻላል፤ ዋናው የሰው አንደበት ካለባባሰው በቀር ይላሉ፡፡ ይሁንና በሁሉም የእርቅ ስርዓት ላይ መብልና መጠጥ ይኖራል፡፡

በማናቸውም ቀላልና ከባድ ስርዓቶች ላይ በዋናነት ማሽላ ወይም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ሹላይታ›› ይባላል፡፡ ‹‹ሹላይታ›› የኮንሶ ዋና ማሽላ ነው፡፡ ልጅም አሁን እህል ነክ ነገር ሲያቀምሱት መጀመሪያ ሹላይታውን ነው የከብት ውጤቶችን ከመቅመሱ በፊት፡፡ ስለዚህ ሹላይታው /ማሽላውና የከብት ወተት አብሮ ይቀርባል፤ ጨውና በሶብላ ይገባበታል፡፡ እዚህ ላይ በሶብላው ጥሩ መዓዛ ያለው ሲሆን፣ እርስ በርስ ጥሩ መዓዛ ይኑራችሁ፣ እንደጨው ጣፍጡ፣ ማሽላው እህል ስለሆነ እህል በልታችሁ ኑሩ እንደማለት ነው፡፡ በስርዓቱ ላይ ምርቃት እንዳለ ሁሉ እርግማንም አለ፡፡ እርግማን ክፉ ነገር፣ የተደበቀ ነገር ሲኖር፣ ሰዎች ይሄን እህል ከቀመሱ በኋላ አደራጊው የተሰወረበት ወይም የጠፋበት ሲሆን፣ የእርግማን ስርዓት ይደረግና ሠዎች እህል ቀምሰው ቃልኪዳናችን ይጠበቅ፣ ፈጣሪ እንደዚህ አይነት

ድርጊት የሚፈፅሙ፣ ክፉ ነገር ፈፅመው የሚሰወሩትን ያጋልጥ፣ አሁንም ያደረገው ወይም ያጠፋው ሰው በዚህ ዓይነት ምልክት ታይቶበት ይጋለጥ ብለው የሚረግሙበት ስርዓትም አለ። ሌሎች ሰላማዊ ሰዎች ደግሞ በዳውራዎች የሚመረቁበትም ሁኔታ አለ።

በብሔረሰቡ ዕርድ የሚከናወንባቸው ሁኔታዎች ለየት ያሉ ክስተቶች መሆናቸው ከላይ ተጠቅሷል። ይኸውም ጦርነት ነክ፣ የሰው ደም ማፍሰስ ከሆነና ነፍስ ግድያ ናቸው። ይሁንና በዚህ ደረጃ የቀረበው ከነፍስ ግድያ ጋር ተያይዞ በመሆኑ እርዱ በበግ ወይም በፍየል ይሆናል። ለእርድ የምትመረጠውም ወልዳ ያቆመች በግ ወይንም ፍየል ስትሆን ዋና ምክንያቱም በተለያየ መከራና ክስተት ውስጥ ረጅም ጊዜ ያሳለፈች ናት፣ ብዙ በመውለድም ችግር ያየች ናት፤ ስለዚህ እነሱም የቀጠለ ዘር እንዲኖራቸው፣ እድሜያቸው ካበቃ በኋላ እንዲያልፉ ረጅም ዕድሜ እንዲኖሩ መልካም ምኞትን ለመግለጽ ሲባል ይመረጣሉ። የስርዓቱ አፈጻጸም የተመረጠችው በግ ወይንም ፍየል ከታረደች በኂላ ጠበኞች በፈረሱና በቅዱስ ውኃ/ማልዶ ማንም ሰው ሳይቀዳው የተቀዳ የምንጭ ውኃ/ እንዲታጠቡ ይደረጋል። በፈርሱና በቅዱስ ውኃ መታጠባቸው ተምሳሌትነቱ ከደሙ ንፁህ መሆንን፣ መንፃትን ያመለክታል።

እርዱ የሚከናወነው ግድያ በተፈፀመበት ቦታ አሊያም በጠበኞቹ በአንደኛቸው ግቢ በዋናነት በሟች ግቢ ሲሆን፣ ይህ የሚሆነውም ቤተሰቡ ጉዳት የደረሰባቸው ስለሆኑ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ስርዓቱን መፈጸም ዕርቁን እንዳለማውረድ ይቆጠራል ሲሉ ከላይ የተጠቀሱት መረጃ አቀባዩ ያብራራሉ፡፡ በዚህ የዕርድ ስርዓት ወቅት ዋነኛ ተሳታፊ የሚሆኑት ገላጋይ የተባሉና በብሔረሰቡ የመጀመሪያ ሚዜ ተብለው የሚወሰዱት ዳውራዎች (መንፈሳዊ አባቶች) ናቸው፡፡

እነዚህ መንፈሳዊ አባቶች በዚህ ስነ-ስርዓት ላይ ወሳኝ አካል ናቸው።ዕርዱን በተመለከተ የሚያከናውኑት በዕድሜ ገፋ ያሉ ሽማግሌዎች ሲሆኑ፣ እንደሁኔታው ወጣቶችም ሊያርዱ ይችላሉ ብቻ አቅሙ ይኑራቸው እንጂ፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎች በስነ-ስርዓቱ ወቅት ምርቃታቸው ስለሚያስፈልግ ሽማግሌዎች እንዲያርዱ ይደረጋል። በዕርዱ ወቅት ለስጋ ማቅረቢያና መመገቢያ የሚያገለግል ገበቴ፣ ማረጂያ ቢለዋ፣ ከቅዱስ ዕጸዋት(ላጋንታና ሳጋንታ) እንዲሁም የሰገን ወንዝ አፈር ይቀርባል። በዚህ ስርዓት እነዚህን ቁሳቁሶችና ነገሮች የሚያቀርቡት ከሁለቱም ወገን ያሉ ተወካዮች ሲሆኑ፣በዋናነትም አደራዳሪ (ገላጋይ)

አካል ይሆናሉ። ዕርዱም ጠዋት ማለዳ ይከናወናል፡፡ ማለዳ መመረጡ ማለዳ መልካምና አዲስ ቀን በመሆኑ ምንም ዓይነት መጠጥ ሳይቀመስ የሚፈጸም ስለሚሆን ይመረጣል።

በስርዓቱ ከቀረቡት ነገሮች የሰገን ወንዝ አፈር ተምሳሌታዊ ፍች ቅዱስነትን ለማመልከት ነው። ይኸውም ወንዙ ከተለያየ አካባቢ አፈር ይዞ ይጓዛል፡፡ ከተለያየ አካባቢ ይዞ የሚመጣውም መጥፎና ጥሩ ነገርን ነው። ስለዚህ በዚያ ሁሉ አጥቦናል፤ ነጽተናል ለማለት ነው። ሌላው የ‹‹ሀንሳቢታ›› ቅጠል ነው። የዚህ ቅጠል አስፈላጊነት ፈርሱና ቅዱስ ውኃው ተደባልቆ አካባቢው ይረጭበታል፡፡ ጠበኞችም በቅዱስ ውኃውና ፈርሱ ይታጠቡበታል፤ የተረፈውን ደግሞ ወደ ገዳይ ግቢ በመውሰድ ይረጩታል፡፡ ይህ መሆኑ ከደሙ ንጹህ መሆንን፣ መንጻትን ያመለክታል፡፡ በዚህ ስርዓት የታረደችው በግ ወይም ፍየል ደም ጉድጓድ ተቆፍሮ ይቀበርና ይሸፈናል።

ይህ መደረጉ ደም መልካም ነገር አይደለም  ቁጣ፣ መቅሰፍት፣ ወረርሽኝን የመሳሰሉትን ያስከትላል ተብሎ  በመታመኑ ነው። ሌላው በዚህ ዕርድ ስርዓት ወቅት ከብቱን በመያዝ የሚሳተፉት አቅም ያላቸው ገለልተኛ የሆኑ ወጣቶች ሲሆኑ፣ በዚህ ስርዓት የሚችና የገዳይ ቤተሰብ፣ የቅርብ ቤተዘመዶችና አስታራቂዎች ይገኛሉ። ይህ መሆኑ የሚች ወገን ቅሬታውን እንዲያነሳ፣ ገዳይም ጥርጣሬ እንዳይኖረውና ይቅርታውን እንዲያገኝ፣የቅርብ ቤተዘመድም የውስጥ ቅሬታ በቤተዘመድ መካከል እንዳይፈጠር፣ አስታራቂዎችም እንዳስታራቂነታቸው የስርዓቱ አካል በመሆናቸው ይገኛሉ። ይህ ከተደረገ በኋላ የበዳይና ተበዳይ ቤተሰቦች ደመኞች ሆነው አይታዩም። በፈርስና በቅዱስ ውኃ እንደታጠቡት ሁሉ፣ በአንድ ቅል አብረው እንዲጠጡና አብረውም እህል እንዲቀምሱ ይደረጋል።

ይህ ስርዓት በሚች የፈሰሰውን ደም የመተካትና የማንጻት ስራ ሲሆን፣ ለማንጻት ፈርስ የሚመረጥበት ምክንያት ከብቶች የሚመገቡት የተለያዩ ዕፅዋትን በተለይም የቅዱስ ዕፀዋት ድብልቅ የሚገኝበት በመሆኑ፣ ቅዱስ ዕፀዋቱ የሰላም ማምጫ ተምሳሌት ናቸው በማለት ይመርጡታል። በዚህ ዕርቀ ሰላም ይወርዳል። በዚህ ሁኔታ የተካሄደው ስነ-ስርዓት ሙሉ በሙሉ ከተፈጸመ በኋላ ‹‹መልካሙ ሁሉ ይምጣ›› በሚል የሽማግሌዎች ምርቃት ስነ-ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡ በሁለቱም ወገኖች ሕይወት እንደነበረ ይቀጥላል ማለት ነው። ይህ ስርዓት በአንዳንድ ፓሌታዎች ወይም መንደሮች ሚች ሳይቀበር በፊት ይፈፀማል ሲሉ በተመሳሳይ ዕለት ከመረጃ አቀባዩ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት

መረዳት ተችሏል። ይህ መዋቅር ወይም ስርዓት አሁንም ድረስ በባህሉ የሚተገበር እንደሆነም ይገልጻሉ (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 19)።

መረጃ የሌላቸው ማናቸውም ጉዳዮች በፖቅላ የዳኝነት ደረጃ ይታያሉ። በፖቅላ ደረጃ ለሚታዩ ጉዳዮች ምስክር አይቀርብም። ጉዳዩ የሚጣራው በልዩ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም ከሁለቱም ወገኖች /ጠበኞች/ ጉዳያችንን በትክክል ይገልፅልናል፣ ያስረዳልናል ብለው ያመኑበት አካል ሀሳባቸውን ቀርቦ እንዲገልፅ ብቻ ይፈቀዳል፡፡ ምስክርነት ግን አይፈለግም። በዚህ ደረጃ ምስክር የማይጠራበት ምክንያት ‹‹ምስክር ከተጠራ አድልኦ አለ ተብሎ ስለሚታሰብና በባህላዊ ስርዓቱ ደግሞ አድልኦ የተወገዘ ነገር በመሆኑ አይፈቀድም›› (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 20) ሲሉ ያስረዳሉ። መረጃ የሌላቸው ጉዳዮች በፖቅላ ደረጃ እንዲታዩ የሚደረገው ጉዳዩ በደረጃ ባሉ ችሎቶች ታይተው ከሁለቱም አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ነው።

በመጀመሪያ በከንታ ደረጃ ታይተው ጠንከር ሲሉ በፓሌታ ደረጃ እንዲታዩ ተደርገው ጉዳዩ ከሁለቱም አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ማለት ነው፡፡ በፖቅላ ደረጃ የሚፈቱ ግጭቶችን ውሳኔ የሚወስነው ፖቅላ ቱማው /የጎሳ መሪው/ ነው። በፖቅላ ደረጃ የሚቀርበው ውሳኔ ከሽማግሌዎችና ከቱራይታዎች ጋር በጋራ የታየው ሲሆን፣ የውሳኔ አሠጣጡ የራሱ ስርዓት ያለው ነው ይህም ጠበኞች ወይም ተጋጪዎች በቅድሚያ ውጭ እንዲወጡ ተደርጎ በጋራ የተወሰነውን ውሳኔ ቀርበው እንዲሰሙ በማድረግ ነው። በተወሰነው ውሳኔ ቅሬታ ያለው አካል ካለ ቅሬታውን እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም አሳማኝ ከሆነ ተሻሽሎለት ለሌላኛው ተስማሚ መሆኑ ተጠይቆ ሁለቱም ከተስማሙበት ውሳኔው የፀና እንደሚሆን ከመረጃ አቀባዩ ካላ ገዛኸኝ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ መረዳት ተችሏል (ጋሞሌ፣ ጥር 24፣ 2006 ዓ.ም፣ 20)፡፡

ሌላው የአካል ጉዳት ማድረስ (አካል ማጉደል) ሲሆን፣ ይህም በብሔረሰቡ ከባድ ወንጀል ሆኖ የሚታይ ነው። ለዚህ ወንጀል መንስኤው የዕለት ጠብ፣ ከንብረት ጋር ተያይዞ በአፍ እላፊና በእርሻ መሬት ሳቢያ እንዲሁም ቀጥታ ለመምታት ወይንም ለመከላከል ሲባል በአጋጣሚ የሚከሰት ነው፡፡ የአካል መጉደል ሲባል  እጅና እግር መሰበር፣ ጥርስ መውለቅ፣ ዓይን መጥፋትና  ከባድ ቁስለት (ጭንቅላት ላይ) መከሰት ናቸው።

በፖቅላ ደረጃ ይህን መሰሉ ጉዳይ በቤተዘመድ አካባቢ የተከሰተ ከሆነና ጉዳቱ ለከፋ ችግር የማያደርስ ከሆነ ቂሞታ (ሽማግሌዎች)፣ ዳውራና የጎሳ መሪ (ፖቅላ ቱማው) በጋራ ይመለከቱትና በይቅርታ እንዲታለፍ ወይም እንዲፈታ ያመቻቻሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው የአካል ጉዳት ከባድ ከሆነና ካሳ ወይም ማገገሚያ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ለተለያየ ወጪ የወጣ በሚል፣ ለወጌሻ በአጠቃላይ ለህክምና የወጣ በሚል ሙሉ በሙሉ አካል ያጎደለው ሰው እንዲሸፍን ወይም እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ውሳኔ የሚሰጠውም ቁስሉ ሙሉ በሙሉ ሲድን ይሆናል፡፡

በዚህ ሂደት ጉዳዩን የሚመለከቱት አካላት የመጀመሪያ ስራቸው ጠበኞችን አቀራርቦ በይቅርታ እንዲተላለፉና በዳይ ማስታመም ካለበትም ተበዳይን የማስታመምና የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት በማሳሰብ ይሆናል፡፡ ይህ ለመጀመሪያዎቹ ሳምንታት በየቀኑ ተበዳይ ቤት በመሄድ ይሆናል፡፡ በሁለተኛው ሳምንት ለውጥ ካለው በሶስት ቀን አንዴ ሄዶ የመጠየቅ ግዴታ ይጣልበታል፡፡

በዚህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተጎጂው ሲያገግም የመጨረሻ ውሳኔ በተጎጂው ቤት በመገኘት በዳይ ካሳ እንዲከፍል ይወሰናል፡፡ ይህን መሰሉ ክስተት ሲፈጠር የአፈታት ሂደቱ በቅድሚያ የተበዳይ ወገን ለአካባቢው መሪዎች ማለትም ለቂሞታ (ሽማግሌዎች) ወይም ሰንቀሊታዎች ጉዳያቸውን ያቀርባሉ፡፡ በማግስቱ የአካል ማጉደል ወንጀል የፈጸመው በዳይ ሽማግሌዎችን ወደተበዳይ በመሄድ አማልዱኝ ሲል አማላጅነት ይልካል፡፡ በዳይ እንኳ ባይፈቅድ ዘመዶቹ ጉዳዩ በድርድር እንዲፈታ ሽማግሌዎችን ይልካሉ፡፡

ሽማግሌዎችም ጉዳዩን ይዘው ወደተበዳይ በመቅረብ ምራቃቸውን በቁስሉ ላይ ሶስት ጊዜ እንትፍ እንትፍ በማለት የሄዱበትን ጉዳይ ያስረዳሉ፡፡ ሶስት ጊዜ መትፋታቸው ፈውስ ቶሎ እንዲመጣ፣ እንዲድን የመልካም ምኞት ምልክት እንደሆነ መረጃ አቀባዩ ያስረዳሉ፡፡ የተበዳይ ቤተዘመድም እስኪ እንምከርበት እና ምላሻችንን እንስጥ ይላሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም በማግስቱ ምላሻቸውን ለመስማት ወደተበዳይ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ጉዳዩ እንደምታዩት ከፍተኛ ነው፡፡ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አይታወቅም፡፡ ስለዚህ እስኪድን ድረስ ብናየው የተሻለ ይሆናል ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ምርቃቱን ሰጥተው ይመለሳሉ፡፡

በመጨረሻም የበዳይ ወገን ተበዳይን እንዲጠይቅ፣ አስፈላጊ ነገር እንዲያቀርብ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ አልፎ አልፎ ተበዳይ በራሱ ይህንን እራሴ ልቻልና በመጨረሻ ላይ ይተካዋል

ሊል ይችላል፡፡ ክትትሉ ቀጥሎ ተበዳይ ሲያገግምና ቁስሉ ሙሉ በሙሉ ሲድን ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በዳይ ላይ የካሳ ክፍያ ተጥሎ እርቅ ይወርዳል፡፡ በእርቅ ስርዓቱ የተጠቀሱት በሙሉ ይገኛሉ፡፡ የምርቃት ሥርዓት ያከናውናሉ፡፡ እህል በጋራ ይበላሉ፣ ጨቃ በአንድ ቅል ይጠጣሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰላም ይወርድና ይለያያሉ፡፡

ይሁንና በዳይ ወንጀሉን መፈጸሙ ታውቆ አልከፍልም፣ አካል አላጎደልኩም ብሎ ቢክድ አንተ ካላደረግህ ያደረገውን አካል አቅርብ ይባላል፡፡ በአጠቃላይ የባህል መሪዎች ማዕቀብ ይጥሉበታል፡፡ ከማህበራዊ ግንኙነት ይገለላል፡፡ ነገ ገለህም ትክዳለህ ይባላል፡፡ ብዙ ጊዜ ይህን መገለል በመፍራትና ከአካባቢው መባረርም ስለሚኖር መካካዱ አይኖርም መጀመሪያ ክዶ በኋላ ተጸጽቶ አድርጌያለሁ አዎ ብሎ ቢያምን ለምን መጀመሪያ አላደረግሁም ለምን አልክ በሚል ቅጣት ይጣልበታል እንደ ግትር አቋምነቱ ታይቶ በሬ ድረስ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል (ካላ ገዛኸኝ፣ ጋሞሌ፣ ጥር 24፣ 2006 ዓ.ም፣ 21)፡፡ እነዚህ ሁሉ ከባድ ቅጣቶች ወንጀለኞችን ወደመካዱ እንዳያዘነብሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

## 4.6 በባህላዊ ስርዓቱ ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችና የተሰጡ ውሳኔዎች

Katz (1965: 356) የተባሉ ምሁር ባቀረቡት የጆርናል ጽሁፍ ላይ የግጭት ዓይነቶችና የሚከሰቱባቸውን ምክንያቶች አስመልክተው በ3 (ሶስት) እንደሚከፈሉ ይገልጻሉ፡፡ እነርሱም የኢኮኖሚ፣ዕሴትና የስልጣን ግጭቶች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ለነዚህ ግጭቶች መንስኤ የሚሆኑት ደግሞ ውስን የሀብት ክምችትን በግል ለመቆጣጠር በሚኖር ፍላጎትና ስልጣንን ለማቆየት ወይም ከፍ ለማድረግ በሚፈጠር ሽኩቻ መሆኑን አያይዘው ያብራራሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት በኮንሶ ብሔረሰብም ለግጭት መንስኤ ሆነው በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች ሀብት ንብረትን አስመልክቶ በዋናነት ከመሬት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ሴት ልጅን ከመድፈር ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ፣ ከላይ ከተጠቀሰው ደግሞ ስልጣንን ከመሻት፣ ከውኃ አጠቃቀምና ከግጦሽ መሬት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ መሆናቸውን በመስክ ቆይታ ወቅት በተደረጉ ቃለመጠይቆች መገንዘብ ተችሏል፡፡

መሬት ለኮንሶ ሕዝብ የደም ስርና የሕይወት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በመሬት የተነሳ የሚፈጠር ግጭት በቀላሉ አይበርድም፡፡ በመሆኑም በተደጋጋሚ ይከሰታል። ይሁንና ተደጋግሞ እንደመፈጠሩ መፍትሄ የሌለው ግን አይደለም፤ የባህል ስርዓቱ ለዚህ ያበጀው ከቀላል እስከከባድ የሚደርስ ቅጣት አለው። በዚህ ረገድ የሚከሰተው ግጭት አሁን አሁን መጠኑ የቀነሰ ቢመስልም ከሌሎች ግጭቶች በከፋ ዛሬም የመሬት ግጭት በቀዳሚነት የሚነሳ ጉዳይ ነው። የመሬት ግጭት ብዙውን ጊዜ መንደር ከመንደር (ፓሌታ ከፓሌታ) በቡድን በመደራጀት የሚፈጽሙት ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ግጭቶች ሲከሰቱ ጦርነት እስከማስነሳት ይደርሳሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ብዙ ሰዎች ይሞታሉ። በዚህ ዓይነቱ ግጭት ለሞቱ ሰዎች ካሳ የላቸውም። ሞቱም አይባልም። አይለቀስላቸውም። ታመው አልሞቱ ለመሬታቸው ለድንበራቸው ሲሉ ነው ይባላል። ከለቅሶ ይልቅ ደስታ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ግጭቶች ለባህላዊ ስርዓቱ ተደጋግመው ከሚቀርቡት በቀዳሚነት ተጠቃሽ ይሆናል።

በመስክ ቆይታ ወቅት ከአቶ ኪሮስ ጃርሶ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ከመሬት ጋር ተያይዞ በብሔረሰቡ ግጭቱ በተደጋጋሚ እንደሚከሰትና በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዳኝነት እንደሚያገኝ፣ እርሳቸውም በሽምግልናው የተሳተፉ ስለመሆናቸው የደርግ ጊዜ ሶስት አብነቶችን እንደማሳያ በማንሳት ያስረዳሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም 37)።

## አብነት አንድ

*"ከመሬት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ግጭቶችን በማስታረቅ ብዙ ተሳትፎ አለኝ በወጣትነቴም በመንግስት ስራ ሆነ በባህላዊ መንገድ በአመራርነት ሰርቻለሁ ልምዱ ስለነበረኝ ብዙ ተሳትፌያለሁ በዚሁ ልምዴ ቀደም ሲል በደርግ ወቅት 1970ዎቹ ውስጥ ነው ዱራይቴና ደራ ቀበሌዎች ወይም መንደሮች በድንበር ተጋጭተው ጦርነት ተከፍቶ ብዙ ሰው ሞቶ በኋላ በሽምግልና ያስታረቅንበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ አሁንም በዚህ መንግስት በኢህአዴግ 1991 ዓ.ም አካባቢ እነዚሁ ቀበሌዎች በዚሁ በድንበር ወይም በመሬት ጉዳይ ተጣልተው ነበር እርቁ ሲፈጸም ተዋናይ ነበርኩ በዕርቁ ወቅት በኮንሶ አካባቢ ያሉ ሽማግሌዎች በሙሉ ከአጎራባች ወረዳም ተጠርተው ላም አንገቷ ብቻ ታርዶ[10] እንዲሁ እንድትቀበር ተደርጎ ዕርቁን እንደፈጸምን አስታውሳለሁ"* ሲሉ ይናገራሉ።

---

[10] የላሟ አንገት ታርዶ መቀበሩ ይህ ድርጊት ዳግመኛ መነሳትም ሆነ መቀስቀስ የለበትም በማያዳግም ሁኔታ ተቀብሯል የሚለውን ለማመልከት መሆኑን ከመረጃ አቀባዩ መረዳት ተችሏል።

## አብነት ሁለት

*"ሌላው አሁንም በደርግ ወቅት ነው ቱርና ካመሌ ቀበሌዎች ወይም መንደሮች በመሬት ተጋጭተው ለሽፍትነት ደረጃ ተዳርሰው እስከመጋደል የበቁበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ ግጭቱ ለ3 እና 4 ቀናት ሳይሆን ለብዙ ወራት የተዋጉበት ነበር በመጨረሻ ከካራትም ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰሚነት ያላቸው ሽማግሌዎች ተጠርተው እኔም ተዋናይ ሆኜ ኦርባሌ የሚባል ወንዝ የሁለቱንም ቀበሌ የሚያዋስን ወንዝ አካባቢ ፍየል ታርዶ እንዳለ እንድትቀበር ተደርጎ ባህላዊ ኑዛዜ ተሰጥቶ ካመሌ ወደኋላ ፊቱን አዙሮ ሲሄድ ቱሮም እንዲሁ ጀርባውን አዙሮ ወደመንደሩ ሲሄድ አስታውሳለሁ ከዚያ ወዲህ እስካሁን ድረስ ያ እየታወሰ ዕርቁ ጸንቶ እስካሁን በሰላም ይኖራሉ"* ሲሉ ያነሳሉ፡፡

## አብነት ሦስት

*"አሁንም በደርግ ወቅት 1976 ዓ.ም ነው ፖርቃራና ገዋዳ ቀበሌያት እንደዚሁ በመሬት ተጋጭተው ተዋግተው ብዙ መሳሪያ ተማዝው እስከ አርባ ሰው የሞተበትን በአካል የተሳተፍኩበት ስለሆነ አስታውሰዋለሁ ይሄ ሁሉ ሆኖ በኋላ በአካባቢው ሽማግሌዎች ከካራት ከፋሻ ከገዋዳ እንዲሁም ከተለያዩ የኮንሶ አገልግሎቶች ሁሉ ሽማግሌዎች ተሰባስበው ቲማያ በምትባል ቦታ ደልቤና ወንዝ አካባቢ ፍየል ታርዶ እንዲሁ እንዳለ እንዲቀበር ተደርጎ የዕርቅ ስርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ ሕዝቡ እስከዛሬ ድረስ በሰላም ይኖራል"* በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሴት ልጅን መድፈር በተመለከተ አሁን አሁን በብሔረሰቡ እምብዛም የሚታይ ባይሆንም በድሮ ጊዜ ግን በተደጋጋሚ ይከሰት ስለነበር በባህላዊ ስርዓቱ ከባድ ቅጣት ይጣልበት እንደነበርና ያ የቅጣት አሻራ ዛሬም ድረስ በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች ስለሚነሳ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርጾ ስለሚገኝ አሁን ባለበት ሁኔታ ለመቀነሱ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው መረጃ አቀባዮቹ ካላ ገዛኸኝና ኪሮስ ሲያብራሩ ፡-

> ***‹‹ሴት ልጅን መድፈር በብሔረሰቡ ከፍተኛ ግጭት የሚያስነሳ ሲሆን፣ ይህን የፈፀመ በጥንት ጊዜ በቁም ሳይገደል እስከመቅበርና ገደል እስከመጨመር የሚደርስ ቅጣት ይፈፀምበት እንደነበር ቀደምት አዛውንቶችን በመጥቀስ ያስረዳሉ፤ ይህ ቅጣትም ከነፍስ ግድያ የባሰ ከፍተኛ ወንጀል እንደነበረ አስረጂ ነው››*** (ጋሞሌ፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 13፤ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 37) በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል ተደጋግመው ባይሆንም አልፎ አልፎ ከስልጣን መሻት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች እንዳሉ ካምብሮ የሚከተሉትን ሁለት አብነቶች በማንሳት ይገልጻሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 40)፡፡

### አብነት አንድ

*"ግጭቱ የተቀሰቀሰው ከስልጣን መሻት ጋር በተያያዘ ሲሆን ወቅቱ በ1966/67 አካባቢ ነው በቃዋሻና ካይሎላ መካከል የተከሰተውን አስታውሳለሁ ከሁለቱ አንዱ የኼላ ስልጣንን ለመረከብ ያቀደ ቡድን ነበር ኼላ ማለት በየ18 ዓመቱ የሚቀያየር የወጣት ትውልድ ቡድን ስልጣን ነው፤ በዚህ ሁኔታ የቀደመው ቡድን ስልጣን አብቅቶ ለአዲሱ ወጣት ትውልድ ማስረከብ የሚገባው ቡድን ነው በወቅቱ በባህላዊ ስርዓት ይህ የአባት ቡድን ስልጣኑን በስርዓት ማስረከብ ሲገባው ማስረከብ አልፈለገም ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግጭት ተፈጠረ፤ በዚያን ወቅት በአካባቢው ድርቅና ረሀብ ስለነበር የመካነየሱስ ድርጅት በሄሊኮፕተር ለተራብ ሰው እህል ያመላልስ ነበር፤ እህሉን በሚያመላልስበት ጊዜ ወጣቱ ክፍል ስልጣኑን መረከብ የሚፈልገው አፍላ ጉልበት ስላለው እህሉን ከመኪና ያወርዳል ያመላልሳል የጉልበት ገንዘብም ያገኛል፤ገንዘብ በዚህ መልኩ ስለሚያገኝ እንዴት ይሄ ያረጀ ቡድን ስልጣኑን አይሰጠንም በማለት የተነሳሱበት ነበር፤ ይሄ በአካባቢው ከዚያ በፊት አልተለመደም፤ ስለዚህ ያንን በመተማመን ይጠጣሉ ማታ ማታ ማሻዋዳ በየሳር ቤት ላይ ያለ እንስራ ነው እሱን ይመታሉ፤ ድንጋይ ይወረውራሉ፤ የሰው አጥር ያፈርሳሉ፤ ጠዋት ማን ሰበረ ማን አፈረሰ ሲባል የወጣቱ ቡድን የሽማግሌው ቡድን ይላል የሽማግሌው ቡድን ደግሞ የወጣቱ ቡድን ነው ይላል ፤በዚህ ሁኔታ መናቆርና መደባደብ ሆነ ህጻናትና አሮጊቶች ከቤት መውጣትና መንቀሳቀስ አይችሉም ነበር፤ በኋላ በባህል ሽማግሌዎች አማካኝነት ከሌላም ቀበሌ እንዲመጡ ተደርጎ ሁለቱን አካላት በማደራደር በሽምግልና ችግሩ የተፈታበትና ሰላም የወረደበትን ጊዜ አስታውሳለሁ"* ሲሉ ይገልጻሉ።

### አብነት ሁለት

*"በምርጫ 1997 ዓ.ም ወቅት ነው ዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ውስጥ ነዋሪው ለሁለት የተከፈለበት ሁኔታን አስታውሳለሁ፤ የመንግስት ደጋፊ ሌላው የተቃዋሚ ድርጅት በሚል በዚህ የቡድን ግጭት ማታ ማታ ድንጋይ በመወራወር ቤት በማፍረስ በመደባደብ ትልቅ ሁከት ተከስቶ ነበር፤ በዚህ ግጭት ቆርቆሮ ቤት የፈረሰባቸው ሰዎች ሁሉ ነበሩ፤ ሰው ሁሉ ከቤት መውጣት ያልቻለበት ብዙ ቀናት የፈጀ ግጭትና ትልቅ ጸብ ነበር፤ ይህም ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ መንግስት ለማስታረቅ ቢሞክርም አልቻለም፤ መጨረሻ ላይ እኔም ባለሁበትና በተሳተፍኩበት በባህል በሞራ ላይ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ችግሩን አቃለው ግጭቱን ፈትተው ይሄው ዛሬ ምንም እንዳልተከሰተና እንዳልተጣሉ መስለው የሚታዩበት ሁኔታ አለ"* በማለት ያነሳሉ።

ሌላው በብሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ላይ በተደጋጋሚ የሚቀርቡት ከውኃና ከግጦሽ መሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ግጭቶች ናቸው። በኮንሶዎች ዘንድ "ፒሻ ዋቃ ና ማ ካ ፒናና ካሶ እክኒ" ውኃ የግል ሳይሆን የእግዚአብሔር ሀብት ነው ይባላል። ለሰውም ለአራዊትም የተሰጠ ስጦታ ነው ይላሉ። ማንም ማንንም ሊከለክል አይችልም። በመሆኑም በኮንሶ የውኃ ምንጮች፣ ጉድጓዶችና ኩሬዎች የሕዝብ ሀብት ናቸው።

አንድ የቀበሌ ገበሬ ማህበር ወይም የቀበሌ አስተዳደር/ፓሌታ በክልሉ ከላይ የተጠቀሱ

የውኃ ሀብቶች ይኖሩታል፡፡ በምንጭ ጠረጋ፣ በኩሬ ቁፋሮና ውኃ ነክ በሆኑ የሥራ ዘመቻዎች ወቅት አጐራባች ቀበሌያት ሁሉ ይተባበራሉ፡፡ በአጋጣሚ አለመግባባቶች ወይም የድንበር ግጭቶች ተፈጥረው እንኳን ቢሆን አንዱ ቀበሌ በራሱ ክልል ውስጥ ካለው የውኃ ተቋም ሌላውን እንዳይጠቀም ማገድም ሆነ መከልከል አይችልም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ከግጦሽ መሬት ጋር በተያያዘ በቀበሌያት መካከል ለግጭት ዋና መንስኤ የሆነው የድንበር ይገባኛል ጉዳይ ተነስቶ ግጭቶች እስካልተነሱ ድረስ ቀበሌያት የቀበሌው የጋራ ይዞታ በሆነው የግጦሽ መሬት ከመጠቀም አልፎ በአጐራባች የግጦሽ መሬት መጠቀም ይችላሉ፤ ይሁንና ይላሉ መረጃ አቀባዮቹ ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ዲኖቴ ኮጫኔና ሳጎያ፡-

> *‹‹አሁን አሁን ከብሔረሰቡ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ፣ ከውኃና ከግጦሽ መሬት ጥበት ጋር በተያያዘ ግጭቶች ይከሰታሉ››* (በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 30፣ 37፣ ቡርቂዳ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 47፣ 49) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ግጭቶች ሲነሡ ከድንጋይ መወርወር ጀምሮ ወንጭፍ መወነጫጨፍ፣ ጦር መወራወርና ጋሻ መመከትን አልፎ በጦር መሳሪያ እስከመታኮስ ይደርሳሉ፡፡ ይሁንና ይህ ሁኔታ እየከፋ ከመምጣቱ በፊት ግን በጐሳ መሪዎች፣ በቱራይታዎች፣ በአፓ-ቲንባዎች፣ በሰንቀሊታዎችና በዳውራዎች አማካኝነት በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ግጭቶቹ እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ዲኖቴ፡-

> ‹‹*በዚህ ስርዓት ላይ ከላይ የተጠቀሱት አካላትና ሌሎች ከአጐራባች ቀበሌያት አግባብ ያላቸው ሰዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ፤የዕርቁም መደምደሚያ ቁብ ፍየል በቁም መቅበር ወይንም ወሬ በማመሳለስ ቀበሌን ከቀበሌ የሚያጋጩ ሰዎች ምላሳቸው ይህንን ተግባር እንዳይደግም ወይም ደግሞ እንዳይፈፅም በሚል የፍየሏን ምላስ ቆርጦ በማውጣት ድርጊቱን ለተሳተፈው ያመለክታሉ፤ በመጨረሻም የፍየሏ ስጋ ሳይበላ እንድትቀበር ትደረጋለች፤ እነዚህ ሁሉ ሂደቶች የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ናቸው፤ ይህ ሁሉ ከመፈጸሙ በፊት ግን የቀበሌያቱ አባላት እየተዋጉ ሳሉ አግባብ ያላቸው ዳውራዎችና የጎሳ መሪዎች በስፍራው ከሄዱ ጦርነቱ ወዲያው ይቆማል፤ ሊወረወር ታስቦ ሊሰበቅ የነበረው ጦር ወደ ትከሻ ይመለሳል፤ ጦረኞቹም በቀጥታ ወደመጡበት ሰው አየኝ አላየኝ በማለት ይመለሳሉ*›› (በደንገልቱ፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 30) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

እዚህ ላይ ሴቶች ለዚህ ዓይነቱ ግጭት መቀስቀስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አቶ ካምብሮና አያኖ በዚሁ የቃለመጠይቅ ወቅት ይገልጻሉ፡፡ ይህ አስተዋጽኦም የሚኖሩበትን ቀበሌ ወንዶች በማሞካሸትና ሌላውን በማጥላላት ለመጀመሪያ ጊዜ ድንጋይ በመወርወርና

ወንዶችን እያደፋፈሩ ለጥሉ በማነሳሳት ስንቅ በማቀበልና ተመትቶ የወደቀውን በማንሳት እንደሆነም ያብራራሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 40፣ 44)፡፡

## 4.7. የፎክሎር ሚና በኮንሶ ባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት

ፎክሎር በህብረተሰብ ውስጥ ያለው ሚና የሚታወቀው ሰዎች እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር (ግንኙነት) ውስጥ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና የሚንጸባረቀበት በመሆኑ ነው፡፡ ከአዎንታዊ ሚና ውስጥ የሚጠቀሰው ሰዎች በሚኖራቸው መስተጋብር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ማገልገሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ሽምግልናን ማንሳት ይቻላል፡፡ በሽምግልና ወቅት ከፎክሎር ዘርፎች ስነቃሎች ማለትም ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረቶች፣ አባባሎች ወዘተ... በሽማግሌዎቹ አንደበት ይነገራሉ፡፡ እነዚህ ስነቃሎች የተጋጩትን ሰዎች ለማቀራረብ ወይም የእርቅ ሀሳብ ለማቅረብ ዋነኛ መሳሪያ ሆነውም ያገለግላሉ፡፡ በተሸምጋዮች በኩልም የተጣሉት ሰዎች ሀሳባቸውን ለሽማግሌዎች ለመናገር፣ የበደላቸውን መጠን ሳይቀር በስነቃል አማካይነት ሲገልጹ ይስተዋላሉ፡፡

በዚህ መነሻነት በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓት የራሱ ሂደትና ስርዓት ያለው ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ሽማግሌዎች ዕርቁ ከጅምሩ የሰመረ እንዲሆን፣ አፈጻጸሙም መልካም እንዲሆን በማለት ንግግራቸውን በአንዳንድ አባባሎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይጀምራሉ፡፡ በኮንስኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ‹ዶይ› በመባል ይታወቃል፡፡

ህብረተሰቡ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ሲገናኝ በንግግርና በጨዋታ መሀል ከሁኔታዎችና ከሚነገረው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ሀሳብን በምሳሌ አጉልቶና አስረግጦ ለማስተላለፍ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይጠቀማል፡፡ በተለይ በሽምግልና ወቅት የጸቡን አላስፈላጊነት ለማስረዳትና አጥፊን ለመውቀስ ወይም የዕርቅን ስርዓት አቅጣጫ ለማስያዝ ሽማግሌዎች በንግግራቸው ጣልቃ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚጠቀሙበት ሁኔታ አለ፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በባህላዊው የግጭት አፈታት ቅድመ ስርዓት፣ በስርዓቱ ጊዜና በድህረ ሰርዓቱ ወቅት አገልግሎት ላይ በመዋል ለስርዓቱ ዕውን መሆን ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለዚህም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከመረጃ አቀባዮች በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ መልኩ የተገኙ አብነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የዕርቅ ስነ-ስርዓት ሲከናወን የአገር ሽማግሌዎች ስርዓቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚከተለውን በማለት ይጀምራሉ፡፡ ልመናው (አባባሉ) በመገኛ ቋንቋውና ወደ አማርኛ ተመልሶ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

| **አባባሉ በመገኛ ቋንቋው** | **ወደአማርኛ ሲመለስ** |
|---|---|
| ዋቃ እኖ ኦሊ ቻዶ | እግዚአብሄር እስከመጨረሻው ከእኛ ጋር ይሁን፡፡ |
| ሱፓ ኦራታ ኤታኖ | ወደ ሆድ የሚገባ ሁሉ ስምም ይሁን፡፡ |
| ቃታንባያ ቃራ ዋቃ | አድልኦ በፈጸሙ ላይ እግዚአብሄር የፈላ |
| ፒሻ ኩብና ቱቆ | ውሃ ይድፋባቸው፡፡ |
| አፋን ታካን | በአንድ አንደበት ተናጋሪ እንሁን፡፡ |

ካሉ በኋላ "ዋቃ ኢሽን ኦሊ ዳቾ" እግዚአብሄር ከናንተ ጋር ይሁን በማለትና ዕርቁ እንዲሰምር፣ እግዚአብሄርም እርቁን እንዲመራው በመለመን የስርዓቱን መጀመር የሚያበስሩበት አባባል ነው፡፡ እነዚህም አባባሎች በእያንዳንዷ እንቅስቃሴ ወቅት ስርዓቱ እንዳይደናቀፍና ያለአንዳች መሰናክል ወደተፈለገው አቅጣጫ እንዲጓዝ እግዚአብሄር የሚለመንበት ነው፡፡ የልመናውም ቃል በእርቅ አስፈጻሚዎቹም ሆነ በዕርቅ ፈጻሚዎቹ ዘንድ በውስጥ እንዲሰርጽና የሚቀበሉት እንዲሆን፣ ስርዓቱም ያለአድልኦ በትክክለኛው መንገድ ይፈጸም ዘንድ አባባሎቹ የቅድመ መማጸኛ ሃሳቦች በውስጣቸው መያዛቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ከዚህ በታች የቀረቡት 3 (ሶስት) ምሳሌያዊ ንግግሮች በስርዓቱ መንደርደሪያ በሽማግሌዎች የሚቀርቡ ናቸው፡፡

| **አባባሉ በመገኛ ቋንቋው** | **ወደአማርኛ ሲመለስ** |
|---|---|
| ፋታው ፋቴ ጫርሳ ቢቴ ፋላ | ፍለጥ ቁረጥ ዞሮ ዞሮ ሽማግሌ ይቸገርበታል፤ |
| | ተጨንቆም፣ ተጠብቦም ዕርቅ ያወርዳል፡፡ |
| ቂሞታ ኡታ ኦራ ዳማኒ | ሽማግሌ አር ያበላል፣ ሽማግሌ በዚህም በዚያም ያሳምናል፡፡ |
| ኦራ ኦሊ ደክኖ እደራኒ | በዕርቅ የሚተዳደሩ ረጅም ዘመናት ይኖራሉ፡፡ |

እያንዳንዳቸው የሚያስተላልፉትን መልዕክት ስንመለከት ከሳሽና ተከሳሽ (በዳይና ተበዳይ) ችግሮቻቸውን ያለአንዳች መሸፋፈን ወይም ፍራቻ በግልጽ ደፍረው እንዲናገሩ የሚያበረታቱ፣ ጉዳዩ ቀላልም ሆነ ከባድ ሽማግሌ የሚፈታው መሆኑን የሚያበስሩ፣ የሽማግሌዎችን ሚና የሚያመለክቱና ለዕርቅ መዘጋጀት የመልካም ሰው ባህሪና ዕርቅ አውርዱ የሚል መልዕክትን የያዙ ናቸው።

የዕርቅ ስነ-ስርዓት ከመጀመሩ አስቀድሞ እና ከስርዓቱ መንደርደሪያ በተጨማሪ በብሔረሰቡ ዘንድ የዕርቅ ስርዓቱ የሚፈጸምባቸው ባህላዊ ቦታዎች በራሳቸው ተጽዕኖ ያላቸው ናቸው ተብሎ ስለሚታመን በስነ-ስርዓቱ ወቅትና ከስርዓቱ በኋላ የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም ጉዳዩን ወደዕልባት ያደርሳሉ። ከዚህ በታች የቀረቡት 5 (አምስት) ምሳሌያዊ ንግግሮች በስነ-ስርዓቱ ወቅትና ከስርዓቱ በኋላ በሽማግሌዎች የሚቀርቡ ናቸው።

| አባባሉ በመገኛ ቋንቋው | ወደአማርኛ ሲመለስ |
|---|---|
| ቶላ ኦሊ ደክኖ እደራኒ | በሀቅ የሚደራደር ቤተሰብ ዕድሜው ይረዝማል። |
| ዱካታ ኦላ | እውነት ጥገት ላም ናት። |
| ዱካታ ቃራ ዋቃ ፒታ ሳህኒ | እውነት ትመነምናለች እንጂ አትሞትም። |
| ኬራ ኩያታ ኩያታ ቃብኒ<br>ኦ ሀልኬታ ቃብኒ | የቀን ሌባ ቀን የሌሊት ሌባ ሌሊት<br>ያጋልጠዋል። |
| ኦራባ አላውኖ አሊ ናማንካሊ | መልካም ምላስ ጠብን ታበርዳለች። |

ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በእርቅ አፈጻጸም ስርዓቱ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ አላቸው። ይህም ጠበኞቹን ወደትክክለኛው አቅጣጫ ከመምራት ባሻገር እውነቱን እንዲናገሩ የመገፋፋትና እርቁንም በማፋጠን ረገድ ሚና እንዳላቸው አስረጂ ሆኖ የቀረበ ነው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት 9 (ዘጠኝ) ያህል ምሳሌያዊ ንግግሮች በተመሰሳይ እንዲሁ በስርዓቱ ጊዜና በስርዓቱ መደምደሚያ የሚቀርቡ ናቸው።

| አባባሉ በመገኛ ቋንቋው | ወደአማርኛ ሲመለስ |
|---|---|
| ቂሞታ ካ ዋቃ ታካ | ሽማግሌዎች በእግዚአብሄር ይመሰላሉ። |
| ቂሞታ ቃራን ኦፌ ላጺንንቻን | ከሽማግሌዎች ቃል ፈጽሞ አይወጣም/ አይታለፍም። |

| | |
|---|---|
| ዋ ቂሞታ ፒሻን ቱቅቴ | ሽማግሌዎች እንደውሀ የተፉት፣ የወሰኑት፣ የሆነ፣ ያለፈና የማይደገም ነው። |
| ሎላ ታርቤ ቃቃባምንቾ | ያለፈ ደራሽ ውሀ አይመለስም። |
| ኾራታ ላኪን ቃብቶ | የቅጣት ወይም የውሳኔ ሁለት የለውም። በዛም አነሰም አንዴ ነው። |
| ቂሞታ ቶቶፓ ናማን ካሊ | ሽማግሌዎች ከሞት አፋፍ ይመልሳሉ። ያድናሉ። |
| ናማ እሲ ቃሮባ ኮላታ ቲቲኒ | በዕርቅ ድርድር ወቅት ሁሉም ንጹህ ነኝ ባይ ነው። |
| ካፊታ ቃራ ኮራ ዳኒ ማ ኦፈ ቃራ ቃኒንቻን | የጎሳ አባልን በገንዘብ እንጂ በነገር አይረዱትም። |
| ኾራ ኦራ ቶአንተኒንቾ | ቅጣት ማንንም ማህበረሰብ አላበለጸገም። |

እነዚህ የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሽማግሌዎች በስርዓቱ ያላቸውን ሚና ከእግዚአብሄር ጋር በማመሳሰል የሚናገሩትና የሚወስኑት የተከበረ መሆኑን፣ ከሽማግሌዎችም የሚሸሽግ ነገር አይኖርም ብንሸሽግ ተጎጂ እንሆናለን፣ ያለፈን ነገር ማስታወስ አይገባም የሚል መልዕክት ይዘዋል። ስለዚህ በግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ የተለያዩ አባባሎች፣ ምሳሌዊ ንግግሮች እንዲሁም ልዩ ልዩ በድርጊት የሚገለጹ ክንውኖች የተፈጠረውን ግጭት በማርገብና ወደ እልባት በመውሰድ ረገድ ምን ያህል ሚና እንዳላቸው ከቀረቡት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል ማለት ነው።

## 4.8. የባህላዊ ስርዓቱ ፋይዳ

እንደቡድን ተወያዮቹ ገለጻ ከሆነ ኮንሶዎች ባለፉት አምስትና ስድስት መቶ ዓመታት ከዚያም በላይ በሆነ የዕድሜ ዘመናቸው በውስጣቸው የሚፈጠሩ ከቀላል እስከከባድ ግጭቶቻቸውን በራሳቸው ዕልባት በመስጠት በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓታቸው የሚታወቁ ሲሆን ዛሬም ድረስ እየተገለገሉበት ይገኛሉ። ማህበረሰቡም ስርዓቱን ከልጅነት ጀምሮ በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች እየተማረው ተዋህዶት አብሮት ያደገ ስለሆነ ከልጅ አስከ አዋቂ ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ ተገዢ በመሆን ለዘላቂነቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ ስርዓት አስተማማኝነትም ሆነ ዘላቂ መሆን በዋናነት የሚጠቀሰው በባህላዊ የዳኝነት ስርዓቶች ውሳኔ ያገኙ ልዩ ልዩ ጉዳዮች በማህበረሰቡ (በበዳይና በተበዳይ) ዘንድ ተፈጻሚ መሆናቸው ነው ይህንንም ከላይ ከቀረቡት አባባሎች መረዳት ይቻላል። በማህበረሰቡ ዘንድ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት አከናዋኝ ዳኞች የተሰጠ ማንኛውም ውሳኔ ይከበራል (ኪሮስ፣ በደንገልቱ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 34)። ለዚህ ስርዓት አለመገዛት ብሎም ላለመገዛት አዝማሚያ ማሳየት በራሱ ለተጨማሪ ቅጣት ይዳርጋል፤ ከመኖሪያ ቀዬ ያሰድዳል፤ ከተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችም ያስገልላል።

ማህበረሰቡ እጅግ ተቀራርቦ የሚኖር በመሆኑ ከማህበራዊ አገልግሎቶች መነጠሉ ግለሰቡን ለከፋ ችግር ይዳርገዋል። እነዚህ ሁኔታዎች በራሳቸው ለስርዓቱ መቀጠል ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ ሌላ በቡድን ውይይት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በማህበረሰቡ ዘንድ በአንድ ወቅት የተከሰተ ግጭት በአገር ሽማግሌዎች ከተፈታና "ኡንታ ሎካዬን" እህል ታኝኮ ወይም ተቀምሶ ከተተፋ ወዲያ "የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን" እንደሚባለው ጉዳዩ ዳግመኛ አይነሳም፡፡

በሌላ ዕርቅ ላይ እንደ ምሳሌ ከማንሳት ውጪ ፣ይህ አካሄድ በመደበኛው የህግ ስርዓትም ተቀባይነት እንዳለው ይገልጻሉ። በሁለቱ ወገኖች የተፈታውን ጉዳይ ሌላ አካል ቢያወሳው ይወገዛል። ዕውነት ቢኖረውም ማለትም የተበደለ ወገን እንኳን ቢሆንም እንደበደለኛ ይቆጠራል። ጠላትነቱም የበደለው ወገን ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ይሆናል ይላሉ።

እንደመረጃ አቀባዮቹ ዲኖቴ ኮጫኔና ሳጎያ አገላለጽ ከሆነ፡-

> ***‹‹በኮንሶዎች ዘንድ ሐንጩፍታ ቱፈን ኤላ ኦሪንክቶ የተተፋ ምራቅ መልሶ አይላስም ፤ኡታ ኮኬ ኦፈ ቆይንንቻን የደረቀ አር ተመልሶ አይርስም እየተባለ ስለሚነገር አንዴ በዕርቅ ያለቀ ወይም የተደመደመ ነገር ዳግም አይነሳም፤ ተጋጪዎችም ከዕርቅ በኋላ ወዲያው ወደ ሰላማዊ ህይወት ይመለሳሉ፤ ከማህበራዊ ግንኙነትም ሆነ ከስነ ልቡና አንጻር በከፍተኛ ሁኔታ ይለወጣሉ፤ የተነቃቁም ይሆናሉ››*** (ቡርቂዳ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 46፣ 48) ሲሉ ይገልጻሉ።

ይህ ደግሞ የስርዓቱን አዎንታዊ ጎን ይበልጥ ያጎላዋል። ምክንያቱ ደግሞ ማህበረሰቡ እጅግ ተጠጋግቶና ተቀራርቦ የሚኖር በመሆኑ፣ የእርሻ መሬቱም የተያያዘ በመሆኑ፤ እንዲሁም ማህበራዊ ተቋማቱ የተቀራረቡና ተጠቃሚነታቸውም የጋራ ከመሆኑ አንጻር

አንድነታቸውና ህብረታቸው የጠነከረ ነው። ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚኖር ሕዝብ (ማህበረሰብ) የጠፋበት ሰላም ዳግም ተመልሶ ሲመጣለት፣ የነበረው ግጭት ሲበርድና መልካም ድባብ ሲፈጠርለትና የቀደመ ማህበራዊ ግንኙነቱ ሲቀጥል ማየት ፋይዳው እጅግ የጎላ እንደሆነ የቡድን ተወያዮች አቶ ገሀኖ ሶካና አቶ ፈረንጨታ (በደንገልቱ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም) ሀሳቡን በማጠናከር ይናገራሉ።

የኮንሶ ብሔረሰብ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ይልቅ በባህላዊ ስርዓቱ መዳኘትን ይመርጣሉ። ለዚህ ደግሞ እንደመሰረታዊ ምክንያት የሚያስቀምጡት ባህላዊ ስርዓቱ በዲሞክራሲያዊ መርህ የሚመራ፣ አድልኦ የሌለበትና ፍትሀዊ መሆኑ፣ ምስክሮች በባህላዊ ስርዓት መሀላ ስለሚፈጽሙና ትክክለኛ የምስክርነት ቃል ስለሚሰጡ፣ የዕርቅም ሆነ የዳኝነት ስርዓቱ ብዙ የስራ ጊዜ የማይሻማ መሆኑ፣ የዕርቅም ሆነ የዳኝነት ስፍራው ከመኖሪያ ሰፈር አለመራቁ፣ በቋንቋው መዳኘቱ፣ ስርዓቱ በዕርቅ መደምደሙ፣ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ቦታዎችም በባህላዊ እምነት ተፅዕኖ ስላላቸው ፍርዶች ሁሉ በአብዛኛው ትክክለኛ ናቸው ተብሎ ስለሚታመንና የመሳሰሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊ ስርዓቱ ሕያው መሆኑ፣ ማህበረሰቡም የሚኖረው በባህላዊ ስርዓቱ ውስጥ መሆኑና የዕለት ተዕለት ኑሮው የተሳሰረውም በስርዓቱ ውስጥ በመሆኑ የሚመርጠው መሆኑን በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር በሞራ ከንታ የተካሄደውን የሁለት ቀላል የግጭት ዓይነቶች የአፈታት ስርዓት አስመልክቶ ከአካል ምልከታው ጎን ለጎን በባህላዊ ስርዓቱ ፍርድ ያገኙትን የወ/ሮ ሻካያ ሴንዴኮንና የአቶ ገለቦ አንጎኖን ከዕርቅ በኋላ ያለን ስሜት በቃለመጠይቅ ለመረዳት በተደረገው ጥረት የነበረውን ምላሽ ማንሳት ይቻላል (ጥር 18፣ 2006 ዓ.ም)።

በብሔረሰቡ "ወንድምን በገንዘብ እንጂ በነገር በማዳላት አይረዳም" እየተባለ ስለሚነገር፣ በባህላዊ ዳኝነቱ የሚሰጡ ፍርዶች ሁሉ ተፈፃሚነት አላቸው። ለፍርዶቹ ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ ግለሰብ ወይም ቡድን ከማንኛውም ማህበራዊ አገልግሎት ቤተሰቡን ጨምሮ የተገለለ ስለሚሆን፣ ለስርዓቱ ተገዢ የመሆንና ስርዓቱን ማክበር በብሔረሰቡ ግድ ይሆናል። ስለዚህ ከዚህ በመነሳት ማህበረሰቡ ይህንን ስርዓት በእጅጉ እንደሚመርጠው በቡድን ውይይት ወቅት በአብዛኛው የቡድን ተወያዮች የተነሳና የተገለጸ ሀሳብ በመሆኑም ጭምር የባህላዊ ስርዓቱን ፋይዳ በእጅጉ ያጎላዋል ማለት ይቻላል።

# ምዕራፍ 5. የባህላዊና የመደበኛው የፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር

የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ ዛሬም ማህበረሰቡ አክብሮ እየተዳደረበት ያለ ትልቅ ተቋም መሆኑ ተገልጿል። ለዚህ ተቋም መጎልበት የማህበረሰቡ ድርሻ የጎላ ቢሆንም መደበኛው የፍትህ ተቋምም አሠራሩን ተቀብሎ በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ በቅንጅት የሚሠራበት ሂደት መኖሩ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል ማለት ይቻላል።

በዚህ ምዕራፍ የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የተመሰረተባቸው ማህበራዊ እሴቶች፣ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት መፍትሄ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ስላለው የግንኙነት ሁኔታ፣ የባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፤ እንዲሁም ለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዘላቂነት እንደስጋት የሚነሱ ተግዳሮቶች ተዳሰውበታል።

## 5.1 ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ የተመሰረተባቸው ማህበራዊ እሴቶች

በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ (ዴኻው) የተመሰረተው በብሔረሰቡ አጠራር "ካላታ" አብሮ በመኖር፣ በመረዳዳትና በመተጋገዝ፣ ወንጀለኛን በማጋለጥና በአካባቢው ሰላምና ፀጥታ በማረጋገጥ ላይ ነው።

ይህ ሀሳብ ጠቅለል ተደርጎ ሲቀመጥ በብሔረሰቡ አጠራር "ኦሲን ካላታ" በማህበራዊ "ኮዳ ኮዲታ" ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም "ሀዩማ" በፖለቲካዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ይቻላል። ማህበራዊ ሲባል ወይም በማህበራዊ ደረጃ የሚጠቀሱት እሴቶች አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላትና መጠጣት፣ አብሮ መስራትና ችግርን በጋራና በቅርበት መፍታት ወዘተ ሲሆኑ፣ ኢኮኖሚያዊ ስንል ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለአብነት አርሶ አደሩን ብንወስድ ለራሱ አርሶ ለመጠቀም አቅሙ ያልቻለውንና አጋዥ የሌለውን መሬቱን በማረስ እራሱን እንዲችል የማገዝ፣ አቅም ላለው መሬት በጊዜያዊነት በመስጠት አርሶ እንዲበላ ቀለቡን እንዲችል የማድረግ፣ ቀለብ የሌለውም ከሆነ በጉርብትና ተካፍሎ የመብላትና የመሸመት አቅሙን በተለያየ ደረጃ መደገፍና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። በፖለቲካ ደረጃ ስንመለከት በኮንሶ ውሸት መናገርም ሆነ በሀሰት መመስከር አልተለመደም። "ወንድምን በገንዘብ እንጂ በማዳላት አይረዱም ይባላል" ይላሉ። ይህ የኮንሶ

ብሔረሰብ የህይወት መርህና ፍልስፍናቸው ነው። ይህ ማለት በኮንሶ ወንጀል ሰርቶ ከማህበረሰቡ ማምለጥ አይቻልም። ወንጀለኛን ለአደባባይ አጋልጦ መስጠት ከቤተሰብና ከቤተዘመድ ይጀምራል። ይህ አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ሰርጿል። ለአካባቢው ሰላምና የተረጋጋ ህይወት መመስረትም የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ይህ የሚያሳየው ደግሞ የማህበረሰቡ ህይወት እርስ በርስ የማህበራዊ ህይወቱም የኢኮኖሚ ደረጃውም እንዲሁም የፖለቲካ ህይወቱ በሀቅ ላይ የተመሰረተ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል። እውነትን እንደባህል ይዞ መምጣት ይበል የሚያሰኝ ትልቅ እሴት ሲሆን ይህ በብሔረሰቡ ባህል ሆኖ ዘልቋል። አንድ ወንጀለኛ ለባህላዊ ህጉ የማይታዘዝና ደንቡን የማይቀበል ከሆነ ጥፋቱ እስኪገባውና ተፀፅቶ እስኪመለስ ድረስ እገዳ ይጣልበታል። ይገለላል።

ይሁንና በዚህ ጊዜ የቅርብ ቤተሰብ በማጋለጥ ተባባሪ የሆነውን ያህል ዘመዱን (ቤተሰቡን) ከተቀጣ በኋላ ችግሩን በመጋራት ረገድም ቀዳሚ ሆኖ ይሰለፋል። ሌላው ለባህል ህጉ መመስረትም ሆነ መዝለቅ ዋነኛ መደላድል ወይም የጀርባ አጥንት ሆነው የሚነሱ ቁልፍ እሴቶች አሉ። ከነዚህ መካከል የ‹‹ኼላ›› ስርዓት በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡

- **ኼላ** ማለት በብሔረሰቡ በስልጣን ላይ የሚገኘው ወጣቱ ትውልድ ማለት ነው። በዚህ ትውልድ በ የ18 ዓመቱ የስልጣን ሽግግርና ርክክብ ይደረጋል። ሥርዓቱ “ኸልታ” ይባላል። ሥልጣን የተረከበው ትውልድ ደግሞ “ኼላ” ተብሎ ይታወቃል። በስልጣን ላይ የሚሆነው ወጣት ትውልድ መሪ “ሰንቀሊታ” ተብሎ ይጠራል። በዚህ የኼላ ስርዓት ዕድሜው ከ19-25 የሆነ ወጣት ትውልድ ተሰባስቦ የትውልዱ የቡድን አባልነቱን ያረጋግጣል። የዚህ ትውልድ ቡድን ዋና ኃላፊነትና ተግባር አባቶች የሚሠሩትን ባህላዊ ስርዓት በቅርበት ሆኖ መከታተልና መማር፣ በአፓ-ቲንባ የሚመራውን የሕዝቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በንቃት መከታተል፣ ሥርዓቱን ከማናቸውም አደጋዎች መጠበቅና መከላከል፣ በባህል ስርዓቱ ላይ ለሽማግሌዎች የመላላክና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን የማመቻቸት ሥራዎች መስራት፣ ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ለምሳሌ የካብ፣ የኩሬ፤ የእርሻ ወዘተ ስራዎችን በማስተባበር መስራት ይጠቀሳሉ። በባህላዊ ዳኝነት ጊዜ የኼላ (የቡድኑ) ተወካዮች መኖራቸው አጥፊው የወጣት ቡድኑን (ኼላው)ን የሚነካ ስራ ከሰራ የቅጣቱን ዓይነትና መጠን እስከመወሰን የደረሰ ስልጣን አላቸው። ኼላው ከሌለ ጉዳዩን

ማስፈፀም ፈፅሞ ስለማይቻል ሁሉም አካል ስራውን የሚሰራው ኼላውን ይዞ ነው ማለት ይቻላል ፡፡

- ሌላው በ "ደ" እና በ "ም" የሚጠራው ቃል ነው፡፡ ቃሉ (ስሙ) ዝም ብሎ በከንቱ አይጠራም፡፡ አስፈሪም ጸያፍም ነው ይላሉ ፡፡ ስሙን አላግባብ መጥራት ኃጢያትም ቅጣትም ያስከትላል፡፡ መልኩ ቀይ ነው፡፡ ሰው ሲጣላና ሲፈናከት ከሰው የሚወጣ ነው፡፡ የ"ደ" ና የ "ም" ፊደላት ጥምረት ስሙን ይሰጣል፡፡ በማንኛውም ሁኔታና መንገድ ከክቡር ሰው ልጅ ደም እንዲወጣ ያደረገ ወይም ያለአግባብ ስሙን ከፍ አድርጐ የጠራ ሰው በሕዝብና በሀገር ላይ መዓትና ቁጣ እንዲመጣ ሰበብ ሊሆን ስለሚችል ለተወሰነ ጊዜ ከፓሌታ ይሰደዳል፡፡ ይህም የሚሆነው አምላክ ያንን ማየትም ሆነ መስማት አይፈልግምና ነው ይላሉ፡፡ ከታየና ከተሰማ የዋቃ ቁጣ በአካባቢው ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ሠላም ሆኖ መኖር ይኖርበታል፡፡ "ዋቃ" የሰው ልጆችን ያከብራል፡፡ የፈጠራቸውም በ"ደ" እና በ"ም" ፊደላት ጥምረት በሚጠራው ‹‹ደም›› ነው፡፡ እሱም የሰው ልጆች ሕልውና ነው፡፡ ስለሆነም በምንም መልኩ ያለ አግባብ ስሙን መጥራት አይገባም፡፡ የኮንሶ ሕዝብ የሠላማዊነቱ መሰረት ይህ ፍልስፍናና እምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

- በኮንሶ ባህል ከባድ ግጭት ከሚባሉት መካከል በዋናነት ሴትን ማባለግና ሌብነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ሁለት የወንጀል ድርጊቶች አስፈሪ ናቸው፡፡ የሕብረተሰቡን ደህንነት የሚያናጉና ሕልውናቸውንም የሚፈታተኑ ናቸው፡፡ በአንድ ፓሌታ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንደ አንድ አካል ይታሰባሉ፡፡ ከእነርሱ ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ወይም አስሩ ሴቶችን በማባለግና በሌብነት የሕዝቡን ሠላምና ደህንነት አደጋ ላይ ከጣሉ የሕዝብ ጤንነት ይበከላል፣ ሰላማዊ ሕይወቱ ይናጋል ይላሉ፡፡ ማህበረሰቡ በእነዚህ ሁለት ወንጀሎች ላይ ትዕግስት ሆነ ይቅርታ የለውም፡፡ አንድ ግለሰብ እየጠዘጠዘ እንቅልፍ የሚነሳውን የተቦረቦረ በሽተኛ ጥርሱን አስነቅሎ ሠላም እንደሚያገኘው ሁሉ ማህበረሰቡም በዚህ ተግባር የተሰለፉ ነውረኞችን አንቅሮ በመትፋትና ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የቅጣት እርምጃ በመውሰድ ሠላምን የማምጣት፣ ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብርን የማረጋገጥ ባህል፣ ስርዓትና ችሎታ አላቸው፡፡ ወንጀሉ የተረጋገጠባቸው ሰዎች ለአንድ ዓመት ያህል ከፓሌታው እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በስራቸው የሚያስተዳድሩዋቸው ሰዎች ካሉ እነርሱንም ይዘው እንዲወጡ

ይገደዳሉ። የቤት እንስሳትና የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎችን ሁሉ ይዘው እንዲወጡ ይደረጋሉ።

ከማህበረሰቡ ርቀው የሚሰደዱበት ቀን ለሕዝቡ ተነግሮ ልጆችና ሴቶች ቅንጭብ ሰብረው በማምጣት ከሚባረሩት ሰዎች ኂላ ኂላ እየተከተሉ ያመጣችሁብንን ክፉ መንፈስ ይዛችሁ ሂዱ እያሉ እያዜሙና የሚረግጡትን መሬት እየመቱ ከፓሌታው ያስወጧቸዋል። አጥፊዎቹም ከፓሌታው እስኪወጡ ድረስ ዞር ብለው ወደኂላ ማየት አይፈቀድላቸውም። ይህም የሚደረገው የተጠቀሱትን ወንጀሎች የሚፈጽም ሰው ክፉ መንፈስ ያረፈበት ሰው በመሆኑ እሱ ብቻ ሳይሆን ያመጣውም ክፉ መንፈስ ከሱ ጋር ከፓሌታው እንዲወጣ ለማድረግ ጭምር ነው። "የቅንጭብ እንጨት የእሳት አደጋንና መሰል ክፉ መናፍስትን ለማጥፋትና አርቆ ለማባረር" ተመራጭ ነው። እንዲሁም ሕዝቡ ይህንን ውርደት አይቶ ከዚህ እንዲማርና እንዲጠነቀቅ የሚረዳ ትምህርት ሰጪ አሠራር ሆኖ ያገለግላል። የተሰደዱ ሰዎች ወደሌላው ፓሌታ ሄደው ጥገኝነት በመጠየቅ የመኖር መብት አላቸው፡፡ የተጣለባቸውን የቅጣት ዘመናቸውን ሲጨርሱ ከፈለጉ ወደ ፓሌታቸው የመመለስ መብት አላቸው። ነገር ግን ለመመለስ አመልክተው ቀነ ቀጠሮ ተደርጐላቸው ሕዝቡ ደግሶና ወጥቶ በታላቅ ስነ ስርዓት ይሆናል። የማንፃት ስነ ስርዓትም ይደረግላቸዋል። ይህም በራሱ ሰፊ የማስተማሪያ መድረክ ነው። በዚህ ጠንካራ ባህል ምክንያት በኮንሶ ብሔረሰብ ሴቶችን ማባለግና ሌብነት እየቀነሱ ያሉ ወንጀሎች ናቸው ማለት ይቻላል። በአካባቢው ሴቶች በማታ ውሃ ለመቅዳት በየጫካ በነፃነት ሲንቀሳቀሱ ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህም ባህላዊ እሴት ለባህላዊ ህጉ የራሱ የሆነ ሚና አለው። ወንጀሎች እንዲቀንሱ በማድረግ የሴቶችን ደህንነት በመጠበቅ፣ የንብረት ደህንነትን አስተማማኝ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

- **ዱካታ** ሌላው ነው። ዱካታ እውነትን የሚገልጽና የሚፈልግ ቃል ነው። በኮንሶ ብሔረሰብ ውሸት ከነውር በላይ የሆነ አፀያፊ ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡ የሰው ልጅ ከዋሸ ሰው መሆኑ ያጠራጥራል የሚል እሳቤ አለ። ሰው ሊሳሳት፣ ሊያጠፋ ይችላል፤ ነገር ግን ሊዋሽ አይገባም። አይችልም የሚለው አመለካከት ሰርጿል። ስለሆነም ዱካታ (እውነት) የኮንሶ ሕዝብ መሠረት ነው፡፡ እውነተኛነት መገለጫቸው ናት። በየቤተሰቡም ሀኪታ (የእውነተኛነት አባት) የሚባል አለ። ሀኪታ ማለት የእውነት አባት እንደማለት

ነው። ይህ የብሔረሰቡ እውነተኛነት ለባህላዊ ህጉ ፍትሃዊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ብሔረሰቡ የሚመራባቸው ማህበራዊ እምነቶችን ስንመለከት ደግሞ በኮንስኛ "ከንታ-ከፋ ነማ" የሚባል ነገር አለ። ይህ ማለት ጎሳ ወንድም ነው ነገር ግን ጎረቤት ይቀርባል እንደማለት ነው። ችግርን በቅርብ የሚሰማ፣ የሚደርስና የሚፈታ ጎረቤት እንጂ ወንድም ወይም ዘመድ አይደለም ይላሉ። እናም ለጎረቤቶቻቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ። ይህም ማህበራዊ ኑሮ የሚጀመረው ከጎረቤት (ከከንታ) ከፍ ሲል በፓሌታ (መንደር) ደረጃ ነው። ይህ ማለት ለአንድ ችግር ወዲያው የሚደርሱት አባት፣ እናት፣ እህትና ወንድም አይደሉም ጎረቤት ነው። ቀባሪም፣ ቀጭም፣ መካሪም፣ መሀሪም ጎረቤት ነው። ስለዚህ በነዚህ ደረጃ ያለው ህይወት እጅግ የተሳሰረና የተቀራረበ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ማለትም በለቅሶ፣ በሰርግ፣ በደቦ ስራ… ወዘተ የተቆራኘ ስለሆነ እንደእምነት ለሁሉም ቅርቡ ጎረቤት ነው በሚል በመከባበርና በመተሳሰብ ይኖራል፡፡

እንደሚታወቀው የኮንሶ ጎሳ ዘጠኝ ነው። ዘጠኙም ጎሳዎች በስብጥር በሁሉም ፓሌታዎች (መንደሮች) በስምምነት ይኖራሉ።ጎሳ ለጎሳ (አንድ ጎሳ) ጎረቤት አይሆንም። ራቅ ብሎ ነው የሚኖረው ይህ የሚሆነው አንድም አንድ ላይ ከሆኑ ሌሎቹን ያጠቃሉ፤ እነሱም ይጠቃሉ ከሚል እምነት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በስብጥር በሁሉም መንደር ራቅ ብለው ይኖራሉ። ይህ በብሔረሰቡ ጎሳው ተቀብሎት ባህል ሆኖ አሁንም ድረስ እየተገበረው ያለ ነው።

በተጨማሪም በብሔረሰቡ መጥፎ ድርጊቶች በባህላዊ እምነቱ ውጉዝ ናቸው ውጉዝ ነገሮችን መፈፀም ከተፈጥሮ ማግኘት የሚገባንን ማናቸውንም ነገሮች አናገኝም ተብሎ ይታመናል። ለአብነት የሰው ደም ማፍሰስ ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ተመሳሳይ የጎሳ ጋብቻ ውጉዝ ነው። ደም ያፈሰሰ ሰው የእንስሳት መስዋዕት በማቅረብ አርዶ በፈረስና በቅዱስ ውኃ(ማለዳ ሰው ሳይቀዳ የተቀዳ የምንጭ ውኃ) አካባቢው ተረጭቶ መፅዳት አለበት አለበለዚያ አካባቢው ረክሷል ይባላል። ከመሬት ጋር በተያያዘ አንዱ ባረሰበትና በዘራበት ላይ ሌላው መጥቶ መልሶ ቢያርስና ቢዘራበት ውጉዝ ነው፤ ይህም በባህላዊ እምነቱ አንድ መልክ ያላት ሴት ፍየል ወይንም በግ ታርዳ በፈረስና በቅዱስ ውኃ አካባቢው ተረጭቶ መፅዳት አለበት። ሴት በግ ወይንም ፍየል መመረጧ ወላድ ስለሆነች፣ አንድ መልክ ያላት

መመረጧ ሀሳቧ ያልተከፋፈለ እንዲሆን ከሚል እምነት የተነሳ እንደሆነ በመስክ ቆይታ ከብሔረሰቡ ተወላጆች ጋር በነበረ ኢ-መደበኛ ውይይቶች ግንዛቤ የተገኘበት ነው፡፡

ፈርስ የሚመረጥበት ምክንያት እንስሳት የተለያዩ የእፅዋት ውጤቶችን (ቅጠላቅጠሎችን) ይመገባሉ፡፡ እነዚህ ቅጠላቅጠሎች ውስጥ ቅዱስ የሆነ ቅጠል እንደ “ሀንሳቢታ” ዓይነት ስላለበት ለማንፃት ይመረጣሉ ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ብሔረሰቡ የሚመራበት ባህላዊ እምነት በርካታ ተከታይ ያለው፤ አብሮት በመኖር ያዳበረው፣ ያደገበት ስለሆነ ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፡፡ በዚህ የባህል ዳኝነት ላይ መቆምም በባህሉ የተለያዩ ማዕቀቦችን ስለሚያስጥል የሚፈራና የሚከበር ነው፡፡ ባህላዊ እምነቱን የሚጥስ ብዙ ማዕቀቦች ይደረጉበታል፡፡

ከመርህ አኳያ ስንመለከት በብሔረሰቡ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ እንደመርህ የሚከተላቸው በርካታ ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ በብሔረሰቡ አጠራር “አታ” ይባላል፡፡ “አታ” ማለት ባህል ማለት ነው፡፡ የኮንሶ ባህል፡፡ ለባህሉ ተገዢ ያልሆነ ሰው ከስርዓት ውጭ የሆነ ነው ማለት ነው፡፡ ለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ተገዢ አለመሆን፤ ያልተፈቀዱና ውጉዝ የሆኑ ድርጊቶችን መፈፀም፣ ክህደት መፈፀም፤ የባህል እምነቱን ማንቋሸሽ፣ የባህል መሪዎችን አለማክበር፣ በተለያዩ ወንጀሎች መጠርጠር በአጠቃላይ ብሔረሰቡ አሜን ብሎ ተቀብሎ እየተዳደረበትና ችግሩን በቅርብ እየቀረፈበት ላለውና አብሮት ለዘላቀው ባህላዊ ህግ አለመገዛት በብሔረሰቡ የባህል ደንብና ስርዓት መሠረት ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡ ለቅጣቱ ተገዢ ያልሆነ ማንኛውም ሰው (ነዋሪ) ከመኖሪያ ቀዬው ይገለላል፡፡ የተለያዩ ማዕቀቦች ይጣሉበታል፡፡ ለአብነት ከጎረቤት ከሰላምታ መለዋወጥ ጀምሮ እሳት እንዳይጭር፣ ጨቃ እንዳይገዛ ወዘተ….. ይደረጋል፡፡ የወንጀሉ ቅለትና ክብደት ታይቶ እስከወዲያኛው ቤቱ (መኖሪያው) በቅንጭብ ተመትቶ ይባረራል፡፡ በቅንጭብ መመታቱ ዘርህ አይበረክት፤ ይጥፋ፣ አይመልስህ እንደማለት ነው፡፡

ይህ ለብሔረሰቡ የባህል ህግ እንደመርህ “ገዢ” ስርዓት ሆኖ አሁንም ድረስ እያገለገለ ይገኛል፡፡ ሌላው በብሔረሰቡ እምነት አንድ ድብቅ ወንጀል ተፈፅሞ እውነቱን ለማግኘት “ሻኻ” ወይም መሀላ መፈፀም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ለጥቃቅን ጉዳይ “ሻኻ” ላይ አይደረስም፡፡ “ሻኻ” አይፈፀምም፡፡ ይሁንና ማንም ሰው ወንጀል ሰርቶ ቢክድ “ሻኻ” ይፍረድ ይባላል፡፡

በብሔረሰቡ እምነት እውነትን ካልያዙ ወደ “ኻኻ” መቅረብ አይደፈርም። እውነትን ሳይዙ ወደ ‹‹ኻኻ›› መቅረብ ብዙ መዘዝ አለው በማለት ያምናሉ። ስለዚህ ወደዚህ ቦታ እንሂድ ከተባለ አጥፊው ሳይወድ በግዱ ያምናል። ይህ ሁኔታም በነበሩት ስርዓቶች ሁሉ ኮንሶዎች ለፍርድ ለምስክርነት ሲቀርቡ በባህላዊ ሞራዎች ላይ በ “ሞራ-ኻኻ” መሀላ ፈጽመው የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ታማኝነት ነበረው። አሁንም ባለው ስርዓት ይህ ሁኔታ በተለይ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት መፍትሄ ያጡ ጉዳዮች ወደዚህ ይመራሉ።ይህ ደግሞ ለባህላዊ ስርዓቱ መዝለቅ ምሰሶ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

እንደ አብነት “በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የኮንሶ ወረዳ ፍርድ ቤት የሚባል ነበር በደርግ ጊዜ በተመሳሳይ ነበር አሁንም በኢህአዴግ አለ እየሠራ ይገኛል የኮንሶ ሕዝቦች በነበሩት ስርዓቶች ሁሉ መረጃ ያጡ አሊያም የሌላቸው ጉዳዮች መጀመሪያ በዚህ ጨርሳችሁ ኑ የሚባልበት ሁኔታ ስላለ አሁንም እየተሰራበትና እየተተገበረ ይገኛል” ሲሉ በቡድን ውይይት ወቅት ከተወያዮች የተገኘው መረጃ ያመለክታል (በደንገልቱ፣ ጥር 2006 ዓ.ም)።

## 5.2 በመደበኛው የፍትህ ተቋማት መፍትሄ የሚሰጣቸው ጉዳዮች

ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን በተለይ አስገድዶ መድፈርን፣ ድብደባን በተለይ የሕጻናት የአካል ቅጣትን መዳኘት እንደማይችሉና ስልጣኑ እንደሌላቸው ዋና ሳጅን አማረች ስንታየሁ የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ሴቶችና ሕጻናት ክብካቤ ባለሙያ ትገልጻለች። በማስከተልም፡-

> ‹‹*ወደመደበኛው የፍትህ ስርዓቱ ተደጋግመው የሚመጡ ጉዳዮች በብዛት የሕጻናት ድብደባና በጋብቻ ላይ ጋብቻ ወይም ድርብ ጋብቻ ናቸው፤ መደበኛው ህግ ድርብ ጋብቻን ይከለክላል የባህል ህጉ ግን ይፈቅዳል፤ ወንጀል መሆኑ ቀርቶ እንደባህል ያዩታል፤ የአቅም ጉዳይ ስላለና የሚከታተላቸውም ስለማይኖር ብዙ ጊዜ በአካባቢው የትዳር መሰረት የሚናጋውና ፍቺ የሚበዛው በዚህ ምክንያት ነው፤ ልጆችም በዚህ ምክንያት ለጎዳና ህይወት ይዳረጋሉ፤ ይህ ጉዳይ በብዛት ወደወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ተደጋግሞ የሚቀርብና የሚታይ ነው፤ ከድብደባ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ቤተሰቦች ልጆቻቸው አጠፉ ብለው እጆቻቸውን በእሳት የሚያቃጥሉ አሉ ይህን መሰሉ ወንጀል ሲከሰት በባህሉ እንኳ ቢደብቁ በጥቆማ ተከታትለን በመድረስ ጉዳዩ በመደበኛው ህግ እንዲታይ በማድረግ ብዙ ውሳኔዎች ተሰጥተዋል*›› (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 52) ለዚህም አብነቶችን ማንሳት ይቻላል ስትል ትገልጻለች።

## አብነት አንድ

*"በ2004 ዓ.ም ጥቅምት ወር ላይ ነው ዶካቱ ቀበሌ ፎራ ውስጥ ነው አባት ልጁ ሰረቀ ይልና እጁን በገመድ አስሮ እሳት ውስጥ ይከተዋል፤ ሰፈርተኛውም አይቶ ዝም ይላል ልጁ የታሰረበት ያባብጣል፤ ለፖሊስ ጥቆማ የሚሰጥ ይጠፋል፤ ከዚያ ልጁ ከታሰረበት እየተንፏቀቀ ወጥቶ መኪና መንገድ ይደርሳል ከዚያ በመንገድ የሚያልፍ ሚኒባስ ከሌላ አካባቢ ሲመጣ ያየውና ይዞት ወደ ወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ያመጣዋል፤ ከዚያ ልጁን ስናየው እጁ አይሰራም ከዚያ መረጃ እንዳይጠፋብን የሕጻናት ማቆያ ስላለን እዚያ እንዲቆይ ተደርጎ አባቱ ተይዞ መጣ ምርመራ ተደረገበት ልጁ እዚያው እያለ ምርመራውን አጣርተን በአባት ላይ አንድ አመት ከስድስት ወር አስፈርደን ወላይታ ማረሚያ ቤት እንዲላክ አድርገናል"* (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 53) በማለት ትገልጻለች፡፡

በዚያው ዓመት ይህ ወንጀል የተፈጸመበት ቀበሌ ትምህርት ለመስጠት ስንሄድ ኸረ የአሁን መንግስት ደግሞ እንዴት አድርገን ልጆቻችንን እንቅጣ፣ ስንቀጣ በህግ እየተከሰስን በሚል ብዙ ጥያቄዎች አነሱ፡፡ እኛም አለመረዳት ይሆናል፤ ግንዛቤ ላይኖር ይችላል፡፡ ቅጣት ሲባል ደረጃም ዓይነትም አለው፡፡ የራሳችሁን ልጅ አትቆጡ፣ አትቅጡ አላልንም ስትቀጡ በአርጩሜ መግረፍ፣ መቆንጠጥ ትችላላችሁ በሰውነት ላይ አደጋ የሚያደርስ ነገር ማድረግ ተገቢ አይደለም፡፡ ያስጠይቃል ነው የምንለው አልናቸው፡፡ እኛን አትዩ በህግ የተቀመጠ ነገር ነው እየሰራን ያለነው ብለን አልናቸው፡፡

አሁን በዚህ ሁኔታ ሕጻናት ችግር ሲገጥማቸው በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወንዶችና ሴቶችን ያቀፈ የሕጻናት ፓርላማ ተቋቁሟል፡፡ አንድ ችግር ሲገጥማቸው እራሳቸው ያመለክታሉ፡፡ ራሳቸው ተደራጅተው የራሳቸው ሊቀመንበር መርጠው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በዚህ ረገድ በስፋት እየሰሩና ከፍተኛ ለውጥም አለ ስትል በተመሳሳይ ዕለት በነበረ ቃለመጠይቅ ትገልጻለች፡፡

## አብነት ሁለት

*"ታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ነው ኮልሜ ማሶያ ቀበሌ ነው ልጅቷ የ6 ዓመት ልጅ ናት ወላጅ እናቷ ህጻን ጠብቂ ብያት ጥላብኝ ሄደች በሚል የህጻኗን ብልት በእሳት ታቃጥለዋለች ጥቆማ ደረሰን ልጅቷ መጣች አስረከቡን አሳከምናት ሊያት አሏት አያቷን አጠገባችን አድርገን እግሯ ከታጠፈ ለቁስሉ ጥሩ ስለማይሆን በየቀኑ እያጠብን እያሳከምናትና እየተከታተልናት እንገኛለን፤ እንደመንግስት የበጀት እጥረት አለብን፤ትኩረትም አይሰጡንም፤ ጭስ ውስጧ ይገባል በሚል ማሳየት ፈልገን ነበር የገንዘብ እጥረት ስላለብን ይህን ማድረግ አልቻልንም የቀረን የሀኪም ማስረጃ ነው፤ ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ወንጀሎችን አይመለከቱም፤ ቢደብቁም በጥቆማ እንደርስበታለን፤*

***በዚህ ላይ እኛው ውሳኔ እናሰጣለን፤ እነሱ ስልጣኑም የላቸውም"*** (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 20፣ 2006 ዓ.ም፣ 53) ስትል ትገልጻለች፡፡

## 5.3 ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከመደበኛ የፍትህ ተቋማት ጋር ያለው የግንኙነት ሁኔታ

### 5.3.1. ከፍርድ ቤትና ዐቃቢ ህግ እንዲሁም ከጸጥታና አስተዳደር ጋር

በኮንሶ ብሔረሰብ መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህላዊ የፍትህ ስርዓት ጋር በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ የሚሰራበት፣ በጋራ ችግሮችን በመወያየት ለመፍታት የሚሞክርበት አሠራር እንዳለው በመስክ ቆይታ ወቅት ከፍትህ አካላት ባለሙያዎች ጋር በጽ/ቤታቸው በነበረ ቃለመጠይቅ ከአንዳንድ አብነቶች መረዳት ተችሏል፡፡

ከፍትህ አካላት በወረዳው ፍትህ ጽ/ቤት የክስ አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ከሆነችው ወ/ሮ ተዋበች ተስፋዬና ከዐቃቤ ህጉ አቶ ጌድዮን ጌታሁን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት አከናዋኞችና የመደበኛ ፍትህ አካላት በጋራ የሚሠሯቸው ስራዎች እንዳሉ በተለይ በባህላዊው ስርዓት ውሳኔ አግኝተው በውሳኔው ቅሬታ ሲኖራቸው በቀጥታ ወደፍትህ በአቤቱታ መልክ እንደሚቀርቡ በዋናነትም ከማህበራዊ ኑሮ መገለልና ከእምነት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶችን እንደሚመለከቱ ይጠቅሳሉ (የኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 56፣ 57)፡፡

በዚሁ በመስክ ቆይታ ወቅት ለመረጃ ስብሰባ በወረዳው ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ አጥኚዋ በተገኘችበት ጊዜ አንድ አዛውንት ከማህበራዊ ኑሮ ተገለልኩ በሚል አቤቱታ ለማቅረብ እንደመጡና በምን ምክንያት እንደተገለሉ በአካል ከግለሰቡ ጠይቃ መረዳት የቻለችው ይህንኑ የፍትህ አካላቱን ሀሳብ ያጠናከረ ነበር፡፡ ከማህበራዊ ኑሮ የሚያስገልሉ ምክንያቶችን በተመለከተ፦

> ‹‹***ከማህበራዊ ኑሮ ለመገለል መነሻ ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ለአብነት በመንደሩ የተለያዩ ወንጀሎችን ለምሳሌ እንደስርቆት፣ ድብደባ ወዘተ ፈጽመው በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ውሳኔ አግኝተውና በውሳኔው ቅሬታ ሲኖራቸው ጉዳያቸውን ወደጽ/ቤቱ አቤት ለማለት የሚቀርቡ ናቸው"*** (ማቴዎስ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም፣ 58)፡፡

አቤቱታ ወደ ጽ/ቤት ይዘው ሲመጡ ግን ብዙ ጊዜ የመካድ፣ ወንጀሉን ሳንፈፅም ነው እንደዚህ ዓይነት ቅጣት የጣሉብን፤ እኛም ከማህበራዊ ኑሮ እንዳያገሉን ብለን ቅጣቱን ተቀብለናል፤ ነገር ግን የተጣለብን ቅጣት ከአቅማችን በላይ ነው፡፡ ወንጀሉንም አልፈፀምንም

ብለው ይክዳሉ፡፡ በዚሁ መነሻነት ቅጣቱን የወሰኑባቸው ሰዎች አቤቱታው ላይ ስለሚጠቀሱ በደብዳቤ (አባሪ አራት) ቢሮ ድረስ እንዲመጡ በማድረግ አንድ ሰው ሲቀጣ አቅምንና የኑሮ ሁኔታን ያገናዘበ መሆን እንዳለበት መክረን ተነጋግረን ከማህበራዊ ኑሮ ማግለል የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነው የሀገራችን ህገመንግስት የማይደግፈውና ህገመንግስቱን የሚጻረር አሰራር እንደሆነ በመግለጽ በቅድሚያ በራሳቸው ጉዳዩን እንዲያስተካክሉና እንዲፈቱ አሊያም በጋራ በጉዳዩ ላይ በመነጋገር እናስማማለን፤ እንፈታለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለሙያዎችን በመላክ ከሚመለከታቸው የባህል መሪዎች ጋር በውይይት እንዲፈቱ እናደርጋለን ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ዐቃቤ ህጉ አቶ ጌድዮን በዚህ ላይ ሲያክሉ ወደመደበኛው የፍትህ ስርዓት የማይመጡና በባህላዊ መዋቅሩ የሚፈቱ ብዙ ጉዳዮች እንዳሉ ጠቅሰው ጉዳዩ ፍ/ቤቱ ቀርቦ እየታየ እያለ ጠበኞች እኛ ጉዳያችንን በሽምግልና በእርቅ ጨርሰናል ወይንም ተከሳሽ ቀርቦ ከሳሽ ላይ ሽማግሌ አንስቼ እታረቃለሁ የሚል ከሆነ ቢያንስ አንድ የቀጠሮ ጊዜ ይሠጠዋል፡፡ ይህም ከሽማግሌ በቂ ምክርና እገዛ ያገኛል ከሚል ነው፡፡ በመጨረሻ እኛም ቢታረቁ አንቃወምም በሚል ድጋፍ እናደርጋለን፡፡ ሌላው ክስ ያቀረብነው እኛ በምንሆንበት ጊዜ ተከሳሽ ማስረጃ ሆኖ ነው ለኛ የሚቀርበው በዚህ ጊዜ ተከሳሽ ቀርቦ አይ እኔ በሽማግሌ እታረቃለሁ የሚል ሀሳብ ካቀረበ ቀጥታ የምንጠይቀው በእርቁ ላይ ያላችሁ አስተያየት ምንድነው የሚል ይሆናል፤ እዚህ ላይ ወንጀል ነክ ከሆነ ለምሳሌ የአስገድዶ መድፈር፣ የነፍስ ግድያ፣ ጠለፋ ወዘተ ክስ ሆኖ እንታረቃለን ቢሉ አንቀበልም ወንጀል ነውና፡፡ ይህ በእርቅ የሚፈታ አይደለም፤ ይሄንን አንቀበልም ይላሉ፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በተለይ በእርቅ የሚያልቁ ከማህበረሰቡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች መገለል ሊሆን ይችላል ምንም እንኳ የባህል መዋቅሩ በዚህ ላይ ጠንከር ያለ አቋም ቢኖረውም በጋራ በመነጋገር ችግሩ የሚቃለልበትንና በሰላም የሚፈታበትን መንገድ በመነጋገር እንፈታለን ይላሉ፡፡

እዚህ ላይ በአካባቢው ከባድ ወንጀል ተደርገው ከሚወሰዱት መካከል የአስገድዶ መድፈር፤ የነፍስ ግድያና የአካል ድብደባ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች መደበኛ ህጉ የሚያያቸውና ውሳኔ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ቀደም ሲል የባህል መዋቅሩም ጉዳዩ በቀጥታ ሲቀረብለት በዋናነት የሚመለከታቸው ጉዳዮች ነበሩ፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ ደግሞ

በቅንጅት የሚሠራበት አሠራር ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ከነፍስ ግድያ ጋር ተያይዞ ያለ ቤተሰባዊ ችግር በባህላዊ የእርቅ ድርድር ሲፈታ የተሻለና ዘላቂ ሰላም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ መደበኛው የፍትህ አካላት በባህላዊ መዋቅሩ እንዲታይና እንዲፈታ የሚፈቅድበት ሁኔታ መኖሩን መረጃ አቀባዩ የከርቲታ ጎሳ መሪ ካላ ገዛኸኝ ጋሞሌ ቀበሌ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት ይገልጻሉ (ጥር 16፣ 2006 ዓ.ም፣ 10)፡፡ ከፍትህ አካላት ቀርቦላቸው የፈቱትን አብነቶች በማንሳትም እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

## አብነት አንድ

*‹‹በ2004 ዓ.ም የተከሠቱ ሁለት የድንገተኛ ነፍስ ግድያዎችን አስመልክቶ በጋራ አይተን የፈታንበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ፤ ሟች የዴበና ቀበሌ አካባቢ ተወላጅ ሲሆን በሞተር ሳይክል የገደለው የቦረና ተወላጅ ነበር ይህ አደጋ እንደተከሰተ የተበዳይ ቤተሰቦች በመጀመሪያ ለፍትህ አካላት መርማሪዎች ጉዳያቸውን ምስክር አቅርበው አስመስክረው ያቀርባሉ ፤ከዚያም የበዳይ ወገን ገዳይ ሆስፒታል ገብቶ ጉዳት ላይ እያለ ከተበዳይ ወገን ጋር ድርድር ማድረግ ፈለጉና ጥያቄ ለተበዳይ ወገን በሽማግሌና በእምነት ተወካዮች አማካኝነት አቀረቡ ከመደበኛው የፍትህ አካላት በኩልም ስልክ ተደውሎ ይህን ጉዳይ ማደራደር ትችላለህ ወይ አሉኝ እኔም የሟችን ቤተሰብ ነው የምጠይቀው እነሱ ሲፈቅዱ ነው የሚል መልስ በወቅቱ ሰጠሁ ፈቃደኝነታቸውን ሲሰጡኝ መልሼ ወደፍትህ ቢሮ ደወልኩ ከዚያ በወኪሎቼ አማካኝነት አደራድሬ ከስምምነት የደረሱበትንና የተፈታበትን ሊጋጣሚ አስታውሳለሁ››* (ጥር 16፣ 2006 ዓ.ም፣10)፡፡

## አብነት ሁለት

*“በ1997 ዓ.ም የአራት ቀበሌያት የዱራይቴ ዶካቱ ጃርሶና ደራ በመሬት ጉዳይ ላይ በተከሰተ የእርስ በርስ ግጭት መነሻነት የሰው ሕይወት አልፎበታል፣ ንብረት ወድሟል፣ የእርሻ ሰብሎችና ቋሚ አትክልቶች እንደቡና ሸፈራው ሞሪንጋ ሙዝ ወድሟል፤ ቀፎ ተጥሏል ከእነእንጨቱም የተቃጠለ ነበር በዚህ ጊዜ የፍትህ አካላቱም አመራሩም ሙሉ በሙሉ ጉዳዩን ለባህል መዋቅሩ ለጎሳ መሪው በመተው ከሽማግሌዎች ጋር ብቻ በመሆን እንድንፈታው ያደረጉበትን አስታውሳለሁ፤ በአፈፃፀሙ ላይ የፍትህ አካላቱ በየደረጃው ያሉ የተለያዩ አመራሮች እንዲገኙ ተደርጎ ሰላም ወርዷል ሕዝቡም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለምንም ፀብ በሰላም እየኖረ ይገኛል”* (ጥር 16፣ 2006 ዓ.ም፣ 10)፡፡

በወረዳው መደበኛ ፍ/ቤቱ አሰራሩን በማሻሻል ወንጀልን በጋራ ከመከላከልና ከመቀነስ አኳያ ከማህበረሰቡ ግብዓት ለማግኘት ወርዶ የሚሰራበት ጊዜም እንዳለ የፍትህ አካላቱ ወ/ሮ ተዋበች ተስፋዬና አቶ ጌዴዮን ያነሳሉ፡፡ በተለይ ከፍትህ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ በተደረገ ፍተሻ የባህል መዋቅሩ የተሻለ እንደሆነና መደበኛው የፍትህ ስርዓት ግን ክፍተት እንዳለበት የተማረበት ጊዜም እንዳለ አብነት በማንሳት ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ በኮንሶ

ብሔረሰብ ለባህል ህጉ ተገዢ ያልሆነ ሰው ከባድ ወንጀሎችን ፈጽሞ ለአብነት እንደስርቆት፣ ደም ማፍሰስ፣ በማህበረሰቡ የተፈጠሩ ምስጢሮችን አሳልፎ መስጠት ወዘተ ዙሪያ የተወሰነበትን ቅጣት አለመቀበል ከተለያዩ ማህበራዊ ማዕቀቦችና መገለሎች አልፎ እስከወዲያኛው ከቀዬው (ከመኖሪያ አከባቢው) እስከመባረር የደረሰ ቅጣት አለው። አልፎ አልፎ የሚቀጡት ቅጣት ከባድና ሕዝቡም የሚተባበርበት ብሎም አንድ የሚሆንበት ስለሆነ በአካባቢው የሚከሰቱ ጥፋቶችን በመቀነስ ረገድ የፍትህ ስርዓቱንም በማገዝ በኩል የባህላዊው ስርዓት አስተዋፅኦ አለው ይላሉ።

በአጠቃላይ የግንኙነት ሁኔታውን አስመልክቶ ተበዳዮች በባህል መዋቅሩ የሚጣልባቸው ቅጣት ሲከብዳቸው አቤቱታቸውን ይዘው ሲመጡ በቅርበት በመነጋገር በጋራ ለማስማማትና ለመፍታት ይሞከራል። ከአቤቱታዎች ጋር ተያይዞ በእርቅ እንዲያልቅ ስንጠየቅም እርቁን ፍርድ ቤቱ በመፍቀድ ይተባበራል። በዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ከባህላዊው ስርዓት ጋር የቅንጅት ስራ አለን ሲሉ በጽ/ቤታቸው በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት የሚከተሉትን አብነቶች እንደአስረጂ በማንሳት ይገልፃሉ (የኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም)።

**አብነት አንድ**

ከእምነት ጋር ተያይዞ የተፈጠረን አለመግባባት ባህል እንደባህል መከበር አለበት በሚል ፍርድ ቤት የሰጠው የፍርድ ውሳኔ እንደማሳያ፡-

***"በሐምሌ ወር 2005 ዓ.ም ኮልሜ ላይ ማደሪያና ግዛባ ቀበሌ ውስጥ በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችና በባህል እምነት ተከታዮች መካከል ግጭት ተከስቶ ፖሊስ ጉዳዩን ተከታትሎና በፍርድ ቤት ታይቶ ሰላም የወረደበት ሁኔታ ነበር ብዙ ጊዜ በባህል እምነት መሰረት ሞራ ይሰሩና ሴት ልጅ በአጠገቡ አታልፍም፣ በተለይ የወር አበባ ላይ ከሆነች አሮጊት አዛውንት ካልሆነች በቀር ይላሉ በጊዜው አክራሪ ኃይማኖተኞች ባህልን እናጠፋለን ብለው የተነሱ ስለነበሩ ከፍተኛ ጦርነት ተፈጠረ፤ የባህል ሰዎችም ለባህላችን ዘብ እንቆማለን እንሞታለን አሉ፤ ከሁለቱም ወገን የተወሰኑ ሰዎች ታሰሩ ብዙ ግርግርም ተፈጠረ በኋላ በቀበሌው ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ኮሚቴ ስላለ ጉዳዩ ተጣርቶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ማግኘት አለበት ተባለ፤ ሞራ በእያንዳንዱ ቀበሌ አለ ባህል በባህልነቱ መከበር አለበት ኃይማኖትም እንዲሁ ለምን እንደዚህ ይደረጋል በሚል ጉዳዩ ወደፍርድ ቤት ሄዶ ከዚያ ጉዳዩ ተረጋጋ፤ በጊዜው በጉልበት እንገባለን የሚሉ ስለነበሩ የአካባቢው ሽማግሌዎች በየሞራው ጥበቃ ማድረግ ጀመሩ፤ በኋላ ምርመራው ተጣርቶ ባህል መከበር አለበት በሚል ለባህል አጥፊዎች ለአካባቢው ባህል ተቃዋሚዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ሰላም የወረደበት ሁኔታ ነበር"*** (የኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 56-57)።

## አብነት ሁለት

መደበኛ የፍትህ ስርዓት የፍትህ አሰጣጡን በመፈተሽ አሰራሩን የተሻለ ለማድረግ ባደረገው ጥረት ከማህበረሰቡ ያገኘው ግብዓት እንደማሳያ፡-

*"በ2005 ዓ.ም በተጨባጭ በአከባቢው የተከሰተ ጉዳይ ነው በማለት በኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የክስ አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ የሆነችው ወ/ሮ ተዋበች ተስፋዬ ስትገልጽ በወቅቱ የአካባቢው ማህበረሰብ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ፍትህ ባለማግኘቱ ባለሙያዎች የተገመገሙበት በየቀበሌው ስንቀርብ የተገኘው ግብዓት ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ይልቅ ባህላዊ መዋቅራችን ይሻለናል ምክንያቱም በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ፍትህ እያገኘን አይደለም ወንጀል የሰራው ሳይመስከርበት በነፃ በገንዘብ እየወጣ ነው ተመስክሮበትም ቢሆን ከዳኛ ጋር በሙስና እየተመሳጠረ እየወጣ ነው ፍትህ የለም በማለት የባህል መዋቅሩን የመረጠበትን ወቅት አስታውሳለሁ"* (የኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 57)፡፡

## አብነት ሦስት

የባህል ህጉ አስገዳጅ ማዕቀብና የቅንጅት ስራው እንደማሳያ፡-

*"በ2006 ዓ.ም ቢርቢርሳ ቀበሌ ውስጥ ከብት ይሰረቅና በባህል የፍትህ ስርዓቱ ተጠርጣሪዎች ቀርበው ከብቶቹን የሰረቃችሁ እናንተ ናችሁ በስርቆቱም ተባባሪ ናችሁ በሚል የተወሰኑ ሰዎችን የገንዘብ ቅጣት ይጥሉባቸዋል፤ ክፈሉ ይባላሉ፤ በወቅቱም ድርጊቱን መፈጸማቸውን ያምናሉ፤ በኋላ ግን ክፍያው ሲከብዳቸው ጉዳዩን ወደመደበኛው የፍትህ ስርዓት በማምጣቱ አቤት ብለዋል፤ ወደ ፍትህ ሲመጡ ግን የመካድ ሁኔታ ነበር፤ እኛ አልሰረቅንም መጀመሪያ ለምን አመናችሁ ለምንስ ተቀበላችሁ ሲባሉ ማህበረሰቡ የሰረቃችሁት እናንተ ናችሁ በሚል ሚስቶቻችንና ልጆቻችንን ሊያገሉብን ሲሉ ያንን በመፍራት ብቻ ነው ያመነው እንጂ እኛ አላደረግንም አሉ፤ በኋላ ግን ጉዳዩ ጊዜ ወስዶ በጋራ ተጣርቶና ታይቶ ሰላም የወረደበትና የተፈታበት ሁኔታ ነበር"* (የኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት፣ ጥር 21፣ 2006 ዓ.ም፣ 57-58) ፡፡

## አብነት አራት

የግል ተበዳይ ከማህበራዊ ኑሮ አገለሉኝ በሚል ለወረዳው ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ አቤት ያሉበት ተጨባጭ መረጃ እንደማሳያ፡-

አቶ ጋርሞ ቢጭቶ የደራ ቀበሌ አያና ንዑስ መንደር ነዋሪ ሲሆኑ፣ እኚህ ሰው በቀበሌያቸው በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ለምን ትናገራለህ ተናጋሪ ለምን ትሆናለህ በሚል ከመኖሪያ ቀያቸው ጨቃ ገዝተው እንዳይጠጡ፣ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ሠላምታ

እንዳይለዋወጡ ምግብ ገዝተው እንዳይበሉ፣ በአጠቃላይ ማህበራዊ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ከቀበሌው (ከመንደራቸው) በመገለላቸው ይህንኑ አቤቱታ ለኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ ለማቅረብ በመጡበት ወቅት አጥኚዋ ለመረጃ ሰብስባ በጽ/ቤቱ አካባቢ ስለነበረች ግለሰቡን በአካል የማነጋገር እድል አግኝታ ነበር፡፡ ግለሰቡን በመቅረብም ከየት ቀበሌ እንደመጡ፣ ለምን እንደተገለሉ፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርባላቸው በአስተርጓሚ ሳጅን አርካይዶ ጉዮላ በኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ የሚሊሻ የስራ ሂደት ተወካይ አማካኝነት ምላሽ አግኝታለች፡፡ ተበዳይ አቶ ጋርሞ ቢጪቶ በምላሻቸው፡-

> *‹‹ከምኖርበት ደራ ቀበሌ በቀበሌው ውይይቶች ላይ ለምን ትናገራለህ በሚል ከተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ስለአገለሉኝ ይህንኑ አቤት ልል ነው ወደ ወረዳው ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ የመጣሁት፤ መገለሉ ቤተሰቦቼን ሳይጨምር እኔን ብቻዬን ሲሆን እስከወደያኛው ወደአካባቢው እንዳልመለስ ነው ያደረጉኝ፤ በመንገድ ላይ ራሱ እንገድልሃለን እያሉ እየዛቱብኝ ስለሆነ መፍትሄ ባገኝ ብዬ ወደዚህ መጥቻለሁ››* (የኮንሶ ወረዳ ጸጥታና አስተዳደር ቢሮ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም፣ 58)፡፡

### 5.3.2 ከፖሊስ ጋር ያለ ቅንጅታዊ አሰራር

ለአንድ አካባቢ ባህል ዕድገት ማህበረሰቡ ለባህሉ የሚሰጠው ትኩረት ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡ ‹‹የኮንሶ ብሔረሰብ ለአካባቢው የባህል ስርዓት ትልቅ ግምት ይሰጣል ያከብረዋል በዚህ ምክንያት ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ በአካባቢው ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ይበልጥ እየሰራ ይገኛል መደበኛ የፍትህ ስርዓቱንም በከፍተኛ ሁኔታ እያገዘ ወንጀሎችን እየቀነሰ ይገኛል›› በማለት መረጃ አቀባይዋ በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት ትገልጻለች (ዋና ሳጅን አማረች፣ የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 53)፡፡

በአካባቢው ባህሉ ባይኖር፣ ባህሉን ከህጻንነት ጀምሮ ቅጣቱንም፣ ማዕቀቡንም፣ መገለሉንም ወዘተ እየተማሩት ባያድጉ ኖሮ ወንጀሉ የባሰ እየከፋና ከቁጥጥር በላይ ሊሆን እንደሚችል አያይዛ ታብራራለች፡፡ ባህሉ ብዙ ነገር ይዟል፡፡ ለመደበኛው የፍትህ ስርዓት ትልቅ እገዛ አለው፤ በመደበኛ የፍትህ ስርዓት አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሞ ሲመጣ መረጃ ፈጽሞ ማግኘት አይቻልም፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ወደቀበሌው (መንደሩ) ወደ ባህል መዋቅሩ እንዲሄዱ ነው የምናደርገው፡፡ በዚያ ደረጃ የሚመለከተውን ሳያደርጉ ወደፖሊስ መምጣትና ማመልከት የለባችሁም ይባላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ይያዛሉ ይህ አንድ የግንኙነት ማመላከቻ ነው፡፡ ይሁንና በነሱ ደረጃ ማየት የማይገባቸውን እንደአስገድዶ መድፈር፣ የአካል ቅጣት

ወዘተ የማየት ስልጣኑ ስለሌላቸው ጣልቃ እንገባለን፤ ይህን ሲሰሩ ከተገኙም እንቀጣለን፤ እንማማራለንም ትላለች፡፡ ከዚህ ውጭ አብዛኛው በሚሰሯቸው ስራዎች መደበኛውን የፍትህ ስርዓት በተለይ ከወንጀል መቀነስ አኳያ ባህላዊ ህጉ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ትገልጻለች፡፡ የባህል ህጉ ብዙ ጉዳዮችን ባይዝልን ኖሮ ለመደበኛ የፍትህ ስርዓቱ ብዙ ፈተና የሆኑ ጉዳዮች ይገጥሙ ነበር፤ ስለሆነም ከተጠቀሱት ከባድ ወንጀሎች ውጭ በቅንጅት የሚሰሩ መሆናቸውን የሚከተሉትን አብነቶች በማንሳት ትገልጻለች (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

በኮንሶ ብሔረሰብ ጥንቆላ የሚባል ነገር አለ፡፡ በጥንቆላ የማመን፡፡ በጥንቆላ ይህን ያህል ሰው ጨረሰብኝ፣ ይህን ያህል ገንዘብ ካልከፈልክ ተብዬ እንደዚህ አስጨርስብሀለሁ ተባልኩ የሚሉት ነገር አለ፡፡ ይህ ወደወንጀል ስለሚያስኬድ ወደህግ በማምጣት የነገሮቹን መሰረት ነው የምናጣራው፡፡ ይሄ ነገር መነሻው ከየት ነው? ከየትስ መጣ? የሚለውን ከባህል ሰዎች ጋር በጋራ እንመረምራለን፡፡ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ እናደርጋለን፡፡ ለዚህም የሚከተለውን እንደአብነት ማንሳት እንደሚቻል ትገልጻለች፡፡

### አብነት አንድ

*"በህዳር ወር 2006 ዓ.ም ላይ ካመሌ ቀበሌ እንደዚህ ዓይነት ነገር ተከስቶ ነበር ወንድማማቾች ናቸው ይጣሉና በባህሉ መሰረት አንደኛው ላይ የገንዘብ ቅጣት ይወስኑበታል፤ የተወሰነበት ወንድም ገንዘቡን ለመክፈል አቅም አልነበረውምና ወንድምየው ካልተከፈልኩ በሚል ጠንቋይ ቤት ይሄድና መተት ያሰራበታል፤ የወንድሙ ሁለት ልጆች ይሞታሉ፤ የልጆቹን ሞት መንስኤ ወንድም አሳወቀም ልጆቹን ቀብሮ እያለ ድጋሚ ከጠንቋዩ መጥሪያ ይደርሰዋል፤ ወንድምየው ይህ ሲደርሰው የጥሪ ወረቀቱን ይዞ ወደፖሊስ ጽ/ቤት ያመጣል፤ በባህል ይህን ያህል ገንዘብ ተወስነ መክፈል ካልተቻለ ህግ ወዳለበት መሄድ ሲገባ እንደዚህ ዓይነት ነገር መፈጸሙ አግባብ አይደለም በሚል ይህን ያደረገውን ወንድም ይዘን አሰርነው በባህሉ መሰረት ተናግሮ ከዚያ ገንዘቡ እንዲቀነስልህ ማድረግ ስትችል እንዴት እንደዚህ ታደርጋለህ ብለን ሁለትና ሶስት ቀን እንዲታሰርና ምርመራውም እንዲጣራ ተደረገ የዚያ ቀበሌ አመራሮችና የአካባቢ ሽማግሌዎችን ጠርተን እንዴት እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ይወሰናል ቢቻል እነዚህን ሰዎች የማስታረቅ የማስማማት ሁኔታ መፍጠር እንጂ፤ እነዚህ ወንድማማቾች ናቸው ነገ ብዙ ነገሮች ላይ የሚደራረሱ ማስታረቅና ማስማማት ሲገባ እንዴት እንዲህ ዓይነት ነገር ታደርጋላችሁ በሚል እንደገና በጽ/ቤቱ በኩል ማስተካከያ ተደርጎ ሁለቱንም ወንድማማቾች ሽማግሌዎች ያደረጉትና የፈጸሙት ስህተት መሆኑን ገልጸን ተማምነን ተቀብለውት ጠበኞቹን በጋራ አስማምተን ወደየመጡበት በሰላም እንዲሄዱ ያደረግንበት ሁኔታ ነበር"* (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 54)፡፡

የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ከአካባቢው ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በቅንጅትና በመተጋገዝ የሚሰራቸው ስራዎች አሉ ለምሳሌ የ ሞራ ምረቃ ስነ ስርዓት ሲኖር ልዩ የበዓል ዝግጅት ይኖራል በዚህ ጊዜ ከጸጥታ ጋር ተያይዞ በፖሊስ በኩል የጥበቃ ስራ ይሰራላቸዋል መስተንግዶም ከሆነ አባላት ይመደቡላቸዋል ሞራ ለመስራት ከሆነም የገንዘብ መዋጮ ሳይቀር ድጋፍ በማድረግ እገዛ እንደሚደረግ ትገልጻለች ከዚህ ባሻገር ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ አንዳንድ ጉዳዮችን በተለይ ከአስገድዶ መድፈር ጋር ተያይዞ ያለውን አይመለከትም ትላለች፡፡

ይህ ዓይነቱ ወንጀል ሲከሰት ገፍተው ወደህጉ አይመጡም እዚያው በአካባቢው ይፈታሉ ይሁንና እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ተከታትለን ጣልቃ በመግባት በህግ እንዲታይ አድርገን ውሳኔ የምናሰጥበት ሁኔታ አለ ለዚህ ጉዳይ ለሽምግልና የሚቆሙ ሰዎችን ሁሉ ለህግ የምናቀርብበት ሁኔታም አለ በማለት የሚከተለውን አብነት ታነሳለች፡፡

### አብነት ሁለት

***"የካቲት 2005 ዓ.ም አንዲት ልጅ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተፈጽሞባት እኛ ጉዳዩን በህግ ይዘን እያጣራን እያለን በጎን ደግሞ ጉዳዩን በሽምግልና ለማስታረቅ ሽማግሌዎች የላኩበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ እኛም ይህን ሁኔታ በጭምጭምታ ሰምተን እነዚያን ሽማግሌዎች ጭምር ይዘን አስረን በኮንሶ ከፍተኛ ፍ/ቤት አስገድዶ የደፈራትን እስከ 20 ዓመት የደረሰ ቅጣት እንዲወሰንበት አድርገናል በወቅቱም ወንጀሉ ወደህግ ቀርቦ እያለ በሽምግልና እንዲታረቁ ያደረጉ ሰዎችም ከ500-1000 ብር የደረሰ የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ ያደረግንበት ሁኔታ ነበር"*** (የኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 55)፡፡

### 5.3.3 ከሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ቢሮ ጋር ያለ የቅንጅት ስራ

በኮንሶ ብሔረሰብ ለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከሚቀርቡና ከባድ ተብለው ከሚፈረጁ ወንጀሎች መካከል ሴት ልጅን መድፈር ዋነኛው እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በተለይ በድሮ ጊዜ ሴት ልጅን የደፈረ በባህሉ ርኩስ መንፈስ የተጸናወተው፣ የተወገዘ አድርገው ስለሚቆጥሩት የመጨረሻ የቅጣት ውሳኔው በቁሙ ገደል ጨምሮ እስከመግደል የደረሰ አሊያም በረሀብ እስከመግደል የደረሰ ቅጣት ይጠብቀው ነበር፡፡ ይህ ከነፍስ ግድያም ቅጣት የከበደ እንደነበር ከተለያዩ የመረጃ አቀባዮች የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ይህ ወንጀል በመደበኛው የፍትህ ተቋም የሚዳኝበት ሁኔታ እንደተፈጠረና ህብረተሰቡም ይህን መሰል ወንጀል የሚፈጽሙትን በማጋለጥ ረገድ ተባባሪ እንደሆነና

ቅጣቱን በመደበኛው ፍርድ ቤት ካገኘ በኋላ ወንጀለኛ ስለሆነ ወደቀደመ መንደሩ እንደማይመለስ የቀድሞው የባህል ቅጣቱም ተለውጦ ከአካባቢው እስከመባረር፣ ከማህበራዊ አገልግሎት እስከማቀብ የደረሰ ቅጣት እንደሚጣልበት ተገልጿል፡፡ ከዚህ ባለፈ የድሮው ቅጣት ጫና ፈጥሮ ሴት ልጅን መድፈር በአካባቢው በጣም የበዛም አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ሴት ልጅን ከጨለመ ምንጭ ቦታ ውኃ ለመቅዳት፣ እንጨት ለቀማ በየጫካው ማየት የተለመደ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ እዚህ ላይ ለሴቶች መደፈርም ሆነ መባለግ እንደምክንያት ሆኖ የሚነሳው ባሎቻቸው የሞቱባቸውና በቆይታቸው ብቸኛ መሆናቸውን በማየት የሚከሰቱ፣ ለረጅም ጊዜ በተለያየ ምክንያት ተለይተዋቸው ሲቆዩና የወንዶቹ በስካር መንፈስ ያለፈቃዳቸው የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ቀደም ሲል በባህላዊው የፍትህ ስርዓት ዳኝነት የሚያገኙ ሲሆን፣ ይህም በባህሉ አንዲት ሴት ተደፈረች ማለት በባህል መዋቅሩ ከባድ ቅጣት ይጣልበት ነበር፡፡ ቅጣቱም በቁሙ ገደል እስከመጨመር የደረሰ ነበር፡፡ ያባለገም ከሆነ ማሳ (የሞራል ካሳ) ከፍሎ ሴትየዋን መጠቅለል አለበት፤ ልጃገረድም ከሆነች ሁለተኛም ሆነ ሶስተኛ ሚስት አድርጎ የማግባት ግዴታ ነበረበት፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ድርብ ጋብቻንም ሆነ አስገድዶ መድፈርን ከሚከለክለው መደበኛ የፍትህ ስርዓት ጋር የሚጻረርና ቅጣቱም ሰብዓዊ ክብርን የሚነካ በመሆኑ በኢህአዴግ መንግስት በመደበኛ የፍትህ ስርዓት እንዲታዩ ተደርገዋል፡፡ እዚህ ላይ ጉዳዮቹ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ተለውጠው ይታዩ እንጂ አሁንም መረጃ አጠናክሮ በመስጠትና ወንጀለኞች ተገቢውን ቅጣት እንዲገኙ በማድረግ ረገድ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት በመተባበር እንደሚሰራ ከመረጃ አቀባዮቹ በተለያየ ደረጃ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ይሁንና በዚህ ረገድ ያለው ሁኔታ ወንጀሉን እንደቀነሰ ቢታመንም ሙሉ በሙሉ የለም ማለት እንደማይቻል በመስክ ቆይታ ወቅት በኮንሶ ወረዳ የሴቶችና ህጻናት መብት ደህንነት ማስጠበቅ ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ከሆነችው ከወ/ሮ ብርቂ ገልሲሞ ጋር በወረዳው የሴቶችና ሕጻናት ቢሮ በተደረገ ቃለመጠይቅ፡-

> ‹‹*በኮንሶ ወረዳ ሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ቢሮ ወደቢሮው ከሚመጡ እንደ አስገድዶ መድፈርና የሰው ሚስት ማግባት በአጠቃላይ ሴቶችና ህጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ከባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ጋር በቅንጅት እንሰራለን*›› (ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 55) ስትል ትገልጻለች፡፡

በኮንሶ ብሔረሰብ በሴት የሚመጣ ግጭት ማብረጃ የለውም፡፡ የሰውን ሚስት ማግባት የሰው ሚስት ሆና ወይም እከሊት ከእከሌ ጋር እንዲህ ዓይነት ግንኙነት አላት ተብሎ የነውር ድርጊቱ በገሀድ ከተሰማ ከፍተኛ ግጭት ይነሳል፡፡ በተለይ የአንድ ቀበሌ (መንደር) ወንድ የሌላን ቀበሌ ሴት ከደፈረ ከፍተኛ ግጭት ይፈጠራል፡፡ በዚህ ምክንያት አብዛኛው ግጭቶች በሴቶች የሚፈጠሩ ናቸው ትላለች፡፡ ወደቢሮ በብዛት የሚመጡትም አስገድዶ መድፈርና የሰው ሚስት አስኮብልሎ ማግባት እንደሆኑ ትገልጻለች፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ወደቢሮው የሚያመጡበት ዋና ምክንያትም በሴቶች ቢሮ በኩል እንዲሄድና ተሰሚነትም እንዲኖረው፣ የህግ መሰረት አለውም እንዲባል፣ ከዚህ ሌላ አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች ጉዳይ ሲባል የሚፈርድ ስለሚመስላቸውም ጉዳያቸውን ወደሴቶች ቢሮ ያመጣሉ ትላለች፡፡

ይሁንና እነዚህን ጉዳዮች በሴቶች ጉዳይ ቢሮ በኩል ለማየት ይሞከራል፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ መልሰን ወደባህል ነው የምንልከው ትላለች፡፡ ወደባህል የሚመለሱበትን ምክንያት ስትገልጽም የመጀመሪያው እንደወረዳ የሴቶች ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ማለት "ጥርስ የሌለው አንበሳ" እንደማለት ነው፤ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ በባህል ደንብ መሰረት በሽማግሌ ታይቶ፣ ተደራድረው የተስማሙበትን ውሳኔ ለቢሮው እንዲያሳውቁ ነው የምናደርገው፡፡ ተበዳይዋ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት በሰጠው ውሳኔ ካልተስማማች ጉዳዩ በህግ የሚታይበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

በባህሉ መሰረት በሽማግሌ እንዲፈቱ ተደርጎ ካልተቻለ በህግ የሚታይበትን ሁኔታ እናመቻቻለን ትላለች፡፡ በባህሉ መሰረት የሰው ሚስት ያገባ ወይም የደፈረ "ማሳ" ነው ይባላል፡፡ "ማሳ" ማለት በብሔረሰቡ አጠራር የሞራል ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበት፣ ተጠያቂ እንደማለት ነው፡፡ የሞራል ካሳ ይከፍላል፡፡ ስለዚህ ይህን የፈጸመ ቅጣቱን ተቀብሎና ፈጽሞ በሰላም ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይሄ ካልተፈጸመ በቀጥታ ግጭት ውስጥ ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው ግጭት የግለሰብ ብቻ አይሆንም የአንድ ቀበሌ ወይም ማህበረሰብ ግጭት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይሄ ሁሉ ከመሆኑ በፊት በመደበኛው ህግም የሚያዘው ይያዛል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን በባህል ነው የሚፈታው፡፡ ሲፈታ በባህሉ መሰረት የሚደረገው ቁብ ፍየል ወይንም ጊደር ለዚህ ተብለው የተሰየሙ ሰዎች አሉ የተለየ ቦታ ይወስዱና ያርዳሉ፡፡ ደሙንም ያፈሳሉ፡፡ የታረደውንም ስጋ የተጋጩ ሰዎች እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡ በዚህም የተፈጠረው ግጭት ይጸዳል፡፡ ከዚህ በኋላ ሰላም ወርዷል ይባላል፡፡

ሰው እርስ በርስ ግንኙነት መፍጠር አለበት በሚል በዚህ መልኩ ዕርቁ ይፈጸማል፡፡ ከዚህ አንጻር ከባህላዊ ስርዓቱ ጋር በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በጋራና በቅንጅት እየሰሩ መሆናቸውን የሚከተለውን አብነት በማንሳት ትገልጻለች፡፡

### አብነት አንድ

*"ህዳር ወር 2006 ዓ.ም አርፋይዴ ቀበሌ መንደር ሴትየዋ የብአይዴ ቀበሌ ሰው ናት አትወልድም ብሎ ባሏ ጥሏት ይሄዳል፤ በዚህ ምክንያት ከዘመዶቿ ጋር ስትኖር ከጎረቤት ጊዜ ጠብቀው ይደፍሯታል አትወልድም የተባለችው ሴትዮ ታረግዛለች፤ የአካባቢው ሰዎች ባሏ ጥሏት ቢሄድም የሰው ሚስት ናትና እንዴት አረገዘች በሚል እሷን ይይዛሉ፤ ማነው ያስረገዘሽ ማነው አንቺን ያገባው ይሄን ሰው ማውጣት አለብሽ ትባላለች ሰውየው ለዘመናት እንኳ ቢተው በባህሉ ህጋዊ በሆነ መልኩ ሰላልተፋታች በባህሉ መሰረት ሰውየው የግድ ‹ማሳ› የሞራል ካሳ መስጠት አለበት ተባለ፤ በኋላም ጉዳዩን ይዛ ወደሴቶች ጉዳይ ቢሮ መጣችና አመለከተች፤ ሰውየው እኔ አይደለሁም ብሎ ሲክድ እሷ ታውቃለችና በባህላቸው ማሳመኛ ስላላቸው ወደቀበሌው ወደሽማግሌ ጉዳዩን መለስነው፤ ያስረገዘው ሰውዬም አመነ፤ ሰዎቹም እርስ በርስ ከመጋጨት ድነው በዚህ መልኩ በባህል በሽማግሌዎች የጨረሱበት ሁኔታ አለና ይህን ማንሳት ይቻላል"* (የኮንሶ ወረዳ ሴቶችና ሕጻናት ቢሮ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 55)፡፡

በዚሁ የቃለመጠይቅ ወቅት ከሴቶችና ህጻናት መብት ጋር በተያያዘ ያሉ ስራዎችን ስትገልጽ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት እንደሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ የተወሰነ የሚጠቀስ እንቅስቃሴ እንዳለ ታነሳለች፡፡ ከትምህርትና ውርስ ጋር በተያያዘ በባህሉ መብታቸው የተከበረ አይደለም፡፡ በመደበኛው ስንሄድ ግን ሕጻናትም ሆነ ሴቶች እንዲማሩ ብሎም በህግ የተቀመጠላቸውን የውርስ መብት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ባህሉ ግን ይህን ይቃወማል፡፡ ለዚህ ደግሞ አብነቶችን ማስቀመጥ እንደሚቻል ትገልጻለች፡፡

### አብነት አንድ

*"በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴዎች ምክር ቤት ተጠርተው በህገ መንግስት ላይ ስልጠና እየተሰጣቸው እያለ በህገ መንግስቱ ላይ የሴቶች መብት በወንጀለኛ ህግ ላይ የውርስ መብት እንዳላቸው የሚገልጽ ነው ብሎ አሰልጣኙ ሲያቀርብ ስልጠናውን ከሚወስዱ ቋሚ ኮሚቴዎች መካከል የተወሰኑት ይህ የኛን ባህል የሚቃረን ነው እንዴት ሴት ልጅ ትወርሳለች ይባላል ውርስ ለሴት ልጅ እንዴት ተብሎ ያሉትን ማንሳት ይቻላል"* (የኮንሶ ወረዳ ሴቶችና ሕጻናት ቢሮ፣ ጥር 15፣ 2006 ዓ.ም፣ 55-56)፡፡

### አብነት ሁለት

*"በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም እዚሁ ምክር ቤት ላይ ነው ስለውርስ እየተማማሩ እያሉ አንዱ ተነስቶ ውርስ ስትሉ እኛ የምናወርሳቸውን ትምህርት እያስተማርናቸው ነው ፤ተምራ ይዛ ወደባሏ ነው የምትሄደው ይሄን የኛን ንብረት አይደለም ወይ ይዛ የምትሄደው ያሉትን እንዲሁ አስታውሳለሁ ትላለች፤ ወደ መደበኛው የፍትህ ስርዓት ስንሄድ ሴት ልጆች ይደገፋሉ፤ በዚህም ለውጥ እየመጣ እንደሆነ ትገልጻለች ብዙ ሴቶች እየተማሩ ነው በዚህም የራሳቸውን መብት ማስከበር ጀምረዋል፤ በተለይ የሕጻናት መብትን ከማስከበር አንጻር ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሴትና ወንድ ያሉበት የኮንሶ ሕጻናት ፓርላማ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም ከተቋቋመ ጀምሮ ከፍተኛ ለውጥ አለ ይህ ፓርላማ እንደ ኢትዮጵያ የመጀመሪያና ሞዴል ሆኖ የተሰራው በኮንሶ ነው ያሰራውም የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛ አለ በተለይ ሴት ልጅ አትማርም በሚል ወንዱም ቢሆን በተለይ ታላቅ የተባለ በቤት ውስጥ አይማርም፤ ምክንያቱም ቤቱን የሚመራ የሚያስተዳድር ስለሆነ መማር የለበትም የሚል አቋም ስላለ በዚህ ምክንያት ነው ድርጅቱ የተቋቋመው፤ ሴትን ልጅ ማስተማር በብሔረሰቡ ነውር ነበር፤ አሁን ግን ሴትን ልጅ ማስተማር ክብር ነው። ሴት ልጅ ብትማር ለባሏ ነው እኛ አስተምረን አስተምረን ልክ እንደውርስ ይዛ ትሄዳለች የሚለው የባህል ዕምነት ተከታይ ሰዎች አባባል በመደበኛው ትንሽ ለውጥ እየታየበት ነው ማለት ይቻላል፤ በአጠቃላይ በዚህ ረገድ የብሔረሰቡ የባህል እምነት ተከታዮች በተወሰነ ደረጃ ያለውን ለውጥ እየተገነዘቡ ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት የመላክና የማስተማር ሁኔታ ተጀምሯል"* (የኮንሶ ወረዳ ሴቶችና ሕጻናት ቢሮ፣ ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም፣ 56)።

## 5.4 የባህላዊ ሽምግልና ስርዓቱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

በኮንሶ ብሔረሰብ የባህላዊ ሽምግልና ስርዓቱ ብሔረሰቡን በማገልገል በቆየባቸው ዘመናት እንዳሰራር እንዲቀጥልበት የሚበረታታበት (ጠንካራ ጎኖች) እና ቀርነቶች (ድክመቶች) እንዳሉት ከተለያዩ መረጃ ሠጪዎች ጋር በነበረው የመስክ ቆይታ መረዳት ተችሏል። ስለሆነም በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የባህላዊ ስርዓቱ ጥንካሬና ድክመቶች ቀርበዋል።

በዚሁ መሰረት ዋና ዋና ብርታቶች (ጠንካራ ጎኖች) የሆኑት፣

- በብሔረሰቡ ማንኛውንም ጥፋት ወይም ከቀላል እስከ ከባድ ጥፋት ወንጀል ሠርቶና በባህላዊው የፍትህ ስርዓት ላይ ቀርቦ ወንጀልን መካድ ለተጨማሪ ቅጣት ስለሚዳረግ ክህደት አለመኖሩ፣
- ማንኛውም ወንጀል ቢሰራ በማህበረሰቡ ተባባሪነት መረጃ አለመሰወሩ ምስክርም ቀርቦ ትክክለኛውን ጉዳይ በመመስከር (በሀሰት መመስከር ለተለያዩ ለከፋ ችግር ይዳርጋል ተብሎ በባህሉ ስለሚታመን) ግጭቶችን በአጭር ጊዜ በመፍታት ወደ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መቻሉ፣

- ከባድ ወንጀል ሰርቶ ከማህበረሰቡ ማምለጥ ወይም መሰወር አለመቻሉ በዚህ ተግባር የተጠረጠሩ ወይንም ሲሰሩ የተያዙ ሰዎች ከማህበራዊ ኑሮ እስከመገለል የደረሰ ከባድ ቅጣት ስለሚጠብቃቸው በዚህ ረገድ ያሉ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ መምጣታቸው፣
- ለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዘላቂነት ህፃናት ከልጅነታቸው ጀምረው በቃል እየተማሩት በተግባር እያዩት እንዲያድጉ፣ ለባህላዊ ህጉ ተገዢ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ቤተሰብ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መሆኑ ከዚህ ባለፈ የባህል መሪዎች በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች ስርዓቱንና ደንቡን የማስተማርና የመቀስቀስ ሁኔታ እያዳበሩ መምጣታቸው፣
- በባህላዊ የፍትህ ስርዓት ጠበኞች ጉዳያቸው በእርቅ ስለሚቋጭ የአሸናፊና የተሸናፊ ሁኔታ አለመኖር በዚህም ቅራኔ ይዘው አለመሄዳቸው ለዘላቂ ሰላም የሚበረታታ ተግባር መሆኑ፣
- ጠበኞች በባህላዊ የፍትህ ስርዓት ሲቀርቡ ባህላዊ እምነቱ ሁሉንም ጥፋቶች ሆነ ያሉ ችግሮችን ዘርዝረው እንዲናገሩ ስለሚያደርጋቸው ለሽማግሌዎች የድርድር ሂደት ወይንም የውሳኔ አካሄድ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ፣
- በአካባቢው መደበኛው የፍትህ ስርዓቱ እንደባህል ህጉ ጠልቆ እየሰራ ባለመሆኑ ከስርዓት የሚወጡ ሰዎችን በመያዝ ረገድ የጎላ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ በፍትህ አካላቱ አንደበት ሳይቀር የተመሰከረለት መሆኑ፣
- ጠበኞች እና ወንጀለኞች በባህል መዋቅሩ ተገስፀው፣ እንደጥፋታቸው ተቀጥተው ወደ ማህበራዊ ኑሮአቸው ስለሚመለሱ ትዳር አለመፍረሱ፣ ቤተሰብ (ልጆች) አለመበተናቸው በዚህ በኩል የተሻለ ስራ እየሰራ መገኘቱ፣
- የተለያዩ ወንጀሎች ተሰርተው (ተፈፅመው) እና መረጃ ኖሮአቸው በመደበኛው የፍትህ ስርዓት መታየት ቢችሉ ጥሩ ስራ ሊሠራ ይችል ይሆናል፤ ይሁንና በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ላይ የሚቀርቡ ጉዳዮች ብዙ ጊዜ መረጃ አይገኝላቸውም፡፡ በተለይ እንደአካባቢው የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ብዙ ጊዜ የሴቶች ጉዳዩ ሲባል የሴቶችን ችግር የሚፈታ ይመስላል፣ ነገር ግን አይደለም፡፡ የሴቶች ጉዳይ ማለት "ጥርስ የሌለው አንበሳ" ማለት ነው፡፡ በሚል የተገለፀበት ሁኔታ

አለና ከዚህ አንፃር የባህል መዋቀሩ መደበኛውን የፍትህ ስርዓት እያገዘና ወንጀልን እየቀነሰ መሆኑን መጥቀሳቸው፡፡

በሌላ መልኩ የባህላዊ ሽምግልና ስርዓቱ ድክመቶች (ቀርነቶች) የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በባህላዊ ስርዓቱ በአጥፊዎች ወይንም በወንጀለኞች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች የቤተሰብ አቅምን ያላገናዘቡ፣ ከማህበራዊ አገልግሎት ማቀብ ብቻ ሳይሆን የሚደረግበት ከቀዬው (ከመኖሪያ አካባቢው) እስከወዲያኛው መባረር መሆኑና የቅጣት አወሳሰኑ ወጥነት የሌላቸው በመሆናቸው ለባህላዊ ስርዓቱ በአስተማማኝ ሁኔታ መቀጠል ችግር እየፈጠረ መሆኑ፣ ለአብነት ቅጣት ሲበዛባቸው የቅጣት ውሳኔውን ይዞ ወደ መደበኛው የፍትህ ስርዓት በመሄድ አቤት የሚሉበት ሁኔታ እየተፈጠረ መምጣት፣
- ከባድ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች የመጨረሻ የቅጣት ውሳኔ ከማህበራዊ ህይወት (ኑሮ) ማግለል፣ ማዕቀብ መጣል (ለአብነት እሳት እንዳይጭሩ፣ ከማንም ጋር እንዳይገናኙ ልጆች በጋራ እንዳይጫወቱ ማድረግ) ወዘተሲሆን፣ ይህ ከስነ-ልቡና አንፃር ትልቅ ቅጣት (ገደብ) በመሆኑ በመደበኛው የፍትህ ስርዓትም እየተነቀፈ ያለ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል ጥረት አለማድረግ፣
- በብሔረሰቡ ጎሳዎች በስብጥርና እርስ በርስ በመከባበር የሚኖሩ ሲሆን የተለያዩ ከባድ ወንጀሎች ሲፈፀሙ በተለይ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ለሚቀርቡ ወንጀሎች መረጃ የማጥፋት (መረጃ ያለመስጠት)፣ በምስክርነት አለመቅረብ (አለመመስከር) ለመደበኛው የፍትህ ስርዓት አሰራር እንቅፋት መፍጠር እና ወንጀልን በጋራ በመከላከል ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ማሰናከል፣
- ባህላዊ ህጉ በጽሁፍ የተደገፈ ባለመሆኑ ማናቸውም የቅጣት ውሳኔዎች (ቀላል ሆነ ከባድ) በዘፈቀደና ወጥነት የሌላቸው መሆኑ አልፎ አልፎ ለአድሎአዊ አሰራር በር እየከፈተ መምጣት፣ ይህ ደግሞ ለባህላዊ ህጉ ዘላቂነት ችግር እየፈጠረ መሆኑ፣
- አንዳንድ ወንጀሎች በባህላዊ ህጉ መሰረት ለእርቅ ድርድር ቀርበው ወንጀሉን አልሰራሁም ብለው ሲክዱ ወይንም መረጃ ሲያሸሹ ከፍተኛ ግርፍያ የሚከተላቸው መሆኑ፣ ይህ ደግሞ ህጉ በአንድ በኩል አካላዊ ድብደባን እያወገዘ በሌላ መልኩ

ግርፊያ መፈፀሙ ሰብአዊ መብትን የሚነካ፣ የመደበኛው የፍትህ አሰራሩንም የሚፃረር መሆኑ፣

- በባህል ህጉ የሚቀርቡ የተለያዩ ችግሮች በተለይ የሴቶች በደሎች በግድ ወደ እርቅ ስለሚገፋፉአቸው ጉዳዩንም በእርቅ መፈፀም ስለሚፈልጉ እጅግ የተበደሉ ሴቶች ትዳር በቃኝ ብለው የቆረጡ እንኳን ቢሆን ግዳጅ ስለሚኖርበት ሴቶችን ለበለጠ ጉዳት መዳረጉ፣
- ሽምግልና ላይ የሚቀመጡ ሰዎች የጥቅማ ጥቅም ፈላጊነት ስሜት መኖር ይሄን ያህል ካልሰጣችሁን ብሎ የመጠየቅ በርግጥ ለግልጋሎታቸውና ለሚያባክኑት ጊዜ ክፍያ ስለሌላቸው ከድርድሩ በኋላ አስፈላጊ ቢሆንም የጥያቄው አቅጣጫና አዝማሚያ ጥሩ አለመሆን የነበረው ስርዓት ፈሩን እየለቀቀ ያለበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑ፣
- በሽምግልና ወቅት አድልኦ መታየት መጀመሩ አንድ አቅጣጫ የመያዝ፣ ነገሩን የማድበስበስ ሁኔታዎች ብቅ ብቅ ማለትና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣ ለባህላዊ ስርዓቱ ዘላቂነት የራሳቸው የሆነ ተፅዕኖ ስለሚኖራቸው ከወዲሁ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚገባና አዝማሚያው በአጭሩ መቀጨት እንዳለበት ይገልፃሉ። ምክንያቱም እንደዚህ አይነት አሰራሮች እያደጉ መምጣታቸው የባህል ስርዓቱ ዘላቂነት ላይ አጠያያቂ ሁኔታ ውስጥ መክተት ብቻ አይደለም ዘላቂ ሰላምን ያበላሻሉ፤ ህብረተሰቡን ያሻክራሉ፣ ጥላቻና ጦርነትን ያስነሳሉ፤ ግድያ፣ ድብደባና መፈነካከትን መወጋጋትን ወዘተ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

## 5.5 ለባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዘላቂነት እንደስጋት የሚነሱ

በብሔረሰቡ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ዋናው የፍትህ ተቋም ሆኖ ከዛሬ አምስትና ስድስት መቶ ዓመት በፊት ጀምሮ ዛሬም ድረስ እያገለገለ ይገኛል። ይሁንና አሁን ባለበት ሁኔታ ዘላቂነቱን የሚፈታተኑ አንዳንድ እንደስጋት የሚታዩ ለውጦች እየተከሰቱ ነው። በተለይ ከውሳኔ አሰጣጥ ጋርና የባህል ስርዓቱን ከመዳፈር አኳያ በተጨባጭ እየታዩ ያሉ ለውጦች አሉ። ይህ ደግሞ ለብሔረሰቡ የባህል ተቆርቋሪዎች የሚዋጥ ነገር ባለመሆኑ ሀይ ሊባሉ ይገባል" ሲሉ ኪሮስ ጃርሶና ካላ ገዛኸኝ በየመኖሪያ ቤታቸው በተደረገ ቃለመጠይቅ ስጋታቸውን የሚከተሉትን አብነቶች በማንሳት ይገልጻሉ።

እንደ ካላ ገዛኸኝ አስተያየት ከሆነ *"በአሁኑ ሰዓት የባህላዊ ስርዓቱ አካሄድ ሲታይ ትክክለኛ መሠረቱን ጠብቆ በትክክል እየሄደ ነውም ኢይደለምም ለማለት ያስቸግራል* በተለይ ከውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ" ይላሉ፡፡ ለዚህም የሚከተለውን አብነት ያነሳሉ፡፡

## አብነት አንድ

*"የዛሬ 4 ዓመት 2002 ዓ.ም ላይ ነው ከአንድ ቀበሌ ወደኔ የመጣ የሁለት ወንድማማቾች ጉዳይን አስታውሳለሁ፤ የጠቡ መነሻ መሬት የንብረት ክፍፍል ነበር፤ጉዳዩ በጎሳቸው እንደቤተሰብ ታየ ጎሳቸው መፍታት አልቻለም ከዚያ ወደ ከንታ ከከንታ ወደፓሌታ ተሸጋግሮ በባህላዊ ምክር ቤቱ ቢታይም ከእነሱም አቅም በላይ ሆነ፤ ምክንያቱም ቡድንተኝነት ጥቅማ ጥቅም መፈለግና አድሎ ስለነበረ መከፋፈል ነበረበት፤ አንዱ ከገባበት ክፍል አንቶቻቸውም የተከፋፈሉበት ፍፁም ወደ አንዱ ያደላበት ሁኔታ ነበር፤ ከዚህ በኂላ ነገሩ ሳይፈታ ሲቀር ምንም ዓይነት እርቅ ላይ ሊደርሱ ባለመቻላቸው ጉዳዩ ወደ እኔ ተመራና ጉዳዩን ከፓሌታ ተወካይ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ የአንዱ ካገባበት ከአንቶቻቸው ከጎሳቸውም ከሌላም ጎሳ ወኪሎች አብረን ስንመለከት በግምት 1 ሰዓት ከ 30 ደቂቃ ፈጅቶ ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር ያየሁት፤ በርግጥም የሚያዳሉ መሆኑን ነበር የተረዳሁት፤ እንዳያውም የሌለ ታሪክ ለማምጣት የሚሞክሩበት ሁኔታ ነበር፤ ከጎሳው ታላቅ ናቸው ተብሎ የታሰቡ ሰዎች ናቸው በነሱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በትክክል ያውቃሉ ከኔ በፊት የሆነ ነገር እኔ የማውቀውን ነገር ገልብጠው ይናገሩ ነበር፤ እኔ በዚህ ጊዜ በጣም አፈርኩባቸው፤ በቃ እንግዲያውስ እናንተ በታች ባሉት ደረጃዎች አይታችሁታል አልተቻለም ይፈታል ብላችሁ ነው ወደኔ የላካችሁት አሁን ለኔ ተውልኝ የማደርገውን ዝም ብላችሁ ተከታተሉ እኔ በትክክል እያስኬድኩ ከሆነ አድምጡኝ መጨረሻ ላይ አስተያየት ትሰጡኛላችሁ እያበላሸሁ ከሆነ አስቁሙኝ አርሙኝ ከዚህ ውጭ ማንም እንዲናገር አልፈቅድም እኔ ከነሱ ጋር ያለውን ሁኔታ እየጠየቅሁ ወደዚያ እየሄድኩ ስጠይቅ መጨረሻ ላይ ነገሩ እየሄደልኝ እየሰመረ መጣ፤ ነገሩን ወደመተማመን ደረጃ ላይ ደረሱ፤ መጨረሻ ላይ ቃሉ ምን መሆን አለበት፣ ማሳረጊያው ምን መሆን አለበት እስኪ ሀሳብ ስጡኝ ስል እኔንና አደራዳሪዎችን ረስተው ምንድነው ያደረጉት እራሳቸው እርስ በርስ ነው በዚያው የተቻቻሉት እኔ ይህን ትቼልሀለሁ አንተ ይህን ተውልኝ ተባባሉ፤ እስከ ክስ ደረጃ ሄደው ነበር እዚያው ክሱ እስከ አመራር ደርሶ ቀርቦ መፍታት አልተቻለም ይህን ጉዳይ በዚህ መፍታቴን አስታውሳለሁ፤ እኛ የራሳችንን የውሳኔ ሀሳብ ሳናቀርብ ራሳቸው የጨረሱበት ሁኔታ ነበር፤ ስለዚህ ይሄ በፅሁፍ ውል ይስፈርልን አሉ እኔም ያሉትን ነገር ማስታወሻ እየያዝኩ እሄድ ስለነበር ከፅሁፍ ማስታወሻዬ በመነሳት ውሳኔ ፃፍኩኝ አነበብኩላቸው በትክክል ቃል በቃል ተረጎምኩላቸው ተረዳን በቃ ይሄ ይሁን አሉ ፈረሙ አንደኛው የውል ፊርማ እዚሁ አንደኛው ፓሌታ፣ ኮፒ በሁለታችን እጅ አንዱ አንድ ኮፒ ለራሱ ሌላኛውም እንዲሁ አንድ ኮፒ እንዲይዝ ዋናው ኦርጅናሉ እዚህ እኔጋ እና የመጨረሻ ውሳኔ ይህን ያፈረሰ ሰው ምን እንደሚቀጣ ጭምር አስቀምጠን በፅሁፍ ውል አድርገን ጨረስነው መጨረሻ በድርድሩ ላይ የተገኙ ሠዎችን ጠየቅሁ አንዱ በሚገርም ሁኔታ ነው እኔ የሆነ ጉዳይ አለኝ በቃ ወደዚህ ነው የማመጣው አለኝ በጣም ደስ ስላለኝ አለ፤ በርግጥም አመጣ ፈታንለት ፤እና በዚህ መልኩ ነው ችግር እንዳለና ማዳላት እንዳለ የተረዳሁት የማዳላት ሁኔታ ነገሮችን ያበላሻል ስለዚህ በትክክል ይሄዳል አይሄድምም ለማለት የተቸገርኩት ከዚህ አንፃር ነው›› ሲሉ* ይገልጻሉ (ጋሞሌ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 21-22)፡፡

## አብነት ሁለት

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ላይ ልዩነት መኖሩን ''ጥንትና አሁን ለውጥ አለ" ሲሉ ኪሮስ ጃርሶ በተመሳሳይ ዕለት በነበረ የቃለመጠይቅ ወቅት ‹‹ፊትና ዛሬ›› በማለት በንጽጽር የሚከተለው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ለውጡን ይገልጻሉ።

*‹‹ፊት አንደኛ የኮንሶ ማህበረሰብ በስራ አመዳደቡ ኻውዳና ኤታንታ ተብሎ በሁለት ይመዳባል፤ ኻውዳ በንግድ የሚተዳደረው ሲሆን፣ ኤታንታው ደግሞ በእርሻ የሚተዳደረው አርሶ አደሩ ነው፤ ኤታንታው" ብዙ ጊዜ ጨዋ ነው አይዋሽም ተብሎ የሚነግርለትና የሚታመንበት ነው፤ ኻውዳው ግን ከስራው ባህሪ የተነሳ የዕደጥበብ ውጤቶችን ስለሚሸጥ ዋጋ ሊጨምር ይችላል በሚል ሞራ ላይ ግጭት በሚፈታበት ወቅት የሚናገረው ኤታንታው" ብቻ ነበር ያውም ሀንሳቢታ ወይንም ቅጠሏን በእጁ ይዞ ሀንሳቢታ ብዙ ጊዜ የሰላም የእውነት ማብሰሪያ ምልክት ነው ተብሎ ስለሚታመን ኤታንታዎች ሲናገሩ ክብር ይኖረዋል፤ ነገሩ ሁል ጊዜ እውነት ነው በሚል እነሱ ብቻ እንዲናገሩ ይደረጋል፤ ኻውዳዎች ግን ከዳር ነው የሚቀመጡት መሀል ገብተው እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም ሲናገሩም ሊያዳሉ ይችላሉ በሚል ጭምር ሌላው ኻውዳዎች" ሀንሳቢታ ይዘው ሞራ ላይ አይናገሩም ነበር ዛሬ ግን እነሱ ናቸው ዋና ተዋናዮች ለውጥ አለ፤ ሁለተኛው ፊት ልጅ እግር አይናገርም ነበር ሽማግሌ ብቻ ነበር የሚናገረው ልጅ እግር ግፋ ቢል እከሌን ጥራ እንዲህ አድርግ ተብሎ እንዲላክ ይደረጋል እንጂ አይናገርም ዛሬ ልጅ እግርም መብት ነው ብሎ ለመናገር ይሞከራል ይናገራልም ይህም ለውጥ ነው፤ ሌላው ሴት ልጅ ድሮ ሞራ ላይ አትቀመጥም አትናገርም ነበር ዳር ሆና ነበር የምትናገረው ዛሬ ግን መሀል ሆና ለመናገር እየሞከረች ነው ይህም ሌላው ለውጥ ነው፤ ሌላው ሰው ድሮ ወደ ባህላዊ ዕምነት ሲመጣ ባህላዊ ዕምነቱን ይዞ ነበር የሚመጣው ዛሬ ግን ክርስትና ነው በሚል የባህላዊ እምነቱ አካሄድ እየተረገጠ ነው ከዚህ በተጨማሪ አንድ ጉዳይ በከንታ ይነሳል ከንታ ላይ ውሳኔ መስጠት ካልተቻለና ጠንከር ብሎ ከተገኘ ወደ ፓሌታ ይወሰዳል ወደ ካርሞቴ ሞራ ፓሌታ እዚያ ግጭቱን ለመፍታት ይሞከራል አሁንም ነገሩ ጠንከር ብሎ ከተሰማ ከተካካዱ ወደ ትልቁ ሞራ ወደ መሀላ ሞራ ሞራ ኻኻ ይላካል ዛሬ ይሄ ሁሉ እየቀነሰና እየጠፋ ነው››* (በደንገልቱ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 35) በማለት ያስረዳሉ።

ኬዞች(አብነቶች) እንደማሳያ *አቶ ኪሮስ ሁለት ጉዳዮችን ያነሳሉ፡፡*

> *‹‹ከከባድ ግጭቶች መካከል የሰው ህይወት ማጥፋት አንዱ ወንጀል ነው፤ ድሮ የነፍስ ግድያ ወንጀልን የሚመለከቱትና የሚፈቱት የባህል ሽማግሌዎች፣ አፓ ቲንባዎችና ዳውራዎች ናቸው ዛሬ ግን መደበኛው የፍትህ ስርዓት ሆኗል*›› (በደንገልቱ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 36) በማለት ያስረዳሉ።

*‹‹በብሔረሰቡ ሴትን ልጅ መድፈር ከባድ ወንጀል ነው ከዛሬ አንድ መቶ ዓመት በፊት በብሔረሰቡ ሴት ልጅ የደፈረ በቁሙ ገደል ውስጥ በመጨመር እንዲሞት ይደረግ ነበር አሁን ግን በመደበኛው ፍ/ቤት እንዲታይ ተደርጎ በዚያው ውሳኔ ይሰጥበታል ከፍ/ቤት ውሳኔ በኋላ ደግሞ ማህበረሰቡ ወንጀለኛ ነው ብሎ ስለሚያምን ወደመንደሩ እንዳይመለስ ይደረጋል››* ይህም ለውጥ ነው ሲሉ ይገልጻሉ (በደንገልቱ፣ ጥር 19፣ 2006 ዓ.ም፣ 36)።

# ምዕራፍ 6. ትንተናና ቁዘማ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እስከ አሁን በዚህ ጥናት ውስጥ በተመለከተው መሠረት በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ጠቅለል ያለ ትንተናና ገለጻ ቀርቧል። ይኸውም በግጭት አፈታት ሥርዓቱ ውስጥ ማህበራዊ መሠረት የተጣለላቸው ተቋማትና መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው፣ በአፈፃጸም ሂደት ውስጥ እምነታዊ ስነ-ስርዓቶች ከሚሰጡት ፍች፣ ትርጉምና ግንዛቤ አንፃር፤ እንዲሁም ማህበረሰባዊ እንድምታዎች ደግሞ ካላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳዎች አኳያ በዚህ ክፍል ውስጥ ይተነተናሉ።

## 6.1 ማህበራዊ መሠረት የተጣለላቸው ተቋማትና መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው

የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት፣ አደረጃጀትና አወቃቀር እንደ ጉዳዩ ዓይነት የተለያዩ ባህላዊ ችሎቶች ሲኖሯቸው፣ የዳኝነት ዓይነቶቹም ሆነ ደረጃቸውና የዳኝነት ቦታዎቹ የተለያዩ ናቸው። የነዚህ ባህላዊ ተቋማት አደረጃጀትም በ3 (ሶስት) ደረጃዎች የተከፈሉ ሲሆኑ እነዚህም ሞራ-ከንታ የመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ ችሎት፣ ሞራ-ፓሌታ ሁለተኛ ደረጃ ባህላዊ ችሎት እና ፖቅላ ሶስተኛ ደረጃ ባህላዊ ችሎት ተብለው የተደራጁ ማህበራዊ የዳኝነት ተቋማት እንደሆኑ ተመላክቷል።

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ችሎቶች በቅርብ ጓደኞች አካባቢና በቤተሰባዊ ጉበኤ የሚዳኙ የችሎት አደረጃጀቶች ሲሆኑ፣ ሁለቱም በጥቅሉ ቤተሰባዊ (ፓሌታዊ) የዳኝነት ችሎቶች ሲባሉ ሦስተኛው ግን በጎሳ መሪ ዳኝነት የሚከናወን ስለሆነ ጎሳዊ (ፖቅላዊ) የዳኝነት ችሎት ተብሎ እንደሚታወቅ ለመግለጽ ተሞክሯል። በነዚህ ባህላዊ *የፓሌታዊና የፖቅላዊ* የዳኝነት ችሎቶች እልባት ሊገኝላቸው ያልቻሉ ግጭቶችና አለመግባባቶች ደግሞ ኻኻ ተብሎ በሚታወቀው *የመሀላ ስነ-ስርዓት* ፍፃሜ እንዲያገኙ የሚደረግ መሆኑ ተጠቁሟል።

ባህላዊ የፍትህ ስርዓት አወቃቀሩ በነዚህ የተለያዩ ባህላዊ የችሎት ደረጃዎችና ትውፊታዊ ተቋማት አደረጃጀቶች የሚታይ ሲሆን እንደ ግጭቶቹ ዓይነት፣ የግጭቶቹ ቅለትና ክብደት እየታየ ከቀላል እስከ ከባድ በመፈረጅ ጉዳዮች በየደረጃው በሚገኙ እና በተዋቀሩ *ማህበራዊ የሞራ* ፍርድ ቤቶች እንደሚከናወኑ ተገልጿል። ይህም ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ፅኑ ባህላዊ፤ ማህበራዊና እምነታዊ መሠረት ያለው ሲሆን የማይናወጥ ባህላዊ የፍትህ ብያኔዎችን መስጠት ብቻ ሳይሆን በሚወሰነው ብያኔም ማህበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ ወደ

ነበሩበት እንዲመለሱም እንደሚደረግም ቀደም ባሉት የጥናት ምዕራፎች ውስጥ እንዲሁ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

በ3ቱም (ሶስቱም) የመዋቅር ደረጃዎች ያሉ የስርዓቱ አስታራቂዎች እንደደረጃቸው በየደረጃው ለሚቀርቡላቸው የግጭት ዓይነቶች በግጭት አፈታት ስርዓቱ ወቅት የየራሳቸው ሚና ያላቸው መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ ብዙ ጊዜ ከጎደኛና ከቅርብ ወዳጅ ያለፉ ቀላል ግጭቶች በመጀመሪያው የችሎት ደረጃ (በሞራ-ከንታ) መፍትሔ የሚያገኙ ሲሆኑ፣ በዚህ ደረጃ መፈታት ያልቻሉና ጠንከር ያሉ ጉዳዮች በዋናው ሞራ (በሞራ-ፓሌታ) ወይም በቤተሰባዊ ጉባኤ ደረጃ ተላልፈው መፍትሄ የሚሰጣቸው መሆኑ ተገልጿል፡፡ በነዚህ ደረጃ ታይተው ዕልባት (መፍትሔ) ማግኘት ያልቻሉ ጉዳዮች ደግሞ ወደ ፖቅላ ደረጃ ተሸጋግረው የጎሳ መሪው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል፡፡ ከዚህ የመጨረሻ የዳኝነት ችሎት የዘለሉና በዚህ ደረጃ ያልተቋጩ ጉዳዮች ደግሞ በኻኻ ወይም መሀላ በመፈጸም የሚጠናቀቁ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ ይህ ተቋማዊ አደረጃጀትና መዋቅርም እስከ አሁን ድረስ እየተሰራበት ያለና ሕያው ማህበራዊ ስነ-ስርዓት ሆኖ አገልግሎት እየተሰጠበት እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮች የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ብዙ ጊዜ በማህበረሰቡ የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶች በየደረጃው ባሉ የባህል ችሎቶች ዕልባት የሚያገኙ ናቸው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ከነሱ በላይ ሲሆንና ጉዳዩን መፍታት ካልተቻለ በኻኻ ወይም መሀላ በመፈጸም ዕልባት ይሰጣል፡፡ መረጃ አቀባዮቹ ይህንኑ ሲያስረዱም በብሔረሰቡ ወደ መሀላ የሚያስኬዱ ጉዳዮች ዋነኛ ምክንያት ግን ዕውነትን ፍለጋ እንደሆነ ነው፡፡ አንዳንድ ጉዳዮችን አጣርቶና አስመስክሮ ውሳኔ ለመስጠት ሲያስቸግር ወይም መንስኤያቸው የማይታወቁ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ወይም በምስጢር የተፈጸሙ ድርጊቶች ሲፈጠሩ እውነቱን ለማውጣት ሲፈለግ ኻኻ አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን እነዚሁ በመስክ ስምሪት ያገኘኋቸው መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

ይህን ሃሳብ ከመደበኛው የፍርድ አሰጣጥ ሂደት ጋር በማነፃፀር ስንመለከተው መደበኛው አሰራር በየደረጃው የተዘረጋ የራሱ መዋቅራዊ የፍርድ አሰጣጥ ሂደት አለው፡፡ ውሳኔ ለማግኘት በዚያ በተዘረጋ የመዋቅር ሂደት ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኮንሶ ብሔረሰብ ዘንድም ምንም እንኳን በፍትህ አካሄዱ በወንጀለኞች ላይ የሚጣሉ ቅጣቶች የቤተሰብ አቅምን ያላገናዘቡና አወሳሰኑ ወጥነት የሌለው ቢሆንም ባህላዊ የግጭት

አፈታት ስርዓቱ በየደረጃው ውሳኔ የሚያሳልፍባቸው ባህላዊ የችሎት ተቋማት እንዳሉትና አደረጃጀቱም ከጥንት ጀምሮ ተዘርግቶ በአገልግሎት ላይ እንደሚገኝ ተመልክተናል። ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ *የሞራ ፍ/ቤቶች* የህብረተሰቡን ባህላዊ የፍትህ ስርዓት እንዲያገለግሉ የተዘረጉ ባህላዊና ማህበራዊ የፍትህ መዋቅሮች ናቸው። ዛሬም አገልግሎታቸው የተቋረጠ አይደለም። ከነዚህ መሠረታዊ ሀሳቦችና ትንታኔዎች በመነሳት ብሔረሰቡ ከመደበኛው የፍትህ ሥርዓት በበለጠ በራሱ የባህል ህጎችና ድንጋጌዎች ተመርኩዞ ከላይ በተጠቀሱት ባህላዊ *የሞራ ፍ/ቤቶች* ለአብዛኛው ጉዳዮቹ መፍትሔ በመስጠት የሚተዳደር መሆኑን መረዳት ይቻላል። የማንኛውም የህብረተሰቡ አባል ምርጫ ካልሆነ በስተቀር በባህላዊውም ሆነ በመደበኛ የፍትህ ስርዓቶች መርጦ መጠቀሙ እስካሁን ችግር ያለበት ጉዳይ ሆኖ አይታይም።

## 6.2 በባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ የልዩ ልዩ ትዕምርቶች ፍችና ፋይዳ

በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ የራሱ የሆነ ሂደትና የአፈፃፀም ስርዓት ያለው ነው። ከዚሁ ጋር ስርዓቱ የሚከናወንበት የራሱ ጊዜ /ሰዓት/ ዕለትና ቦታ እንዳለው በመስክ ቆይታ ከመረጃ አቀባዮች ጋር በነበረ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያስረዳ መሆኑ ተገልጿል። መረጃ አቀባዮቹ ይህንኑ ሲያስረዱም "ጊዜና ሰዓቱን በተመለከተ ሁልጊዜም ጠዋት /ማለዳ/ ከብት ሳይሰማራ ሰው ከእንቅልፉ ሳይነሳ፣ እህል ውኃ ሳይቀመስ ቀደም ብሎ ሽማግሌዎች የሀንሳቢታ ቅጠል በመያዝ፣ ፊታቸውን ሳይታጠቡና እህል ሳይቀምሱ የሚፈጽሙት ስነ-ስርዓት" እንደሆነ ይገልፃሉ።

ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው ጉዳይ ቢኖር እያንዳንዱ ትውፊታዊ ስነ-ስርዓት ተምሳሌታዊ /ትዕምርታዊ ፍች/ያለው መሆኑን ነው። በዚህ ዓይነቱ ሂደት ስርዓቱ ማለዳ የሚመረጥበት ዋና ምክንያት ሰው እህል፣ ውኃ ሳይቀምስ የሚናገረው ነገር ሁሉ እውነትን መሰረት ያደረገ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ማለዳ ላይ በንፁህ አዕምሮ ሰዎች በጥሞና ለመደማመጥ፣ ለመስማማትና ለመከባበር አስተሳሰባቸው ቅንነት የተላበሰ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብም ነው። የ"ሀንሳቢታ" ቅጠል ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እርጥብ ቅጠልና ሳር መያዝ እርቅ ማውረድና ሰላምን ለመፍጠር የተስፋ ምልክት ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው።

ይህ ስርዓት በአብዛኛው በኢትዮጵያ በሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህልና እምነት ውስጥ በተመሳሳይነት የሚከናወን ነው፡፡ ይህም በጐ እሴትና መልካም ተመክሮ ነው ዛሬ በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ እየተፈጸመና እየተተገበረ ያለው፡፡ ተመክሮው ሰላምን ከመፈለግ አኳያ የሚከናወን በመሆኑ ዘመን አልሻረውም፣ ጊዜ አልጣለውም፣ በመደበኛ የፍትህ ስርዓትም ተተክቶ አገልግሎቱን አላቆመም፡፡ ስርዓቱ ዛሬም ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ነገም ቀጣዩ ትውልድ ተረክቦ የሚገለገልበት እንደሆነም ካሉት ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን ባህላዊው የፍትህ ሥራዓቱ ካለው ጠንካራ ማህበራዊ መሠረትም መገንዘብ ተችሏል፡፡

በሞራ-ከንታ ደረጃ የሚፈቱ ቀላል ግጭቶች ከግለሰብ፣ ከቤተሰብና ከጐረቤት ግጭት ያልዘለሉ ጉዳዮች መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ደረጃና በዚህ መልኩ የተፈጠሩ ግጭቶች በይቅርታና በቀላል ቅጣት ዕልባት የሚያገኙ ናቸው፡፡ ጠበኞችም በይቅርታ ሰላማቸው ከተመለሰና እርቅ በማህላቸው ካወረዱ በኋላ ያስያዙት የኸራታ ገንዘብ ተመልሶላቸው እርስ በርስ በመጨባበጥ ወይንም እጆቻቸውን ወደ ሰማይ እያነሱና እያወዛወዙ በቃ ሰላም ወርዷል በማለት ከሞራው በተለያየ አቅጣጫ ይወጣሉ፡፡ በተለያየ አቅጣጫ እንዲወጡ የሚደረገውም ሰላም መውረዱን ለማመልከት ነው፡፡

በመረጃ አቀባዩቹ መሠረት ባለጉዳዮቹ በተለያየ አቅጣጫ መውጣታቸው ሰላም የመውረዱ ምልክት ብቻ ሳይሆን በተለያየ መንገድ ሲሄዱ በሚሄዱበት መንገድ ሁሉ እግዚአብሔር በፀጋና በመንፈስ የሚከተላቸው መሆኑንም ለማሳየት እንደሆነ ባለፉት ተከታታይ ምዕራፎች ተገልፆአል፡፡

ይህ በኮንሶ ብሔረሰብ ዘንድ ከዕርቅ በኋላ ጠበኞች በተለያየ አቅጣጫ በመውጣት የሚያከናውኑት ስነ-ስርዓት ተምሳሌታዊ ወይም ትዕምርታዊነት አለው፡፡ ይኸውም ማለት ሰላም ካለ ሁሉ ነገር አለ፤ በነፃነት መንቀሳቀስ አለ፤ ከስጋት ነፃ የመሆን ዕድሉም ሰፊ ነው፡፡ ሰላም ካለ በራስ መተማመኑ ሁሉ አለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል የነበረው ሰላም ሲደፈርስበት፣ ጠብና ጥላቻ ተፈጥሮ ስጋት ላይ ሲወድቅ ማህበራዊ ህይወቱ ይናጋል፡፡ ስለዚህም ሰዎችን ይጠራጠራሉ፣ በራስ መተማመኑም ይጠፋል፡፡ ሁሉም ነገር የሸሸና የራቀ ያህል ሆኖ ባዶነት ይሰማዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሰላሙ

ሲመለስ ግን እነዚህ ሁሉ ስጋቶች ይጠፉና የሰላም አየር መተንፈስ ይቻላል፤ መረጋጋትም ይፈጠራል፣ ሰላማዊ ህይወትንም መምራት ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ስለዚህም በማንኛውም ሁኔታ ጠብና ቅራኔ ውስጥ የገቡ ሰዎች ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ህይወታቸው ሲመለሱ በተለያየ አቅጣጫ እየሄዱም ቢሆን የሚረግጡት መሬት ሰላም የወረደበት፣ የሚተነፍሱት አየር ሰላማዊ መሆኑንና በሙሉ እምነት ይቅር እንደተባባሉ ሁሉ እግዚአብሔርም በፀጋውና በመንፈሱ ይቅር ብሎአቸው እንደሚከተላቸው እምነት ያድርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ውስጥ ጠበኞች ከጠባቸው ተመልሰው ዕርቀ-ሰላምን አውርደው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ሰላሙ የወረደበትን አግባብና እንድምታ የሚረዱት ዕርቀ ሠላምን እግዚአብሔር ፈቅዶታልና አምላክ በመንፈስ ይከተለናል የሚል ትዕምርታዊ ፍች፣ ትርጉምና ግንዛቤ በመስጠት ነው፡፡

በብሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደትና በአፈፃፀም ስርዓቱ ወቅት ስነ-ስርዓቱ በ3/ሶሥት/ ሽማግሌዎች ቅደም ተከተል ልመና፣ ተማፅኖና ምርቃት የመጀመሩ ምስጢር የራሱ የሆነ ተምሳሌታዊ /ትዕምርታዊ ፍች/ ያለው መሆኑን በቡድን ውይይት ወቅት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክት ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ ብዙ ጊዜ “ሞራ” ላይ በሽምግልና ደረጃ ለዳኝነት የሚቀመጡት አባላት በ3ቱ (በሦስቱ) የማህረሰቡ የትውልድ የዕድሜ እርከን ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህም በ1ኛ ደረጃ የሚታዩት የመጀመሪያ ትውልድ ተብለው የሚጠሩት “በአያትነት” ደረጃ ያሉ የእድሜ ባለፀጋዎች ወይም በብሔረሰቡ አጠራር “ጫብሳ” የሚባሉት ናቸው፡፡ በ2ኛ ደረጃ የሚታዩት ደግሞ ተከታይ ትውልድ ተብለው “በአባትነት” ደረጃ ያሉ አባቶች ወይም በብሔረሰቡ አጠራር “ቃዋሻ” የሚባሉት ናቸው፡፡ በ3ኛ ደረጃ የሚታዩት ግን ቀጥሎ በኃላፊነት ላይ ያለው ትውልድ ተብለው በወጣትነት ደረጃ ያሉ ጎልማሶች ሲሆኑ በብሔረሰቡ አጠራር “ካይሎላ” የሚባሉት ናቸው፡፡

ይህ 3ቱ (ሦስቱ) የእድሜ ቅደም ተከተል ያለምክንያት የሆነ አይደለም፡፡ ህብረተሰቡ በ3ት (በሦስት) ቁጥር ላይ ያለውንም ተምሳሌታዊ /ትዕምርታዊ ፍች/ ምን እንደሆነ ትኩረት እንድንሰጠውም ያደርገናል፡፡ በመስክ ወቅት የቡድን ተወያዮቹ ይህንንም ሀሳብ ሲያስረዱ የዕድሜ ቅደም ተከተሉ ስርዓትና ስነ-ስርዓቱ በ3ቱ የእድሜ ክልል ሰዎች መጀመሩ አያት ከሁሉም ቀዳሚ እንደሆነ ተደረጎ ሰለሚቆጠር ነው፡፡ ለአያቶች ትልቅ ክብርና ቦታ ስለሚሰጥ ነው፡፡ ከአያት ቀጥሎ ተከታዩ አባት ስለሆነ ለወላጅ አባትና አሳዳጊ እንዲሁ

በደረጃው ማህበራዊ ክብር ይሰጣል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው ትውልድ ውክልና የሚሠጠው በተመክሮ ስለ ፍትህ ስርዓቱ አሠራር ትምህርት እንዲቀስምም ለማድረግ ነው፡፡

በመጨረሻ ግን ቀጣይና ተረካቢው ትውልድ የሚባል የህብረተሰቡ ክፍል በታዛቢነት በስነ ስርዓቱ ላይ እዲቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ ይህ ትውልድ በብሔረሰቡ አጠራር "ማቃይሳ" ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ በታዛቢነት እንዲገኙ ቢደረግም ሁኔታው ግዴታም ሆነ ወሳኝነት የለውም፡፡

ይህ ሂደት በሁሉም የግጭት አፈታት ስርዓት ውስጥ እንደ "ቀመር" የሚያገለግል ነው፡፡ አሁንም እየተሰራበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡ እናም ስርዓቱ በአያት ቡራኬ፣ ፀሎትና ምርቃት መጀመሩ አያት ከአባትም ሆነ ከልጅ በዕድሜ ቀዳሚ ስለሆነ ነው፡፡ አያት በዕድሜ ባለፀጋነቱ ክፉና ደጉን የለየ በመሆኑ ምንም ቢመጣ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የሚጠራ ሰው አያት ነው፡፡ አንድም ሁሉም ከሱ ይጀምራል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዕድሜ ቅደም ተከተል ሁሉም ይመጣል የሚል እንደምታም አለው፡፡ የዳኝነቱም አካሄድ፣ ትምህርቱም ሆነ የስነ-ስርዓቱ አሰራር በየደረጃው የሚመጣው እና የሚቀጥለው ብሎም ከትውልድ ትውልድ መውርስ የሚቻለው የዘር ሀረግን መሠረት አድርጎ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ተምሳሌትነቱና ትዕምርታዊነቱም ከዚሁ የዘር ሀረግ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ነው፡፡

ከዚህ 3ቱ የትውልድ ቅደም ተከተል ስርዓት የምንረዳው ጉዳይ በርካታ ቁም ነገር ከቁጥሩ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም 3 /ሶሥት/ ቁጥር በራሱ ትዕምርታዊና እምነታዊ ቁርኘት ስላለው ነው፡፡ 3 /ሶሥት/ ቁጥር በህብረተሰቡ ዘንድ የህይወት ዑደትን የሚያመለክት ነው፡፡ የዕድሜ ቅደም ተከተሉ የትውልድ የመተካካትን እና "ከአያት-አባት-ልጅ" የዘር ሀረግ መወራረስን የሚያሳይ የ3ት ደረጃ ዑደትን የሚያመለክት ስለሆነ ነው፡፡

የፍትህ ስርዓቱ ታላቅንና አባቶችን አክብሮ መቀበልን የሚጠይቅ ግዴታዎች አሉት፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱን በቅብብሎሽ የማዝለቅ እና ከትውልድ ትውልድ የማውረሱ እንድምታ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የኮንሶ

ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ በ3ቱ የዕድሜ ቅደም ተከተል ላይ የማይናወጥ ፅኑ መሠረትን ይጥላል፡፡

## 6.3 በባህላዊ የፍትህ አፈፃፀም ወቅት የሚታዩ ልዩ ልዩ ስነ-ስርዓቶች

እንደማንኛውም ብሔረሰብ ሁሉ በኮንሶ ብሔረሰብ ዘንድ የሰው ደም ማፍሰስ አሊያም ነፍስ ማጥፋት ከባድ ወንጀል መሆኑ ከመረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ‹‹በብሔረሰቡ ዘንድ የሰው ልጅ የተሰራውም ሆነ የተፈጠረው ከተከበረው ደም ነው›› የሚል እምነት አለ፡፡ ስለዚህም ደም የሚለው ቃል በከንቱ መጠራት የለበትም የሚል ብቻ ሳይሆን በደም ማፍሰስና በህይወት ማጥፋት የሚከሰቱ ግጭቶች በቀላሉ የማይፈቱና ውስብስብ የፍትህ ስርዓት ሂደቶችንና ማህበራዊና እምነታዊ ስነ-ስርዓቶችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ወንጀለኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ደግሞ ለዓመት ያህል ከሚኖርበት ቀዬ እንዲሰደድ፣ ከዘመድ አዝማድ እንዲገለል ይደረጋል፡፡ ደም አፍሳሹ ከቀዬው እንዲሰደድ፤ ከዘመድ አዝማድ እንዲገለል ብሎም ከጎሳው አባላት እንዲነጠል ሲወሰን የመንደሩ ዳውራዎች /መንፈሳዊ አባቶች/ የሰው ደም የፈሰሰበትን ቦታ በማህበረሰቡ ተባባሪነት የቀረበን በግ ወይም ፍየል አርደው ደሙን በመርጨት አካባቢውን ከግፍና ከበደል የሚያነፁበት ማህበራዊና እምነታዊ ስነ-ስርዓት እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

በዚህ ስነ-ስርዓት ውስጥ ወንጀሉ በተፈፀመበት አካባቢና ቦታ ደም መርጨቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ከእምነት ጋር የተቆራኘ ቂምን የመሻር፣ እርቅን የማውረድ እና ተበዳይን የማፅናናት እንድምታ አለው፡፡ ትዕምርታዊ ግንዛቤውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህንንም መረጃ አቀባዩቹ ሲያስረዱ በቦታው ደም በመፍሰሱ አካባቢው ረክሷል፡፡ ይህ የረከሰ ቦታም የእንስሳት ደም በማፍሰስና በመርጨት ማንፃት ይቻላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ይህ ስርዓት ካልተከናወነ በደል ወይም ነፍስ በማጥፋት ግፍ በመፈፀሙና በዚህ ምክንያት ብቻ ፈጣሪ ስለሚከፋ በአካባቢው ዝናብ ይጠፋል፤ ወረርሽኝ ይገባል፤ እግዚአብሔርም ይቀጣናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህም ይህ ሁሉ ከመከሰቱ በፊት የዕርድ ስነ-ስርዓቱ ተከናውኖ የደም መርጨቱና አካባቢውን በግፍ ከረከሰበት ሁኔታ ማፅዳቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ተብሎ ግንዛቤ ስለሚወሰድ ነው፡፡ ደሙ በዚህ መልክ ሲረጭ፤ ስጋውን በተመለከተ የተወሰነውን ከየብልቱ በመቆራረጥ በአካባቢው ዙሪያ-ገብ ተበትኖ ይጣላል፡፡ የቀረው ሥጋ ተጠብሶ ህብረተሰቡ በጋራ እንዲቃመስ ይደረጋል፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው በዙሪያው ያለ

መንፈስም ከስርዓቱ ይቋደሳል ተብሎ ስለሚታመንበት ነው፡፡ ይህ ሁኔታም የራሱ የሆነ ትዕምርታዊ ፍች አለው፡፡

በተመሳሳይ ደግሞ ዕርቅ ወርዶና ሽምግልናው ተሳክቶ የሰው ደም ያፈሰሰውና ነፍስ ያጠፋው ግለሰብ የአንድ ዓመት የስደት ጊዜውን ጨርሶ ወደ ቀድሞ ቀዬው በሚመለስበት ወቅት ትልቅ ስነ ስርዓት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ ከሳምንት በፊት ለአካባቢው ማህበረሰብ ጥሩንባ እየተነፋ በዳዩ እንደሚመጣ በልፈፋ ይነገራል፡፡ ለዚህ ተብሎም ባህላዊ መጠጥ ወይም “ጨቃ” ይዘጋጃል፡፡ የፓሌታው ኼላ በወጣቶች መሰባሰብ ይሞላል፡፡ በፓሌታው መግቢያ በር ላይም እሳት በማንደድም በዳዩ እሳቱን /ረመጡን/ ረግጦ እንዲገባ ያደርጉታል፡፡ የወጣት ትውልድ አባላትም ጋሻና ጦር ይዘው ይጠብቁታል፡፡ የነዚህ ክስተቶች ትዕምርታዊ ግንዛቤውና ትውፊታዊ እምነቱ የራሱ የሆነ ማህበራዊ እንድምታ አለው፡፡ ይኸውም እሳት ወይም ረመጥ ረግጦ የመግባቱ ተምሳሌትነት እና ትውፊታዊ እምነቱ በነፍስ አጥፊው ላይ ያደረው እርኩስ መንፈሰ የሚወጣበት አካሄድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በዳዩ ከቀዬው ሲሄድ እና ሲሰደድ አብሮት የነበረው እርኩስ መንፈስ ሁሉ ተራግፎ እና ከእርኩስ መንፈሱ ተላቆ ወደ ህብረተሰቡ የሚቀላቀልበት ሽግግር በዚህ ዓይነት ስነ-ስርዓት ሊፈፀም ይችላል ተብሎ ግንዛቤ ስለሚወሰድ ነው፡፡ ወጣት የሆነው ትውልድ ጋሻና ጦር ይዞ እዲቀበለው የሚደረገው ደግሞ ለበዳዩ የጥፋትህን ጊዜ በአግባቡ ጨርሰህ ወደ መንደርህ መጥተሃል ዳግመኛ እንዲህ ዓይነት ግጭት ውስጥ እንዳትገባ የሚል ትዕምርታዊ ግንዛቤ ለመስጠት ነው፡፡

በዚሁ ስነ-ስርዓት ወቅት ሽማግሌዎቹ ማሽላ በጥርሳቸው ይፈነክቱና አኝከው ይተፋሉ፡፡ በተጨማሪም “ጨቃ” የተሰኘውን የብሔረሰቡን ባህላዊ መጠጥ ቀምሰው እንትፍትፍ ይላሉ፡፡ ይህ እህሉንም ሆነ መጠጡን ቀምሶና እንትፍትፍ ማለቱ የሚታይበት እንደምታው፣ ግንዛቤውና ተምሳሌትነቱ ዕርቅ የሚፀናበት መንገድ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲከናወን በዕርቁ ላይ ከኛ ጋር የሆነ እና እኛ የማናየው የታላላቅ አባቶች የሙት መንፈስ አብሮን ሰለሚገኝ ይህን ስነ-ስርዓት ስናከናውን እሱም ተቋዳሽ በመሆኑ ይኸው የአባቶች የሙት መንፈስም ሳይቀር ይቅርታን ያወርዳል ተብሎ ይታመናል፡፡ የአባቶች የሙት መንፈስ እና አምላክ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ትውፊታዊ እምነት ውስጥ ከፍተኛ ክብር ያለው ጉዳይ ነው፡፡

ይህን ማህበራዊና ትውፊታዊ የእምነት ስነ-ስርዓት በሌላ መልኩ ስናየው ደግሞ የተተፋ ምራቅ ተመልሶ እንደማይላስና የታኘከንም ነገር መልሶ ወደነበረበት መመለስ እንደማይቻል ሁሉ በአባቶች የወረደውም ዕርቀ-ሰላም ወደ ኋላ የማይመለስና በዚህ መልኩ የፀና እንደሚሆን ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛው ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀልም በዋናው "ሞራ" ውስጥ "ኾራ" የተባለው ባህላዊ ጨዋታና ውዝዋዜ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ በጋራ የሚዘፈነው የዘፈን ስነ-ስርዓቱም የሚፈፀመው ማለዳ ላይ ነው፡፡ የዚህ እንድምታና ግንዛቤ በሰላም ከቤተሰቡና ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀሉን ማለዳ ላይ ሁሉም ከቤቱ ሳይወጣ ማብሰር ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር አንድ ወንጀለኛ ከወንጀሉ እንዲማር ቅጣት ያለውን ፋይዳ በአስተማሪነት መንገድ እንዲገለፅ በማስፈለጉ ነው፡፡ የስነ-ስርዓቱ ባህላዊው አሰራር ሰላምን መልሶ በዘላቂነት ለማስፈን ጠንካራ ማህበራዊ መሠረት እንዳለው ያሳየናል፡፡ ያለውም ፋይዳ አንድ ሰው በሚኖርበት ቀዬ ሰላማዊ ህይወት ለመኖርና ለአከባቢው ህግ ተገዢ መሆን እንዳለበት ያስረዳል፡፡ ማህበራዊ ቅጣቱም የሚፈጥረው ተፅዕኖ ማህበራዊ ደንቦችንና ህግጋትን ለማክበር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ነዋሪውም በባህላዊው ህጉ ላይ ያለው ጠንካራ አመኔታ ከሚከናወኑት ስነ-ስርዓቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ምንም እንኳን በጽሁፍ በሰፈረ ህግና ደንብ የተመሠረተ ባይሆንም የባህላዊ ህጉ ተፈጻሚነትና ህጉ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠው ቦታ ከፍተኛ እንደሆነ እስካሁን ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በኮንሶ ብሔረሰብ ውስጥ ሌላው የግጭት መንስዔ ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሴቶችን ማማገጥ ብዙም የተለመደ እንዳልሆነ በመስክ ቆይታ በነበረው የቃለ-መጠይቅ ወቅት ከመረጃ አቀባዮች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክት ያስረዳል፡፡ በብሔረሰቡ ሴቶችን በማባለግ የተጠረጠረና የተረጋገጠበት ሰው የሞራል ካሳ ወይም በብሔረሰቡ አጠራር "ማሳ" እንደሚከፍልና አግብቶ እንደሚወስድ የተደነገገ ነገር አለ፡፡ ካሳ እንዲከፍል ሲጠየቅም የጎሳ አባል ጨመረ በሚል የጎሳው አባላት ወጪውን እንደሚጋሩትም ተጠቁሟል፡፡

ባል ምንም እንኳ ሚስቱ ብታጠፋም ከወደዳትና ሚስቴን እፈልጋለሁ ካለ በቀደመ ባሏ አማካኝነት በፖቃላ ሙግላ ቤት ቀርባ ላጋንዳ (ቅጠል) እና የደረቀ ዳሃንታ (ድፍን ቅል) ቀርቦ ቅሉን በመሰንጠቅ እንደከብት(በግ) በማረድ ከውስጥ ያለውን ፍሬ ማለዳ ከተቀዳ የምንጭ ውኃ ጋር በብሔረሰቡ አጠራር "ቁርበታ" ይደባለቅና ይረጭባታል ይላሉ፡፡ ይህ

ስርዓት መፈፀሙ ተምሳሌትነት (ትዕምርታዊ ፍች) ያለው ሲሆን ይህም እንደንስሀ መንፃትን ያመለክታል ይላሉ፡፡

ይህ ስርዓት ከተደረገ በኋላ "ፖቃቃ" የሚባል የቃል ኪዳን ስርዓት ያለ ሲሆን ይህ ስርዓት ባል ሚስቱን እንደማይበቀል፣ ሚስትም በባሏ ላይ ከእንግዲህ ክፉ እንደማትሰራ ቃል ማስገቢያ ስነ-ስርዓት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የስርዓቱ አፈፃፀም ቅዱስ ውኃውን ወይም "ቁርበታ"ውን 3 ጊዜ እየቀመሱ መትፋት ሲሆን የ3 ቁጥር ተምሳሌትነት (ትዕምርታዊ ፍች) ትውፊታዊ እምነት ከትዳር ህይወት /ከ3 ጉልቻ/ ጋር እንደሚያያዝ በጽኑ ይታመናል፡፡ እንዲሁም ማር፣ ጤፍና ጨቃ አንድ ላይ ቀላቅሎ 3 ጊዜ መዋጥ ሌላው የሚስተዋል ስነ-ስርዓት ነው፡፡ ይህም እህል ውኃችሁ ይስመር፤ የተረጋጋ ትዳር ይሁንላችሁ የሚል የቃልኪዳን መልዕክት አለው፡፡

ከዚህ ማህበራዊና ትውፊታዊ የእምነት ስነ-ስርዓት የምንረዳው ነገር ቢኖር የ3 ቁጥር ሁኔታ ተደጋግሞ መምጣቱና ያለው ተምሳሌታዊ (ትዕምርታዊ ፍች) ጥልቀት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም 3 ቁጥር በተለያየ መልኩ ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ከ3 ጉልቻ እና ከትዳር ህይወት ጋር ተቆራኝቶ መገኘቱ ነው፡፡ ስለዚህም ለ3 ጉልቻ ፅኑ መሠረት ለመጣል የ3ት ጊዜ የስነ-ስርዓት ድግግሞሽ በባህላዊ እና ትውፊታዊ እምነትነቱ ውስጥ ጠንካራ መሰረት እንዳለው ያሳየናል፡፡

በኮንሶ ሁለት የዝናብ ወቅቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ በእነዚህ የዝናብ ወቅቶች የመሬት (ድንበር) ጉዳይ እንደማይታይ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ውስጥ በአግባቡ ተገልፆአል፡፡ ነገር ግን በዚህም ወቅት ቢሆን ድንበር የገፋው ሰው በሽማግሌዎች የተሰጠውን ውሳኔ መቀበል የግድ ይለዋል፡፡ ውሳኔውን የማይቀበል ከሆነ በቦታው ተኼዶ መሬቱን በመምታት ወይም አፈሩን በመበተን በዳዩ ውሳኔውን እንዲቀበል ይገደዳል፡፡ በዚህ ሁኔታ መሬት መምታትም ሆነ አፈር መበተን የራሱ የሆነ ትውፊታዊ የእምነት እንድምታ አለው፡፡ ትውፊታዊ እምነትነቱም መሬትን /ድንበርን/ ከገፋሁ እንዲህ እንደ አፈሩ ብን ያድርገኝ፣ እንደ መሬቱ በድን ያድርገኝ እንደማለት መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ በሌላ መልኩ ስንመለከተው መሀላው በቦታው መሬቱን የመምታት ከሆነ እንደ መሬቱ በድን ልሁን እንደማለት ነው፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ ውስጥ ማንኛውም መተማመን ያልተቻለበት ጉዳይ የመጨረሻውን መፍትሄ የሚያገኘው በመሀላ ስነ-ስርዓት ነው፡፡

ሌላው በብሔረሰቡ ውስጥ ቤት ማቃጠል ከባድ ወንጀል መሆኑን አይተናል፡፡ እንደመረጃ አቀባዮቹ ገለፃም ከሆነ ቤቱን፤ ወይንም የራሱንም ሆነ የሌላ ሰው ቤትን አቃጥላለሁ ብሎ መዛት በራሱ ወንጀል እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ከዚህ አንፃር በብሔረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ቤት ሲያቃጥል ከታየና ከተጠረጠረ የእድሜ ልክ ቅጣት በብሔረሰቡ አጠራር "ቂታሳ" የሚባለው ውሳኔ ይወሰንበታል፡፡ የሚወሰንበትም ውሳኔ የቤተሰቡን ጉልቻ በማጋጨት የመኖሪያውን ቤት ክዳን (የሳር ቤቶቹን ጣሪያ) በአፉ በመድፋት መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ያብራራሉ፡፡ ይህ ትዕምርታዊ ስኑ-ስርዓት የራሱ የሆነ ትውፊታዊ እምነትና እንድምታ አለው፡፡ ይኸውም ጉልቻ በመጋጨቱ ህይወት በቦታው አይቀጥልም የሚል መልዕክት ይሰጣል፡፡ ሰው በበዳዩ ቤት እዳይኖርበትም እርግማን ይሆናል፡፡ ወንጀለኛው ከነቤተሰቡ ከቀዬው ለቆ የሚሰደድበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ለዚህ ደግሞ ማህበረሰቡ ትልቁን ሚና እንደሚጫወት ይታወቃል፡፡

የጉልቻ መጋጨት የሦስት ጉልቻን መዘባት፣ የትዳር መናጋትን፣ የቤተሰብን መበተን ይገልፃል፡፡ ይህ ሁኔታ በሌላ መልኩም ሲታይ ጉልቻ ማጋጨት የትዳር ህይወትን ቀጣይነት አጠራጣሪ ሁኔታ ውስጥ የሚከተው ያደርገዋል፡፡ የሳር ቤቱን በአፉ መድፋትም በቤተሰቡ ህይወት ውስጥ ኑሮ እስከወድያኛው እንዲጨልም የሚያደርግ ክፉ እርግማን እንደሆነ ይታመናል፡፡ ወንጀለኛውም ከቀዬው ከነቤተሰቡ ሲወጣ የአከባቢው ማህበረሰብ ከኋላው በመከተል በቅንጭብ መሬቱን በመምታት ይረግሙታል ይህም የከፋ ዕርግማን እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡

በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ዕርቅ ሲወርድ ምርቃት እንዳለ ሁሉ ጥፋት ሲፈፀምም ደግሞ እርግማንም መኖሩ ይታወቃል፡፡ ይህ ሁኔታ በሁሉም በኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚታይ እምነት ነው ፡፡ የነበረና የሚቀጥል (የማይጠፋ) እንደሆነም ከዕለት ተዕለት ቤተሰባዊና ማህበራዊ ህይወታችን መረዳት እንችላለን፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በተጨማሪም በብሔረሰቡ ውስጥ ዕርድ የሚከናወንባቸው ጉዳዮች ብዙ ዓይነት ናቸው፡፡ ይኸውም ጦርነት ሲከሰት፣ ደም ማፍሰስ ከሆነና ነፍስ ግድያ ሲፈፀሙ ዕርቅ ለማውረድ የሚሉት ትልቁን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ጉዳዩ ነፍስ ግድያ ከሆነ ለዕርድ የምትቀርበዋ እንስሳ “ወልዳ ያበቃች በግ ወይም ፍየል” ናት፡፡

ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ወልዳ ያበቃች እንስሳ የተለያየ የመከራና የችግር ጊዜን ያሳለፈች መሆኗን ለማመልከት ነው፡፡ የስርዓቱ አፈፃፀም በግ ወይም ፍየል ከታረደች በኋላ በፈርሱና በቅዱስ ውኃ ጠበኞች እንዲታጠቡ ይደረጋል፡፡ በፈርስና በቅዱስ ውኃ መታጠባቸው ደግሞ ከደሙ ንፁህ መሆንንና፣ መንፃትን ያመለክታል፡፡ እርዱ የሚከናወነው በሚች ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ የሚች ግቢ የሚመረጥበት ዋና ምክንያት ቤተሰቡ ጉዳት የደረሰባቸው ስለሆነ ነው፡፡ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ስነ-ስርዓቱን ለመፈጸም መሞከር ግን የበለጠ ከጉዳዩ መራቅንና ዕርቁን እስከወዲያኛው እንደአለማውረድ ይቆጠራል፡፡

በዚህ የዕርድ ስርዓት ወቅት ዋነኛ ተሳታፊ የሚሆኑት ገላጋይ የተባሉና በብሔረሰቡ የመጀመሪያ ትውልድ ተብለው የሚወሰዱት ዳውራዎች /መንፈሳዊ አባቶች/ ናቸው፡፡ እነዚህ መንፈሳዊ አባቶች በዚህ ስነ-ስርዓት ላይ ወሳኝ አካል ናቸው፡፡ ዕርዱን በተመለከተ የሚያከናውኑት በዕድሜ ገፋ ያሉ ሽማግሌዎች ሲሆኑ፣ በስነ-ስርዓቱ የሚሳተፉት ወጣቶችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብቻ አቅም ያለውና የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ግን ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎች በስነ-ስርዓቱ ምርቃታቸው ስለሚያስፈልግ ሽማግሌዎች እንዲያርዱ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ሽማግሌዎች የሚመረጡት በዕድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ስለሆኑና ሁሉንም መፈጸምና ማድረግ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ዕርዱም ጠዋት ማለዳ ላይ ይከናወናል፡፡ ማለዳ መመረጡ ደግሞ ማለዳ መልካምና የአዲስ ቀን መጀመርያ በመሆኑ ምንም አይነት እህልና መጠጥ ሳይቀመስ የሚፈጸም ሰለሚሆን ነው፡፡

ግጭቱ የጦርነት መልክ ካለውና ብዙ የህብረተሰብ አባላትን የሚያካትት ከሆነ የዕርድ ስነ-ስርዓቱ የሚፈፀመው በአብዛኛው ከወንዝ ዳርቻ ነው፡፡ የሀንሳቢታ ቅጠልም ከዕርዱ ስር እንዲጎዘጎዝ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነው የወንዝን ቅዱስነትና የቅጠሉን እርጥብነት ለማመልከት ነው፡፡ ከቅጠሉ በተጨማሪ የሚፈለገው ደግሞ በፈርሱና ቅዱስ ውኃው ተነክሮ አካባቢው የሚረጭበት ሁኔታ መከናወን ስላለበት ነው፡፡

ይኸውም ወንዙ ከተለያየ አካባቢ አፈር ይዞ ይጓዛል፡፡ ከተለያየ አካባቢ ይዞ የሚመጣውም መጥፎና ጥሩ ነገር አለው፡፡ ስለዚህም በዚያ ሁሉ ጠበኞችን አጥበናል፤ አካባቢውን ረጭተናል ሁሉንም ከክፉ አድራጎታቸውም አፅድተናቸዋል ለማለት ነው፡፡ ሌላው በዚሁ ስነ-ስርዓት የሀንሳቢታ ቅጠል በጣም አስፈላጊነቱ የሚገለፀው ፈርሱና ቅዱስ ውኃው ተደባልቆ ዋና ጠበኞች የሚታጠቡበት በመሆኑ ነው፡፡ የተረፈው ደግሞ ወደ ዋና ተበዳዮች

ግቢ በመውሰድ ይረጫል። ይህ የሚሆነው ለተበዳዮች መጽናናትን ለማጎናጸፍ መፍትሔ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

በዚህ የዕርድ ስነ-ስርዓት ወቅት የፍየሏ ወይም የበጓ ደም ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበር ተደርጐ ይሸፈናል። ይህ የመደረጉ ትውፊታዊ እምነትም ቁጣን ለማብረድ፣ መቅሰፍትን ለመከላከል እና ወረርሽኝን ለመግታት ተብሎ ስለሚታመን ነው። ስለዚህም ቀሪው ደምና ፈርስ በጉድጓድ ውስጥ ተቀብሮ ቦታው ሙሉ በሙሉ ይሸፈናል፡፡ ሌላው ጉዳይ ደግሞ በዕርድ ሰነ-ስርዓት ወቅት የሚችና የገዳይ ቤተሰብ፣ የቅርብ ቤተ ዘመዶችና አስታራቂዎች ይገኛሉ። ይህም መሆኑ የሚች ወገን ቅሬታውን እንዲያነሳ፣ የገዳይ ወገንም ጥርጣሬ እንዳይኖረውና ይቅርታውን አስተማማኝ ለማድረግ ተብሎ ስለሚታመን ነው። በዕርድ ወቅት ከብቱን በመያዝ የሚሳተፉት አቅም ያላቸው ገለልተኛ የሆኑ ወጣቶች ናቸው።

በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀው ስነ-ስርዓት ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመ “መልካሙ ሁሉ ይምጣ” በሚል ስነ-ስርዓቱ በሽማግሌዎች ምርቃት እንዲጠናቀቅ ይደረጋል። የዚህ ሁሉ ጥረት ውጤቱ ፍትሀዊ ዳኝነትን ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ግጭቶቹ ከመፈጠራቸው በፊት ሁኔታዎች ወደ ነበሩበት ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲመለሱ ለማድረግ ጭምርም ነው። ይህ አሰራር ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱን ከመደበኛ የፍትህ ስርዓቱ አሰራር የተለየ ያደርገዋል፡፡ በአብዛኛውም በህብረተሰቡ ዘንድ በጣም ተመራጭም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

# ምዕራፍ 7. ማጠቃለያና ይሁንታዎች

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያና የብሔረሰቡ ዋና የፍትህ ተቋም የሆነው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ (ዴኻው) የተጋረጡበት ስጋቶች ተወግደው ዘላቂነቱ እንዲረጋገጥ በይሁንታ መልክ የተዘረዘሩ ነጥቦች ይቀርቡበታል፡፡

## 7.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ የኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና የስርዓቱን ፋይዳ ማሳወቅ፣ እንዲሁም የግጭት መፍቻ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን የጐላ ሚና፣ ግጭቶች የሚፈቱበት ሂደትና የሽምግልና ስርዓቱ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ስላለው ግንኙነት፣ በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ ፎክሎርና ሚናቸውን እንዲሁም በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ልዩ ልዩ ትዕምርቶች ያላቸው ፋይዳና በአጠቃላይ የግጭት አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል መተንተንና መግለጽ ነው፡፡

በኮንሶ ብሔረሰብ ግጭት በጥቅሉ "ኦል ዳቤታ ዲኣና" ተብሎ ይጠራል፡፡ ጥል፣ አለመስማማት፣ በሀሳብ አንድ አለመሆን የሚለውን የሚይዝ ሲሆን፣ በዋናነት የሚጠቀሱ 6 (ስድስት) የግጭት ዓይነቶች ሲኖሩ እነዚህ ግጭቶች ቀላልና ከባድ በሚል ተመድበዋል፡፡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (ዴኻ) የተመሰረተው በብሔረሰቡ አጠራር "ካላታ" አብሮ በመኖር፣ በመረዳዳትና በመተጋገዝ፣ ወንጀለኛን በማጋለጥና በአካባቢው ሰላምና ፀጥታ በማረጋገጥ ላይ ሲሆን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የኮንሶ ብሔረሰብ የተለያዩ ግጭቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ሲከሰት ግጭቶቹን የሚፈታበት ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት አለው፡፡ ይህ ስርዓት በአካባቢው ቋንቋ ''ዴኻ-አራራ'' የሚባል ስያሜ ሲኖረው ይህም የዕርቅ ድርድር ስርዓት የሚለውን ይወክላል፡፡ ግጭቶቹ በየደረጃው ባሉና የየራሳቸው አወቃቀር ባላቸው ሶስት ባህላዊ የዳኝነት ችሎቶች ወይም የግጭት መፍቻ ተቋማት (በፓሌታዊ አደረጃጀት፣ ሞራ-ከንታና ሞራ-ፓሌታ፣ በጐሳዊ አደረጃጀት ፖቅላ) የሚፈቱበት ስርዓት እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ከዚህም ሌላ በግጭት መፍቻ ተቋማቱ የተለያዩ አስታራቂዎች እንደሚሳተፉ እና የአስታራቂዎችም ሚናና የመምረጫ መስፈርቱ እንደሚለያይ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከዚሁ ጋር ግጭቶች በነዚህ ደረጃ በተቀመጡ

ባህላዊ የዳኝነት ችሎቶች ከመታየታቸው በፊት ቀላል ጉዳዮች በአካባቢ ሽማግሌዎች አማላጅነትና በቅርብ ጓደኞች እልባት አግኝተው ጠበኞች ወደቀደመ ሰላማቸው እንደሚመለሱ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ከ3 (ሶስቱ) ባህላዊ የዳኝነት ችሎቶች ያለፉ ጉዳዮች ደግሞ የመጨረሻው ስርዓት በሆነው "ካካ" ወይም የመሀላ ስርዓት እንደሚቋጩና ለመሀላ የሚዳርጉ ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶች የእርሻ መሬት ክርክር፣ የድንበር፣ የንብረት መካካድና ስውር ደባዎች ሲፈጸሙና መረጃ የማይገኙላቸው የተለያዩ ጉዳዮች ሲከሰቱ እንደሆነ በአጠቃላይ በየደረጃው ባሉ ስርዓቶች ሽማግሌዎች ጠበኞችን በማስታረቅ ሂደት ደረቅ እህል(ማሽላ) አኝከው በሚተፉት፣ ጠበኞችም ከዕርቅ በኂላ አንድ ስለመሆናቸው በአንድ ቅል በሚጠጡት ባህላዊ መጠጥ(ጨቃ) እንዲሁም እንደወንጀሉ ክብደት ከሚፈጽሙት ዕርድ በኂላ አካባቢውን በደም፣ በፈርስና በቅዱስ ውኃ በመርጨትና በመታጠብ በሚያከናውኑት የማንጻት ስራ ዕርቃቸውን እንደሚያጸኑ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በብሔረሰቡ ቀላል ግጭቶች ከማህበራዊ ጉዳዮችና ከዕለት ተዕለት መስተጋብሮቻቸው ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ የግለሰብ፣ የቤተሰብና የጎረቤት በሚል የሚፈረጁ የግጭት ዓይነቶች መሆናቸው የተጠቆመ ሲሆን፣ እነዚህ ግጭቶች በመጀመሪያው ችሎት በቀናት እጅግ ቢበዛ በሳምንት ዕድሜ ውስጥ በሞራ-ከንታ ደረጃ በሚቀመጡ አካላት ማለትም በፖርሺታ፣ አፓ-ከንታ፣ ቂሞታ-ከንታና ኸሊታ-ከንታ አማካኝነት እልባት ያገኛሉ፡፡ በዚህ ደረጃ መፈታት ያልቻሉ ጉዳዮች ቀላል ግጭቶች በሚል ወደሞራ-ፓሌታ ተላልፈው እልባት የሚያገኙ መሆናቸው በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል የቡድን ግጭት፣ ከሀብት ንብረት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ወንጀል ነክ ተግባራት በከባድ ግጭትነት ተፈርጀው በሞራ-ፓሌታና በፖቅላ ደረጃ መፍትሄ የሚያገኙ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ በሁለተኛው በሞራ-ፓሌታ ደረጃ፡ ቂሞታ-ፓሌታ፣ ኸሊታ-ፓሌታ፣ ሰንቀሊታ፣ አፓ-ቲንባ፣ ዳውራ፣ ፖቃላ ሙግላ (ቱራይታ)እና ሳራዎች በዋናነት ጉዳዩን ለማየት የሚቀመጡ ሲሆን፣ በዚህ ደረጃ ከሞራ-ከንታ የተላለፉ ጉዳዮችና በሞራ-ፓሌታ የቀረቡ ከባድ ግጭቶችን እንደስርቆት፣ ድብደባ፣ ቤት ማቃጠል፣ የመሬት ግጭት፣ ሴት ልጅን ማባለግ ወዘተ ተመልክተው እልባት የሚሰጡ መሆናቸው በጥናቱ ተብራርቷል፡፡

በዚህ ደረጃ እልባት ያላገኙ ጉዳዮች ወደፖቅላ (የጎሳ መሪው) ተላልፈው ያለድርድር የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል። በፖቅላ ደረጃ እንዲታዩ የሚቀርቡት ወንጀል ነክ የሆኑ ተግባራት እንደአካል ማጉደል፣ ድንገተኛ ነፍስ ማጥፋትና ተደጋጋሚ ስርቆት መፈጸም እንደሆኑና በዚህ ደረጃ አፓ-ካፋ፣ ቂሞታ-ካፋ፣ ፖቃላ ሙግላ (ቱራይታ)ና ፖቅላ ቱማው (የጎሳ መሪው) በየደረጃውና በጋራ በማየት ውሳኔ የሚሰጡ መሆናቸው ተገልጿል። በሞራ-ከንታና በሞራ-ፓሌታ ደረጃ ለሚታዩ ቀላል ግጭቶች እንደየደረጃው የኾራታ (የክስ መመስረቻ) ገንዘብ እንደሚያዝ፣ የኾራታ ገንዘቡም ሆነ የቅጣት ደረጃው እንደጉዳዩ ክብደትና ቅለት እንዲሁም እንደ ዳኝነት ሞራው የተለያየ እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል። በተጨማሪም በዚህ ደረጃ ጉዳዩ በድርድርና በምስክር ተጣርቶ ውሳኔ እንደሚሰጥ ጥናቱ ይጠቁማል።

በኮንሶ ብሔረሰብ ለግጭት መንስኤ ሆነው በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች በዋናነት ከመሬትና ውኃ አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ አልፎ አልፎ ደግሞ ከስልጣን መሻትና ሴት ልጅን ከመድፈር ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ መሆናቸው ተነስቷል።

ከዚህ ሌላ ሕብረተሰቡ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ሲገናኝ በንግግርና በጨዋታ መሀል ከሁኔታዎችና ከሚነገረው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ሀሳብን በምሳሌ አጉልቶና አስረግጦ ለማስተላለፍ ምሳሌያዊ ንግግሮችን እንደሚጠቀም፣ በተለይ በሽምግልና ወቅት የጠቡን አላስፈላጊነት ለማስረዳትና አጥፊን ለመውቀስ ወይም የዕርቅን ስርዓት አቅጣጫ ለማስያዝ ሽማግሌዎች በንግግራቸው ጣልቃ ምሳሌያዊ ንግግሮችን (በኮንስኛ አነጋገር ‹ዶይ› በመባል ይታወቃል) የሚጠቀሙበት ሁኔታ እንዳለና ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በባህላዊው የግጭት አፈታት ቅድመ- ስርዓት፣ በስርዓቱ ጊዜና በድህረ- ስርዓቱ ወቅት አገልግሎት ላይ በመዋል ለስርዓቱ ዕውን መሆን ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወቱ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የኮንሶ ብሔረሰብ አባላት ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ይልቅ በባህላዊ ስርዓቱ መዳኘትን የሚመርጡ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። ለዚህ ደግሞ እንደመሰረታዊ ምክንያት የተጠቀሰው ባህላዊ ስርዓቱ ዲሞክራሲያዊና ፍትሀዊ መሆኑ፣ ምስክሮች በባህላዊ ስርዓት መሀላ ስለሚፈጽሙና ትክክለኛ የምስክርነት ቃል ስለሚሰጡ፣ የዕርቅም ሆነ የዳኝነት ስርዓቱ ብዙ የስራ ጊዜ የማይሻማ መሆኑ፣ የዕርቅም ሆነ የዳኝነት ስፍራው ከመኖሪያ ስፍራው አለመራቁ፣ በቋንቋው መዳኘቱ፣ ስርዓቱ በዕርቅ መደምደሙ፣ ውሳኔ

የሚሰጥባቸው ቦታዎችም በባህላዊ እምነት ተፅዕኖ ስላላቸው ፍርዶች ሁሉ በአብዛኛው ትክክለኛ ናቸው ተብሎ ስለሚታመንና የመሳሰሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ያም ሆኖ መደበኛው የፍትህ ተቋም አሠራሩን ተቀብሎ በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ ከባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ጋር በቅንጅት የሚሠራበት ሂደት መኖሩን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በኮንሶ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (ዴኻው) የብሔረሰቡ ዋና የፍትህ ተቋም እንደሆነና ስርዓቱም ህያው ሆኖ ዛሬም እያገለገለ እንደሚገኝ፣ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር በመሰረታዊነት በሚያምኑባቸው ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ችግሮችን እየፈቱ የሚሰሩበት ቅንጅታዊ አሰራር እንዳለና ይህንን በማጠናከር የአካባቢውን ሰላም ይበልጥ በማረጋገጥ ረገድ አሁን ካለው በተሻለ መሰራት እንዳለበት ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም በብሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ለማህበረሰቡ እርስ በርስ ተከባብሮ መኖርም ሆነ ሰላማዊ ህይወት ዋስትና ነው ማለት እንደሚቻል ጥናቱ ያመለክታል፡፡

## 7.2. ይሁንታዎች

- ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ የተፃፈ ህግ ባለመሆኑ የቅጣት ውሳኔው ወጥ አይደለም፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ለዘፈቀዳዊ አሰራር በር ከፍቷል፡፡ ይህ ደግሞ በሂደት የስርዓቱን ዘላቂነት ስለሚፈታተን የሚመለከታቸው አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ወጥ አሰራር ቢዘረጋ፣
- ወንጀልን ሙሉ በሙሉ ለመከላከል እና ለመቀነስ ባህላዊውና መደበኛው የፍትህ ስርዓት በመረጃ አቅርቦት ረገድ በጋራ የሚሰሩበት አሰራር ቢፈጠር ለዚህም ፖሊሲ አውጪዎችና የፍትህ አካላት የባህል መዋቅሩን አሰራር ቢፈትሹና አመቺ የሆኑ የአሰራር ስልቶችን በመደበኛው ፍትህ ስርዓት ማካተት የሚቻልበት ሁኔታ ቢቀየስ፣
- በአጥፊዎች (ወንጀለኞች) ላይ የሚጣለው ማዕቀብና ከማህበራዊ አገልግሎት መገለል እንደጥፋቱ ሁኔታ (ቅለትና ክብደት) ቢወሰን፣ ይህ መሆኑ ደግሞ ልጆችንም ከጎዳና ቤተሰብንም ከመበተን ያድናልና ትኩረት ቢሰጠው፣
- በብሔረሰቡ በየ 18 ዓመቱ የወጣት ትውልድ ቡድን ስልጣን (የኼላ) ሽግግር ስነ-ስርዓት መኖሩ የባህሉን ተረካቢ ወጣት ከአልባሌ ተግባር ከመያዝ አልፎ ከመሰረቱ

ኃላፊነትን የሚሸከም ትውልድ ለመፍጠር አረአያነት ያለው ተግባር ነውና ስርዓቱ ተጠናክሮ ቢቀጥል፣

- በብሔረሰቡ የባህላዊው የፍትህ ስርዓቱን የሚፈታተኑ አንዳንድ ለውጦች መከሰታቸው ለአብነት ለባህል ህጉ አለመታዘዝ፣ የባህል ስርዓቱን ቀጣይነት የሚፈታተኑ አንዳንድ በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ሓይሎችን በመታገል ያለ ቸልተኝነት ከዘላቂነቱ አኳያ ስጋት በመሆናቸው እነዚህን በመከላከል ረገድ የሚመለከታቸው ሁሉ ለባህል ህጉ መቀጠል ቢሰሩ፣
- በሽማግሌዎች የዳኝነት ስርዓት ወቅት የሽማግሌዎችን የጥቅማ ጥቅም ፈላጊነት ስሜት ለመቆጣጠር ብሎም በእንጭጩ ለማስቀረት በሽማግልና ላይ ለሚቀመጡ ሰዎች የተወሰነ ለእህል ውኃም ቢሆን የሚታሰብላቸው ነገር ቢፈጠር፣ ለዚህ ደግሞ ማህበረሰቡ ቀዳሚው ሲሆን፣ የሚመለከታቸው የባህል መሪዎችም ሆነ የፍትህ አካላት ማየት ቢችሉ፣
- በባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ላይ ሴቶች ቀጥተኛ ተሳትፎ እንደሌላቸው ይታወቃል፤ ይሁንና ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መልኩ በየቤታቸው ለትዳር አጋሮቻቸው የሚያነሷቸውም ሆነ እንደአስተያየት በአንዳንድ ሕዝባዊ መድረኮች የሚጠቁሟቸው ሀሳቦች በተዘዋዋሪ መንገድ በችሎቱ የሚቀርቡና ተፅዕኖ ፈጣሪ በመሆናቸው በብሔረሰቡ የሴቶች ቀጥተኛ የባህል ችሎት ተሳታፊነት የሚጀመርበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- የባህል መዋቅሩ ከመደበኛ የፍትህ ስርዓቱ ጋር በቅንጅት እየሰራባቸው ያሉ አንዳንድ ጉዳዮች እንዳሉ ይታወቃል። ይህን አሰራር የበለጠ ለማጎልበት ፖሊሲ አውጪዎች የሁለቱንም የፍትህ ተቋማት አሰራር በመፈተሽ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ አሰራሮችን ከባህላዊ መዋቅሩ ወደመደበኛው የፍትህ ስርዓት የሚገቡበትን ሁኔታ ቢያመቻቹና የባህላዊ ስርዓቱ ድክመቶች የሚባሉትን ደግሞ ለማስቀረት ቢሰራ፣
- በመረጃ አቅርቦትና በምስክሮች የተሳታፊነት ሁኔታ ላይ ባህላዊው የፍትህ ስርዓቱ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር በጋራና በቅንጅት ቢሰራ፣
- በአጠቃላይ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓቱ ጋር በመቀራረብና በመተጋገዝ እየሰራ ያለበት ጅምር እንቅስቃሴ የሚበረታቱ ሆኖ በይበልጥ ቅርበቱንና መተጋገዙን በማጠናከር የአከባቢውን ሰላም ይበልጥ በማረጋገጥ ረገድ ብዙ መስራት ቢቻል።

# ጥቅስማ /References/


Abayneh Kassa. "Indigenous Conflict Resolution Mechanisms in Yeki Woreda, Sheka Zone in South-Western Ethiopia". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2013.

Assefa Tolera. "Ethnic Integration and Conflict the Care of Indigenious Oromo and Amhara Settlers in Aaroo Addis Alem, kuramu area, North Western Wallaga". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 1995.

Amborn, H. "History of Events and Internal Development፡The Example of The Burji-Konso Cluster". In Taddesse BeYene ed. Proceedings of the Eight International Conference of Ethiopian Studies. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies: pp 751-61.

Ayantu Habtamu. "Conflict Over Agricultural Land: The Care of Host Community with Government Sponsored Resettlers and Investers in Sassiga Woreda, Eastern Wallaga". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2012.

Bender, M.L. (ed). *Classification and Distribution of Ethiopian Language in Language Survey of Ehtiopia,* Survey Monograph part I, Addis Ababa (mimeographed), 1969.

Black, p. "Cushitic and Omotic Classification from Language Sciences, mimeographed in Ethiopian Language Miscellania 2". 1972.

Boulding, Kenneth E. *Conflict and Defence፡ A General Theory*, New York: Harper and Row. 1962, pp 4-6.

Caplow, Theodorea. "Further Developments of a Theory of Coalitions in the Triad," American Journal of Sociology Vol. 64; 1962, pp 488-493.

Coser, Lewis. *Continuities in the Study of Social Conflict*. New York; the Free Press,1967.

Daniel Abebe. "Kinship, Marriage and Alternative Dlispute Resolution Among the SAB of the Somali". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2005.

Dejene Gemechu. "Some Aspects of Conflict and Conflict Resolution Among Wolliso Oromo of Eastern Mecha, with Particular Emphasis on the Guma". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2002.

Dinku Lemessa. "Socio-Economic Dimensions of Conflict Induced, Displacement: The Care of Displaced Persons in Addis Ababa". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2003.

Douglas. "*Conflict and Aggression*" in David Levinson and Melvin Ember(eds) Encyclopidia of Cultural Anthropology. New York, Henry Holt and Company, Vol. 1, 1996.

Fisher, Simon et al. *Working with Conflict Skills and Stratagies for Action*. London: zed books Ltd, 2000.

Gemeda Akuma. "The Emergin Dynamics of Socio Religious Controversies and Conflicts in Omo Wadda Woreda Jimma Zone, Oromia National Regional State. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2012.

Gowok, S. M. Alternative Dispute Resolution in Ethiopia: *A Legal Framework*. African Research Review, 2(2); 2008, pp 265-285.

Hallpike, C.R. *The Konso of South Western Ethiopia: A study of The Values of Cushtic People.* Oxford, Clarendon Press; 1972.

Jemal Sano. "The Role of Guma in the Conflict Resolution and Peace building Among the Arsi Oromo with Particular Emphasis on Merti District". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2012.

Kalid Abdinasir. “Indigenious Conflict Resolution Mechanisms Among the Ethopian Marehan Somali clan in Filtu Woreda of Liban Zone, Somali National Regional State”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2011.

Kansite Gellebo. “ Moora: A Study of the Public Place and its Multiple Purposes Among the Konso people of Southern Ethiopian”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Dept. of Social Antropology, 2011.

Katz, D. Nationalism and Strategies of International Conflict Resolution. In H.C. Kelman (ed.), *International behavior: A social psychological analysis.* New York: Holt, Rinehart & Winston, 1965, pp. 356-390.

Kelemework Tafere. “Indigenous Institutions of Conflict Resolution Among the Abala Afar of North- Eastern Ethiopia”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2000.

Lakew Regassa. “Settlement and Clanship Among the Konso”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 1998.

Mamitu Yilma. “Some Aspects of the Status of Women Among The Konso of Southwest Ethiopia”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2002.

Melese Teshome. “Inter-Ethnic Conflicts in Ethiopia & the Case of Karrayu Oromo and Argobba Groups”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2012.

Metasebia Bekele. “ Konso: People and Culture”. Association For Researh and Conservation of Culture, Indigenous Knowledge and Cultural Landscapes; in Authority for Researh and Conservation of Cultural Heritage Special Edition, 2012: pp26-27.

Negash Abebe. “Indigenious Mechanism of Homicide Reparation the Case of ‘GUMAA’ Among Tulama Oromo of Kuyuu District, Northen Shewa”. M.A Thesis, Addis Ababa University, Dept of Social Antropology, 2013.

Oberschall, Anthony. *Theories of Social Conflict,* Annual Review of Sociology, Vol. 4,1978, pp.291-315.

Porter, Jack Nusan. *Conflict and Conflict Resolution:* A Sociological Introduction with updated Bibiliography and Theory Section; New York; University press of America, 1987.

Simmel, George. *Conflict and the Web of Group Affiliations.* (Tr.Kurt H. Wolff and Reinhard Bendix), New York: the free press, 1964.

Solomon Eshete. "Konso Traditional Arcitecture and Housing". in Authority for Researh & Conservation of Cultural Heritage Special Edition, 2012: pp 35-38.

Tarekegn Gebreyesus. "Change and Continuity in the Traditional Institutions and Mechanisms of Local-Governance and Conflict Resolution Among the Wejerat: An Ethno-Historical Study". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2005.

Patz, Tom. ''Overview of Handling Conflict and Preventing Violence ''. *A paper presented on workshop on conflict Resolution*, Nazareth, 2002 .

Watson, E.E. "*Ground Truths: Land & Power in Konso, Ethiopia".* Ph.D Thesis, Cambridge University UK, 1998.

Yilma Sunta. "The Role and Status of Women in the Food System of the Konso, Southwest Ethiopia". M.A Thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 2002.

Yohannes Birhanu. "Conflict and Conflict Resolution anomg the People of Chichera (Micro Level Case Studies from Six Kebeles in Northen Gondar)". M.A thesis, Addis Ababa University, Department of Social Antropology, 1998.

Yonas Beyene. "The Konso Cultural Landscape: Ethiopia's 9$^{th}$ World Heritage Site". in Authority for Researh and Conservation of Cultural Heritage Special Edition, 2012: pp 21-25.

ሀፍታይ ገ/እግዚአብሔር። "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሄረሰብ"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 2003።

ለታሪክ ተሾመ። "የባሌ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2003።

ሙሉጌታ ነጋሳ፡፡ "በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ -ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997፡፡

ሰለሞን ሳህሌ። "ባህላዊ የግጭት አፈታት በሲቡ ስሬ ኦሮሞዎች"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ሰለሞን ተሾመ። "የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በስሬ ኦሮሞዎችና አማራዎች ንጽጽራዊ ጥናት"፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ስለሺ አባተ። "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሰርዓት"፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ሻኮ ኦቶ ቶራ። "የኮንሶ ብሔረሰብና ማንነቱ"። <u>ዜና ልሳን</u>፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ ቅጽ 22፣ ቁ.1፣ 2013፣ ገጽ 1-23።

ብርሃኑ ቦጋለ። "መሷል- ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በአንጾኪያ ገምዛ ወረዳ"። የኤ.ም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2003።

ብርሃን አሰፋ። "ባህላዊ የግጭት አፈታት በወግዲ እና በቦረና ወረዳዎች"፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ተመስገን ምንዋጋው። "ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሄ ስርዓት በደኮ ጋሞ"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣1998።

ተመስገን ታደሰ። “ራጋ ማጋ- ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ሰርዓት በማረቆ ብሔረሰብ”። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጸሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2005።

ነፃነት መኮንን፡፡ “አበጋር -ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ”፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1998።

አለሙ ካሳዬ፡፡ “ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ስርዓት በላሎ ማማ ምድር ወረዳ” ፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999፡፡

አለማየሁ ሃፍቶም፡፡ “ባህላዊ የግጭት አፈታት በራያ አላማጣ ወረዳ”፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2004።

አበበ ኃይሉ። “ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኘዋ ብሄረሰብ”። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999።

አብርሃም ታደሰ። “ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ”። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999።

አንዱ አለም አባተ፡፡ “ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በመኤነት ብሔረሰብ” የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2004።

አየለ ፍቅሬ። “ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ /ወይጦ/ ብሄረሰብ”። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998፡፡

አጸደ ያረጋል። “የኮንሶ ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ገላጭ-ተንታኝ ጥናት”፡፡ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ፣2003።

ደስታ ተክለወልድ። <u>የማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ደበበ ዘውዴ። "በድሬዳዋ አስተዳደር እና በሸንሌ ዞን የሚኖሩ ኢሳዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጸሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2001።

ደጀኔ ደንዳና። "የቦረና ኦሮሞ የግጭት አፈታት ዘዴ"። ኤ.ዲ. ኤም ማተሚያ ቤት፣ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ፣ 2004።

ዲኖቴ ኩስያ። "ኮንሶ"። የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ልዩ ዕትም፣ 2004፣ገጽ 11-13።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ከአዲስ አበባ ዩኔስኮ ጋር ያዘጋጀው። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከኦሞ ወንዝ ሰሜን በሚገኙ 20 ብሔረሰቦች ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ላይ የተደረገ ኢንቬንተሪ። አዲስ አበባ፣ 2001፣ ገጽ21።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ከዩኔስኮ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው። ''የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ኢንቬንተሪ ማንዋል"። አዲስ አበባ፣ 2002።

የደ/ብ/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ም/ቤት የባህል ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም። የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል፣ ሀዋሳ፣ 2001።

የወንድወሰን አውላቸው። "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት"። የኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ይልማ ተፈራ። "የሽምግልና እርቅ ስርዓት በወላይታ"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999።

ዮሴፍ ጌትነት። "ባህላዊ እርቅ በምስራቅ ጐጃም መስተዳድር ዞን በደባይጥላት ግን ወረዳ"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ዮናስ ተሾመ። "በአሚባር ወረዳ የአፋር ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ"። የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ጌታቸው ስንሻው። “ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በጉጂ ኦሮሞ”። በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በቀድሞ የአንትሮፖሎጂ መምሪያ የጥናትና ምርምር ቡድን የተጠና፣ 1998።

------------------። “ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በጌድኦ”። በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በቀድሞ የአንትሮፖሎጂ መምሪያ የጥናትና ምርምር ቡድን የተጠና፣ 1998።

ፈቃደ አዘዘ። <u>የስነ ቃል መምሪያ</u>። አዲስ አበባ፣ በኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም የታተመ፣ 1991።

ፈቃደ፣ አሰፋና ገብሬ (አዳኞች)። “<u>በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ላይ የተከናወኑ ኑትት መዘርዝር</u>” ። አዲስ አበባ፣ 2004።

# አባሪ ሰነዶች

## አባሪ አንድ፡- የአውራ መረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ

1. **ካላ ገዛኸኝ** ይባላሉ፡፡ በብሔረሰቡ ከዘጠኙ ጎሳዎች የአንዱ የከርቲታ ጎሳ መሪ ሲሆኑ፣ ካላ ከርቲታ ይባላሉ፡፡ የዳውራነት (መንፈሳዊ አባትነት) ስልጣንም ደርበው ይሠራሉ፡፡ መኖሪያቸው ጋሞሌ ቀበሌ ከዋና ከተማው ከካራት (ሰባት) ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ዙሪያውን በጫካ በተከበበና ከፍ ብሎ በተሠራ ትልቅ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከቤተሰብና ከዘመድ አዝማዳቸው ጋር ይኖራሉ፡፡ የቤተሰቡ ዋና መተዳደሪያ ግብርና ነው፡፡ ካላ ገዛኸኝ የ46 ዓመት እድሜ ባለጸጋና የ5 ልጆች አባት ሲሆኑ ስልጣኑን ያገኙት ከአባት ወደ ልጅ በሚለው በዘር ሀረግ ነው፡፡ ይህን ስልጣን የተረከቡት በ1994 ዓ.ም የዛሬ 12 ዓመት አካባቢ አባታቸው ካላ ወልደዳዊት ሲሞቱ ሲሆን፣ ለ12 ዓመት ያህል በጎሳ መሪነትና በዳውራነት (መንፈሳዊ አባትነት) አገልግለዋል፡፡ አገልግሎቱ የዕድሜ ልክ ስለሆነ አሁንም በዚሁ የመሪነትና የመንፈሳዊ አባትነት እያገለገሉ ይገኛል፡፡ ለዚህ ጥናት መሳካት አንደጎሳ መሪና እንደዳውራ የሚፈለገውን መረጃ በማቀበል (በመስጠት) ረገድ ቁልፍ አካል ሆነው አገልግለዋል፡፡

2. **አቶ ዲኖቴ ኩስያ** ይባላሉ፡፡ የእሻላይታ ጎሳ ተወላጅ ሲሆኑ ነዋሪነታቸው ዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነው፡፡ አቶ ዲኖቴ ተወልደው ያደጉት በኮንሶ ሲሆን የ60 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ፣ የ10 ልጆች አባትና የልጅ ልጅ ያዩ ናቸው፡፡ እኝህ አዛውንት ቀደምሲል በመንግስት ስራ ላይ በመምህርነት፣ በኮንሶ ባህል ቢሮ በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታ ላይ ለ20 ዓመታት ያህል ፣ከዚያ በኋላ በኮንሶ ሙዚየም በኃላፊነት ለ2 ዓመት ያህል አገልግለዋል፡፡ በአሁኑ ሠዓት በጡረታ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በቋንቋ ረገድ ከኮንሶኛ ቋንቋ ባሻገር የተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ቋንቋን በሚገባ የሚናገሩ በመሆናቸው በግል በጋይድነት አካባቢውን በማስጎብኘት ይተዳደራሉ፡፡ አቶ ዲኖቴ በዚሁ ስራቸው የኮንሶን አካባቢ፣ ባህል፣ የተለያዩ ታሪካዊ ስፍራዎችን በሚገባ እያስተዋወቁ የሚገኙ አንጋፋ የብሔረሰቡ ተወላጅ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቦታው የመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃዎች በማሰባሰብ፣ ከኮንሶኛ ወደአማርኛ በማስተርጎም ለስራዬ መሳካት ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ቁልፍ ሰው ሆነው አገልግለዋል፡፡

3. **አቶ ኪሮስ ጃርሶ** ይባላሉ፡፡ በኮንሶ ወረዳ ዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው፡፡ በዚሁ በኮንሶ ተወልደው ያደጉ የ73 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋና ከ9 ሚስቶች የ31 ልጆች አባት ናቸው፡፡ አዛውንቱ በእድሜ ዘመናቸው በወረዳው በቀበሌው የሚፈጠሩ የተለያዩ አለመግባባቶችን በመፍታትና በሽምግልና ስርዓት ላይ በመሳተፍ ለ21 ዓመት አገልግለዋል፡፡ አሁንም እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ የአዛውንቱ ዋና መተዳደሪያ ግብርና ሲሆን ለዚህ ጥናት መሳካት የተፈለገውን መረጃ በመስጠት በኩል ቁልፍ ሰው ሆነው አገልግለዋል፡፡

4. **አቶ ካምብሮ ጉቾ** ይባላሉ፡፡ በኮንሶ ወረዳ በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው፡፡ አዛውንቱ በዚሁ ቀበሌ ተወልደው ያደጉ ሲሆኑ፣ የ55 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋና የ8 ልጆች አባት ናቸው፡፡ ዋና መተዳደሪያቸውም ግብርና ነው፡፡ በቀበሌው ወይንም በከንታው የተለያዩ አለመግባባቶች ሲከሡቱና ጠበኞች በባህላዊ የሽምግልና ስርዓት እንዲፈታላቸው ሲፈልጉ ለድርድሩ የሚሆን ገንዘብ ወይም (ኾራታ) የሚያስዙት እኝህ አዛውንት ዘንድ ነው፡፡ በዚህ ስራቸው አፓ-ከንታ የሚል ስም አላቸው፡፡ አፓ-ከንታ ማለት የከንታ አባት/ መሪ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ስራ ላለፉት ስድስት ዓመታት ያህል አገልግለዋል፡፡ አሁንም እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ጥናት መሳካት የተፈለገውን መረጃ በመስጠት በኩል ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል፡፡

5. **አቶ አያኖ ጉንጬ** ይባላሉ፡፡ በኮንሶ ወረዳ ዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው፡፡ የአዛውንቱ መተዳደሪም ግብርና ነው፡፡ በዚሁ በኮንሶ ወረዳ ተወልደው ያደጉ የ68 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋና የ8 ልጆች አባት ናቸው፡፡ አዛውንቱ በዚህ የዕድሜ ዘመናቸው በወረዳውና በአካባቢ ቀበሌያቸው በሚፈጠሩ የተለያዩ አለመግባባቶች ወይንም ግጭቶች ላይ በሽምግልና ስርዓት ላይ በመሳተፍ ለብዙ አመታት አገልግለዋል፡፡ አሁንም በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ጥናት መሳካት የተፈለገውን መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

6. **አቶ ዲኖቴ ኮጫኖ** ይባላሉ፡፡ በዶካቱ ቀበሌ ዶካቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው፡፡ አቶ ዲኖቴ ኮንሶ ተወልደው ያደጉና ዋና መተዳደሪያቸው ግብርና ሲሆን፣ በአካባቢያቸው በአገር ሽማግሌነት፣በታሪክ አዋቂነት የሚታወቁ ናቸው በሚል ለተለያዩ ጉዳዮች ማረጋገጫ አድርገው የአካባቢው ነዋሪዎች ይጠቀሙባቸዋል፡፡ አቶ ዲኖቴ የ70 ዓመት አዛውንት፣ የ5 ልጆች አባትና የልጅ ልጅ ያሏቸው ናቸው፡፡ በሽማግሌዎች ዘንድም ብዙ

ልምድ የቀሰሙ ናቸው ተብለው ስለሚቆጠሩ በአካባቢው የተከበሩና በሽምግልና ስርዓት ላይም ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ ናቸው። አሁንም በወረዳ ደረጃ ሳይቀር ለሚካሄዱ ስብሰባዎችና ባህላዊ ውይይቶች በቀዳሚነት ስርዓቱን እንዲጀምሩ እየተጋበዙ የሚያገለግሉ ናቸው። በዚሁ ልምዳቸው ለዚህ ጥናት በአውራ መረጃ አቀባይነት አገልግለዋል።

7. **አቶ ሳጎያ ሮቢያ** ይባላሉ። በዶካቱ ቀበሌ በቡርቁዳ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው። አቶ ሳጎያ ኮንሶ ተወልደው ያደጉ፣ የ58 ዓመት አዛውንትና የ5 ልጆች አባት ናቸው። ዋና መተዳደርያቸውም ቀደም ሲል በመንግስት ስራ በመምህርነት፣ ከዚያም በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በባህል ዘርፍ የኃላፊነት ቦታ ላይ ለብዙ ዓመታት ሠርተዋል። አሁንም በኮንሶ ወረዳ የሕዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት በስነ ሕዝብ ባለሙያነት እየሰሩ ይገኛሉ። አዛውንቱ በባህል ጉዳዮች ዙሪያ ባላቸው ዕውቀት በሽምግልናና በማማከር ስራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ያሉ ናቸው። ለዚህ ጥናት ካላቸው ልምድ በመነሳት በአውራ መረጃ አቀባይነት አገልግለዋል።

8. **አቶ ሽሬ ጮልታ** ይባላሉ። በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ሲሆኑ፣ የ42 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋና የ2 ልጆች አባት ናቸው። አቶ ሽሬ በአካባቢው የሽምግልና ስርዓት ላይ የወጣት ትውልድ ቡድን (ኼላውን) በመወከል (ኸሊታ-ከንታ) በመሆን በሽምግልና ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። አቶ ሽሬ አብዛኛው ውሎአቸው መደበኛ ፍ/ቤት አካባቢ በግል በራፖር ፀሐፊነት ስለሚያገለግሉ ነገር አዋቂ ናቸው ይባላሉ። በዚህ ልምዳቸው የወጣት ትውልድ ቡድንን በመወከል በአካባቢው የሞራ-ከንታ ሽምግልና ስርዓቱ ላይ የላቀ ሚና አላቸው። መተዳደሪያቸው በከፊል ግብርና ሲሆን በከፊል ደግሞ በግል በራፖር ፀሐፊነት በሚያገኙት ገንዘብ ነው ።ለዚህ ጥናት የተፈለገውን መረጃ በመስጠት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

9. **ወ/ሮ ሀገያ ሶካ ካሬ** ይባላሉ። በኮንሶ ወረዳ በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው። ወ/ሮ ሀገያ የቤት እመቤት የ 7ልጆች እናትና የ52 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ናቸው። ወ/ሮ ሀገያ በተለያዩ አካባቢዎችና ሀገራዊ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፌስቲቫል ላይ ብሔረሰቡን በመወከል ባህላቸውን በማስተዋወቅ ከፍተኛ ስራ እየሰሩ የሚገኙ ናቸው። በዚሁ በኮንሶ ተወልደው ያደጉ ባህሉን በሚገባ የሚያውቁና በህይወታቸው ከባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የቅጣት ውሳኔዎችን፣

አሠራሮችን አስመልክተው ብዙ የሚያውቁ በመሆናቸው የተፈለገውን መረጃ በመስጠት አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

10. **ወ/ሮ ኦተያ በርጫሼ** ይባላሉ። በኮንሶ ወረዳ በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው። ወ/ሮ ኦተያ የ4 ልጆች እናት፣ የ50 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋና የቤት እመቤት ሲሆኑ በኮንሶ ተወልደው ያደጉ በአካባቢያቸው በባህል የሚፈፀሙ የተለያዩ አሠራሮችንና የቅጣት ውሳኔዎችን በተለይ ደግሞ ከሴቶች የአካባቢ ተሳትፎ ጋር ተያይዞ በሚሰሩት ስራ በአካባቢያቸው የሚነገርላቸው በመሆናቸው ያላቸውን ተመክሮና ልምድ መሠረት በማድረግ ለዚህ ጥናት ዋና የመረጃ አቀባይ ሆነው አገልግለዋል።

11. **ወ/ሮ ባንሶ ሶካ ኡስያ** ይባላሉ። በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ናቸው። ወ/ሮ ቦንሳ የ38 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ የቤት እመቤትና የ5 ልጆች እናት ናቸው። በዚሁ በኮንሶ ወረዳ ተወልደው ያደጉ ሲሆን ባህላቸውን በሚገባ የሚያውቁ፣ በባህላዊ ስርዓቱ የተለያዩ አለመግባባቶች ሲፈቱ የሚያውቋቸውና የሚሰሟቸው አንዳንድ ልምድና ዕውቀት ስላላቸው ለዚህ ጥናት በአውራ መረጃ አቀባይነት አገልግለዋል።

## አባሪ ሁለት፡- የሌሎች መረጃ ሰጪዎች አጭር መግለጫ

1. **ዋና ሳጅን አማረች ስንታየሁ** ትባላለች። በኮንሶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት የሴቶችና ህፃናት ክብካቤ ባለሙያ ስትሆን በዚህ ወረዳ ተወልዳ ያደገች፣ በዶካቱ ቀበሌ በዶካቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ የሆነችና የ42 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ነች። በዚህ ሙያ ለ21 ዓመት ያህል ያገለገለች ስትሆን፣ አሁንም በዚሁ ስራ ላይ ትገኛለች። ለዚህ ጥናት መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህል መዋቅሩ ጋር ያለውን የቅንጅት ስራ አስመልክቶ የተፈለገውን መረጃ በመስጠት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች።
2. **ወ/ሮ ብርቁ ጌልሰሞ** ትባላለች። በኮንሶ ወረዳ ሴቶች ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት የህፃናት መብት ደህንነት ማስጠበቅ ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ሆና በመስራት ላይ ትገኛለች። ወ/ሮ ብርቂ በዱራይቴ ቀበሌ በደንገልቱ ንዑስ መንደር ነዋሪ ስትሆን የ37 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ናት። ወ/ሮ ብርቂ በዚሁ ሙያዋ ለ6 ዓመት ያህል ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም ድረስ በኃላፊነት፣ ከህዳር ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ


በባለሙያነት እስካሁን በማገልገል ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህ ጥናት ከሴቶች ህፃናት ጋር በተያያዘ መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህል መዋቅሩ ጋር በቅንጅት ከመስራት ጋር ያለውን ሁኔታ በተመለከተ የተፈለገውን መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች፡፡

3. **ወ/ሮ ተዋበች ተስፋዬ** ትባላለች፡፡ በኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የክስ አስተዳደር ዋና ስራ ሂደት አስተባባሪ ሆና በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ ወረዳ በዱራይቴ ቀበሌ ተወልዳ ያደገች፣ የ32 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋና የ1 ልጅ እናት ነች፡፡ በዚሁ ሙያ ለአንድ አመት ያህል ያገለገለች ሲሆን፣ ከዚያ በፊት ለ2 ዓመት ያህል በዐቃቤ ህግነት አገልግላለች፡፡ በአሁኑ ወቅት የኮንሶ አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ሆና እያገለገለች ስትሆን፣ ለዚህ ጥናት መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህል መዋቅሩ ጋር ያለውን የቅንጅት ስራ አስመልክቶ የተፈለገውን መረጃ በመስጠት በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች፡፡

4. **አቶ ጌድዮን ጌታሁን** ይባላል፡፡ በኮንሶ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ባለሙያው የአካባቢው ተወላጅ ሳይሆን ለዚህ ስራ ከሌላ አካባቢ የመጣ የ25 ዓመት ወጣት ነው፡፡ በዚህ ሙያ አንድ አመት ያህል ቆይቷል፡፡ አሁንም በዚሁ ስራ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህ ጥናት መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህል መዋቅሩ ጋር ካለው የቅንጅት ስራ ጋር ተያይዞ የተፈለገውን መረጃ በመስጠት አገልግሏል፡፡

5. **አቶ ማቲዎስ ገልጃ** ይባላል ፡፡በኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ቢሮ በባለሙያነት ይሠራል፡፡ ባለሙያው ያላገባና የ26 ዓመት ወጣት ነው፡፡ ተወልዶ ያደገው ኮንሶ ካራት ከተማ ሲሆን፣ በዚሁ ሙያው ለ2 ዓመታት ያህል አገልግሏል፡፡ አሁንም በዚሁ ስራ ላይ ይገኛል፡፡ ባለሙያው የተለያዩ የብሔረሰቡ ተወካዮች ከሚኖሩበት ቀዬ መገለል ሲደርስባቸው በቅርበት ከባህል መሪዎች ጋር በመነጋገር የሚሰራ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መደበኛው የፍትህ ስርዓት ከባህል መዋቅሩ ጋር ባለው የግንኙነት ስራ ላይ መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ተባባሪ ሆኖ አገልግሏል፡፡

## አባሪ ሦስት፡- የመረጃ አቀባዮችና የልዩ ልዩ ክንውኖች ፎቶና መግለጫ



ሞራ-ክንታ (የዳኝነት ቦታ)



ዋናው ሞራ (ሞራ-ፓሌታ) በጥገና ላይ





የፓሌታው ነዋሪዎች ለደቦ ስራ (ሞራ -ጥገና) በወጡበት ወቅት





ከአውራ መረጃ አቀባዮች ጋር በቃለ መጠይቅ ወቅት

*(በስተግራ፣ የከርቲታ ጎሳ መሪ ካላ ገዛኸኝ፤ በስተቀኝ፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች ዲኖቴ፣ ኪሮስ፣ ሀገያና ካምብሮ)*






*(በስተግራ ዲኖቴ በስተቀኝ ኦተያ ጋር በቃለ መጠይቅ ወቅት)*



ከአቶ ዲኖቴ ኩስያ ቤተሰብ ከወ/ሮ ባንሶ ጋር የመረጃ ልውውጥ በተደረገበት ወቅት







*ከፍትህ አካላት ጋር በቃለመጠይቅ ወቅት*

*(በስተግራ የወረዳው ፍትህ ጽ/ቤት የክስ አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ተዋበች በስተቀኝ አቃቤ ሕግ ጌዴዎን)*





*ከፖሊስና ጸጥታ አካላት ጋር በቃለመጠይቅ ወቅት*

*(በስተግራ ዋ/ሳ አማረች የወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት የሴቶችና ሕጻናት ክብካቤ ባለሙያ በስተቀኝ ማቴዎስ የወረዳው ጸጥታና አስተዳደር ቢሮ ባለሙያ ጋር)*



*ከሴቶች ና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ብርቂ ጋር በቃለመጠይቅ ወቅት*




በኢ-መደበኛ መልኩ መረጃ ለማግኘት በባህላዊ መጠጥ(ጨቃ) ቤት የነበረ ተሳትፎ




የኢ-መደበኛ ና የቡድን ውይይት የመረጃ ስብሰባ ሁኔታ



በነዋሪው የውይይት ጊዜ የነበረ ተሳትፎና በዚህ ሁኔታ በአስተርጓሚዬ አማካኝነት መረጃ ሲሰበሰብ




ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የአካባቢ ሽማግሌዎች (በስተግራ አያኖ) በሞራ-ከንታ ስርዓቱን ከታደሙት በከፊል (በስተቀኝ)



በቀበሌ ውይይት ወቅት ትናገራለህ በሚል ከማህበራዊ ኑሮ ተገለው ከመጡ የብሔረሰቡ ተወላጅ ጋርሞ ጋር  በአስተርጓሚ አማካኝነት ቃለመጠይቅ በተደረገበት ወቅት



ክስ ለመመስረት ተበዳይ
የኾራታ ገንዘብ በማስያዝ ላይ እያሉ
(አያኖ ከንዳ ና ካምብሮ)



(ኪሮስ የሀንሳቢታ ቅጠልና
ቀበሌታ/ዘንግ ይዘው) ወደ
ባህላዊ የዳኝነት ቦታ(ሞራ) በመሄድ
ላይ እያሉ



የሽምግልና ስርዓት ለመከታተል
(ዲኖቴ፣ ሽሬ፣ ኪሮስ፣ አያኖ፣ ከንዳ)
ና አጥኚዋ ስርዓቱ ከመጀመሩ
በፊት የነበረው ድባብ



በሞራው የተገኙ ሽማግሌዎች (ሽሬ ጮልታ
የሽምግልና ስርዓቱን ሲመሩ)



በሽምግልና ሂደቱ ወጣቶች ታድመው




በዕቁብ የማጠናቀቂያ ስርዓት ወቅት የሚከናወን ዕርድ እና የባህላዊ መጠጥ (ጨቃ) ስነስርዓት



የዕድር “ኢቲሬታ” ክፍያ ሲከናወን

## አባሪ አራት፡- ደብዳቤዎች



ቁጥር 1984/88/06

ቀን 12-05-2006

ለጋራ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

ጋራ

ጉዳዩ፡- የአቶ ጋርሞ ቢሻዎ አቤቱታን ይመለከታል፡፡

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው [illegible] ቀበሌው ነዋሪ [illegible] አቶ [illegible] በቀን 12-05-2006 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ስለዚህ፣ [illegible] ህገ-ወጥና ኢሰብዓዊ ድርጊት በመሆኑ ይታወቃል፡፡ [illegible] አቤቱታ አቅርበው [illegible] ነው፡፡ [illegible]፡-

1ኛ, አቶ ጋሎ ዳዬ
2ኛ, አቶ ለማታ ጋቦ
3ኛ, አቶ ጉዳና [illegible]

[illegible] በቀን 14/05/2006 ዓ.ም [illegible]

ከሠላምታ ጋር

[illegible]

ቀን፡12/2006፡ዓ/ም

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

2ኛ [illegible]

3ኛ [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible] 50 [illegible]

[illegible]

[illegible] 50 [illegible]

[illegible]

[illegible]

15/05/2005 [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

1984 / 88 / 2006 [illegible]

12/05/2006 [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

12/5/06

ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የሰገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን
የኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ጽ/ቤት
S/N/N/P/R/State Segen Area People's Zone
Konso Wereda Security and Administration Office

ቁጥር 1956/88/06

ቀን 06-05-2006

ለአቶ አውራጃ አሼ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- አስቸኳይ ጥሪ ስለማስተላለፍ ይሆናል

እርስዎ ለአስቸኳይ ብርቱ ጥያቄ የተፈለጉ ስለሆነ በቀን 07/5/2006 ዓ/ም ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ላይ ኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 03 ድረስ እንድቀርቡ በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዳንኤል ደይጋኔ ኦቶ
Daniel Deigane Otto
የፀጥታ መ/መ/የሥራ ሂደት
አስተባባሪ

Konso Woreda Security and Administration Office.

ቁጥር 1956/88/06

ቀን 07-05-2006

ለአቶ አውራጃ ኦሼ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>አስቸኳይ ጥሪን ስለማስተላለፍ ይሆናል</u>

እርስዎ ለአስቸኳይ ብርቱ ጥያቄ የተፈለጉ ስለሆነ በቀን 12/05/2006 ዓ/ም ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ላይ ኮንሶ ወረዳ ፀጥታና አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 03 ድረስ እንድቀርቡ በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዳንኤል ደይጋኔ ኦቶ
Daniel Deigane Otto
የግጭት መ/መ/የሥራ ሂደት አስተባባሪ

[illegible] 05/2006 [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible] 1000 [illegible]

[illegible]

[illegible] 1000 [illegible]

[illegible] 600 [illegible]

[illegible] 400 [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

1956 / 8:8 / 2006

06 / 05 / 2006

S/N/N/P/R/State Segen Area People's Zone
Konso Woreda Security and Administration Office

ቁጥር 1950/02/06

ቀን 02-05-2006

ለሌጠዋይቴ ቀበሌ አስ/ር ጽ/ቤት

ሌጠዋይቴ

ጉዳዩ፡- የሺን ሣቦታ፣ ዴዋጋዴና የሹቶ ጋርሜሌ ቢዳዎ አቤቱታን ይመለከታል።

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የወል ተከሳይ ቀበሌው ከማህበራዊ ጉዮ አገልለውኛል፣ አዘጋተውኛል ሲሉ በቀን 28/04/06 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል።

ስለዚህ እንደዚህም ወለበጠ ከማህበራዊ ጉዮ ማግለልና ማዘጋት ህግ-ወጥና ኢሰብአዊ ድርጊት በመሆኑ ይታወቃል።

በመሆኑ ዘገዮች በጉዳዩን የመምርና ንብረት የማፍራት መብት ተሠጥቶላቸዋል። ዘገዮች ከማህበራዊ ጉዮ የገለሉ ከሆኑና ጉዳዩ የሚያያዝ ከሆነ አብቻጋርና አፀያፊ ስለሆነ ይህ ታውቆ ለቀን 07/05/2006 ዓ.ም. ረቡዕ ዕለት ተስተካክሎ እንዲፈታ ቢደረግ አለበለዚያ በሚለቱ ፊርማ እንድቀርብ በጥብቅ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ገለዮ ሰሎታ

የፀጥታ መስተዳድርና መፍታት ኃላፊ

ታህሣሥ 28/2006 ዓ/ም

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

**ማረጋገጫ**

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ የግል ስራ መሆኑንና በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም ________________________________________________

ፊርማ-------------------------------------

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ